አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት


# [illegible] አፈታት [illegible]


በ

አንዱዓለም [illegible]

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በመኤኒት ብሔረሰብ

በ

እንዱዓለም አባተ

በስብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍል ትምህርት የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት፡፡

ጥቅምት 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በመኢኒት ብሔረሰብ

በ
እንዱዓለም አባተ

በሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት።

አማካሪ
ፈቃዱ አዘዘ (ዶ/ር)

ጥቅምት 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በመኤኒት ብሔረሰብ

በ

እንዳዓለም አባተ

በሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት፡፡

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ............ ፊርማ ............

ፈታኝ ............ ፊርማ ............

ILS LIBRARY

# ምስጋና

ይህ ጥናት ከውጥኑ ጀምሮ ፍጻሜው እስኪደርስ ልዩ ልዩ አካላት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል። በመሆኑም በሃሳብ፣ በምክርና በገንዘብ ጭምር ላገዛችሁኝ ሁሉ ልባዊ የሆነ ምሥጋና ይድረሳችሁ።

በተለይም አማካሪዬ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ፣ በደከመኝ ጊዜ እንድበረታ፣ በተሳሳትኩ ጊዜ እንድታረም ላደረጉትና በስራው ውስጥ ለነበራቸው ስፊ ድርሻ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድኅረ ምረቃ ትምህርቴን በራሴ ወጪ ከጀመርኩ በኋላ የኢትዮጵያ ደራስያን ማሕበር የጻፈልኝን የስፖንሰር ሺፕ ትብብር ደብዳቤ በመቀበል ትምህርቴን በነጻ እንድቀጥል ስላደረገኝ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማሕበር ትምህርቴን በነጻ እንድማር የትብብር ደብዳቤ ስለጻፈልኝ እና ተቀባይነት ስላገኘ ምስጋናዬ ከልብ ነው። በመስክ ቆይታዬ በአስተርጓሚነት ለተባበሩኝ ለአቶ ብርሃኑ ወርቁ ፣ የትብብር ደብዳቤ በመጻፍና መረጃ በመስጠት ላገዘኝ ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና ለቤንች ማጂ ዞን አስተዳደር፣ በመስክ ቆይታዬ ጊዜ የትራንስፖርት ችግሬን ለመቅረፍ ሞተር ሳይክል በመመደብና ሌሎች እገዛዎች በማድረግ ላገዘኝ ለመኢኒት ጎልዲያ ወረዳ አስተዳደር (በተለይም ለአቶ ሉቃስ)፣ ለጥናቱ ማገገዣ 980.00 /ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ብር/ በማውጣትና ጥናቱ በትንበር ተፈጥሯዊ መቼት ሊሰራ ለተሳፋፊ ሰዎች አበል በመክፈል ለተባበረኝ ለመኢኒት ጎልድያ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግሥት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት (በተለይም ለአቶ በድሉ ካሳ)፣ መረጃዎችን በመስጠት ላገዘኝ ለመኢኒት ሻሻ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግሥት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት፣ በምክር ላገዘሽኝ ወ/ሮ ነጻነት ጆቴ እንዲሁም በቃሉ መጠይቅና በሌሎችም ሥራዎች ለተባበሩኝ ሁሉ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

# አጠቃሎ


ይህ ጥናት በመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ ያተኮረ ነው። በጥናቱ ከቤተመጻህፍት መረጃዎች በተጨማሪ ጥናት ስለሚካሄድበት አካባቢና ማህበረሰብ አጠቃላይ ገጽታ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችና የግጭቶቹ ምክንያቶች፣ ማህበረሰቡ ግጭቶችን ስለሚፈታባቸው ባህላዊ የፍትህ ተቋማት እንዲሁም በብሔረሰቡ ውስጥ ጎልተው የሚታዩ ግጭቶች የአፈታት ሂደቶች በቃለመጠይቅና በምልከታ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

ለጥናቱ ሃያ ሁለት መረጃ አቀባዮች የተሳተፉ ሲሆን፣ ከነዚህ መካከል ዘጠኙ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ናቸው። መረጃዎቹም በመቅረጸ ድምጽ፣ በፎቶ ካሜራ፣ በቪዲዮ ካሜራና በማስታወሻ ተይዘዋል። የተሰበሰቡትም መረጃዎች በገላጭ የምርምር ስልትና በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ለመመርመር ተሞክሯል። ከጥናቱ ጋር ተዛምዶ ያላቸው አራት የሁለተኛ ዲግሪ እና አንድ የመጀመሪያ ድግሪ ጽሁፎችም ተቃኝተዋል።

በጥናቱ በዋናነት የብሔረሰቡን ባህላዊ የግጭት አፈታ ሥርዓት ለማየት ሞክሯል። ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቱ ግጭቶችን እንዴት እደሚፈታ፣በማን እንደሚፈታ እና የአፈታት ሂደቶችን ለማየት ሞክሯል። በተለይ የሰው መግደል እርቅ ሥነ ሥርዓት ሂደት እሻ፣ የመድፈር እርቅ ሥነ ሥርዓት ሂደት ማጠብ እንዲሁም የድንበር እርቅ ሥነ-ሥርዓት ሂደት ቀርበውበታል።

በውጤቱም በብሔረሰቡ ብዙ ጊዜ የሚነሱት ግጭቶች የሰው መግደል፣ የሰው ሚስት መድፈር፣ የድንበር መጋፋት፣የገንዘብ መካካድ፣ የጎሳ ጸብ እና የብሔረሰብ ጸብ /ከሱርማ ብሔረሰብ ጋር/ ናቸው። የግጭቶቹም ዋና ዋና መንሻዎች ስካር፣ አንዱ ያጫትን ሴት ሌላው ሲወስድበት፣ቀብር ላይ በሚደረግ ጭፈራ በሚነሳ ድንገተኛ ጸብ፣ የቆየ ቂምን አስታውሶ አመቺ ቦታ ሲገኝ ጥቃት መፈጸም ናቸው። በብሔረሰቡ የሚነሱ ግጭቶች የሚፈቱባቸው ተቋማት ደግሞ ኮሞሩት /ካህናት/፣ ኙራይ /ቃልቻ/ እና የአገር ሽማግሌዎች መሆናቸውን ለማየት ተችሏል።

# ማውጫ

ገጽ

ማውጫ


አጠቃሎ ........ I

ምስጋና ........ II

1 መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 3

1.1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4

1.1.2 የጥናቱ ዓላማዎች ........ 5

1.1.3 የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ........ 5

1.1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 6

1.1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 6

1.1.6 የጥናቱ ዘዴና መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ........ 6

1.1.7 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና ለችግሮቹ የተሰጡ ምላሾች ........ 8

1.2 የመኤኒት ብሔረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ ........ 9

1.2.1 የመኤኒት ብሔረሰብ ........ 9

1.2.2 መልክአ ምድራዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ........ 10

1.2.3 የመኤኒት ብሔረሰብ አመጣጥና አሰፋፈር ........ 11

1.2.4 ማህበረሰባዊ ተቋም ........ 12

1.2.5 ቋንቋ ........ 12

1.2.6 ጋብቻ ........ 13

1.2.7 የስም አወጣጥ ........ 14

1.2.8 ለቅሶ ........ 14

1.2.9 እምነት ........ 16

1.3 የተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት / ክለሳ ድርሳን ........ 17

1.3.1 የግጥም ምንነት (ብያኔ) ........ 18

1.3.2 የግጥም አይነቶች ........ 19

1.3.3 ስለ ግጥም መገለጫዎች የሚያትቱ ንድፈ ሀሳቦች ........ 20

1.3.4 የግጭት አፈታት ዘዴዎች ........ 21
1.3.5 በአገር ውስጥ የተጠኑ አንዳንድ ባህላዊ የግጭት ሥራዎች ........ 24
2 ግጭት፣የግጭት አፈታት ተቋማትና ሥርዓቶች ........ 28
2.1 የግጭት አሳቤ በመኢኒት ብሔረሰብ ........ 28
2.2 የግጭት አይነቶችና ምክንያቶቻቸው ........ 29
2.3 በመኢኒት ብሔረሰብ ብዙ ጊዜ የሚቀርቡ ዋና ዋና ግጭቶችና የተሰጡት ውሳኔዎች 31
2.3.1 ከሀብትና ከንብረት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች ........ 31
2.3.2 የቤተሰብ ጠብ ........ 33
2.3.3 ወንጀል ........ 35
2.3.4 የቡድን ጠብ ........ 39
3 የመኢኒት ብሔረሰብ የግጭት መፍቻ ተቋማት ........ 43
3.1 ባህላዊ የፍትህ ተቋማት ........ 43
3.1.1 ኮሞሩት /ባላባት/ ........ 43
3.1.2 ዮገሮቢይቻ /የአገር ሽማግሌዎች/ ........ 47
3.1.3 ኘራይ /ቃልቻ/ የባህላዊ ሃይማኖት ........ 49
3.2 ዘመናዊ የፍትህ ተቋማት ........ 50
4 የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ........ 56
4.1 'ኦሻ' /የግድያ እርቅ/ ሥነ ሥርዓት ሂደት ........ 56
4.2 'ማስጠብ' /የደፈራ እርቅ/ ሥነ ሥርዓት ሂደት ........ 77
4.3 'ሸየ' /የድንበር ጠብ/ ግጭት የአፈታት ሂደት ........ 81
4.4 የእርግማን እርቅ ሥነ ሥርዓት ሂደት ........ 82
4.5 የብሔረሰብ ግጭት የአፈታት ሂደት ........ 86
5 በአሁኑ ጊዜ በብሔረሰብ ውስጥ በሥራ ላይ ያለው ግጭት ፈቺ ተቋም ........ 89
5.1 ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ሲታይ ........ 91
5.2 መደበኛው ፍርድ ቤት ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ሲታይ ........ 97
5.3 መደበኛ ፍርድ ቤት እና ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ያላቸው ትብብር ........ 99
5.4 ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ለመደበኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ያለው አስተያየት ........ 105
5.5 መደበኛው ፍርድ ቤት ለባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ውሳኔ ያለው አስተያየት ........ 109

6 በመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት ሥርዓት ላይ የተደረገ አጠቃላይ ትንተና .................... 110

6.1 የባህላዊ የፍትህ ሥርዓት ማህበራዊ እሴቶች .................... 111

6.2 የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ጥንካሬዎች እና ድክመቶች ምንነት .................... 116

6.3 ጠበኞች ወደ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት እንዲሄዱ የሚያደርጋቸው መሰረታዊ ምክንያት .................... 121

6.4 ባህላዊ ሥርዓቱ ማህበራዊ ሰላምን የማምጣትና የማስጠበቅ ፋይዳው .................... 122

6.5 የባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ከጊዜ፣ ከቦታና ቢሮክራሲን ከማስቀረት አንጻር .................... 124

6.6 ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ከአረጋውያን፣ ከህጻናትና ከሴቶች አንጻር .................... 126

ማጠቃለያ .................... 129

ይሁንታ .................... 132

ጥቆማ .................... 134

# 1. መግቢያ

ማንኛውም ብሔረሰብ የራሱ የሆኑ የማንነት መገለጫዎች አሉት፡፡ የመኢኒት ብሔረሰብም ማንነቱን የሚገልጹለት በርካታ ባህሎች አሉት፡፡ ብሔረሰቡ ከበርካታ የማንነቱ መገለጫዎች ውስጥ አንዱ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ነው፡፡

የመኢኒት ብሔረሰብ በውስጡ እና ከውጪ የሚገጥሙትን ግጭቶች የሚፈታበት የራሱ የሆነ እና ለዘመናት ጠብቆ ያቆየው ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓት አለው፡፡ ይህ ጥናት የሚያተኩረውም በዚሁ በመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ ነው፡፡

ጥናቱ ስድስት ምዕራፎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ አጥኚው ይሄንን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሳው ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ፣ ጥናቱ የቀረበበት መንገድ፣ ጥናቱ የተተነተነበት ስልት እንዲሁም የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት እንዲሁም የመኢኒትን ብሔረሰብ ማህበረ ባህላዊ ማንነት፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታና አካባቢያዊ መገለጫ ተካትተውበታል፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ ውስጥ የመኢኒት ብሔረሰብ ያሉት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ምንነት ተገልጿዋል፡፡ ተቋማቱም የኮምሩት /ባላባት/ ወይም የጎሳ መሪዎች፣ የአገር ሽማግሌዎች እና የባህላዊ ሃይማኖት መሪዎች /ቃልቻዎች/ ናቸው፡፡ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ አደረጃጀት፣ የመሪዎቹ አመራረጥ እንዲሁም የሚያይዋቸው የግጭት አይነቶች ቀርበዋል፡፡

በሦስተኛ ምዕራፍ ውስጥ የመኢኒት ብሔረሰብ ያሉት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ግጭቶችን ሲፈቱ የሚከተሏቸው የግጭት አፈታት ሂደቶች ተቀምጠዋል፡፡ በዚህም ስር የገደያ ግጭት አፈታት ሂደት፣ የሰው ሚስት መድፈር ግጭት አፈታት ሂደት፣ የድንበር ጠብ አፈታት ሂደት እንዲሁም የብሔረሰብ ጠብ አፈታት ሂደት ተዘርዝረዋል፡፡

አራተኛው ምዕራፍ በመኢኒት ብሔረሰብ ውስጥ ጎልተው የሚታዩና ወደ ግጭት መፍቻ ተቋማቱ ብዙ ጊዜ የሚቀርቡ ግጭቶች አይነት እንዲሁም በመፍትሄነት የተሰጡ ውሳኔዎች ተገልጸዋል፡፡ የከብት ዝርፊያ፣ የመድፈር፣ ግድያ፣ ስርቆት፣ የብሔረሰብና የጎሳ ጸቦች ከአይነተኛ ውሳኔዎች ጋር ቀርበዋል፡፡

አምስተኛው ምዕራፍ የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ከመደበኛው ፍርድ ቤት ጋር ያላቸው ግንኙነት ቀርቦበታል። ሁለቱ ግጭት መፍቻ ተቋማት ለህብረተሰቡ የሚሰጡት የተናጠል ሚናና የትብብር ሥራዎች እንዲሁም አንዱ በአንደኛው ውሳኔ ላይ የሚያሳድሩት ተጽእኖ ተቃኝቶበታል።

በጥናቱ ስድስተኛ ክፍል ውስጥ የመኢኒትን ብሔረሰብ ውስጥ ያሉ የግጭት አይነቶችና ሰበቦቻቸው፣ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋሞችንና የአፈታት ሥርዓት ሂደታቸውን እንዲሁም ከመደበኛው ፍርድ ቤት ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲሁም ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቱ ለሌቶች፣ ለህጻናትና ለአረጋውያን የሚሰጠው ተዳስሶበታል። ከዚህ በተጨማሪ የጥናቱ ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳቦች የተዘረዘሩ ሲሆን ካርታና መረጃ የሰጡ ሰዎች ዝርዝር ተካትተዋል።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የሰው ልጅ ታሪክ በየምዕራፉ፣ በየምዕራፉ ከተሰደረበት ዘመን ጀምሮ ግጭቶች ተለይተውት አያውቅም። ሰው ማህበረሰባዊ ፍጡር የመሆኑ ጉዳይ ደግሞ ስርስ በርስ ግጭትም ይሁን ለሌሎች ግንኙነቶች ተጋላጭ እንዲሆን አድርጎታል።

የግጭትን ምንነት ከተገለጹት መካከል Leslau "ትግል፣ ልዩነት፣ አለመስማማት፣ ጠብ፣ ውጊያ፣ ግጭት፣ አለመግባባት /conflict of opinion/ እንደሆነ ይገልጻል(1973፣236)። እንዲሁም ግጭት ከድንገተኛ ጥል፣ ካልታሰበ አደጋና ከጦርነት ጋርም እንደሚተሳሰር ደስታ በመዝገበ ቃላት ፍቾቸው አስፍረዋል። "... መታ፣ ኮረከመ ፣ለተመ፣ ተመተመ ገጩን። ግጭት/ቶች/ ... መግጨት፣ መገጨት፣ ድንገተኛ ጥል፣ ዕለተ ጠብ፣ ያልታሰበ አደጋ፣ የጊዜ ጦርነት" (ደስታ 1962፣249)።

ሰላም ለማንኛውም ማህበረሰብ አስፈላጊና የህይወቱ ዋና ቁልፍ እንደሆነ ግልጽ ነው። ወልዶ ለመሳም ይሁን ዘርቶ ለመቃም የሚቻለው ማህበረሰቡ ሰላሙ የተጠበቀና የተረጋጋ ህይወት መኖር ሲችል ነው። ነገር ግን ግጭቶች በተለያዩ መንገዶች ሊከሰቱ ይችላሉ።

አንድ ማህበረሰብ በውስጡ የሚከሰቱ ግጭቶችን የሚያስወግድባቸው የራሱ የሆኑ መዋቅሮች ፣ ደንቦች እና ሂደቶች ይኖሩታል። እነዚህኑ ግጭቶች እንደ አይነት አይነታቸው በመለየት፣ ለግጭቶቹ ይበጃሉ የሚላቸውን መፍትሄዎች ለመስጠት ግጭቶቹን የሚያስወግድባቸው የራሱ የሆኑ ባህላዊ የፍትህ ተቋማት ይኖሩታል። ማህበረሰቡም ከራሱ የወጡ የግጭት አስወጋጅ አካላት በሚሰጡት ብያኔ ይተዳደራል። ማንተመሥላሴ በዚህ ጉዳይ የሚከተለውን ሀሳብ ይሰነዝራሉ። "ያገር ሽማግሌች ይመረጡና በሸንጎ ተቀምጠው የእድር ደንባቸውን በጠንከረ ሁኔታ ይወስናሉ" (ማንተመሥላሴ፣ 1960፣ 16)።

የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች እንዳሏቸው ሁሉ የዚህ ጥናት ትኩረትም በተጠኘው በመኢኒት ብሔረሰብ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና የግጭት አይነቶችንና ምክንያታቸውን፣ ግጭቶቹን የሚፈቱት ተቋማት ማንነትና የአፈታት ሂደታቸውን ማሳየት ይሆናል።

### 1.1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በመኢኒት ብሄረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ እንድሰራ ምክንያት ከሆኑኝ ውስጥ አንደኛው ጉዳይ ፖፒሌሽ ሚዲያ ሴንተር በ2002 ዓ.ም. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ያተኮሩ ድርሰቶች እና እውነተኛ የህይወት ታሪኮች እንዲጻፍለት አድርጎ ነበር። እኔም በዚህ ጊዜ ወደ አገራችን ደቡባዊ ክልል የመጓዝ እድል አግኝቼ ነበር። በወቅቱም ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ከፍትህ አካላት ጋር ባደረኩት ውይይት ስለ መኢኒት ብሄረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት መስማቴ አንደ አንድ መነሻ ሆኖኛል።

በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት በቤንች ማጂ ዞን ፍትህና ጸጥታ መምሪያ የትምህርት ምርምርና ስልጠና ክፍል በየሦስት ወሩ እያዘጋጀ የሚያወጣው ‹‹ያካር›› ጋዜጣ በሚያዚያ እና ቤሐምሌ ወር 1999 ዓ.ም በባህል አምዱ ሥር ስለ ብሄረሰቡ ያወጣውን የባህላዊ የፍትህ ሥርዓት በማንበቤ በጉዳዩ ላይ የበለጠ እንዳስብና የተሻለ ግንዛቤ እንዳገኝበት አድርጎኛል።

ከላይ ያገኘኋቸውን መረጃዎችና አንዳንድ ተጨማሪ ንባቦችን በማካሄድ ፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር በ2000 ዓ.ም ባወጣው "ሙሉ ሰው" በተሰኘው የአጫጭር ልቦለዶች መድበል ውስጥ በውድድር ያለፈ "እኛ" የተሰኘ አጭር ልቦለድ አሳትሜያለሁ። እንዲሁም በ2002ዓ.ም መጨረሻ ላይ በግሌ ባሳተምኩት "ሦስቱ ትዝታዎች" የተሰኘ የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ ውስጥ ስለብሄረሰቡ እንድጽፍ ምክንያት የሆነኝ ሲሆን በብሔረሰቡ  ላይም የበለጠ ምርምር እንዳደርግ ተጨማሪ ግፊት ሆኖኛል።

ከዚህ በተጨማሪ በ2002 ዓ.ም ታህሳስ ወር ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ከብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን ጋር ተሳስሮ በተከበረው 5ኛው ዓለም አቀፍ የፌዴራሊዝም ኮንፈረንስ ላይ ለመሳተፍ ወደ አዲስ አበባ የመጡ የአካባቢው ተወላጆች እና የባህል ልዑካንን አነጋግሬ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ አሁንም የሚካሄድ መሆኑን ስለገለጹልኝ በባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቱ ላይ የበለጠ ጥናት እንዳካሂድ እንድወስን አድርጎኛል።

### 1.1.2 የጥናቱ ዓላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል። እነሱም፡-

1. የመኢኒት ብሔረሰብ ውስጥ የሚከሰቱ ዋና ዋና ግጭቶችንና ምክንያታቸውን ማሳየት
2. የመኢኒት ብሔረሰብ የግጭት መፍቻ ሥርዓት ላይ ብዙ ጊዜ የሚቀርቡ የግጭት አይነቶችና የሚሰጡ ውሳኔዎች መግለጽ።
3. የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትን መግለጽ
4. የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ሂደት ምን እንደሚመስል ማሳየት።
5. ግጭት ለመኢኒት ብሔረሰብ አባላት ምን እንደሆነ መግለጽ?
6. በመኢኒት ብሔረሰብ በባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓትና በዘመናዊ የፍትህ ሥርዓት መካከል ያለውን ግንኙነት ምን እንደሚመስል ማሳወቅ።
7. የመኢኒት ብሔረሰብ ለባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ያለውን አመለካከት ማሳየት።

### 1.1.3 የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች

ጥናቱ ሊመልሳቸው የሚችሉ ጥያቄዎች፡-

1. በመኢኒት ብሔረሰብ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችና የግጭት አይነቶች ምንምን ናቸው?
2. የመኢኒት ብሔረሰብ የግጭት መፍቻ ሥርዓት ላይ ብዙ ጊዜ የሚቀርቡ የግጭት አይነቶችና የሚሰጡ ውሳኔዎች ምንድናቸው?
3. መኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ምን ምን ናቸው ?
4. የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ሂደት እንዴት ይፈጸማል?
5. ግጭት ለመኢኒት ብሄረሰብ አባላት ምንድነው? የግጭት መከሰቻ ምክንያቶችስ ምን ንም ናቸው?
6. በመኢኒት ብሔረሰብ በባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓትና በዘመናዊ የፍትህ ሥርዓት መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?
7. የመኢኒት ብሔረሰብ ለባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?

## 1.1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

ጥናቱ የሚከተሉት ዋና ዋና ጥቅሞች ይኖሩታል። እነሱም፡-

1. የመኢኒት ቤሔረሰብ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት ምን እንደሚመስል ቀርሶ ማስቀመጥ።
2. የመኢኒት ቤሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ያለውን ምልአት ጉድለት ማሳየት እና ድክመቶቹ ታርመው ጥንካሬዎቹን ይዞ እንዲወጥል ለማስቻል።
3. በመኢኒት ቤሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ የግጭት አፈታ ሂደቶች ምን እንደሚመስሉ ለሌላው ማሳወቅ።
4. በመኢኒት ቤሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ከዘመናዊ የፍትህ ሥርዓት ጋር ያለውን ግንኙነት በማሳየት ለፖሊሲ አውጪዎች መረጃ መስጠት።
5. በቤሔረሰቡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዙሪያ ወደፊት ለሚሰሩ ምርምሮች መረጃ መስጠት

## 1.1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተካሄደው በደቡብ ቤሔር፣ ቤሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት በቤንች ማጂ ዞን በመኢኒት ሻሻ እና በመኢኒት ጎልዲያ ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ አስራ ሦስት ቀበሌዎች ነው።

የመኢኒት ብሄረሰብ በመኢኒት ሻሻ እና በመኢኒት ጎልዲያ ወረዳዎች የሚገኝ ሲሆን ከእነዚህ ወረዳዎች ውስጥም ጀሙ እና ባቹማ የተባሉት ሁለት የወረዳዎቹ ከተሞች የዚህ ጥናት ዋነኛ ማዕከል ናቸው።

## 1.1.6 የጥናቱ ዘዴና መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች

ጥናቱ በመኢኒት ቤሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ላይ በመሆኑ የግጭት አይነቶችንና ምክንያታቸውን፣ የባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱን ምንነት፣ የግጭት አፈታት ሂደቶችን፣ ከመደበኛ ፍርድ ቤት ጋር ያለውን ተዛምዶና ቅራኔ ጭምር የሚመረምር ነው። ከዚህ በተጨማሪም ማህበረሰቡ ለዚህ ሥርዓት ያለውን አመለካከት በጥልቀት የሚዳስስ በመሆኑ ገላጭ / Descriptive / ዘዴን ይጠቀማል። ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በምልከታ፣ በቡድን ... 

ስለ መኤኒት ብሔረሰብ አጠቃላይ ገጽታ ለማግኘትና ተዛማጅ ሥራዎችን ለመዳሰስ የቤተ-መዛግብት ፍተሻ አካሂጃለሁ። ወደ ማህበረሰቡ ዘልቆ ለመግባት ደብዳቤዎችን ከክልሉ ርዕሰ-ከተማ ሀዋሳ እንስቶ በተዋረድ ለቤንች ማጂ ዞን አስተዳደር እንዲሁም አስተዳደሩም ለመኤኒት ጎልዲያ እና ለመኤኒት ሻሻ ወረዳዎች ደብዳቤ ጽፎልኝ ትልቅ ትብብር ከመኤኒት ጎልዲያ ወረዳ አስተዳደር፣ ከወረዳው ባህል ቱሪዝምና የመንግሥት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት አግኝቻለሁ።

የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የመጀመሪያ ደብዳቤዬን ተቀብሉ በመኤኒት ብሔረሰብ አጠቃላይ ማንነት ላይ የተጻፈና ያልታተመ መረጃ በመስጠት ትልቅ ትብብር አድርጎልኛል። የመኤኒት ጎልድያ ወረዳ ደግሞ ጥናቱ ለወረዳችን ትልቅ ፋይዳ አለው ብሉ በማመን መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ ለጉዳዩ እውቀት ያላቸውን ሰዎች ከማፈላለግና ከመጠቆም ጀምሮ ሁነኛ የሆነ አስተርጎሚ በመመደብና ለአስተርጓሚውም አበል በመክፈል በተለያዩ የወረዳው ቀበሌዎች በመዘዋወር የተሟላ መረጃ እንዳገኝ ረድተኛል። ወረዳው ከዚህ በተጨማሪ ከሚያዚያ 8 2003ዓ.ም እስከ ግንቦት 3 ቀን 2003ዓ.ም ድረስ በአካባቢው ስቆይ ለመንንገር አስቸጋሪ በሆኑት ቀበሌዎች ሞተር ሳይክልና ነጅውን በመመደብ ድካሜን ለማቅለል ትብብር ያደረገ ሲሆን በትንብር ተፈጥሯዊ መቺት የአሻ /ኛሰው መግደል እርቅ/ሥነ ሥርዓትን ለማስቀረጽ እንዲረዳኝ በወቅቱ ጉዳዩን እንዲከውኑ የተሰበሰቡት ሰዎች የጠየቁኝን ከፍተኛ ወጪ /ለጥናት ከሚመደበው በጀት አንጻር/ በመጋራት ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ብር በማውጣት አበል ከፍሉልኛል።

ከባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ውስጥ "አሻ"ን በቪዲዮ ካሜራ ያስቀረጽኩ ሲሆን ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቱ ያለውን መዋቅር፣ የአፈጻጸሙን ደንብ፣ እውድ እና ፋይዳ በሚገባ ለማወቅ ከብሄረሰቡ ታዋቂ የሆኑትንና ተቀባይነት ያላቸውን ፣ የብሄረሰቡን ባህል፣ ወግ እና ልማድ ጠንቅቀው የሚያውቁትን እና በባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቱ ተሳታፊ የሆኑትን የአገር ሽማግሌዎች እንደዲሁም የተለያዩ የመንግሥት አካላትን ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃ ሰብስቢያለሁ። በመጨረሻም በተለያዩ መንገዶች የተገኙትን መረጃዎች ትክክለኛነትና አሳማኝነት ለማረጋገጥ ባህሉንና ወጉን ጠንቅቀው ያውቃሉ ካልኳቸው የብሄረሰቡ ተወላጆች ጋር የቡድን ውይይት አካሂጃለሁ።

### 1.1.7 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና ለችግሮቹ የተሰጡ ምላሾች

ማንኛውም ጥናት ያለ ውጣውረድ፣ ያለ ስፊ ትዕግስትና ጥረት ስኬታማ አይሆንም። ይሄንን ጥናት በማካሄድበት ወቅትም የተለያዩ ችግሮች ማጋጠማቸው አልቀረም። በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙኝ ችግሮች በርካታ ቢሆኑም ዋና ዋና የሆኑት የሚከተሉት ናቸው።

- የበጀት እጥረት። እንዲህ አይነት ጥናቶች በባህሪያቸው በርካታ ሰውን ለክዋኔያቸው ያሳትፋሉ። በእኔ ጥናት ውስጥ በተለይ የእሻ ክፍያውን /የሰው መግደል እርቅ ስርዓት ሂደት/ በቅንብር ተፈጥሯዊ መመቼት ለመጠቀም የገዳይና የተገዳይ ወገኖች እንዲሁም አስታራቂ ሽማግሌዎች በአውራ የመረጃ አቀባይነት ሲሳተፉ ቁጥራቸው ከሰባ ሰው በላይ ዩኒቨርስቲው የሰጠኝ ገንዘብ ሊሸፍነው አልቻለም። ይሄም እጥኘው በአካባቢው ከሚቆይበት ቀን፣ ከሚያስፈልገው የትራንስፖርት፣ የምግብና የመኝታ ወጪ ጋር ተዳምሮ ሲገኝ ችግሩ ከባድና ፈታኝ መሆኑ ግጽ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የሰዎች ምንም አይነት ትብብር ከገንዘብ ክፍያ ውጭ ለማድረግ ፈቃደኛ አይሆኑም። በተለይ ጥናቶች እንዲህ ከመሀል አገር ርቀው ሲሰሩ የበጀት እጥረቱ እጅግ ከፍተኛ ይሆናል።
- የጊዜ እጥረት። ጥናቱን ለማጥናትና በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ ሰፋ ያለ ጊዜ ለመቆየት አለመቻል።
- የትራንስፖርት አለመኖር። ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ከፍተኛ የሆነ የትራንስፖርት ችግር ያለበት መሆን።
- የመብራት አለመኖር። ቀኑን ሙሉ የተሰበሰበውን መረጃ ምሽቱን አደራጅቶ ለማደርና አንዳንድ ተጨማሪ ጥያቄዎችንና ውይይቶችን ወዲያው ለማድረግ አለመቻል። ይሄም የጊዜ እጥረቱ ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድሯል።

ለችግሮች የተሰጡ ምላሾች

ይህ ጥናት በሚካሄድበት ወቅት ፈታኝ ሆኑ ችግሮች የነበሩ ቢሆንም እነዚህን ችግሮች በመቋቋምና መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ርምጃዎችን በመውሰድ ጥናቱን ማካሄድ ተችሏል።

- የበጀት ችግርን ለማስወገድ ዩኒቨርስቲው ከሰጠው በጀት ያላነሰ ከግል ኪስ ተጨማሪ ገንዘብ በማውጣት፣ የመአኒት ጎልድይ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግሥት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት የሰው መግደል እርቅ ሥነ ሥርዓት እሻ በቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቱ ላይ

ለተሳተፉ የተወሰኑ ሰዎች 980 /ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ብር/ በማውጣት እና አበል በመክፈል እገዛ በማድረግ እንዲሁም ለእለት የሚሆንን ወጪ በመቆጠብ ችግሩን ለመቋቋም ጥረት ተደርጓል።

- የጊዜውን እጥረት ለማስወገድ ሌሊቱን በሻማ ብርሃን ለመስራት ተሞክሯል። በመሆኑም 125 ገጽ ስክርብ /ጥሬ መረጃውን/ እና ዋና ጥናቱን በከፍተኛ ትጋት ለመስራት ተሞክሯል።
- የትራንስፖርት አለመኖርን ጉዳይ የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግሥት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት አልፎ አልፎ በሚመድበው ሞተር ሳይክል በየገደሉና ወንዝ ውስጥ በመጓዝ፣ ለሞተር ሳይክል የሚሆን ነዳጅ አልፎ አልፎ ከኪስ ገንዘብ አውጥቶ በመሙላት፣ በአጋጣሚ በሳምንት አንዴ በሚመጣ የጭነት መኪና ሰዓትን ጠብቆ በመጓዝ እንዲሁም ከሁለት ሰዓት በላይ ለተከታታይ ቀናት በእግር መጓዝ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል።

## 1.2 የመኢኒት ብሔረሰብ ማህበረ- ባህላዊ ዳራ

በዚህ ርዕስ ስር የመኢኒት ብሔረሰብ፣ ብሔረሰቡ የሚገኝበት መልክዓምድራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበረ ባህላዊ ማንነት፣ የጥናቱ ምንነት፣ የጥናቱ ንድፈ ሃሳብ እና የተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት ተዘርዝረዋል።

### 1.2.1 የመኢኒት ብሔረሰብ

የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በውስጡ ከ 56 በላይ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ይኖሩበታል። ክልሉ በውስጡ 13 ዞኖች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የቤንች ማጂ ዞን አንዱ ነው። የቤንች ማጂ ዞን በሰሜን ከሸኮ ዞን፣ በደቡብ ከኬንያ፣ በምዕራብ ከሱዳንና በምስራቅ ከካፋ ዞን ጋር ይዋሰናል። በ1999ዓ.ም. የተደረገው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ እንደሚያመለክተው በአጠቃላይ 659.046 የሚደርስ ህዝብ መኖሪያ ነው። የቤንች ማጂ ዞን በውስጡ ቤንች፣ ዲዚ፣ መኢኒት፣ ሸኮ፣ ሱርማና ዝልማሙ (ባሌ) የተባሉ 6 ብሔረሰቦች ይኖሩበታል። (የደ/ብ/ብ/ህ/ ፕሮፋይል፣2001)

በቤንች ማጂ ዞን ውስጥ ካሉት ብሔረሰቦች አንዱ የሆነው የመኢኒት ብሔረሰብ የዞኑን ደቡብ ደቡብ ምዕራብ ክፍል በመያዝ በአብዛኛው በመኢኒት ሻሻ እና በመኢኒት ጎልዲያ ወረዳዎች ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ፕሮፋይል እንደሚያስረዳው ከዞኑና ከተጠቀሱት ሁለት ወረዳዎች በተጨማሪ በተወሰነ ደረጃ በካፋ ዞን በዴቻ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ በርካታ መንደሮች ውስጥ ይገኛል፡፡ ብሔረሰቡ በዋንኛነት በሚኖርባቸው ወረዳዎች ውስጥ የካፊች፣ የቤንችና የአማራ ማህበረሰብ አባላት በተለያየ መጠን ከብሔረሰቡ ጋር ይኖራሉ፡፡ በ1999ዓ.ም. በተደረገው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሰረት የመኢኒት ብሔረሰብ ብዛት 151.489 ነው፡ (የደ/ብ/ብ/ህ/ ፕሮፋይል፣2001)፡፡

## 1.2.2 መልክአ ምድራዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ

የመኢኒት ብሔረሰብ በዋናነት የሚኖርባቸው ሁለት ወረዳዎች መኢኒት ጎልዲያ እና መኢኒት ሻሻ ናቸው፡፡ የመኢኒት ጎልዲያ ወረዳ ዋና ከተማ ባቹማ ስትሰኝ የመኢኒት ሻሻ ወረዳ ዋና ከተማ ደግሞ ጀሙ ትባላለች፡፡ በሁለቱ ወረዳዎች ውስጥ ያሉት የብሔረሰቡ አባላት በባህል፣ በቋንቋ፣በእምነት እና በሌሎች እሴቶቹ አንድ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ወረዳዎቹን በተናጠል እንመለከታለን፡፡

መኢኒት ጎልዲያ፣

የመኢኒት ጎዲያ ወረዳ ዋና ከተማ ባቹማ ከአዲስ አበባ 645.28፣ ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ሀዋሳ በ915 እንዲሁም ከዞኑ ዋና ከተማ ሚዛን ተፈሪ 85 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ የቆዳ ስፋት 1658.5 ስ.ኪ.ሜ ነው ሲሆን የአየር ንብረቱ ደግሞ 79.34% ወይና ደጋ፣ 21.66% ቆላ ነው፡፡ የወረዳው ዓመታዊ አማካኝ የሙቀት መጠን 17.60c ሲሆን የምትገኘው 501-2500 ሜ. ከባህር ጠለል በላይ ነው፡፡ መኢኒት ጎልዲያ ስሟን ያገኘችው ከአንድ ድንጋይ እንደሆነ አውራ የመረጃ አቀባዩና አስተርጓሚዬ አቶ ብርሃኑ ወርቁ ነግረውኛል፡፡ "መኢኒት ጎልድያ ከዚህ በፊት መሀል ባቹማ ከተማ ውስጥ የሆነ ጠፍጣፋ

ድንጋይ ነበር። እሱ በብሄረሰቡ ስም "ጎሉ" ነው የሚባው "ጎሉ" ማለት መፍጫ፣ ወፍጮ ነው። ወፍጮ ስለሚመስል በዚያች ድንጋይ ነው መኢኒት ጎልድያ የተባለችው።"[1]

መኢኒት ሻሻ፣

የመኢኒት ሻሻ ወረዳ ዋና ከተማ ጀሙ ከአዲስ አበባ 675.28፣ ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ሀዋሳ በ945 እንዲሁም ከዞኑ ዋና ከተማ ሚዛን ተፈሪ 115 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች። የመኢኒት ሻሻ ወረዳ የቆዳ ስፋት 3143.5 ስ.ኪ.ሜ ሲሆን የአየር ንብረቱ ደግሞ 20% ወይና ደጋ፣ 80% ቆላ ነው። የወረዳው ዓመታዊ አማካኝ የሙቀት መጠን 17.6- 27.50c ሲሆን የምትገኘው እንደ መኢኒት ጎልዲያ ሁሉ 501-2500 ሜ. ከባህር ጠለል በላይ ነው። መኢኒት ሻሻ ስሟን ያገኘችው በአካባቢው ካለ ተራራ ነው። "መኢኒት ሻሻ በዚያ ትልቅ ጉም የሚባል ተራራ ነበር። በዚያ ዝናብ ሊጥል በሚልበት ጊዜ ጉም ይይዛል። ጉም በሚይዝበት ጊዜ 'ያቺ ሻሸ የሚመስለው ምንድነው? እዚያች ጋ "ጉሚ" ወይም "ሻሻ" ብለው ይጠሯታል።"[2]

### 1.2.3 የመኢኒት ብሔረሰብ አመጣጥና አሰፋፈር

የመኢኒት ብሔረሰብን አመጣጥና አሰፋፈርን በተመለከተ በርካት ያሉ አፈ- ታሪኮች እና ጡፈ-ታሪኮች ተዘግበው ይገኛሉ። ከቤንች ማጂ ዞን የህዝብ ቤተ- መጻሕፍት ያገኘሁት ያልታተመ ጽሑፍ የብሔረሰቡን አመጣጥ በተመለከተ የተሰጡትን አራት አፈ-ታሪኮች በቅደም ተከተል አስፍሯል።

የመጀመሪያው አፈ-ታሪክ ብሔረሰቡ ከነገደ ኩሽ ከመሃል አገር ፈልሰው ወደ ደቡብ ምዕራብ የመጡ ናቸው የሚል ሲሆን ሁለተኛው አፈ-ታሪክ የብሔረሰቡ አመጣጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የብሄረሰቦች ፍልሰት ጋር የተያያዘ እንደሆነና ከ3000ዓ.ዓ. በፊት ከደቡብ ሱዳን ፈልሰው ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከገቡት ጎሳዎች እንደ ቤጃ እና ከመሳሰሉት አንዱ ነው የሚል ነው። ሦስተኛው አፈ-ታሪክ ደግሞ ቢጋሞ ጎፋ ክ/ሀገር በእሞ ሸለቆ አካባቢ ከብት እያረቡ ሲኖሩና ከብቶቻቸው በበሽታ ሲያልቁባቸው አካባቢውን ጥለው እንደመጡና አሁን ባሉበት ጸንተው እንደ ቆዩ የሚያትት ሲሆን አራተኛው አፈ-ታሪክ ደግሞ በብዙ የብሔረሰቡ አባላት የሚነገረው የእሞን ወንዝ ተሻግረው መምጣታቸውን የሚተርክ ነው። እኔም የብሔረሰቡን የት

---

[1] ቃርጥኑ፣ ሚያዚያ 2003
[2] ቃርጥኑ፣ ሚያዚያ 2003

መጣንት በስፍራው ተገኝቼ ባደረኩት ቃለ መጠይቅ ከአውራ የመረጃ አቀባዮቼ የሰማሁት ቢሌረሰቡ ከደቡብ እሞ መምጣቱን ነው።[3]

## 1.2.4 ማህበረሰባዊ ተቋም

አንድ ማህበረሰብ የራሱ የሆኑ ባህሉችና ወጎችን የሚጠብቅበት ማህበራዊ ተቋም ይኖረዋል። ይህም ተቋም የማህበረሰቡ አባላት ማዕከላዊነትን ጠብቀው እንዲንቀሳቀሱ ያግዛቸዋል። የመኢኒት ቤሌረሰብ አባላት እንደብሄረሰብ የጠነከረ የእርስበርስ ትስስር እንደሌላቸውና በጎሳ መሪዎቻቸው አመካኝነት እንደሚመሩ አወቀ እንደሚከተለው ገልጾዋል።

"መኢኒቶች የጠነከረ የእርስበርስም ሆነ የፖለቲካ ትስስር የላቸውም። እያንዳንዱ የመኢኒት ማህበረሰብ የራሱ ሆነ መሪ ማለትም ኮሞሩትስ አላቸው። ከኮሞሩትስ በታች ያሉት መሪዎች ኮሞሩትስ በይቶ ይባላሉ። እነዚህ መሪዎች ማህበረሰቡን ለማዘዝ የሚያስችል ሀይል የላቸውም ነገር ግን ከሀገር ሽማግሌዎች የመጣን ትእዛዝ ያስፈፅማሉ።" (Aweke, 2000፣111)

በመኢኒት ቤሌረሰብ ውስጥ ከስልሳ በላይ ጎሳዎች እንዳሉ የመኢኒት ጎልዲያ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግሥት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ በድሉ ይገልጻሉ። እነዚሁ ጎሳዎች የራሳቸው ባባቶች /የጎሳ መሪዎች/ አሏቸው። የጎሳ መሪዎቹ አሁን ድረስ ከፍተኛ ተሰሚነት አላቸው። በመኢኒት ቤሌረሰብ በርካታ ማህበረ ባህላዊ ተቋማት አሉ። በነዚህ ማህበረ ባህላዊ ተቋማት ውስጥ ባባቶች፣ ቃልቾችና የአገር ሽማግሌዎች ህዝቡን በመምራት፣ በመገሰጽና በመምከር ትልቁን ድርሻ እየተጫወቱ ይገኛሉ።

## 1.2.5 ቋንቋ

የመኢኒት ቤሌረሰብ የሚናገረው ቋንቋ "መኢኒትኛ" ሲሆን ቋንቋው ከሱርሚክ ቋንቋዎች አንዱ መሆኑንና ከቴርማ፣ ከቻይ፣ ከባሌሲ /የዚልማሙ ቋንቋ/ ከቦዲና ከሙርሲ ብሔረሰብ ቋንቋዎች ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው አቶ ይገዙ በ1995ዓ.ም. በሱርሚክ ቋንቋች ላይ ያደረጉትን ጥናት ጠቅሶ የክልሉ ህዝብ ፕሮይል አስፍሯል። (የደ/ብ/ብ/ህ/ ፕሮፋይል፣2001)

---

[3] ቃለ፣ ሌሚንቶ፣ ብርሃኑ፣ ካሳ፣ ሚያዝያ 2003

### 1.2.6 ጋብቻ

በደ/ብ/ብ/ህ/፣ በብሔረሰቦች ምክር ቤት በባህል፣ቋንቋ፣ታሪክና ቅርስ ጥናት ተቋም በ2001ዓ.ም ባዘጋጀው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ፕሮፋይል ላይ በመኢኒት ብሔረሰብ የተለመዱ ሦስት ዋና ዋና የጋብቻ አይነቶች እንዳሉ ይዘረዝራል ። እነሱም ጋመን በቤተሰብ ስምምነት የሚፈጸም ጋብቻ ፣ ቀሬን ጉራቤት /የጠለፋ ጋብቻ / እና ቀነስኢ /የውርስ ጋብቻ/ ናቸው። (የደ/ብ/ብ/ህ/ ፕሮፋይል፣2001)

በመኢኒት ብሔረሰብ ከሚፈጸሙት የጋብቻ አይነቶች አንደኛው በቤተሰብ ስምምነት የሚፈጸም ጋብቻ ጋመን ነው። በቤተሰብ ስምምነት የሚፈጸም የጋብቻ አይነት ለሴቷ ቤተሰብ ወንዱ ከ7-12 ከብቶችን እንዲሁም ለሙሽራዋ 500 ብር ጥሎሽ ይሰጣል። አግቢውና የአግቢው ቤተሰብ አቅም ካላቸው የጥሎሹ መጠን ከ15-30 ከብቶች ሊደርስ ይችላል።[4]

ሁለተኛው የጋብቻ አይነት የጠለፋ ጋብቻ ቀራን ጎራቤት ነው። በጠለፋ የሚፈጸም ጋብቻ ጠላፊው ድርጊቱን ከፈጸመ በኋላ ሽማግሌዎች ወደ ልጅቷ ቤተሰብ ይልካል። የተላኩት ሽማግሌዎችም ከልጅቷ ቤተሰብ ጋር ተነጋግረው ስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ ሁለት ከብቶች ጥሎሽ እንዲሰጥ ያደርጋሉ። ጠላፊው ከተወሰነ ጊዜ ቆይታ በኋላ ተጨማሪ ሁለት ከብት የሚሰጥበትን ሁኔታ የሚያመቻቹበትና ጋብቻውን የሚያጸኑበት ነው ።[5]

የመኢኒት ብሔረሰብ ሦስተኛው የጋብቻ አይነት የውርስ ጋብቻ ነው። እንዲህ አይነቱ ጋብቻ የሚፈጸመው ታላቅ ወንድም በሞት ሲለይ ታናሽ የታላቁን ሚስትና ሀብት በመውረስ ልጆቹን እንዲንከባከብና ሌላ ባዕድ ገብቶ በሟች ሀብትና ንብረት እንዳይጠቀም ለመከላከል ታስቦ ነው። ብሔረሰቡ ወንድ ልጅ ለጥሎሽ የሚሆን በቂ ከብት ካለውና ሀብታም ከሆነ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት ይችላል። በዚህም ሳቢያ አንዳንዴ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት የፈለገና በቂ ከብት የሌለው መስዋዕትነት ከፍሎ ከአጎራባች ብሔረሰቦች በጉልበት ዘርፎ ጥሎሽ ያቀርባል።

ከጋብቻ ጋር በተያያዘ ብሔረሰቡ ለሴት ልጅ ክብረ ንጽህና ልዩ ቦታ ስለሚሰጠው ከጋብቻ በፊት ማንኛዋም ልጃገረድ ከወንድ ጋር ግንኙነት እንድትፈጽም አይፈቀድላትም። ይህንን ፈጽማ

---

[4] መሰሉ ኢላኔ ሚያዚያ 2003

[5] በደሉ ኣኔ ሚያዚያ 2003

ብትገኝ ወይም ብትደፈር ተገርፋ በደም እንድትታጠብ ትደረጋለች። የደፈራት ወንድ የቤሔረሰቡን ባህል በመጻፈርና ሥርዓቱን በመተላለፍ ተፈርጆ ከሁለት እስከ ሦስት ከብት ለቤተሰቦቿ በካሳ መልክ ይሰጣል። (የደ/ብ/ብ/ህ/ ፕሮፋል፣2001፣Zerihun፣2008)

## 1.2.7 የስም አወጣጥ

በመኢኒት ብሔረሰብ ስም አወጣጥ የራሱ የሆነ ልማድ አለው። መኤኒቶች ድንገት ደራሽ እንግዳ በአካባቢያቸው መጥቶ እያለ እናትየዋ ብትወልድ ልጁ በእንግዳው ሰው ስም ይሰየማል። ከዚህ በተጨማሪ ተላያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎችም ላይ ብትወልድ የሚወለደው ልጅ ከአጋጣሚዎቹ ጋር ተሳስረው የተሰየሙ ቋሚ ስሞችን ይወርሳል። "Child naming in Me'init depends on different occurrences. For example, if a child is born when a guest is visiting his/her families' house the newborn child gates the name of the guest." (Aweke,2000፣114)

እንዲት እናት ከትልቅ ሰው የቀብር ስነ-ስርአት ስትመለስ ወይም የቀብር ስነ-ስርአት ላይ ልጅ ከወለደች ሞይና ብላ ሀየኑን ትሰይማቸዋለች። የመኤኒት እናት ከገቦ ስትመለስ ወይም ከቦርዴ ቤት ስትወጣ ልጅ ከወለደች ኑርጌ ወይም ሹሉዋ ብላ ትጠራዋለች።

## 1.2.8 ለቅሶ

በመኢኒት ብሄረሰብ የለቅሶና የሀዘን አፈጻጸም ሥርዓት በእድሜ፣ በጾታና እንድ ሰው በሚኖረው ማህበራዊ ከበሬታ ይወሰናል። የመኢኒት ብሄረሰብ ዘመድ ሲሞት ለሟች ያለውን ፍቅርና ሀዘን የሚገልጸው የከብቱን ግንባር በድንጋይ ቀጥቅጦ ከብቱን በመግደል መሆኑን በመስክ ቆይታዬ በቢያገሊች ቀበሌ አቶ አኛኛ ዶሪከሪ ሞተው ተመልክቻለሁ።

በዙውን ጊዜ ለአንድ ሰው የሚገደለው የከብት ብዛት የሚወሰነው በሟች ሰው ያገቡ ሴቶች ልጆች ብዛት ነው። ከብቶቹን የሚያመጧቸው የሟች ያገቡ ሴቶች ልጆች ናቸው። የመረጃ አቀባዬ አቶ ጥጋቡ መንገሻ አባታቸው ሲሞቱ አስራ ሁለት ከብት እንደተቀጠቀጠላቸው ነገረውኛል። በአቶ አኛኛ ዶሪከሪ የቀብር ሥነ-ስርዓት ላይም በርካታ ጥጆች ሲቀጠቀጡ በስፍራው ተገኝቼ ተመልክቻለሁ። ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ ከብት የሚቀጠቀጠውና የሚገደለው በሽማግሌ ወይም በአባውንቶች የቀብር ሥነ ስርዓት ወቅት ነው። በቀብር ሥርዓቱ

ለሟች በርኅታ ከብት የሚቀጠቀጠው ሟቹ በቀጣይ ህይወቱ / ከሞት በኋላ ባለ ህይወት / ከብቶቹን እያረባ ይኖራል በሚል እምነት እንደሆነ የመረጃ አቀባዩና አስተርጓሚዩ አቶ አቶ ብርሃኑ ወርቁ ነግረውኛል።[8] በቤሌረሰቡ ዘንድ አንድ ሰው ሲሞት እስከ አራት ቀን ድረስ አስከሬኑ ተቀምጦ ዘመድ ከያለበት ተጠርቶ እስኪመጣ ይጠበቃል። ህዝቡም ከእኩለ ለሊት ጀምሮ እስከ ንጋት ድረስ በከበሮ በመታጀብ የሀዘን ጭፈራ ይጨፍራል። ከአራት ቀን በኋላ አስከሬኑን በእንቁጢጥ አስቀምጠው ከተገደሉት ከብቶች በአንዱ ቆዳ ላይ ጠቅልለው በማሰር በክብር ጉድጓድ ውስጥ ይቀብሩታል።

ሟች ከተቀበረ በኋላ መቃብሩ አጠገብ ጎጆ በመስራት ቤተሰቦቹ እስከ ሦስት ወራት ያህል መቃብሩን ይጠብቃሉ። በመስክ ቆይታዬ በአቶ እኛኛ መቃብር ላይ የተሰራውን ጎጆ ቤተሰቦቻቸው ከአስራ አምስት ቀን በላይ ሲጠብቁ አይቻለሁ። ይህንንም የሚያደርጉበት ምክንያት ቃምኡት / ሰው የሚበላ ሰው/ ቆፍሮ አውጥቶ ይበላዋል ብለው ስለሚያምኑ ነው። ከሦስት ወራት በኋላ ግን ሸሉ/ቦርደ/ በማዘጋጀት ጎጆውን ያፈርሳሉ። ህጻናት ሲሞቱ ባህላዊ የለቅሶ ዘፈን አይከናወንም።

በለቅሶ ሥርዓቱ ላይ ዘመዶች የሆኑ ተሰብስበው ጥቁር ስስ ካባ አድርገው ግንባራቸው ላይ በሚያስሩት ገርዳላ መሳይ ጨርቅ ስር የሲላ (ላልቶ ይነበብ) ላባ ሰክተው፣ እግራቸው ላይ ገንባሌ አጥልቀውና ሲርጡ ድምጽ የሚያወጣ ቃጭል አስረው አስከሬኑ ያረፈበትን ጎጆ እየዞሩ ሲጨፍሩ አይቻለሁ። ጭፈራው ከጠዋት እስከ ማታ / እስኪቀበሩ ድረስ የቀጠለ ነበር/ በመኢኒት ቤሌረሰብ የአንድ ጎሳ አባላት ጋብቻ አይፈጽሙም። በተለይ በእንደዚህ አይነቱ የጭፈራ ሥርዓት (ቀብር) ላይ የተለያዩ ጎሳ አባላት የሚገናኙበት ስለሆነ መጥፎ ሁኔታዎችም የሚያስተናግድበት አጋጣሚ አለ። በተለያየ ምክንያት ቅሬታና ቁርሾ ያላቸው ሰዎች ሲገናኙ ግጭት ሊፈጥሩበና አልፎ አልፎም እስከ መጋደል ድረስ ሊደርሱ ይችላሉ። እንደዚህ አይነቱ መጥፎ አጋጣሚ ካጋጠሟ ሰዎች ውስጥ ወ/ሮ ዱጊያ ኮንኩላይ የሚከተለውን ነግረውኛል።

> እድሜዬን በውል አላውቅም ያኔ በግምት ከ8 እስከ 10 ዓመት እሆን ነበር። ወንድሜ ሰውዬውን የገደለበት ምክንያት ሰውዬው ሚስቱን ስለደፈረበት ነው። ደፍረው በጠራራ ፀሐይ ጫካ ውስጥ ወስዶ ደፈራት። ከዚያ ወንድሜ በዚያ ጊዜ የወረዳው ኢገማ (የኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበር) ሊቀመንበር ዋና ሰብሳቢ ለነበረው አቶ ሴላ ከሪሮ ይነግረዋል። አቶ ሴላ 'ሚስትህ በጠራራ

---

[8] ብርሃኑ ፣ ሚያዚያ 2003

> ስትደፈር ለምን ዝም ትላለህ? አትገድለውም ወይ?' ብሉ ሲነግረው ሄዶ ገደለው። . . . ብዙም ሳይቆይ አንድ ዘመድ ሞቶብን ጎማ ቀበሌ በዘፈን ላይ /ለቅሶ ላይ/ ተገናኙና በጠራራ ፀሐይ በጦር ወግቶ ገደለው።[7]

ሌላው ለየት ያለ የለቅሶ ሥርዓታቸው ደግሞ ማህበራዊ ክብር ያለው አባወራ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ በሞተበት ስፍራ መኖር ለጤና አይበጅም በሚል የሟች ቤተሰቦች በሞላ አካባቢያቸውን ለቀው የሚሰደዱበት ነው። የቀድሞ መኖሪያቸውን ጥለው ሲሰደዱ በህይወት ዘመኑ ያፈራቸውን ንብረቶቹን፣ የመኖሪያ ቤቱንና በመኖሪያ ቤቱ አካባቢ የሚገኘውን ማንኛውንም ነገር ከጎጆው ጋር በእሳት አቃጥለው ይሄዳሉ። በሚደርሱበት ሰፈርም አዲስ ጎጆ በመቀለስ አዲስ ኑሯቸውን ይጀምራሉ። (Zerihun፣2008)

## 1.2.9 እምነት

በመኢኒት ብሔረሰብ አምላክ ቱማ /Tumma/ ወይም የሪ /Yerry/ ይባላል። ይሄውም ከሰዎች በላይ የሆነ ነው። አምላካቸው የሁሉ ነገር ፈጣሪ የሆነና በሰማይ የሚኖር ነው። የመኢኒት ብሔረሰብ አባላት የሪ የተባለውን የአምላካቸውን መጠሪያ በመደበኛነት ይጠቀማሉ። የሪ ቤት እንደሌለውና የሚኖረውም በእያንዳንዳቸው ልብ ውስጥ እንደሆነ ያምናሉ። ቱማ የሚለውን የአምላካቸውን ስም ደግሞ ከዝናብ ጋር በማያያዝ ይጠቀሙበታል።

የመኢኒት ብሔረሰብ የሃይማኖት ታሪክ በሦስት የተለያዩ ዘመናት ሊታይ እንደሚችል ዘሪሁን ይጠቅሳል። የመጀመሪያው ዘመን የመኢኒት ብሔረሰብ ያራሱ የሆነ የሃይማኖት ፍልስፍና ይዞ ቱማ/Tumma/ን እና የሪ/Yerry/ን ማምለክ የጀመረበት ዘመን፣ ሁለተኛው ዘመን አሁን ድረስ በስፋት ያለና መኢኒቶች ሃይማኖትን ከአጎራባች ማህበረሰቦች ማለትም ከካፋና ከቤንች በመዋስ የጀመሩበትና በጠንቋይና በቃልቻ ማመን የጀመሩበት (በተለይም ኔሪ የተባለው ቃልቻ ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበረሰባዊ ኃይልን የተቀዳጀበት ጊዜ) እና ሦስተኛው ዘመን ደግሞ ዘመናዊ ሃማኖቶች ማለትም የኦርቶዶክስ ክርስትና፣ የሙስሊም እና የፕሮቴስታንት ሃይማኖቶች መምጣት የጀመሩበት ነው። ስለዚህ ጉዳይ ዘሪሁን የሚከተለውን ጽፏል፤

> The first epoch constituted the time when, from the beginning, the me'enit practiced their own religious philosophies and rituals based on the Tumma and

[7] ፌሰሃ፣ ሚያዚያ 2003

> Yerri concepts. ... The second epoch represented the time when the me'enit began borrowing religious concepts and practices from the nighboring ethnic groups, notably the Keffa and Bench. ... the third epoch in the religious history of the me'enit may be termed as the epoch of "modern" religions.[8]

በአጠቃላይ የመኢኒት ብሔረሰብ ሃይማኖት ሲዳሰስ አሁንም ድረስ ባህላዊ የእምነት ተቋማቱ / የቃልቻ አስተዳደሩ/ በቆላው በተለይም በመኢኒት ሻሻ የሚያገለግል ሲሆን በመኤኒት ጎልድያም አብዛኛው ህዝብ የዚሁ እምነት ተከታይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የፕሮቴስታንት ሃይማኖትም በተለይም ለከተማ ቅርብ በሆኑ ቀበሌዎች ስፊ ተቀባይነት እያገኘ ነው፡፡ አውራ የመረጃ አቀባዮቼ እንደነገሩኝ ደግሞ ወጣቱ ክፍል የመጤውን ሃይማኖት / ፕሮቴስታንት/ እየተቀበለ እንደሆነና በእድሜ ገፋ ያሉት እና በቆላ የሚኖሩት በሙሉ በቃልቻ እንደሚያምኑ ነግረውኛል፡፡[9] እኔም ጥናቱን ጥካሄድኩበት ጊዜ በቢያጌሊች መንደር በአቶ አኛኛ ዶሪከረ የቀብር ቀን በአካል ተገኝቼ ቀጥራቸው ከሃያ የማያንሱ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች በምስጋናና በዝማሬ ክበር እየሙቱ ሥርዓቱን ሲታደሙ አይቻለሁ፡፡

## 1.3 የተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት / ክለሳ ድርሳን

በዚህ ርእስ ስር የግጭት ምንነት (ብያኔ)፣ የግጭት አይነቶች፣ ስለግጭት መንስኤዎች የሚያትቱ ንድፈ ሀሳቦች፣ የግጭት አፈታት ዘዴዎች፣ እንዲሁም ከግጭት ጋር በቀጥተኛ መልኩ ተያይዘው በትምህርት ክፍሉ እና ከትምህርት ክፍሉ ውጭ የቀረቡ የተለያዩ ጥናቶች የሚዳሰሱበት ነው፡፡ ስለ ግጭት ምንነት፣ መንሻ ምክንያቶችና የግጭት አይነቶች፣ ግጭት ስለሚያስከትለው የተለያ ገጽታ የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ ጊዜያት የየራሳቸውን ድፍየና አቅርበዋል፡፡ የስነ ልቡና፣ የስነ ልሳን፣ የስነ ሰብእ፣ የሕግና የፖለቲካ ተመራማሪዎች እንደየ ዘርፍና እንደየ አመለካከታቸው ብያኔያቸውን ሰጥተዋል፡፡

---

[8] Zerihun 2008

[9] ሊማንቶ፣ ሌላ፣ ዋዋቹ፣ ሚያዚያ 2003

### 1.3.1 የግጭት ምንነት (ብያኔ)

የሰው ልጅ ከፍጥረቱ ጀማሪ አንስቶ እሁን እስከደረሰበት የእድገትና የሳይንስ ዘመን ድረስ የተለያዩ ግጭቶች ወይም ጠቦች ተለይተውት እንደማያውቁ ብዙ ምሁራን የሚስማሙበት ጉዳይ ነው።

ግጭት ወይም ጠብ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች እንደሆኑና በተላውጦ እንደሚያገለግሉ የገለጸው ጎቨር /Gover/ ነው። ጎቨር ስለ ግጭት ምንነት የሚከተለውን ብሏል። በእርሱ አስተያየት "ግጭትና ጠብ በአብዛኛው በተለዋዋጭነት የሚያገለግሉ ቃላት ናቸው።" (Gover፣1976፣655 )። ፊሸር እና ሌሎች /Fisher Etal/ ደግሞ ግጭት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር ተቃርኗዊ ስሜትና እንዳቸው እንዳቸውን ለመቆጣጠር ካላቸው ጽኑን ፍላጎት የተነሳ ተቃራኒ ግቦችንና እንቅስቃሴዎችን ይዞ እንደሚፈጠር በሚከተለው ጥቅስ ያስረዳሉ ። "Conflict is a relationship between two or more parties (individual or group) who have or think they have incompatible goais" (Fisher፣1982፣567)

የኢታልን ሀሳብ የሚያጠናክርና ተቀራራቢ ሀሳብ ሚሰነዝረው ሌላው ተመራማሪ ደግሞ ሌቪንሰን(Levinson) ነው። ግጭት በፍላጎት አለመጣጣም የተነሳ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል የሚፈጠር ነው "Conflict refers to perceived divergent interest between two or more parties " (Levinson፣1996፣237) ከላይ የተጠቀሰው ድፍየና የተቃርኖው መጸነሻ አንድ አይነት የሆነ የጋራ ፍላጎት ነው። የሰው ልጆች ደግሞ በጋራ በሚኖሩባት ምድር ላይ የፍላጎት አለመጣጣም ዘወትራዊና ተደጋጋሚም እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ለዚህም ነው ዛርትማን (Zartman) ግጭት ሊወገድ የማይችል በሰው ልጆች የእርስበርስ ግንኙነት ወቅት ካላቸው ምርጫና ፍላጎት ጋር የተጋመደ ነው የሚል ሀሳብን የሰነዘረው።"... Conflict is an evitable aspect of human interaction, an avoidable concomitant of choices and dicisions. " ( Zartman,1991,299)

በሌላ መልኩ በተለያየ መቀስቀሻ መንገዶች የሚከሰቱት ግጭቶች የአዳዲስ ለውጦች ምንጭ የመሆን እድላቸው ሰፊ ነው። ኮዘር (Coser) ማንኛውም ህብረተሰብ በውስጡ ባለው የግጭት ተንኳሽነት በለውጥ ሂደት ተሳታፊና የላቀ አስተሳሰብ ባለቤት ይሆናል። (Coser,1970,25)

የሚል አስተሳሰብ ሲሰነዝር የእሱን ሀሳብ የሚያጠናክርና የግጭት መኖር ለማህበረሰብ አዳዲስ ለውጦች መፈጠሪያና ተፈጥሯዊ ማነቆዎችንም ማስወገጃ እንደሆነ የሚያስተነትኑት ደግሞ ራምስ ቦትሀምና ሌሎች ናቸው። "ግጭት ለማህበራዊ ለውጥ ተፈጥሯዊ እንቅፋቶችን በማስወገድ አዳዲስና የተለያዩ እሴቶች፣ ልማዶችና ፍላጎቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል" (Ramsbotham,Etal,1984.)። ይሁን እንጂ በማንኛውም መልኩና በየትኛውም ደረጃ የሚከሰት ግጭት ይብዛም ይነስም በግለሰብ፣ በቡድን እና በማህበረሰብ ላይ የራሱ የሆነ በጎ ወይም መጥፎ ተጽእኖ ይኖረዋል።

የግጭትን አሉታዊ ጎን በማጉላት በሰው ልጅ ማህበረሰባዊ ግንኙነት ሰላምን የሚያደፈርስ፣ አሉታዊ ተጽእኖ ያለውና እሴቶችን የሚያናጋ እንደሆነ ሩሚልን (Rummel,2007) ዋቢ በማድረግ መስፍን ይልማና መስፍን ባንታየሁ ገልጸዋል። ( Mesfin,2007) ሄንሪክ ዎልፍጋንግ ደግሞ ግጭት ከአዎንታዊ ጎኑ ውጭ አሉታዊ መልክ እንዳለው ግልጽ መሆኑን ካብራራ በኋላ የግድ መፈታትና መወገድ እንዳለበት ገልጸዋል። "Conflict must be resolved, and made to disappear" (Wolfgang,1997,3) የግጭት አሉታዊና አፍራሽ ጎኑ የሚገለጠው ግጭት ውስጥ የገቡት ወገኖች መጨረሻ በሚገኘው ውጤት ተጠቃሚ ሳይሆኑ ሲቀሩና ያገኙትም ጥቅም እንደሌለ በተሰማቸው ጊዜ እንደሆነ ያብራራው ደች (Deutch) የግጭትን አዎንታዊ ጎን ሲገልጸ ግጭት ገንቢ የሚሆነው ግጭት ውስጥ የገቡት ወገኖች በውጤቱ ሲደሰቱና በግጭቱም ሰበብ ያጡት ነገር የሌለ መሆኑን ሲገነዘቡ ነው በማለት ገልጽዋል (Deutch,1973,17 )። በአጠቃላይ ከላይ ከተሰጡት የተለያዩ እሳቤዎች በመነሳት ግጭት ለማህበረሰባዊ እድገት የራሱ ሆነ ጠቃሚና ጎጂ መልኮች እንዳሉት ሆኖም በእለት ከዕለት የህይወት ተራክቦ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚከሰት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

## 1.3.2 የግጭት አይነቶች

የግጭት አይነቶች በርካታ እንደሆኑ ምሁራኑ ይገልጻሉ። ይሁን እንጅ ዘርፈ ብዙ የሆኑት ግጭቶች በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ የሚገናኙበት ወይም የሚጓደኑበት የጋራ ባህሪያት አያጡም። እናም አንዱን በአንዱ ውስጥ በማዋገን ዋና ዋና የሆኑትን ለይቶ ማመላከት ይቻላል። ዋና ዋና የግጭት አይነቶች በሦስት እንደሚከፈሉ ክራይድሰር (Kreidier) ሲገልጽ የሀብት ክፍፍል፣ የፍላጎት አለመጣጣም እና የእሴቶች ግጭቶች እንደሆኑ ጠቅሷል። እነዚህን ዋና ዋና የግጭት አይነቶች ዘርዝሮ ሲያስረዳም የሀብት ክፍፍል ተመጣጣኝ የሆነ የመሬትና

የውሃ ክፍፍል በሌለበት ሚፈጠር፣ የፍላጎት አለመጣጣም የፍላጎትን አለማግኘትና የፈለጉት ጉዳይ በሌላ ሲያዝ ያንን የራስ ለማድረግ በመፈለግ የሚፈጠር እንዲሁም የእሴቶች ግጭት የአንድ ማህበረሰብ የተለያዩ እሴቶቼ በሌላ ወገን ሲጣሱ የሚፈጠር እንደሆነ ገልጧል፡፡ (Kreidier,1984)

ይሁን እንጂ የተለያዩ ምሁራን የግጭት አይነቶችን የሰደሩበት መደብ፣ የሰፈሩበት ቁና እና ያጊደኑበት መልክ ለየቅል ነው፡፡ ከዚህም አንጻር ምሁራኑ የግጭት አይነቶችን በመዘኑበት መስፈሪያና ባነጸሩበት አቅጣጫ መልክ መልክ በመስጠት ተንትነውታል፡፡ ከተሳታፊዎች አይነትና ብዛት በመነሳት ግላዊ (intra-personal)፣ግለሰባዊ (inter-personal)፣ የቡድን ውስጥ (intra-group)፣ የቡድኖች( inter-group)፣ የሀገር ውስጥ (intra-state) እና የሀገራት (inter-state) በማለት የመደበው ደግሞ መድኃኔ ነው፡፡ (Medhane,2004,3)

## 1.3.3 ስለ ግጭት መንስኤዎች የሚያትቱ ንድፈ- ሀሳቦች

አንዳንዶች የግጭቶቹን ሰበብ የራሱ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ማንነት እንደሆነ ሲያስተነትኑ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ሰው በተፈጥሮው የተነሳ የሚፈጥረው ሳይሆን ሰው ማህበረሰባዊ እንስሳ በመሆኑ አንደኛው ከአንደኛው ጋር በሚያደርገው ማህበረሰባዊ መስተጋብር እንደሆነ አስረግጠው ያስረዳሉ፡፡ በአንጻሩ ሰው ማህበራዊ ፍጡር በመሆኑ በሚፈጥራቸው የጋራ ማንነትና የማንነት መገለጫዎች ሳቢያ ፖለቲካዊና መሰል ግጭቶችን መውሰዱ የግድ እንደሆነ የሚያብራሩ በርካታ ምሁራን አሉ፡፡

ስር የሰደደ ድህነት መጠኑን እያበዛና እየጸነነ ሲሄድ የሰው ልጅ የዘር ብዜት መጠን ወይም የህዝብ ብዛት በፍጥነትና በአስደንጋጭ ሁኔታ ማሻቀብ በሚጎትተው ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትርምስ ግጭቶች እዚህም እዚያም እንዲከሰቱ ሰበብ ይሆናል፡፡ ይሄንን የሀሳብ መስመር ተከትለው ከተሰጡት ድፍየናዎች አንዱ ከማሕበራዊ ሳይንስ ጎራ የሆነው ኩፐር ነው፡፡ ኩፐር ስለ ግጭት መቀስቀሻና ሰበቡ የሰው ልጅ የሚያደርጋቸው ማሕበራዊ ተራክቦዎች ማለትም ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣እና ፖለቲካዊ ግንኙነቶች እንደሆነ አስቀምጧል (Kuper,1996,124)፡፡

ሌላው ዋና የግጭት መቀስቀሻ ሰበብ ደግሞ የእኩልነት መብት መጓደል ነው፡፡ የእኩልነት መብት መጓደል ቀጥተኛ የግጭት መቀስቀሻ እንደሆነ በርካታ ምሁራንም ያስተነትናሉ፡፡ ከእነሱም ውስጥ ጄንግ ይጠቀሳል፡፡ (Jeong,2000,34) የግጭት ሰበብ ስልጣንና ሀብት

በጥቂቶች መዳፍ ውስጥ መውደቁ ነው። ጥቂቶችም ይሄንኑ ሀብት ለመጠቀም ስልጣናቸውን መከታ እንደሚያደርጉና ሌላውን መጨቆኛ ስለሚያደርጉት የብዙሀኑ ጥያቄ የግጭት መቀስቀሻ ሰበብ መሆኑ አይቀርም ። ይሄንን ሀሳብ ካርል ማርክስ ማስተንተኑን ሌዊስ ኮዘር ሲገልጸዋል "... Conflict is rooted in the social system in which both scarce resources and power found under the command of a few." (Coser,1959) ፍትሀዊና የተማከለ የሀብትና የስልጣን ክፍፍል አለመኖር የሰብዓዊ መብት ጥሰትን ያመጣል። ህዝብን ለማያባራ እንግልት የሚያጋልጡ ቀውስ በመዳረግም ማህበረሰባዊ ተቋማቱ እየተናጉ የእርስበርስ ጦርነትና ብጥብጥ እንዲስፋፋ ያደርጋል። እንዲህ አይነቱ የግጭት መንስኤ ደግሞ በአፍሪካ ውስጥ ለሚከሰቱ ግጭቶች ዋና መሰረታቸው እንደሆነ አዴዴጂ (Adedeji,1999,94) በሚከተለው መንገድ ያብራራዋል።

## 1.3.4 የግጭት አፈታት ዘዴዎች

በዓለማችን ውስጥ በተለያዩ አህጉሮች ያሉ ሀገራት ሉአላዊነታቸውን ጠብቀው በመከባበርና ቢጋራ ጥቅሞቻቸው ዙሪያ በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ በመተጋገዝ ይኖራሉ። እንደመደጋገፍ፣ መረዳዳታቸው ሁሉ በተቃራኒው በመካከላቸው የሚከሰቱ በርካታ አይነት ግጭቶችም ያስተናግዳሉ። እናም እነዚህን ግጭቶች በማርገብና በመፍታት ሀገራት ሰላማቸውን ጠብቀው ቢጋራ ምድራቸው ላይ በሰላም እንዲኖሩ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ደንቦችንና ህጎችን ያወጣሉ። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትና የአፍሪካ ህብረት፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች ግጭትን ከመፍታትና ሰላምን ከማስፈን አንጻር ያላቸውን አተያይ በዚህ ርዕስ ስር እንመለከታለን።

- የግጭት አፈታት ዘዴ በዓለም አቀፍ ደረጃ

ዓለም ከፍተኛ የሰው ልጆች እልቂት ካስተናገደችበት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በ1945 ዓ.ም. የተመሰረተው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት በዓለም ላይ ሰላምን በዲፕሎማሲና በተባበሩት መንግሥታት ሰላም አስጠባቂ ኃይል አማካይነት ሰላምን እንዲያሰፈጽሙና ኃላፊነቱን እንዲወጣ ስጥቶታል። በዓለማቀፍ ደረጃ ግጭትን ለመፍታት ኃላፊነት ያለበት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስር የተደራጀው የጸጥታው ምክር ቤት ኃላፊነቱ በዓለም ላይ የሚከሰቱ ግጭቶችን መቆጣጠርና ማስወገድ ነው።

የድርጅቱ ቻርተር አንቀጽ 39 ድርጅቱ ዓለም ዓቀፍ ችግሮችን የመመርመር፣ የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብና የመወሰን ስልጣን እንዳለው አስቀምጠዋል። ድርጅቱ በመተዳደሪያ ቻርተሩ ውስጥ በተለያዩ አንቀጾች የግጭት ማስወገጃ ደንቦችንም አስቀምጧል። አንቀጽ 33 ቁጥር 1 ላይ የሰፈረው ደንብ፣ የዓለም አቀፉን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ አዳጋች ሆኖ ከቀጠለ በግጭት ውስጥ ያሉ ፓርቲዎች በቅድሚያ በስምምነት (Negotiation)፣ እውነትን በማፈላለግ (Enquiry)፣ በድርድር (Meditation)፣ በእርቅ (Conciliation)፣ በሦስተኛ ወገን ዳኝነት (Arbitration) በህጋዊ ስምምነት (Judical settement)፣ በአካባቢያዊ ድርጅቶች እገዛ (Resort to regncies) ወይም እራሳቸው በመረጡት ሰላማዊ መንገድ መፍትሄ መፈለግ አለባቸው በማለት አስቀምጧል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሀገራት መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመቆጣጠር መልዕክተኛ ቡድኖች ግጭት ወደ ተነሳባቸው የተለያዩ አገሮች ልኳል። በኢትዮጵያና ኤርትራ፣ በቦስኒያ ሄርዞጎቪኒያ፣ በአፍጋኒስታን፣ በሴራሊዮን፣ በላይቤሪያ ያደረጋቸው እንደአብነት የሚጠቀሱ ናቸው። ይሁን እንጂ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተለያዩ ሀገራት ያደረጋቸው ሰላም የማስከበር ሥራዎች ዘላቂ ሰላምን ከማምጣት አንጻር ውጤታቸው ሚዛን የሚደፋና አመርቂ እንዳልሆነ የተለያዩ አካላት ይተቻሉ።

- የግጭት አፈታት በአፍሪካ አንድነት ድርጅትና በአፍሪካ ህብረት የህግ ሰነዶች

ከሰባቱ የክፍለዓለማችን አህጉራት አንዷ አፍሪካ ብዙ ግጭቶች የተፈጠሩባት አህጉር ናት። እጅግ ብዙ ህዝብም አልቆባታል። እጅግ ዘግናኝና አስቃቂ ግድያዎች የተፈጸሙባት ምድርም ናት። አፍሪካውያንም እነዚህን ግጭቶች የሚያስወግዱበት የራሳቸው ድርጅት አቋቁመዋል።

በ1963ዓ.ም ዓላማውን የአፍሪካ ሀገራት አንድነትና ወዳጅነትን የማጠናከር አድርጎ የተመሰረተው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አብይ አላማዎቹን በቻርተሩ አንቀጽ 2፣1 ላይ እንደሚከተለው ዘርዝሯቿል።

- ✓ በመላው አፍሪካ ውስጥ የቅኝ አገዛዝ ሥርዓትን ማጥፋት፣
- ✓ የአፍሪካ ህዝቦችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል እንዲሁም
- ✓ የተባበሩት መንግሥታት ስምምነቶችንና የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን ማክበር ናቸው። (O.A.U.1963,2,1)

ድርጅቱ በቻርተሩ Article 19 ላይ የድርድር፣ የእርቅ እና የሦስተኛ ወገን ዳኝነት እንዲመሰርቱ ለአባል ሀገራቱ ይፈቅዳል። (Article 19)። የለውጥ ጉዞዎችን በማድረግ በ2000 ዓ.ም. የተቋቋመው የአፍሪካ ህብረት የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 3 ደግሞ አብይ ዓላማዎቹ አድርጎ የሚከተሉትን አስቀምጧል። የአባል አፈራቱን የድንበር ወሰን ማክበር፣ በአገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት፣በአገሮች መካከል የዘር ማጥፋትና የሰብአዊ መብት ረገጣዎች ሲከሰቱ ጣልቃ መግባት፣ በሰላም የመኖር መርህን ማዳበር፣ የአባል አገሮች ሰላምና ደህንነት ማክበርና ዲሞክራሲያዊ መረጋጋቶችን፣ ሰብዓዊ መብቶችን፣ የህግ የበላይነትንና መልካም አስተዳደርን ማጠናከር ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ በአፍሪካ የተለያዩ ዞኖች የኢኮኖሚ ትብብርና ውህደት ለመፍጠር በማለትየጠቋቋሙ አራት የአፍሪካ ህብረት አጋዥ ድርጅቶች አሉት። ይሁን እንጂ እነዚህ የየተጣናው ድርጅቶችም ሆኑ ህብረቱ የአህጉሪቷን ሰላም በማስጠበቅና ዘላቂ መፍትሄ በመስጠት ያበረከቱት ፋይዳ ሚዛን የሚደፋ እንዳልሆነ በብዙ ምሁራን ይተቻል። (Cervenka,1977)

- የኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች ከግጭት አፈታት አንጻር

ዘመናዊ የህግ ሥርዓት በኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት አገሪቱ በፍትሃ ነገሥት ትተዳደር እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። እስከ 15ኛው ክፍለ ዘመንም ድረስ ይሄው ፍትሃ ነገሥት አገልግሏል። "በ15ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተተርጉሞ አገራችን የገባው የርግ ህግ ነበር።" (አምሳሉ፣1976፣64)። በ1948ዓ.ም. ተሻሽሎ የወጣው የኢትጵያ ህገ-መንግሥት ዘመናዊነት አልነበረውም። የሥርዓቱን የበላይዎች እንጂ የህዝቡን መሰረታዊ ጥያቄዎች በያዘ መልኩ የወጣ አልነበረም። በ1980ዓ.ም. በአገሪቱ የወጣው ህገ- መንግሥትም ለባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ቦታ የሰጠ አልነበረም። በአንቀጽ 34፣4 ላይ በባህል የህግ ሥርዓቶች ላይ ለሚፈጸሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ህግ ሊወጣ እንደሚችል አስቀምጧል። በ1987 ዓ.ም. የወጣው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ህገ-መንግሥት ጥቂት ባህላዊ እሴቶችን በማካተት ከቀደሞቹ የተሻለ ነው። በዚህ ህገ- መንግሥት ውስጥ የተካተቱትን የህግ ሰነዶች ከዚህ ቢታች ለማየት እንሞክራለን።

አንቀጽ 9 ህጉ መንግሥቱ የህጎች ሁሉ የበላይ እንደሆነ ተደንግጓል። አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 የግልና ቤተሰብ ህግን በተመለከተ በባህል ወይም በሌሎች መዳኘትን ይፈቅዳል። የሃይማኖትና የባህል ፍርድ ቤቶችና ለማቋቋም ወይም እውቅና ለመስጠት የሚያስችለው አንቀጽ ደግሞ አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ 5 ነው። ጠቅለል ባለ መልኩ ለባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ጥርት ያለና ተገቢ እውቅና የሰጡ አንቀጾች አልተካተቱም ።

- የፍትሐብሔር ህግ

በ1960ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ህግ ውስጥ የልማድ ጋብቻዎች፣ በባልና ሚስት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በሽምግልና እንዲፈቱ፣ ለመጋባት ወስና ውል ያፈረሰ ካሳ እንዲከፍል፣ ከጋብቻ በፊት ክብረ ንጽህናዋን የተደፈረች ሴት በአገር ሽማግሌውች ወይም በቤተ ዘመዶች ታይቶ ካሳ እንዲከፈላት፣ በጋራ መጠቀሚያ መሬቶችና ተጠቃሚዎች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶች በአገሩ ልማድ እንዲፈቱ እድሉችን ሰጥቷል።

## 1.3.5 በአገር ውስጥ የተጠኑ አንዳንድ ባህላዊ የግጭት ሥራዎች

ይህ አጭር ዳሰሳዊ ጥናት የሚያተኩረው በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ በተሰሩ የ2ኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች እንዲሁም በአንድ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ነው። በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል እንዲሁም ከሌሎች የትምህርት ክፍሎች ወደ 18 የሚደርሱ ጥናታዊ ጽሁፎች ያገኘሁ ሲሆን፣ ለዚህ ጥናት የማቀርባቸው አምስቱን ብቻ ነው። አብርሃም ታደሰ (1999) "ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሔረሰብ"፣ ይልማ ተፈሪ በ1998ዓ.ም. "የሽምግልናና እርቅ ሥርዓት በወላይታ"፣ የወንድወሰን አውላቸው በ1998ዓ.ም.፣ ተመስገን ምንዋጋው በ1998ዓ.ም. "ህገረሰባዊ የግጭት መፍትሄ ሥርዓት በዶኮ ጋሞ" እና የዳንኤል አሰባቸው ፣ 1984ዓ.ም "ጋብቻ ትውፊት በመኢኒት ብሔረሰብ" ናቸው። ጥናቶቹንም የመረጥኩበት ከእኔ ጥናት ጋር ቅርበት አላቸው ያልኳቸውን በደቡብ ብሄር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ውስጥ በተሰሩ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ላይ ስላተኮሩ ነው። ከዚህ በተጨማሪ አንዱ የመጀመሪያ ድግሪ ጥናት የርዕስ ልዩነት ቢኖረውም በቀጥታ ያተኮርኩበት ብሔረሰብ ላይ የተሰራ በመሆኑ መርጨዋለሁ። ጥናቶቹ ያነሷቸውን ዓላማዎች፣ የተከተሉትን የንድፍ ሃሳብ ስልት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴያቸውንና የመረጃ መሰብሰቢያ ምንጮቻቸውን እንዲሁም የንለዩና የማጠቃለያ ትንታኔያቸውን አይቻለሁ።

1999ዓ.ም. አብርሃም ታደሰ "ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሔረሰብ" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረበው ጥናት ነው። የጥናቱ ዓብይ ዓላማ በሲዳማ ብሔረሰብ ውስጥ የሚከናወኑትን ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች፣ ሥርዓቶችና ደንቦች ማጥናት፣በብሔረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱትን የተለያዩ የግጭት አይነቶች መጠቆምና እነዚህን ፍጭቶች በባህላዊ መንገድ የሚፈቱት አካላት የትኞቹ እንደሆኑና በእርቁ ወቅት የሚጫወቱትን ሚና ማጥት ነው። በጥናቱ እንደተጠቆመው በአብዛኛው የሚከሰቱት የግጭት አይነቶች ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ መሆናቸውን አሳይቷል። ከዚህ በተጨማሪም የተወሰኑ ተረትና ምሳሌዎች ለባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓተ ተፈጻሚነት የሚጫወቱትን ሚና አመላክቷል። ጥናቱ አብይ ትኩረት ያደረገው ሽምግልናና ተረትና ምሳሌዎች ለእርቅ ሥርዓቱ ያላቸውን ሚና እንጅ የክዋኔዎቹ ትዕምርታዊ ትርጉሜ እንዲሁም ተቋማቱ ያላቸውን ፈርጀ ብዙ ፋይዳዎች ትኩረት አልሰጠም።

ይልማ ተፈሪ በ1998ዓ.ም. "የሽምግልናና እርቅ ሥርዓት በወላይታ" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበው ጥና አንዱ ነው። በጥናቱም የወላይታ ብሔረሰብ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀምባቸውን ተቋማት ገልጾዋል። ጭግላ፣ጨቆ፣ጨሜ፣ሜታ እንደሆኑ።በነፍስ ግድያ የግጭት አፈታት መሰረት ሰው የገደለ በሚስጥር ሽማግሌዎችን ያነጋግራል። ከዚያም ለሟች ቤተሰብ ይላካል። የሟች ቤተሰብ ለእርቁ ፈቃደኛ ሲሆኑ ገዳይ ፊቱን ጥላሸት ተቀብቶና ደረቅ የከባ ቅጠል ሰውነቱን ሸፍኖ ወልደው ያበቁ ላምና በግ ጎትቶና አንገቱን አቀርቅሮ እንዳጠፋና ምህረት እንደሚያስፈልገው እየተናገረ ከሽማግሌዎች ሥር ይቀርባል። እርቁ ከወረደ በኋላ ገዳይ ያመጣቸውን እንስሳት ሽማግሌ ባርኮ ደማቸውን እያጠቀሰ ገዳይንና የሟችን የቅርብ ቤተሰብ ከዚያም የሁለቱንም ወገኖች በሙሉ መሀል ግንባራቸውን እንደሚቀባቸው በጥናቱ አሳይቷል። ጥናቱ ሥርዓቱን ሂደት የመግለጽ እንጂ የሚከወኑት ሥርዓቶች ፋይዳቸውንና ትርጓሜያቸውን አላሳየም።

የወንድወሰን አውላቸው በ1998ዓ.ም. "የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደርና የግጭት አፈታት" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረበው ጥናት ነው። ይህ ጥናት ያተኮረው የግጭት ምክንያቶች፣ የግጭት አይነቶችና የግጭት መፍትሔዎችን ማመላከት ላይ ነው። በአካባቢ ድንበር መጋፋት፣ ስርቆት፣ ቤት ማቃጠልና ንብረት ማጥፋት የግጭት መንሻ ምክንያቶች እንደሆኑ ገልጾጸዋል።የግጭት

አይነቶች ከሆኑት ውስጥ የቤተሰብ የልጆች፣ የጎሳ ሲሆኑ ለተጠቀሱት የግጭት አይነቶች የተጠቀሱት የግጭት መፍቻ ተቋማት ደግሞ የመኖሪያ አካባቢን እና ጎሳን መሰረት አድርገው የተዋቀሩ ሁለት አይነት ተቋማት ናቸው። እነዚህም ተቋት ስምንት አይነት የአስተዳደር መዋቅር አላቸው። እነሱም ቤተሰብ፣ ቤተ-ዘመድ፣ጎሳ፣አካባቢ፣ጀፎሮ፣ቃያ፣ክፍለ ጉራጌ እና የጆካ የተሰኙ ናቸው። ተቋማቱ ግጭትን የሚፈቱት በሽምግልናና እርቅ እንዲሁም ዳኝነት በማየት ነው። በአጠቃላይ ጥናቱ ሀገረሰባዊ አስተዳደርና ግጭት የመፍቻ ሥርዓቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።

ተመስገን ምንዋጋው በ1998ዓ.ም. "ሀገረሰባዊ የግጭት መፍትሄ ሥርዓት በዶኮ ጋሞ" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረበው ጥናት ነው። በጥናቱ ውስጥ ዋና ዋና ግጭቶች የሚመነጩት በነፍስ ገድያ፣በንኦ፣በድንበር፣ የሰው ሚስት በመድፈርና በዘመዳሞች መካከል በሚፈጸም የግብረ- ሥጋ ግንኙነት ነው። እነዚህን ግጭቶች ሚፈቱት መለኮታዊ ኃይል እንዳላቸው የሚታመኑ ሹማንምት እንደሆኑ ጥናቱ ይጠቁማል። ሽማምንቱም እርቁን የሚያከላሁዱት በአደባባዮች ነው። የሚፈጠሩትን ግጭቶች ለመፍታት ስምንት ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት አሉ። ማካ፣ኒቃ-አቃ፣ካሬ፣በላና ደና፣ኤሬርሶ እንደሆኑ ገልጾዋል።

ሌላው የዳንኤል አሰባቸው ፤ 1984ዓ.ም "ጋብቻ ትውፊት በመኢኒት ብሔረሰብ" የሚል ጥናት ነው። በጥቱ ውስጥ ዓላማ አድርጎ ካስቀመጣቸው ውስጥ ጠንካራና በአብዛኛው መልኩ ደካማ ጎን የሚንጸባረቅበትን ይህን ትውፊት፣ ማንኛውም ኢትጵያዊ ዛሬ ነገ ሳይል እንዲያስተምርና እንዲያሳውቅ ፤ ለወደፊቱ ከጥናቱ ጋር የተመሳሰለ አልያም እሱኑ መሰል ጥናት በዳበረ መልኩ ማቅረብ ለሚሹ ምሁራንም ሆነ የተለያዩ ግለሰቦች መንደርደሪያ እንዲሆን ነው። ጥናቱም የሚያጠነጥነው የትና ምን አይነት ህይወት እንደሚኖሩ በአብዛኛው አጥኚዎችም ሆነ ጥናት አቅራቢዎች ብዕር ባልተዳሰሰው እጅግ 'ሁዋላ ቀር' በሆነውና ለማመን እንኳን አስቸጋሪ የሆነ አያሌ ባህሎች በተስገሰገበት በመኢኒት የጋብቻ ትውፊት ላይ እንደሆነም አስፍሯል። ስለ ብሄረሰቡ ማንነትና የት መጣኑት፣ ስለተደረጉ ጦርነቶች፣ ስለ መልክአ ምድሩና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ፤ የመኢኒት ብሔረሰብ አባላት የአስተሚጪት ሥነ- ሥርዓትና የሰርግ ሥነ- ሥርዓት አንስቷል። ከዚህ መተጨማሪ የመኢኒት ብሔረሰብ ሰርግ ትውፊታዊ ድራማዊ ገጽታዎች / የድራማ አላባውያን/ እንዳለው አንስቷል። እነሱንም ከዋኝ፣ ተመልካች፣

አልባሳትና ቁሳቁስ፣ ሙዚቃና ጭፈራ፣ የመታያ ስፍራዎች፣ ቃለ- ምልልስ እና ገፀ- ቅብ መሆናቸውን ገጽዋል።

በአጠቃላይ የዳንኤል ጥናት መሰረታዊ የጥናት ፎርሞችን ያልተከተለ ሲሆን ብሔረሰቡን ኋላ ቀር እና ባህሉንም ደካማ እያለ የሚተች ነው። ይህ ደግሞ ተገቢ አስተያየት አይደለም። የትኛውም ማህበረሰብ ያከበራቸውና የኔ መገለጫዎች ናቸው ያላቸው ማህበረ- ባህላዊ ጉዳዮቹ ኋላ ቀር ሊያሰኙት አይገባም። ይህ አይነቱ አስተያየት በማንነቱ የሚኮራንና የብዙ ባህል ባለቤት የሆነን ህዝብ ካለመረዳት የሚመጣ ነው። ባህል ትክክል አይደለም ማለት የኔ ባህል ነው ትክክል የሚል አንድምታ ስላለው መታረም የሚገባው ነው። ይልቁንም እኔ በጥናቴ ያረጋገጥኩት የሙኢኒት ብሔረሰብ በማንነቱ የሚኮራና የራሱ የሆነ እጅግ ብዙና ድንቅ ማህበረ-ባህላዊ ሀብቶች እንዳሉት ነው።

ከላይ ያየናቸው አራቱ ጥናቶቹ በአጠቃላይ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ ምንነት፣ አወቃቀር፣ ለማህበረሰቡም የሚሰጡት ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ፣ የባህላዊ ተቋማቱ አንዳንድ የግጭት አፈታ ሂደቶችን፣ ግጭቶችን በሚፈቱበት ሰዓት የሚጠቀሟቸውን ስልቶችን ማሳየት፣ የግጭት ምክንያቶችንና አይነቶችን ማሳየት፣ የባህልዊ አስተዳደሮችን ፋይዳ ማሳየትና ቀርሶ ማስቀመጥን ዓላማ አድርገው በመነሳታቸው ከኔ ጥናት ጋር ያገናኛቸዋል። ይሁን እንጅ እያንዳንዱን ባህላዊ የግጭት አፈታት ሂደት ላይ የሚደረጉና የሚታዩ ትዕምርቶች ትርጉም ተብራርተው ባለመቀመጣቸው ከኔ ጥናት ጋር ያላቸው ልዩነት ነው።

የዳንኤል ጥናት በሚጠናው ብሔረሰብ ማንነት ላይ በማተኮሩ እንዲሁም የቡሔረሰቡ ማህበረ-ባህላዊ ጉዳዮችን በመዳሰስ አንድንት ሲኖረን እሱ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ አተኩሮ በመስራቱ እና እኔ የማህበረሰቡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ በማተኮሬ እንለያያለን። ከዚህ በተጨማሪ ዳንኤል በጥናቱ ብሔረሰቡ ኋላቀር እንደሆነ የገለጸበት መንገድ ተገቢ ያልሆነና እንዲያውም ብሔረሰቡ ለዘመናት ጠብቆ ያቆያቸው በርካታ ትዕምርቶችና እውቀቶች እንዳሉት የኔ ጥናት የሚያሳይ በመሆኑም ጭምር ነው።

# 2. ግጭት፣የግጭት አፈታት ተቋማትና ሥርዓቶች

በዚህ የጥናቱ ዋና አካል ወይም ክፍል በሆነው ርዕስ ስር የመኤኒት ብሔረሰብ አባላት ለግጭት ምንነት የሚሰጡት ትርጓሜ፣ በብሔረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱት የግጭት አይነቶችና የግጭቶቹ የመነሻ ምክንያታቸው እንዲሁም ግጭት የሚፈታባቸው ተቋማት ማንነት ከሚከተሉት የግጭት አፈታት ስልት ጋር በዝርዝር ቀርቧል።

## 2.1 የግጭት እሳቤ በመኤኒት ብሔረሰብ

የመኢኒት ብሔረሰብ ግጭት ለሚለው ቃል የሚሰጠው ትርጉም እንደየ ሰው ማንነትና ነገሮችን የመረዳት ብቃት የተለያየ ቢሆንም የሁሉም ትርጓሜና ብየና በይዘቱ የተለያየ አይደለም።

ጠብ ወይም ግጭት "ከጃን" ወይም "ካማን" ተብሎ በብሄረሰቡ ይጠራል። በሁለትዮሽ መካከል የሚፈጠር በመሆኑም "ካሽን" በመባል ሊጠቃለል ይችላል። "ከጃን" ጥል ማለት ሲሆን "ካማን" ደግሞ ጦርነት ማለት ነው። ወልደየስ ይሄንን ሀሳብ እንደሚከተለው ይገልጹታል። " ከጃንና ካማን ሲተረጎሙ አንድ ናቸው። ጦርነት እንደማለት ነው።"[10]

ግጭት ከጸብነቱ ባሻገር የህይወትና የሰላም ጸር መሆኑን የሚገልጹት ደግሞ አቶ ብርሃኑ ናቸው። ግጭት ለህብረተሰቡ ጥቅም እንደሌለውም እንደሚከተለው ይናገራሉ "ግጭት ህብረተሰብን ከህብረተሰብ እንዲጋጭ የሚያደርግ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ጥቅም የሌለው፣ ማህበረሰቡ ከአንዱ ቦታ ወደ አንዱ ቦታ እንዲፈልስና ልማት እንዳያለማ የሚያደርግ፣ አንዱን ጎሳ ከአንዱ ጎሳ ጋር እንዲጋጭ የሚያደርግ እንዲሁም ለልማት ፀር የሆነ ነገር ነው።"[11]

በብሔረሰቡ ለግጭት የሚሰጠው ብያኔ በአብዛኛው ተቀራራቢ ነው። ሰላም አደፍራሽነቱ፣ አንባቢ ማናጋቱ፣ ዘረፋ ማምጣቱና በአንድ ሰው ተነስቶ ለሌላው የመትረፉና መተላለቅን ማምጣቱ ነው። የፖሊስ ባልደረባው መኮንን የሚከተለውን ሀሳብ ይሰነዝራሉ። "ግጭት ሰላም አደፍራሽ ነው። ኑሮውን አንባቢውን ያናጋል። ለማረጋጋት ከፍተኛ ኃይል ይጠይቃል። በአንድ ሰው የተነሳው ሁከት ለሌላው ይተርፋል። ዘረፋንም ያመጣል።"[12] ይሄንኑ ሀሳብ ኬኒ ቀኛዝማች ጋሊ "ጥፋት ያጠፋል።" ሲሉት አቶ ሰዒድ "መተላለቅን፣ እርስ በርስ መገዳደልን ያመጣል።"

[10] ወልደየስ፡ ሚያዚያ 2003
[11] ብርሃኑ፡ ሚያዚያ 2003
[12] መኮንን፡ ሚያዚያ 2003

ይላል። ግጭት በወንድማማቾች ወይም ሰዎች መካከል የሚፈጠር በትናንሽ ቂሞች እንዲሁም ባለመግባባት የሚመጣ እንደሆነና እየሰፋ እንደሚሄድ የሚገልጡ አሉ። ዋና ሳጅን አሸናፊ ቺሬዋሌ የሚከተለውን ሀሳብ ይሰነዝራሉ። "በመኤኒት ብሄረሰብ ጠብ ወይም ግጭት የሚባለው በሁለቱ ወንድማማቾች ወይም በሁለት ሰዎች መካከል ባለመግባባት የሚነሳ ነገር ነው። በትናንሽ ቂሞች ተያይዞ የሚነሳና እየሰፋ የሚሄድ ነው። ብዙ ጊዜ አለመግባባት የሚነሳው መጠጥ ከጠጡ በኋላ ትንሹን ነገር እያሳደጉ ወደ ትልቅ ነገር በመሄዳቸው ነው።"[13]

በመኢኒት ብሔረሰብ በተለይም ከተለያዩ ጎሳዎች ሰው ሰውን ከገደለ ጸቡና እልቂቱ እጅግ ከባድ፣ ለማብረድም ፈተና የሚሆን ነው። ይሁን እንጅ ኮሞሩቶች /ባላባቶች/ ወይም የአገር ሽማግሌዎች ወይም የሃይማኖት አባቶች በመሀል ከገቡ በዳይ ተበዳይን ከሶ ግጭቱ ይረግባል። "የኔ ጎሳ የሌላውን ጎሳ አንድ ሰው ቢገድል የኔ ጎሳ አንድም ሰው ሳይቀር አገር ለቆ ይሰደዳል። የሟች ቤተሰብም የኛን ያለውን ነገር ያወድማል፣ ሰብስቦ ወስዶም ለቅሶ ላይ ቁጭ ብሎ ይመገባል። የሟች ቤተሰብ ይሄንን ሲፈጽም የገዳይ ቤተሰቦች ኮምሩት /ሽማግሌዎች/ ፈልጎ አስገግጊ ይልካል። በመሃል ኮምሩት ከገባ ሁሉም ነገር ይቆማል።"[14]

ግጭትን ከግለሰብና ከጎሳም አርቀው የተመለከቱና በመኢኒት ሻሻ አካባቢ አልፎ አልፎ የሚፈጠረውን የብሔረሰብ ጸብ መሰረት አድርገው ሀሳባቸውን የገለጹም አሉ። ግጭቱ መዋደትን፣ መሰደድን፣ መገዳደልንም እንደሚያመጣ ገልጸዋል "ጠብና ግጭት ማለት ባለመስማማት በሁለት ብሔረሰብ መካከል የሚፈጠር ጥል ነው። ይሄ ጠብ የሚያመጣው ነገር መጣትም፣ መዋደትም ሊያመጣ ይችላል። መሰደድም፣ እርስ በርስ መገዳደልም ሊኖር ይችላል።"[15]

## 2.2 የግጭት አይነቶችና ምክንያቶቻቸው

በመኢኒት ብሔረሰብ ውስጥ የተለያዩ ምክንያቶች የብሔረሰቡን አባላት ለግጭት ያነሳሷቸዋል። እነደየ ግጭቶቹ አይነት መቀስቀሻ ምክንያቶች በርካቶች ናቸው። ከእነሱ ውስጥም የጠብ መነሻቸው፣ በርደ ጠጥቶ በመስከር፣ መድፈር፣ አንዱ ያጫትን ሌላው ከኋላ መጥቶ ሲጠስድበት፣ የድንበር መግፋት፣ ስርቆት አይነቶቹ የሚጠቀሱ ናቸው። በገበያ እና ሀዘን ቦታ

---

13 አሸቤ፣ ሚያዚያ 2003
14 ወልደገብ፣ ሚያዚያ 2003
15 ካሣ፣ ሚያዚያ 2003

ላይ /ጭፈራ አለ/ እዚያ ላይ የቆየን ቂም አንስቶ የሚፈጠር ግጭት አለ፡፡ አቶ ብርሃኑ የሚከተለውን ይላሉ፡፡ "ማህበረሰቡ አንድ ቦታ ላይ ተቀምጦ በሚጠጣበት ሰዓት አንዳንዱ ሰው ይሰክራል፡፡ በዚያ ሰዓት የመጋጨት ሁኔታ አይቀርም፤ በእኛ አካባቢ በአብዛኛው የግጭት ምክንያቶች ሴትን የመድፈር፣ የድንበር መጋፋት፣ አንደኛው አጭቶ ሌላው ሲያገባበት ግጭት ይነሳል፡፡"[16] በሁለቱም ዋና የቤሔረሰቡ ወረዳዎች ውስጥ ዋና የግጭት ሰበብ ሆኖ በብዛት የሚታየው መጠጥ ነው፡፡ በመጠጥ የተነሳ በርካታ ግጭቶች ተከስተው ከፍተኛ ጥፋትን ያመጣሉ፡፡ በመኢኒት ሻሻ ወረዳ ኮሞሩት/ባላባት/ የሆኑት ኬኒ ቀኛዝማች ጋሲ የግጭት ሰበቡ አረቄና የአረቄ ንግድ መሆኑን ይገልጣሉ፡፡ "እዚህ አካባቢ ግጭቶች እንዲበዙ ያደረገው አረቂ ነው፡፡ አረቂው በብዛት እየመጣ፣ የአረቄ ንግድ እየተስፋፋ፣ የጥይት ንግድ እየተስፋፋ በአካባቢ ጸጥታ እየጠፋ ግጭቶች እየተስፋፉ ነው፡፡"[17] የኮሞሩቱን አባባል የሚያጠናክር ሀሳብ የሚሰነዝሩት ደግሞ በመኢኒት ጎልዲያ ነዋሪ የሆኑት ዋዬች ጃሻ ናቸው፡፡ ዋየች ኮሞሩት አሻ በመሆን አራት ጊዜ የተጋደሉ ሰዎችን ያስታረቁ ቢሆንም እሳቸው ራሳቸው በመጠጥ ተነሳስተው ወንድማቸውን መግደላቸውን ነግረውኛል "የተጋጨነው ከሁለት ታናሽ ወንድሜ ነው፡፡ ከተማ መጥተን በርጼ፣ ጠላና ጠጅ ቀላቅለን ጠጣን እሱ ሞቅ አለውና ሰደበኝ ከዚያ በኋላ መታኝ፡፡ እኔም እንዴት ታሳፍረኛለህ ብዬ በመንገድ ስንመጣ በጩቤ ወጋሁት፡፡"[18] እንደ ዋየች ሁሉ ሰው ለመግደል ያበቃው አረቄ መሆኑን የነገረኝ በዚሁ ሰበብ ከአገር ርቆ አስራ አራት ዓመት በሽፍትነት የኖረው አቶ ጥጋቡ መንገሻ ነው፡፡ "በአብዛኛው የኛ ሰው ይጠጣል፣ ከመጠጥ የተነሳ ይጋጫል፡፡ ያው እኛ መኤኒቶች ስንጠጣ አንችልም፡፡ አንድ ሰው አንድ ከብት በስምንት መቶ ብር ሸጩለት ነበር፡፡ እየጠጣን ስጠይቀው እንዴት አረቂ ቤት ትጠይቀኛለህ ብሎ በጦር ሊመታኝና ሆዴ ላይ ሲወጋኝ እኔ ደግሞ በጦር ስወጋው በመካከሉ ሞተ፡፡"[19]

በአጠቃላይ በቤሔረሰቡ የሚታዩ ግጭቶች ከሀብትና ከንብረት ጋር ተያይዘው ከሚከሰቱ ግጭቶች ውስጥ የመሬት መግፋት፣ ከብት ዝርፊያ፣ ብድርና የመሳሰሉትን የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ቤተሰብ ተኮር ከሆኑት ጸቦች ውስጥ ከጋብቻና ከውርስ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ድብድብና ግድያን የመሳሰሉ ሲጠቀሱ የቡድን ጠቦች ከሆኑት ውስጥ በጎሳና ጎሳ፣ በብሔረሰብና በብሔረሰብ መካከል የሚነሱትን ግጭቶች ይመለከታል፡፡

[16] ብርሃኑ፣ ሚያዚያ 2003
[17] ኬኒ፣ ሚያዚያ 2003
[18] ዋየች፣ ሚያዚያ 2003
[19] ጥጋቡ፣ ሚያዚያ 2003

## 2.3. በመኢኒት ብሔረሰብ ብዙ ጊዜ የሚቀርቡ ዋና ዋና ግጭቶችና የተሰጡት ውሳኔዎች

በዚህ ርዕስ ስር በመኢኒት ብሄረሰብ ውስጥ በዋናነት ጎልተው የሚታዩ ግጭቶችና እነዚህ ግጭቶችን ለመፍታት በተለያዩ ተቋማት የተሰጡ አይነተኛ ውሳኔዎች ቀርበዋል። እነሱም ከሀብትና ከንብረት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች፣የቤተሰብ ጠቦች፣ የተለያዩ ወንጀሎች፣የውድን ጠቦች ናቸው።

### 2.3.1. ከሀብትና ከንብረት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች

እነዚህ መሬትን፣ ድንበርን፣ የግጦሽ ቦታን፣ የውኃን፣ የከብት ዝርፊያን፣ ብድርንና የመሳሰሉትን ምክንያት አድርገው የሚነሱ ጠቦች ናቸው።

በመኢኒት ብሔረሰብ ብዙውን ጊዜ የከብት ዝርፊያ ያጋጥማል። ዝርፊያዎች ደግሞ የሚፈጸሙት በስውር በመሆኑ ዘራፊውን ለማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል። አንድ ከብቱ የጠፋበት ሰው ወደ መንግሥት አካላት ከማመልከት ይልቅ የከብቱን ወሳጅ ማንነት ለማወቅ አልያም ለማስረገም ወደ ቃልቻ ይሄዳል። ብዙ ጊዜ ሰርቋል የተባለ ተጠርጥሮ ወደ ቃልቻዎች ከቀረበ በቃልቻዎች ፊት መዋሸትና መረገምገም ስለሚፈራ እውነቱን ይናገራል። በአብዛኛው እምነት የተሰረቀበት ሰው ማስረገሙ እንደማይቀር ስለሚታመን አንድ የተረገመ ሰው ምንም ጊዜ ቢሆን እርግማኑ እንደሚደርስበት ያምናል። እናም የእርግማኑ ውጤት መታየት ሲጀምር ተረጋሚው ጥፋቱን አምኖ የተረገመበት ቃልቻ ሄዶ ጋ ሄዶ እርቁን እስካልፈጸመ ድረስ እርግማኑ ከልጅ ወደ ልጅ እየተሸጋገረ የዚያ ሰው ቤተሰቦች የሆኑ በሙሉ ያልቃሉ። አንዳንድ ጊዜ የተረገመው ሰውና የቅርብ ዘመዶቹ ይሞቱና እርግማኑን ሄዶ እንዲቀር ወይም እንዲወገድላቸው የሚያደርግ ይጠፋል። በዚህም የተነሳ እርግማኑ ረጅም ዓመት ያስቆጥራል። ኮሞሩት አሻ ሲሚንቶ ሲማቻ እንዲህ አይነቱንና አራት አስርት ዓመታት የደፈነ የእርግማን ታሪክ እንደሚከተለው ነግረውኛል።

> ድሮ አንድ ከብት ሲሰረቅና የወሰደው ሲጠፋ ትልቅ አውጫጭኝ ይደረጋል። ያኔ አውጫጭኝ ትልቅ ነገር ነበር። እና በኃይለሥላሴ ዘመን ጨበራ ከተማ ሲሉ የሚባል ሰው ጊደር ይሰርቃል። እናም በዘመኑ ካብትይመር የሚባል ባላባት ነበር። እሱ አውጫጭኝ ጠራና የሰረቀው ጠፋ። ታዲያ የኔ አያት /የአባቴ አባት/ እና ካብትይመር ለከተማው ሰው ሲሉ /ለህዝቡ ሲሉ/ ሁለት ከብት አውጥተው

> ሰጡ። በጊዜው ከብቱን ከሰጡ በኋላ ፎሮሽዋ የሚባለው ቃልቻ ጋ (የአሁኑ ቃልቻ አወቀ አባት ናቸው) ሄደው አስረገሙ። እርገምልን አሉት - እረገመላቸው። ከዚያ ጊደሯን የሰረቀው ሰው ጊደሯ እየወለደችለት ወተቷን እየጠጣ ይቆያል። ሆኖም ግን እርግማን ስላለበት በመጀመሪያ እራሱ ሞተ። ከዚያ ሚስቱ ሞተች፣ ልጆቹ ቀጠሉ። እየቆየ የቅርብ ዘመዶቹ ጋ ጉዳዩ መምጣት ሲጀምር እነሱም ተረድተው ለህይወታቸው እያሉ ከብት እያዋጡ እስከ አሁን አስራ አራት ከብት ሰጥተዋል። አሁንም አልቀረም የካቲት 9 2003 ላይ አራት ከብቶች ይዘው መጡ። አሁንም እየከፈሉ ነው። ምክንያቱም በጊዜው አጥፍቻለሁ፣ አጥፍተናል እርግማኑ ይነሳልን ብሎ የመጣ ስለሌለና ካሳ ከፍሎ የእርቁ ማጸናና እርግማን ማስቀረያ ጋምጫለች /ዝንጅብል/ ስላልሄደ ነው። እየከፈሉ ያሉት ያኔ ወተት የጠጡ ናቸው። ሰውየው የቅርብ ዘመዶቹ ካስረገሚው ጋር እርቅ መፈጸምና ጋምጫለች መብላት አለባቸው። የአጎት ልጅ፣ የአክስት ልጅ፣ ከውጪ የሚወለዱም ናቸው የከፈሉት። ሰውየው ጊደር የሰረቀው ሞቷል። ወንድሞቹም የሉም። ከእነሱ ትንሽ ልጅ ቢኖር ከቃልቻው ጋር መጥቶ ከእነዚያ ሰዎች አልያም ቤተሰቦቻቸው ጋር እርቁን መጨረስ እና እርግማኑን ማስነሳት አለበት። ጊደሯ የተሰረቀችው በኃይለሥላሴ ነው። ሰውዬው የተረገመውም በዚያ ጊዜ ነው። ክፍያው ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ነው እየተከፈለ ያለው። በጣም የቅርብ ዘመድ፣ ወንድም፣ እህት፣ ወይም ልጅ አልያም የልጅ ልጅ ቢኖራቸው መጥቶ 'የኔ አያት ወይም የኔ ቅድመ አያት አጥፍቷል' ብሎ ከአስረጋሚ ዘመዶች ጋር ጋምጫለች /ዝንጅብል/ ነክሰው፣ ቡና "ዳንጋ ካደረጉ" /ለሁለት ከጠጡ/ ይሄ እርግማን ይቆማል።[20]

ከከብት ዘረፋና እርግማን ጋር የተያያዙ በርካታ ጉዳዮች ያጋጥማሉ። የሚከተለውም ታሪክ ዲልቀባ ጣያ በተባለ ቀበሌ የተከሰተ ከከብት ጋር የተገናኘ ታሪክ ነው። ታሪኩ ደግሞ የተፈጸመው ይሄንን ጥናት ለማጥናት ወደ አካባቢው ከሄድኩ ከአንድ ወር በፊት ነው። ታሪኩን የነገሩኝ ቀልፍ የመረጃ አቀባዩ በድሉ ናቸው።

> በጥቅምት 2003 ዓ.ም ደግሞ ዘንድሮ "ዲልቀባ ጣያ" ቀበሌ ላያ ብርሃኑ ከመዳ የሚባል ወጣት ልጅ አለ። የአንድን ድንኪራይ የተባለ ሰው ከብት በጦር ይወጋል። ቀጥሎ ፈረስ ይወጋል። ሰውየው ከብቱንና ፈረሴን ወጋብኝ ብሎ ቀበሌ ክስ ያቀርባል። ልጁም እኔ ላምህንና ፈረስህን ስወጋ ያየ ሦስት ምስክሮች ካለ አቅርብ ብሎ ይከራል። ሰውዬው ግን ማስረጃ ያጣል። ከዚያ የተወጋበት የድንኪራይ ሰውዬ ሽናፕ የተባለው ቃልቻ ጋር ይሄዳል። እናም ሽናፕ ብርሃኑን ያስመጣዋል። የተጠራውም ብርሃኑ የሚባለው ሰው እኔ ላሙንም ፈረሱንም አልወጋሁም ምስክር ካለ ያቅረብ ይላል። ቱሞም ተከሳሹን "አልወጋህም? "ይጠይቀዋል። "አልወጋሁም" ይላል ሰውዬው። ደግሞ "ትምላለህ?" ብሎ ሲጠይቀው "እምላለሁ" ብሎ ይምላል። "እጅን ትመታለህ?" ሲለው "እመታለሁ"

[20] ሌማንቶ፣ ሚያዚያ 2003

> ብሎ እጁን መትቶ ይመለሳል፡፡ ከዚያ በሳምንቱ ብርሃኑ ሰው ይገድላል፡፡ ቀጥሎ በሳምንቱ እራሱ በሰው በጦር ተወጋ፡፡ ከዚያ በኋላ ምልክቱ መሆኑን ሲያውቅ ቱሞ ጋር መጥቶ ፈረሱንም ወግቶ እንደገደለ አምኖ እሱ ወደ እስር ቤት ሄዶ ዘመዶቹም ንብረቱም ተካፈሉ፡፡[21]

የከብት ዘረፋ ጋር በተያያዘ በቃልቻዎች መፍትሄ ያገኙ ብዙ ጉዳዮች አሉ፡፡ አንዳንዴ በዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት በቀበሌ ፍርድ ሸንጎ ላይ በሚቀርብ የሀሰት ማስረጃ የአንዱ ንብረት ወደ ሌላው ሊሄድ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ባለንብረቱ ወደ ቃልቻ ወይም ወደ ባላባት ሄዶ ንብረቱን እንዲያስመልስለት ጥያቄውን ያቀርባል፡፡ እናም ባላባቱ የማጣራት ሥራዎን ሲሰራ በውሸት የመሰከረ ስህተት እንደሰራ በመንገር ይቅርታ ይጠይቃል፡፡ በሀሰት የሄደ ንብረትም ይመለሳል፡፡

> ባቹማ ከተማ ውስጥ በ1999 ዓ.ም አንድ ከብት ወደ ዲልቀባ ቀበሌ ተሰርቆ ይሸጣል፡፡ ከዚያ ከተማ ውስጥ ያለ ትልቅ ሰው ፍርድ ቤት ሄዶ ንብረቱ የአቶ አከሊ ነው ብሎ ይመሰክርለታል፡፡ ሰውየውም ውሣኔውን ከተቀበለ በኋላ ንብረቱ ወደ ሌላው ሰው እንዲሄድ ይደረጋል፡፡ ይሁን እንጂ የግል የሆነ ንብረቱ ወደ ሌላ ከሄደ፣ የኔ ነው ብሎ ፍርድ ቤት ክስ የመሰረተው ሰው ከብቱን ከተረከበ በኋላ እውነተኛው የከብቱ ባለቤትና ተጎጂ የነበረው ሰው ጥቅምት እሸት ቀበሌ /ኬ ቤንች መረዳ ውስጥ/ ግራዝማች አሉ እዚያ ሄዶ ጉዳዩን ያቀርባል፡፡ ከዚያ በኋላ ያ መስካሪ ተጠርቶ ሲጠየቅ እኔ የመሰከርኩት በሀሰት ነው ብሎ ከብቱ ለቀድሞ ባለቤት የተሰጠበት ሁኔታ አለ፡፡ ፖሊስ በዚህ በኩል ከባላቶቹም ጋር ጥሩ እየሰራ ነው፡፡[22]

ከላይ ለማየት እንደሞከርነው በአብዛኛው የሚፈጠሩት ግጭቶች ማስረጃ የለሽና በስውር የሚፈጸሙ በመሆናቸው የሚፈቱት በቃልቻና በባላባቶች ነው፡፡

## 2.3.2. የቤተሰብ ጠብ

እነዚህ ከጋብቻ፣ ከልጆች፣ ከውርስ ወዘተ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ግጭቶች ናቸው፡፡ ቤተሰብን በተመለከተ ከፍተኛ የሆነና ተደጋጋሚ ግጭት የሚፈጠረው የሰው ሚስት ጋር በሚፈጠር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው፡፡ ከባሏ ውጭ ወዳም ይሁን ተገዳ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመች ሴት በደም ታጥባ እና ከሷ ጋር ግንኙነቱን የፈጸመው ሰው የካሳ ክፍያ እስካልሰጠ ድረስ ግጭቱ አይበርድም፡፡

---

[21] ብርቁ ፡ ሚያዚያ 2003

[22] አሸኔ ፡ ሚያዚያ 2003

ጉዳዩ የተፈጸመው በመኤኒት ጎልድያ ወረዳ፣ በጨበራ አገልግሎት፣ በዱማ ዳሽ ቀበሌ፣ በዳርጉ መንደር ነው፡፡ የባሬ ሦስት ቀን የወንድሜ ጃላው ጃሻ ሚስት ተደፈርኩ ትላለች፡፡ የተደፈረችው ወልዳለች፡፡ የሦስት ልጆች እናት ነች፡፡ የደፈረው በዚያው አካባቢ የሚኖር አንድ ጎረምሳ ነው፡፡ አባቱ አቶ ቾም ይባላል፡፡ ደፋሪውም የኔ ዘመድ ነው፡፡ በመጀመሪያ ከተማ ጠጥተው ይመለሳሉ፡፡ የኔ ወንድም ደግሞ ሁለት ሚስቶች አሉት አንዷ ጋር ሲያድር ይሄ ደግሞ ብቸኛነቷን አረጋግጦ ሄዶ በር ከፍቶ ስክራለችና ይገናኛታል፡፡ በማግስቱ ክሱ ተፈጠረ እስታረቅን፡፡ ከዚያ ጠራንና የፍየል አንጀት አነበብን፡፡ እናም መድፈሩን አረጋግጠን ለወንድሜ አንድ በሬ እንዲከሰው አድርገናል፡፡[23]

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መንገሻ ያጋጠመውን አውግቶኛል፡፡ ይሁን እንጂ መንገሻ በነገረኝ ታሪክ ውስጥ የደም እጥበቱ የተካሄደው አብዛኞቹ የመረጃ አቀባዬ እንደነገሩኝ የሴቷን እግር ሳይሆን የነጣ ቅጠል በአንገቷ ተደርጎ በላዩ ላይ ደሙ እንደፈሰሰ ነው፡፡ መንገሻ እንደዚህ ቢልም ሌሎች ግን እጥበቱ በዚህ መልኩ እንደማይካሄድ ነግረውኛል፡፡

አንድ ልጅ ለቅሶ ላይ እያለን ወደ ጥቅምት እሸት የሚባል ቀበሌ ጠጥቶ ሰክሮ መጥቶ ቤት ከፍቶ ሴትየዋን ደፈረ፡፡ ከዚያ ጠዋት ስንመጣ ሴትየዋ ለባልዋ ቡና አልሰጥ አለች፡፡ ከዚያ ምን ነው ስንል ማታ "ግዛው መጥቶ ደፈረኝ" አለች፡፡ ግዛውም ቀበሌውን ትቶ ወደ ሸካ ሻሻ ሸሸ፡፡ ከዚያ ሽማግሌዎች ሲጠይቁት ትክክል ነው ፈጽሚያለሁ ብሎ መልዕክት ላከ፡፡ ከዚያ አንድ ጊደር ለባልየዋ ካሳ ላከ፡፡ ከዚያ አንድ በግ አምጥቶ በዱላ ቀጠቀጠና ደም ሲወጣ የቆጮ ቅጠል መሀል ላይ ተሰንጥቆ የሴትየዋ አንገት ላይ ተደርጎ በላዩ ላይ ደሙ ይፈሳል፡፡ ከዚያ በኋላ ሴትየዋ ወደ ቤቱ ተመለሰች፡፡[24]

ከነቢሾ ጋር በተያያዘ ግጭት ሴትየዋ ተደፈርኩ ስትል የተጠረጠረው ሰው ፍየል ገዝቶ በማምጣትና በእንጨት በመቀጥቀጥ አንጀቱ በአንጀት አንባቢዎች ይነበባል፡፡ በንባቡ ውስጥ ሴትየዋ በትክክል መደፈሯ ወይም ከአንድ በላይ ሰው ደፍሯት እንደሆነ ወይም ደፍሯል የተባለው ሰው በሀሰት የተወነጀለ እንደሆነ አጣርተው ይናገራሉ፡፡ አንጀት አንባቢው ቃንግሪ ኪጌብጣቸውና አንጀቱን አንብበው ትክክለኛነቱን ካረጋገጡት ውስጥ የሚከተለውን ነግረውኛል፡፡

የጢ ዶሪክሪ ልጅ ሚስት ተደፈረችና መጥታ ለሽማግሌ ተናገረች፡፡ ከዚያ እኔ ተጠርቼ የተቀጠቀጠውን ፍየል አንጀት አነበብኩት፡፡ ሰውየው ጋር ፈጽማለች ደግሞ ከዚህ ሌላ ሌላ ሰውዬ አለ አውጪ ካላወጣሽ ትሞቻለሽ ብዬ ነገርኳት፡፡

---

[23] [illegible]፡ ሚያዚያ 2003

[24] መንገሻ፡ ሚያዚያ 2003

> ትክክል ነበር የሆነ ሰውዬ እስ ደብቄ ነው ብላ ተናገረች፡፡ እና ሁለተኛውም ሰውዬ መጥቶ ፍየል ገደለና አነበብኩት ትክክል ነው፡፡ እሱም አምኗል[25]፡፡

የአንጆት ማንበብ ለአንባቢዎቹ የተሰጠ ጸጋ በመሆኑ በጣም የተደበቁ ታሪኮችም ይወጣሉ በዚህም የተነሳ መሰረታዊ የሆኑ የትዳር መናጋቶችም ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ በመኤኒት ጎልድያ ወረዳ ባኒ ቀበሌ የተከሰተውም ሁኔታ ይሄንኑ የሚያሳይ ነው፡፡ ባል በአንጆት ንባብ የሚስቱን ድብቅ ማንነት በማወቁ ከሰዎች ጋ ከመጋጨት ውጭ የማተርፈው የለም በማለት ወደ ቤተሰቦቿ በመመለስ ሲያገባት የከፈለውን ጥሎሽ እንዲመልሱለት አድርጓል፡፡

> በቀደም፣ በቅርብ ጊዜ ባቹማ ባኒ አካባቢ አጋጣሚ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ተደፍራ በአንጆት ታይቶ እስከ አምስት ሰው ጋር መተኛቷ ተረጋግጦ እሷ እያወጣች እየወጣች እነዚያ ይሄንን ችግር የፈጠሩ ሰዎች እያንዳንዱ እየገደለ እያጠበ፣ እያጠበ የሄደበት ሁኔታ አለ፡፡ ሴቷ አሁን ያለው ባሏ ለቤተሰቦቿ ወስዶ አስረክቧል አምስትም ወንዶች ተጠርተው መጥተው ካሳ ከፍለዋል እና ከወንድዬው ጋ እርቅ አድርገው የሴቷ ችግር እንደሆነ አይቶ ለቤተሰቦቿ ወስዶ እዚህ ብትቀመጥ እኔን ታሳስተኛለች በሚል መልሶ ድሮ ጥሎሽ የሰጠው ተመልሶለታል ጥር ውስጥ 2003 ነው ይሄ የሆነው፡፡[26]

ከዚህ በተጨማሪ አልፎ አልፎ የአንጆት ንባቡን የሚጠራጠሩ አሉ፡፡ እንደዚህ አይነት ሰዎች በመኖሪያቸው ብዙ ክፉ ነገር እንደሚደርስባቸውና እንደሚጎዱም ይታመናል "አዎ አንዷ አንጆት አንብቤ ሌላ አለብሽ ብያት የለብኝም ብላ ካደች ፡፡ የዛሬ ሁለት ዓመት አካባቢ ስለደበቀች ሞተች፡፡"[27] ቀደም ባሉት ጊዜያት በደርግና ከዚያ በፊት የገደለ አሻ ከከፈለ በመንግሥት የማይታሰር የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የገደለ ሰው ወደ እስር ሲሄድ አሻው በዘመዶቹ እየተከፈለ አሻውን ጨርሶ ሲመጣ በሰላምና በነጻነት ይኖራል፡፡

### 2.3.3. ወንጆል

ወንጆል ድብድብና ግድያ የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ በብሔረሰቡ በብዛት ከሚፈጸሙ ግጭቶች ዋንኛው ግድያ ነው፡፡ ግድያው በተለያዩ ሰበቦች ይፈጠራል፡፡ በአብዛኛው ግድያ የተፈጸመው ግን በመጠጥ ኃይል በመንሳሳት በትናንሽ ንግግሮችና ያለፈ ቂርሾ በማስታወስ ነው፡፡ ዋየች የገዛ ወንድማቸውን ስለሰደባቸውና ስለመታቸው ገድለውታል፡፡ በተፈጠረባቸው ድንገተኛ ንዴት ወንድማቸውን ገድለው እጃቸውን ለፖሊስ በመስጠት ከእስር ሲወጡ አሻውን ከፍለዋል፡፡

---

25 [illegible] ሚያዚያ 2003
26 [illegible] ሚያዚያ 2003
27 [illegible] ሚያዚያ 2003

> ሰኔ 14 ቀን 1994 ዓ.ም ነው። የተጋጨነው ከሁለት ታናሽ ወንድሜ ነው። ከተማ መጥተን ቦርዴ፣ ጠላና ጠጅ ቀላቅለን ጠጣን እሱ ሞቅ አለውና ሰደበኝ ከዚያ በኋላ መታኝ። እኔም እንዴት ታሳፍረኛለህ ብዬ በመንገድ ስንመጣ በጩቤ ወጋሁት።ቀጥታ ፈርቼ እኔም እጄን ለፖሊስ ሰጠሁ። እሱ በህይወት እያለ ነው እኔ እጄን የሰጠሁት። እሱ ሀኪም ቤት እያለ ነው የሞተው። እጄን የሰጠሁት ወዲያው ጩበራ ነው። ከዚያ ወደ በቾማ ነው ከዚያ የነፍስ ጉዳይ የሚታየው በዞን ስለሆነ የቤንች ማጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው ውሣኔውን የሰጠኝ። እስር ቤት እያለሁ መሞቱን ሰማሁ። ሚስቶቼ ወንድሜ ነውና መቀበሪያና ከብት ስጡ። እንደገናም እናንተን ሊያባርሯችሁ ስለሚችሉ የጦር መመለሻ ወይፈን ስጡ። የእሻው ሥነ ሥርዓት እኔ ግዳጄን ፈጽሜ እስከመለስ ጠብቁኝ ብዬ ለሽማግሌ ነገርኩ እነሱም ጠበቁኝ። የተፈረደብኝ ስምንት ዓመት ነው። የታሰርኩት ግን አምስት ዓመት ከአራት ወር ነው። ከዚያ ስመጣ ወዲያው አምስት ከብትና የራሴን ልጅ አወጣሁና ዘመዶቼ ከወንዝ ወዲያ ማዶ እኔ ብቻዬን ከወንዝ ወዲህ ሆኜ እሻውን ከፈልኩ። እኔ ብቻዬን ነበርኩ። እኔን የሚያውቁ ባዳዎቼ ካልሆኑ በስተቀር ዘመድ ነው ብሎ የተጠጋኝ የለም። ሚስቶቼም ጠላት ሆነውኝ ከሌላው ጋር ነበሩ። ከዚያ በጉን ተራምጄ ነው የታረቁኝው። ከዚያን ቀን ጀምሮ ጦር አንስተን ያንን ድንጋይ ከወጋን በኋላ ምንም አናነሳም። አብረን እንበላለን አብረን እንጠጣለን።[28]

አንዳንዴ በተለያዩ ሰበቦች የሚፈጠሩ ቁርሾዎችን ወይም የቆዩ ቂሞችን ምክንያት አድርገው ግድያዎች ይፈጸማሉ። በእሻ እርቅ ሥነ - ሥርዓት ክፍያ እንኳን የሚከፈሉት ከብቶች ተጠናቀው ካልተከፈሉ ያንን መሰረት አድርገው ግድያዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ከዚያ ውጪ ሌሎች የጎላ ጥያቄዎችን መሰረት አድርገው የሚነሱ ግድያዎች አሉ። ቦንካ ኮንኩላይ የተባለው የተባለው የጎግ ቀበሌ ነዋሪ ሚስቱን የደፈረበት ሰው ካሳ ስላልከፈለውና በመናቅ ሚስቱን ስላላጠበለት በጠራራ ፀሐይ ጭፈራ ላይ ገድሎታል። በዚህም የተነሳ ታናሽ እህቱ ዶጊያ ለእሻ እንዴት እንደተከፈለች የሚከተለውን ታሪኳን አውግታኛለች።

> አባቴ አቶ ኩንኩላይ እናቴ ወ/ሮ ዶንግሊ ኩንጉዲ ይባላሉ። ገዳዩ ወንድሜ ቦንካ ኮንኩላይ ነው የገደለው በደርግ ዘመን ነው አቶ ሴላ ኢኮሮዩ የተባለ ሰውን ነው የገደለው። ወንድሜ የገደለበት ምክንያት ሰውዬው ሚስቱን ደፈረበት። ደፋሪው በጠራራ ፀሐይ ውስጥ ሜካ ወስዶ ደፈራት። ከዚያ ወንድሜ እንዳገሩ ደንብ ሰውዬው ሚስቴን ይጠብልኝ ሲል ሰውየው ናቀው። ከዚያ በዚያ ጊዜ ወንድሜ የጠረዳው ኢገማ (የኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበር) ሊቀመንበር ዋና ሰብሳቢ ለነበረው አቶ ሴላ ከሪዮ ይነግረዋል። አቶ ሴላ ሚስትህ በጠራራ ስትዳፈር ለምን ዝም ትላለህ አትገድለውም ወይ ብሎ ነገረው። ከዚያ ብዙም ሳይቆይ አንድ ዘመድ ሞቶብን ጎግ ቀበሌ በዜፈን ላይ /ለቅሶ ላይ ይዘፈናል/ ተገናኙና ወንድሜ በጠራራ ፀሐይ በጦር ወግቶ ገደለው። ከዚያ በኋላ ወንድሜ እጁን ሰጠ። እናቴ ደግሞ

[28] ዶዬ ፣ ሚዛን 2003

> በዚያ ሰዓት ያለችኝ እንቺን በእሻንት ከከፈልን እኛ ወደ ጫካ አንገባም ብላ ሽማገሌ መሀል ገብቶ ለእሻ ተሰጠሁ። ያኔ እድሜዬን በውል አላውቅም ያኔ በግምት ከ8 እስከ 10 ዓመት እሆን ነበር።
>
> በወቅቱ እሻው ሲከፈል። ወንዝ ዳር ሄደን ቤተሰቦቼ ለኛ ለገዳይ ኮምሩቶች ሰጡኝ። ከዚያ በኋላ የኛ ኮሞሩቶች ከወንዝ ወዲያ ላሉ የሚች ኮሞሩቶች ሰጡኝ። እኔ ስሰጥ የሚቼ ህይወት ተነሳ ብለው ሁሉም ጮሁ። የዚያኔ ጩኸቱ የሆነ ህመም ፈጥሮብኛል። ከዚያ አንድ አሮጊት ሴት ተቀበሉኝና ወደ ቤታቸው ተወሰድኩ። ከዚያ ሰዓት ጀምሮ የደረሰብኝ ጥቃት ብዙ ነው። ይቺ የእሻ ናት እያሉ ለቅሶ የመጣ ሁሉ ይኮረኩመኛል፣ ይጎስመኛል። እርር ብዬ አለቅሳለሁ የሚያግዘኝ የለም። ህፃን አገዙ ወፍጮ እፈጫለሁ። ምክንያት እየፈለጉ ይደበድቡኝ ነበር። በተለይ ጠጥተው ሲመጡ ይመቱኛል። ለኔ የተወሰነ ልጅ ነበር እየመጣ ያስቸግረኝ ነበር። ከዚያ በኋላ ደፈረኝ። ቤተሰቡም ከደፈርካት ሚስትህ ናት ብለው ቤት ሰርቶ አስወጣኝ ከዚያ ሁለት ወንድ ልጆች ከወለድኩ በኋላ ሌላ ሚስት ማግባት ፈለገና አባረረኝ። ተባርሬ ከልጆቼ ጋር ተቸግሬ ሳለ የሱ ታናሽ ለምን ታባርራለህ የእሻ ናት ብሎ ወረሰኝ። እሱም ወርሶ ሚስት አድርጎ አንድ ሴት ልጅ ካስወለደኝ በኋላ እንደወንድሙ ሌላ ማግባት ሲፈልግ ይደበድበኝ ጀመር። ከዚያም እሱም አባረረኝ። አሁን ያለሁት ገድሎ በእሻ ያስከፈለኝ ወንድሜ ጋር ነው። ችግር ላይ ነኝ። ሌላ ማግባት አልችልም፣ በሽሽም የእሻ ነኝና ወንድሜን ይገድሉብኛል። እናም እንዲሁ አለሁ።[29]

የጋድያ ወንጀል በድብቅ የሚደረግበት አጋጣሚው ብዙ ነው። ማን እንደገደለው የማያውቁ ቤተ-ዘመዶች የሟቹን ገዳይ ለማወቅ በርካታ ጥረት ያደርጋሉ። አንድም ወደ ቃልቻዎች ሄደው አልያም ወደ ኮሞሩት /ጣዓባቶች ሄደው/ የገዳዩ ማንነት እንዲታወቅ ያደርጋሉ። በጉዳዩ የሚጠረጥሩት ሰው ካለ ወደ ቃልቻው ወይም ወደ ኮሞሩት ሄደው ጉዳያቸውን ያመለክታሉ። ጉዳዩን የሚያዩት አካላት ተጠርጣሪውን ጠርተው የተጠረጠረበትን ወንጀል መፈጸም አለመፈጸሙን ይጠይቃሉ። ተጠርጣሪው ጉዳዩን እንዳልፈጸመ ከተናገረ እውነቱን በመሃላ እንዲያረጋግጥ እርግማንም ይደረጋል። እርግማኑ ከሳሽ በሃሰት ከሶት ከሆነ መከራ በእሱ እና በዘሮቹ ላይ እንዲደርስ ካልሆነና ተከሳሽ ጉዳዩን ፈጽሞ እየካደ ከሆነ እርግማኑ በሱና በዘሮቹ ላይ እንዲደርስ የሚያደርግ ነው። ወልደየስ በቅርቡ በባለ ሀብቶች ዙሪያ የተፈጸመውን ድብቅ የጋድያ ወንጀል በጌሻ አካባቢ፣ በበገሊጌሻ ቀበሌ የሚኖር ቀደም ሲል የዝናብ አዝናቢ ቤተሰብ የነበረው ሻያ እንዴት ጉዳዩን እንዳወጣው ይተርካሉ። ሻያ በአካባቢው በከፍተኛ ደረጃ የሚከበር እንዲሁም እሱን ባናከብረውና ብንቀሽው የሆነ ነገር ይደርስብናል ብሎ ህዝቡ በጣም የሚያምንበት ባላባት ነው።

[29] ዶኒያ ሚሰዪያ፣ 2003

ሻያ ከደርግ ጊዜ ጀምሮ ብዙ የተፋለመ ሰው ነው። ከዚያ በኋላ ኢህአዴግ ከመጣ በኋላ ሸፍተው የነበሩ ሰዎችን የመለሰበት ሁኔታ ነው ያለው። በቅርቡ ኢንቬስተሮች ከፍተኛ ደረጃ እዚህ ሻሻ ወረዳ ላይ የቺሉ ተፋሰስን ይዘው ቦታ ተሰጥቷቸው እየሰሩ እያሉ  አንዱ ይበልጠኛል የሚል ቅናት ያድርበታል። ሌላኛው  ኢንቬስተር ለማሽላ መውቂያ በጣም ታዋቂ የሆነ መካኒክ ከዚያ ይዞ ይመጣል። የመጣው መካኒክ ማሽነሪዎቹን ስለሚያውቅ ከኛ ሲበልጥ ነውና ይሄንን ነገር እንዴት እናድርግ ብለው ይመካከራሉ። ከዚያ መሣሪያና ገዳይ አዘጋጅተው ልክ ገዳዩ መኢኒትን መስሉ አለባበሱን ቀይሮ በመምጣት  ልጁን ሥራ ሰርቶ አርፎ ደክሞ በተኛበት ቦታ ላይ በጥይት ይመታዋል። ሰውዬ ያንን ነገር ሲያደርግ በብሄረሰቡ ተመሣኝቶ ነበር። መካኒኩን የገደለው አንድ መኢኒት ነው ተብሎ በስፋት ተወራ። ኢንቨስተሮች እዚህ ጋ ከመጡ በቀጣይ እ.. ቦታው ይወሰዳል፣ እ… ህዝቡ ይባልጋል በሚል ታሳቢ  ብዙ ነገር ስለነበር ለሰበብ አደረጉበት።  ከዚያ በኋላ ይህ ግዛቱ የሻያ ነውና  ሻያ ወደ ወረዳው ተጠራና መጣ። እነማን ናቸው የሚጠረጠሩት ብሎ ሰዎቹ ተጠሩ። የሱ ሰዎች እዚያ ዙሪያ ላይ ያሉት በሱ እንዲምሉ ተደረጉ። እየመጡ ማሉ።  ሻያ አስማለ ከዚያ ሁሉም ገድያውን እንዳልፈጸሙ ከማሉ በኋላ ሻያ ገዳዩ በፍፁም እኛ ጋ የለም ራሳችሁን ፈትሹ አላቸው። ከዚያ ሲጠናና ክትትል ሲደረግ በቦታው የነበሩት ሀኪሞች እንዲህ ዓይነት ሰውዬ ነው የመታው። እከሌ ነው የመታው ብለው እየጠቆሙ ምርመራው እየተጣራ ሲሄድ  ሀቁ ወጣ። እነሱው ለግድያው ላዘጋጁት ሰው መሣሪያውን በትራክተር ስር አድርገው ይዘውለት የገቡ እንደሆነ ታወቀ። ከዚያ ጉዳዩ ወደ ህግ ቀርቧል። ይሄ በ2002 የሆነ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። [30]

ወደ ቃልቻዎች በመሄድ በማስረገም የሚወጡም በርካታ የግድያ ወንጀሎች ይፈጸማሉ። የመረጃ አቀባዩ መልኪ፡፡

አንዱ ጋዬ ዲጋሳ የሚባል አለ። ባቹማ 02 ቀበሌ በ1990 ዓ.ም ሰው ይገድልና በጥርጣሬ ይታሰራል። ከዚያ ማስረጃ ስለታጣ ይፈታል። ሲፈታም ሰውዬው አሻ አልከፈለም። እናም ተጎጂዎች በሰውር ሄደው ረገሙት። እንደገና ከዚያን ዘመን ጀምሮ ይሰርቅ ነበር። ሰዎቹ እኛ የወሰደውን እናውቅም። የምታውቀው ሺናፕ ነህ ተከታትልልን ጉልበታችን ብለው ወደ ቃልቻ ሄደው ረገሙት። ከዚያ በኋላ ሲመጣ ሆዱ ማበጥ ጀመረ። ታሞ ሊሞት ሲል ተናዘዘ። እከሌን ገድያለሁ፣ የእከሌን በግ ሰርቄ ወስጄ በልቻለሁ ብሎ በቅርብ በ2003 ሞቶ ቀበርነው።[31]

---

[30] ወልደየስ፣ ሚያዚያ 2003

[31] መሰሉ፣ ሚያዚያ 2003

### 2.3.4 የቡድን ጠብ

የቡድን ጠብ ሁለት ጎራ የለዩና የተቧደኑ አካላት የሚያደርጉት ጸብ ነው። ብሔረሰቦች በብሔረሰብና በብሔረሰብ፣ ወይም አንድ ብሔረሰብ ውስጥ ባሉ በጎሳና ጎሳ፣ መካከል የሚነሱትን ግጭቶች ይመለከታል።

- የብሔረሰብ ጠብ

የመኢኒት ብሔረሰብ በዋንኛንት በድንበር መግፋት፣ በከብት መዘራረፍና በሰው ግድያ ከሱርማ ብሔረሰብ ጋር በተደጋጋሚ ይጋጫል። ይሄንን ግጭት ለማብረድ መንግሥትን ጨምሮ ኮሞሩቶች /ባላባቶች/፣ ተዋቂ የአገር ሽማግሌዎች እንዲሁም ቃልቻዎች የየራሳቸውን ጥረት ያደርጋሉ።

በመኢኒት ብሔረሰብ ውስጥ ካሉት ሁለት ወረዳዎች ውስጥ ወደ ሱርማ የሚቀርበውና ተጎራባች የሆነው የመኢኒት ሻሻ ወረዳ ብዙ ጊዜ ከሱርማ ጋር ይጋጫል። የግጭት ምክንቶቹ የከብት መዘራረፍ እንደሆነ ቀልፍ የመረጃ አቀባዬ ይናገራሉ። "በመጀመሪያ ግጭቱ የተነሳው ሱርማ ወደ መኢኒት መጥተው ስድስት ከብት ዘርፈው ይሄዳሉ።"[32]

መኢኒቶች የተሰረቀባቸውን ከብቶች ለማስመለስ ወደ ሱርማ ለመዝመት ሲሉ ኢንፎርሜሽን ደርሷቸው ባላባቶችን አደራጅተን ህዝቡን እንዳረጋጉ የሚናገሩት ደግሞ የመኢኒት ጎልዲያ ወረዳ ፖሊስ አባኘር ከባላባቶች ጋር በመሆን ሊፈጠር የነበረውን ጸብ እንዳበረዱ እንዲህ ይናገራሉ።

> በዴቻ አካባቢ ባቡሹ የተባለ ታዋቂ ባለባት አለ። በረሃው አካባቢ ማዳቻር የሚባል ባላባት አለ። በሱርማና በመኢኒት መካከል በተፈጠረው ግጭት እንደስማን እነዚህ ባላባቶች አነጋግረን ሰዎቹ ወደ ጠብ እንዳይገቡ እንዲመክሩ አደረግን። ከዞኑ እና ከዴቻ ወረዳ ፖሊስ ጋር ተቀናጅተን /ዴቻ ወረዳ በከፋ ዞን ውስጥ የሚገኝ ነው/ ተጋጭዎችን አወያይተን በባላባቶቻቸው አማካይነት ይቅርታ ተጠያቀውና ከብት ቃርዶ ደሙን ተረማምደው እንዲሁም ጦር በድንጋይ በመውጋት መሃላ ገብተው ትልቅ ሥራ ሰርተን ተመልሰናል።

---

[32] [illegible] 2004

> ባላባቶቹ ከመንግሥት ይልቅ በጣም ትልቅ ተሰሚነት በአካባቢው ስላቸው ትልቅ ነገር እያደረጉልን ነው፡፡ [33]

በተደረጉ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ላይ የተገኙት የሱርማ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግሥት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ አብረሃም ባርቡሌ የሚከተለውን ነግረውኛል፡፡

በመጀመሪያ ግጭቱ የተነሳው ሱርማ ወደ መኢኒት መጥተው ስድስት ከብት ዘርፈው ይሄዳሉ፡፡ እንዲያውም አንደኛው ከብት በመንገድ አምልጣቸው ይመለሳል፡፡ ይሄ ወሬ በመኢኒቶች መንደር ተሰማና መኢኒቶች ደግሞ መሳሪያ ይዘው በቡድን ተደራጅተው በመምጣትና ወደ ሱርማ ግባት በመዝለቅ አንድ መቶ አስራ ስድስት የሚደርሱ ከብቶችን ዘርፈው ተመለሱ፡፡ እንደገና ሱርማዎች ተደራጁና ውድምት ከተባለ ቀበሌያቸው ተነስተው ሻልኩት የተሰኘት ቀበሌያቸውን ተሻግረው ማቆር/ጥቁር ውሃ ማለት ነው/ የተባለች መኢኒቶች ቀበሌ በመምጣት በርካታ ከብት ሰረቁ፡፡ በዚህ ጊዜ ከፍተኛ ተኩስ ተከፈተ፡፡ እናም ከመኢኒት ሁለት ሰው ሲሞት አንዱ ቆሰለ፡፡ ከሱርማም ወገን አንድ ሰው ሞቶ አንዱ ቆሰለ፡፡ በዚህ ጊዜ እኔ የሱርማ ወረዳ የጸጥታ አስተዳደር ነበርኩ፡፡ ከዚያ ግጭቱን ለማቆም ከሁለቱም ብሔረሰቦች ያለን አመራሮች ተሰብስበን ውይይት አደረግን፡፡ የቤንች ማጂ ዞን እና ክልሉ እንዲሁም ሜርሲኮር የተባለ ግጭት አስወጋጅ ድርጅትም በጉዳዩ ውስጥ ተሳታፊ ሆኑ፡፡ ከዚያም ከመንግሥት ኃይላት ጋር በመሆን ለሱርማ ሃያ ሁለት ቀበሌ ባላባቶች እንዲገኙ ተደረገ፡፡ በሱርማ ታዋቂ ከሆኑ ባላባቶች ውስጥ ማጂ ገጂ፣ጎቢ፣ ጃዋ፣ካርስ ወርጂ፣ጋር ቡርጂ ሲገኙ በመኢኒት በኩልም ታዋቂ ባላባቶች እንደ ሻያና ቢለሙ ተገኝተዋል፡፡ ከመንግሥት ወገን የክልሉ የጸጥታ አስተዳደር እንዲሁም የአስተዳደሩ የጸጥታ ምክትል ቢሮ ኃላፊው፣ ከዞን አመራሮች እና የወረዳ የፍትህ አካላት ተገኝተዋል፡፡ ለውይይት የተመረጠው ቦታ ማጂ ሆነ፡፡ ከዚያም ሞትና ዘረፋ ይቁም በሚል መሪ ቃል ከፍተኛ ውይይት ተደረገ፡፡ የተዘረፉ ከብቶች በጥቂቱም ቢሆን እንዲመለሱ ተደረገ፡፡ በተገኘ የመረጃ ማሰባሰብ ከሱርማ ላይ ከተወሰዱት ውስጥ ሰማኒ ከብቶች ተመለሱ፡፡ በአንጻሩም ከመኢኒት ከተወሰዱት ውስጥ አስራ ሁለት ከብቶች ተመለሱ፡፡ ከሁለቱም ወገን ያሉ ባላባቶች በመረጧቸው ሦስት ሦስት ባላባቶች አማካይነት በሬ ታርዶ ቃለ መሃላ ተፈጸመ፡፡ ቃለ መሃላው በድጋሚ በጦር ላለመፈላለግና የተዘረፉ ቀሪ ከብቶችን ለማስመለስ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ችግሩ በዘላቂነት አሁን ድረስ አልተፈታም፡፡ በ2004 ከመጋቢት 14 እና 15 በድጋሚ የክልሉ ፕሬዚዳንት በተገኙበት ጥምር ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ ቀጣይ ውይይቶች ይደረጋሉ፡፡

---

[33] አመራ፣ ሚያዚያ 2003

ከሱርማ ጋር የሚፈጠሩት ግጭቶች በተደጋጋሚ እልባት እንዲያገኙ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ጥረቶቹ በተደጋጋሚ እየፈረሱ ግጭቶቹ እንደቀጠሉ ነው፡፡ ወልደየስ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> ይሄንን ግጭት በቅድሚያ ለመፍታት የአገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች እስከ ማጂ ድረስ ሄደው ተነጋግረው ከብት አርደው ከተስማሙ በኋላ ሱርማ ይሄንን ደንብ የሚጥስበትና አሁንም ሌላ ስራ እየሰራ ያለበት ሁኔታ በመፈጠሩ እነዚህም ለሬቬንጅ የሚሄዱበት እነሱን አባረው ከብት ዘረፋ የሚባልበት ነገር አለ፡፡ አሁን ይሄ አለ ግጭቱ ያልቆመበት ሁኔታ አለ፡፡ ይሄንን ግጭት ለማቆም ሱርማ ውስጥ ዝናብ የሚያዘንቡ ባላባቶች አሉ እነሱ የሚያምኑባቸው እኛጋም እነዚህ ሰዎች አሉ፡፡ ከእነሱ ጋር ሄዶ እነሱም አውግዘው የኛዎቹ ታዋቂ ሰዎችን ጉዳይ ሲያከብሩ ሱርማ የማያከብርበት ሁኔታ በመፈጠሩ ግጭቱ እየተባባሰ ሄዶ ትናንትና ሰዎች ሄደው ይሄንን ለማብረድ የሚካሄድ ነገር አለ፡፡ ይሄ ወደፊት እንዴት ይበርዳል አላውቅም፡፡ "ሰውን የመሰለ ነገር ገድለው የእነሱ ከብት መዘረፍ ከሰው ከህይወት እኩል ነወይ" ይሄኛው ይላል፡፡ያኛው ደግሞ ትልቅ ክብር የምንሰጠው ለከብት እንጂ ለሰው አይደለም ይላሉ፡፡[34]

በሙኤኒት እና የሱርማ ብሔረሰብ መካከል ያለው ግጭት ለመፍታት በባህላዊውም ይሁን በዘመናዊ የፍርህ ሥርዓቶች ተደጋጋሚ ሙከራዎች ቢደረጉም እስካሁን የለየና አስተማማኝ የሚባል እርቅን ማውረድ አልተቻለም፡፡ ይህ ግጭት በሂደት ወደፊት የሚፈታበት እድል እንደሚኖር ግን ሁሉም ይስማማሉ፡፡

- የጎሳ ጠብ

በሙኤኒት ብሔረሰብ የጎሳ ግጭቶች የሚቀሰቀሱት አንድ የግድያ ጸብ ከጎሳ ውጭ ሲከሰት ነው፡፡ ገድያው የተፈጠረው ከተለያዩ ጎሳዎች ከሆነ ግጭቱም በሁለቱ ጎሳዎች መካከል ይሆናል ማለት ነው፡፡ በያርጣ ቀበሌ የአማራጭ መሰረተ ትምህርት መምህር የሆነውና በቀደሙት ጊዜያት በሙኤኒት ጎልድያ ሚኒሻ ጽ/ቤት ውስጥ የግጭት መከላከል ሥራ ይሰራ የነበረው አቶ ታዬ መስፍን በእሻ የማስከፈል ሥነ-ሥርዓት ወቅት ከኮሞሩቶች ጋር ሰላምን በማረጋጋት ስራው ያየውን የጎሳ ግጭት ሁኔታ እንዲህ ተርኮልኛል፡፡

> ጉዳዩ ቢጋቺት አገልግሎት ፎልዱ ቀበሌ ነው የተከሰተው፡፡ ጊዜው በጥር 2002 ዓ.ም ነው፡፡ የጌራ እና የባዲንሳ ጎሳዎች ናቸው፡፡ በመጀመሪያ አንድ ገደለ፡፡ ከዚያ እሼውን ሳይከፍል በመቆየቱ እሱን ሊገድሉት ሲሉ ደግሞ እሱ እንዱን ገደለ፡፡ የባዲንሳው ሰው ሁለት ሰው ገደለ፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ እሱን ገደሉት፡፡ የጌራው

[34] ወልደየስ፣ ሚያዚያ 2003

> ሰው ገደለው። ጉዳዩ የከረረ ግጭት ከማምጣቱ በፊት ኮሞሩቶች በመካከል ገቡ። በቤሔረሰቡ ልማድና ደንብ ግድያ ከኖረ ሁሌም አሻ መከፈል አለበት። እናም ሁለቱን ጎሳዎች ለማስታረቅ ሽማግሌዎቹ ብዙ ጥረት አደረጉ። የሚቻቹ ቁጥር ከፍ ስላለ የአሻ ክፍያውም ከፍ ስላለ ሁለት ሰው የሞተበት ጎሳ ትርፍ እንዲከፈለው ጠየቀ። ይሁን እንጅ ከዚህኛውም ጎሳ ሰው ስለሞተ ጉዳዩን ኮሞሩት አሻዎቹ ከፍተኛ ውይይት አድርገውበት የማጣጣት ሥራ ሰርተው ክርክሩ እልባት አገኘ። ሁለቱ ሰዎች አንድ ቀን ስለሞቱ ተጣጡ። ሁለቱም ጎሳዎች ስለሞቱባቸው አሻው ሳየይከፈል ቀረ። መጀመሪያ ለሞተውን ግን ባይ-ጎሳዎች ለጌራዎች አሻ እንዲከፍሉ እንዲከፍሉ ተወሰነ። በዚህም መሰረት አሻው በወንዝ ዳር ተከፈለ። ያኔ የኛ ሥራ ህግ ማስከበር ነበር እንጂ ሌላ ሥራ አልሰራንም።[35]

በሙአኒት ጎልድያ ወረዳ በቢያገሊች፣ በጎማና በዱማ ዳሸ ቀበሌዎች የሚነሱ በርካታ ግጭቶችን በአገር ሽማግሌነትና በኮሞርት አሻነት የዳኙት ዋየች ጃሻ በሁለት ጎሳዎች መካከል የተፈጠረውን ጸብ በኮሞሩት አሻነት እንዴት እንዳስታረቁት በማስታወስ እንዲህ ነግረውኛል።

በመጀመሪያ የጌሊ ጎሳ የ,ጋንጎን ዘር ገደለ። ጠቡ የተነሳው በስካር ነው አረቄና ቦርዴ፣ ጠጅ አቀላቅለው ጠጥተው የተፈጠረ ነው። ጨበራ ከተማ ላይ ወደ ቤታቸው ሲሄዱ ሲል ነው ጠቡ የተፈጠረውና የገደለው። እኔ እቤት ቁጭ ብያለሁ። የገዳዩ አባት መጣና ነገረኝ። ሰውየው ሲመጣ ለራሱ ሁለት ጦር በጁ ይዟል። መንገድ ላይ ከተሰማ እንዳይገድሉት እራሱን ለመከላከል ነው። እየተሽሎከለከ በሌላ መንገድ ነው የመጣው ቆሞ እየተርበተበተ፣ እየተንቀጠቀጠ ነው የነገረኝ። 'እባክህን እጃችን ተሳስቷልና ኪ,ጋንጎ ዘር ,ጋራ አስታርቀን ፣ንገራቸውና እሬሳው የወደቀው በዚህ ቦታ ነው፣ ሬሳቸውን ብቻ አንስተው ወደ ቤታቸው ወስደው ይቅበሩ። ልጁ ገድሏልና እኔ እከፍላለሁ' ብሎ ነገረኝ። እኔን የመረጠበት ዋና ምክንያት የጌ ጎሳ ከሁለቱ ጎሳ ውጪ የሆነ እና በሁለቱ ጎሳዎች መካከል ቢገባ የተከበረና እርቅ ማውረድ የሚችል ነው ብሎ በመምረጥ ነው። እኔም ተናገሮ ያሳምንልኛል፣ ጉዳዩም ዳር ያደርስልኛል ብሎ በማመን ነው።[36] በቤሔረሰቡ የግድያ ግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ ነፍስ ያጠፋ ሰው የሚከሰው ተመኀኘ የሆነ ክፍያን ወይም አሻን ነው። ከላይ በዝርዝር ያየናቸው የግጭት አይነቶች በአብዛኛው በቤሔረሰቡ ውስጥ የሚያጋጥሙ ሲሆን የባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋሞቹ ደግሞ ችግሮቹን እንደ አግባብ አግባብነቸው እየፈቱ የህዝቡ ሰላማዊና የተረጋጋ ህይወት እንዲቀጥል እያደረጉ ነው።

---

[35] ዖቄ፣ ሚያዚያ 2003

[36] ዋየች፣ ሚያዚያ 2003

# 3. የመኤኒት ብሔረሰብ የግጭት መፍቻ ተቋማት

በብሔረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ግጭቶች እንደሚከሰቱ ቀደም ብለን አይተናል፡፡ እነዚሁ ግጭቶች እንደመልክ መልካቸው ወይንም እንደ አይነት አይነታቸው በተለያዩ ተቋማት ይፈታሉ፡፡ በዚያው ልክና መጠንም ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ የየራሳቸው የግጭት አፈታት ሂደትን ይከተላሉ፡፡ ከዚህ በታችም ይሄንኑ ለማየት እንሞክራለን፡፡

## 3.1. ባህላዊ የፍትህ ተቋማት

በመኤኒት ብሔረሰብ ሦስት አይነት ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት እንዳሉ ከዚህ ቀደም ባለ ምዕራፍ ውስጥ የተገለጸ ነው፡፡ እነሱም ኮሞሩት፣ የአካባቢ ሽማግሌዎች እና ቃልቻዎች ናቸው፡፡ የእነዚህንም ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት የግጭት አፈታት ሂደት ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 3.1.1 ኮሞሩት /ባላባት/

ስለ መኤኒት ባህላዊ አስተዳደርና አመሰራረት እንዲሁም እድገት የሚያትቱ በቂ የጽሑፍ መረጃ አላገኘሁም፡፡ ይሁን እንጂ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮቼ ከሆኑት ውስጥ አቶ ብርሃኑ፣ዋየት ጃሻና በድሉ እንደነገሩኝ መኤኒቶች ለዘመናት የተዳደሩት በየጎሳ መሪዎቻቸው /ኮሞሩት/ አማካይነት ነው፡፡ እያንዳንዱ ጎሳ የራሱ የሆነ ኮሞሩት አለው፡፡ በዚህም የተነሳና በብሔረሰቡ ውስጥ ከስልሳ በላይ ጎሳዎች በመኖራቸው መኤኒቶች እንደ ብሔረሰብ ጠንካራ የሆነ ማዕከላዊ የፖለቲካ አመራር ወይም ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት አልነበራቸውም፡፡ ዘሪሁን በዚህ ጉዳይ የሚከተለውን ጽፏል፡፡ "There were a number of komrut in various distrcts. There was no single all-ruling komrut. There were rather several komruts ::"

የኮሞሩት ተቋማት እንደሌሎቹ ተቋማት ውስጣቸው በተለያዩ አካላትና ክፍሎች በተዋረድ የሚመሩ አካላት ያሉት አይደለም፡፡ "በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ ወጥ የሆነና የተደራጀ ኮሞሩታዊ አስተዳደር የለም፡፡ የሚያስተዳድረው ባላባቱ ነው"[37] ኮሞሩቶች በንጽህና የሚኖሩ፣ ወደ ፃድቅነት ያጋደለ ስሜት ያላቸው በመሆናቸው ብዙ ጊዜ ከህዝቡ ጋር በቀጥታ የሚገናኙ

---

[37] ቃለ ፡ ዋየት ፡ ብርሃኑ ሚያዚያ 2003

አይደሉም። በመሆኑም በህዝቡ እና በእነሱ መካከል ጉዳዮች እንዲፈጸሙ የሚያደርጉ ኮሞሮት በይቶ የሚባሉ ሰዎች አሏቸው። አወቀ በዚህ ጉዳይ የሚከተለውን ጽፏል። "መኤኒቶች የጠነከረ የአርስበርስም ሆነ የፖለቲካ ትስስር የላቸውም። እያንዳንዱ የመኤኒት ማህበረሰብ የራሱ የሆነ መሪ ማለትም ኮሞሩትስ አለው። ከኮሞሩትስ በታች ያሉት መሪዎች ኮሞሩትስ በይቶ ይባላሉ። እነዚህ መሪዎች ማህበረሰቡን ለማዘዝ የሚያስችል ኃይል የላቸውም። ነገር ግን ከሀገር ሽማግሌዎች የመጣን ትእዛዝ ያስፈፅማሉ።" (Aweke, 2000፣111)

ኮሞሮቶች ከህዝቡ ጋ የሚገናኙት ለዚሁ ጉዳይ ተብለው በተመረጡ ሽማግሌዎች እንደሆነ የገለጸው ደግሞ ዘሪሁን ነው።" "The comrut would not be directly approached by any person. He would communicate with the people through a special old man assigned for this purpose" Zerihun,2008).

እያንዳንዱ ኮሞሩት በጎሳው ላይ ማህበረሰባዊ፣ ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ የሚያሳድር ነው። ኮሞሩትነት የሚገኘው በውርስ ሲሆን እያንዳንዱ የጎሳ መሪ ስልጣኑን እያወረሰ ይተላለፋል። የኮሞሩትነት ስልጣን ከብሔረሰቡ እኩል እድሜ ያለው ሲሆን ስልጣንም ከልጅ ልጅ እየተወራረሰ የተጓዘ ነው። የመኤኒት መስራች ወይም ቀዳሚው አባት ከሆነው ከዎሬ ወደ ልጁ ሞርቡስ እንዲሁም የልጅ ልጆቹ እየተላለፈ የመጣ ነው። ቁልፍ መረጃ አቀባዩ አቶ በድሉ የኮሞሩት ሥልጣን በውርስ እንደሚተላለፍ የሚከተለውን ይገልጻሉ። "እያንዳንዱ ጎሳ የራሱ የሆነ ኮሞሩት ነበረው። ያ ሰው ሲሞት ኮሞሮትነቱ የሚተላለፈው ለሱ ልጅ ወይም ዘመድ ነው። ንግሥና ለልጅ እንደሚተላለፈው በሥርዓት ነው የሚተላለፈው።"[38] መለኮታዊ የሆነ የመምራት፣ የማዘዝና የመቅጣት ኃይል እንዳላቸው የሚታመንባቸው ኮሞሮቶች ስልጣን የሚተላለፍላቸው በመለኮት ልዩ ምርጫ ነው። ሥልጣን አወራረሱን በተመለከተ ዘሪሁን የሚከተለውን ይገልጻል።

> ኮሞሩት የሆነ አባት ሲሞት ከወንድ ልጆቹ መሀል አንዱ ተመርጦ ኮሞሩት ይሆናል። ኮሞሩት ለመሆን ወንድ መሆን አንዱ መመዘኛ ሲሆን ሴቶች ኮሞሩት ሆነው አያውቁም። ለኮሞሩትነት ምርጫ የሚደረገው ጠዋት ነው። በዘር ሀረጉ ውስጥ ያሉ ይሰበሰባሉ። እናም ሁሉም ባሉበት አንዳች መለኮታዊ ተአምር እስኪፈጸም ድረስ ይጠብቃሉ። ወደ አምላካቸው ቱማ ወይም የሪ ንጉሣቸውን

[38] ፀሐይ ግርማ 2003

> እንዲሰጣቸው ይጸልያሉ። ሁሉም ሰዎች እጆቻቸውን እንዲያጣምሩ እና አይኖቻቸውን እንዲጨፍኑ ይደረጋል። ከዚያ በኋላ ከመካከላቸው አንዱ ማንም ሰው ሳይሰጠው የተለያዩ ነገሮች እንደ ጤፍ፣ ወተትና ማር ይዞ ይገኛል። ይህ ተአምር የተፈጠረለት እና ከዘር ውስጥ የተገኘው ልጅ ወይም ዘመድ ኮምሩት ይሆናል።
>
> The Komrutship was awarded on one of the sons of the Komrut. When a komrut is going to be appointed, all the lineage members would gather at a place. Early in the morning, they would sit and wait to see some supernatural manifestation occur. They would pray to Tumma, or Yeeri. As they pray pleading Tumma to give them a Komrut, all the people being told to clasp their hands and shut their eyes, one of the persons (a male) would be found handling varities of crops such as Teff, and also Milk honey without any human deed. This is the indication of the selection of Kumrut (Zerihun, 2008).

ኮምሩት የሆነ ሰው ከሌላው ሰው በተለያዩ መንገዶች ይለያል። ከአውራሪስ ቀንድ የተሰራ መጠጫ ይኖረዋል። የሚበላው የበግ ሥጋ ሲሆን የፍየል፣ የከብትና የዶሮ ሥጋ አይበላም። የሚጠጣው የማር ጭማቂ ከጥቁር ንብስ ዱቄት ጋር ተደባልቆ የሚዘጋጅ መጠጥን ነው።

ኮምሩቶች የሃይማኖት ሥርዓት የሚያከናውኑበት የተለየ ቤት አላቸው። አንዳንዶቹ ኮምሩቶች ዝናብ አዝናቢዎች እንደሆኑ በህብረተሰቡ ዘንድ ይታመናል። ስልጣኑም የተገኘው ከመለኮታዊ ኃይል እንደሆነ ስለሚታመን በቤኒሻንጉል ኮምሩቶች እንደ ኘራይ /መልአክ/ ልጅ ይቆጠራሉ። ስቤሌሰቡ አባልት ከኮምሩት አፍ የወጣ ቃል በህይወታቸው ላይ ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣ ያምናሉ። ወልደየስ ስለኮምሩት ሻያ የሚከተለውን ነግረውኛል። "ሻያ እንግዲህ በጌሻ አካባቢ የሚኖር ቀደም ሲል የዝናብ አዝናቢ ቤተሰብ የነበረ እና በአካባቢው በከፍተኛ ደረጃ የሚያከብሩትና እሱን ባናከብረውና ብንቆሽው የሆነ ነገር ይደርስብናል ብሉ ህዝቡ በጣም የሚያምንበት ሰው ነው።"[illegible]

ኮምሩቶች ማንኛውንም አይነት ግጭት ይፈታሉ። አንዳንዱ ራሳቸው ቃልቻ ጭምር ሆነው ሊገኙ ስለሚችሉ የቃልቻንና የአገር ሽማግሌዎችን ሥራ ይሰራሉ። ጎሳን ከጎሳ በሚያጋጩ ጸቦች፣ በሰው መግደልና በዘረፋ ምክንያት ግጭት ውስጥ የገቡትን አካላት በማነጋገርና ተገቢውን ፍርድ በመስጠት፣ አስፈላጊ የሆኑ የካሳ ክፍያዎች ጭምር እንዲከፈሉ እና ግጭት

[illegible] ወልደየስ፡ ሚያዚያ 2000

ውስጥ የገቡት ወገኖች በመተማመን ጸቡን እንዲያበርዱ ያደርጋሉ። አቶ ብርሃኑ ኮሞሩቶችን በተመለከተ የሚከተለውን ነግረውኛል። "በጎሳ በኩል አንድ ሰው ሲሞት የሌላው ጎሳ የብቀላ አይነት ያደርጋሉ። ዘመድ ለዘመድ ጎሳ ለጎሳ ይበቀላሉ። ኮምሩት ከገባ ወዲያው ይታረቃሉ።"[13]

የመኢኒት ቤተሰብ ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ግጭት ውስጥ በሚገባበት ጊዜ ከሌላው ቤተሰብ ጎሳ መሪዎች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች ጋር በመነጋገርና በመደራደር ግጭቱ እንዲበርድ በማድረግ ራሳቸው የእርቁ ሥነ ሥርዓት ፈጻሚ በመሆን ያገለግሉ። አንዳንዴ ለቤተሰቡ መነጋገሪያ የሆኑ ክስተቶችም ሲያጋጥሙ ጉዳዩን የሚያጣሩትና መፍትሄ የሚሰጡት ኮሞሩቶች ናቸው። የሚመሩትን ማህበረሰብ በመምራት ግንባር ቀደሙን ሚናም የሚጫወቱ እንደሆኑ ወልደየስ በሚመለከተው መልክ ይገልጹታል።

> ኮሞሩቶች /ባላባቶች/ ማለት በአካባቢው፣ በዚያ ጎሳ ወይም ዙሪያ የሚፈጠሩ ችግሮችን የሚፈቱ፣ ህዚያ ጋ ያለ ህብረተሰብ ሌላውን ሊበድል ቢል የሚከለክሉ፣ አይቻልም ብለው ካሉ እዚያጋ የሚቆምበት እንዲሁም ብሄር ለብሄረሰብ ቢጣላ የራሳቸውን ሰዎች አንድ ነገር አታድርጉ ካሉ የሚቆምበት፣ እነሱ ግንባር ቀደም ሆነው አትጣሉ ካሳዩ ብሄረሰቡ ወይም ጎሳውን መምራት የሚችሉ ናቸው። ተሰሚነት ያላቸው ክፍሎች ሲሆኑ ይሄ ባለቤትነት የሚገኘው በዘር ነው። [14]

የጥንቱ የመኢኒቶች ባህላዊ የአስተዳደር ተቋም፣ የኮሞሩት አስተዳደር በተለይ በደጋው የመኢኒቶች ክፍል እየጠፋ ነው። ቆላው የመኢኒቶች ክፍል የትራንስፖርትም ይሁን ሌሎች ለዘመናዊነት የሚያጋልጡ ጉዳዮች ጋር ያልተዋወቀ በመሆኑ ጭምር የጥንት ባህሉን እንደጠበቀ ያለ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የቆላው ሰው ሰው ገድሎ ወደ ኮሞሩት የሚሄደው በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ብቻ ለመዳኘት ነው። ሰው ገድለው ወደ ቆላው በመሄድ ከአስር ዓመታት በላይ የቆዩትና እስከ ክልሉ አስተዳደር ድረስ በሽፍትነት ጭምር ይታወቁ የነበሩት (አሁን ሰላማዊ ዜጋ ናቸው) አቶ ጥጋቡ የሚከተለውን ብለውኛል። "እዚህ ጋ በሁለት ይከፈላል። በደጋውና በቆላው የደጋው ግጭት ሲፈጠር ወደ መንግሥት ቤት ይሮጣል። የቆላው ግን ወደ ኮሞሩት፣ ወደ ባላባት ቤት ይሮጣል።"[60] አንድና ጠንካራ ማዕከላዊ አስተዳደር ሳይመሰረት በጎሳዎች እንደተከፋፈለ የኖረው የኮሞሮት ተቋም በአጼ ኃ/ሥላሴ አስተዳደር ጊዜ ኮሞሩቶች ምንም አይነት ተቃውሞ አልደረሰባቸውም። ጎሳቸውን በባህላዊ ሥርዓታቸው እያስተዳደሩ ነበር። ይሁን እንጂ ለኮሞሮቹም ይሁን ከበታቻቸቸው ላሉ ለበይቶዎች ፊታውራሪ፣ ግራ አዝማች፣ ቀኝ አዝማች ወዘተ. የሚሉ ማዕረጎች በተጨማሪነት ስልጣን

[60] ጥ.ጋቡ፣ ግ.ቤ.ቃ 2009

ይሰጣቸው ነበር። ከእነዚህ ውስጥ የመረጃ ምንጬ የሆኑት ኮሞሩት ኬኒ ጋሲ በተሰጣቸው ማዕረግ ኪኒ ቀኛዝማች ጋሲ ተብለው እስከ አሁን ድረስ እንደሚጠሩበት ነግረውኛል።

ኮሞሩቶች በደርግ ዘመን ፈታኝ ጊዜ እንዳሳለፉና እንደጨቋኝ ይቆጠሩ እንደነበር ዘሪሁን ይጠቅሳል "During the Durgue's time, however, the komruts had a tough time. They were mistreated and somewere banshed from the land, as they were regarded as the exploiter groups."(Zerihun, 2000) በሌላም በኩል ብዙዎቹ ኮሞሩቶች የደርግን ሥርዓት በመቃወም የትጥቅ ትግል እስከማካሄድ ደርሰዋል። የመረጃ አቀባዩ የአቶ ጥ.ገቡ አባት ፊታውራሪ መንገሻ ደርግን ለዘመናት እንደተዋጉና ኢህአዴግ አገሪቷን ሲቆጣጠር በሰላም እንደገቡ አጫውተውኛል። ወልደየስ ዶሌም ሻያ የተባለው ኮሞሩት ደርግን ብዙ እንደተፋለመና በኢህአዴግ ዘመን ሸፍቶች ሁሉ በሰላም እጃቸውን ለመንግሥት ሰጥተው በሰላም እንዲኖሩ እንዳደረገ ገልጸውልኛል። "ይሄ ሰው እንግዲህ ከደርግ ጊዜ ጀምሮ ብዙ የተፋለመ ሰው ነው። ከዚያ በኋላ ኢህአዴግ ከመጣ በኋላ ሸፍተው የነበሩ ሰዎችን የመለሰበት ሁኔታ ነው ያለው።"[ⁱ] መኢኒት ሻሻ ያገኘኋቸው ኬኒ ቀኛዝማች ጋሲም አሁን ካለው መንግሥት ጋር ተስማምተው እየሰሩ እንደሆነ ገልጸውልናል።

በኢጢቃላይ ኮሞሩት ተቋም በተለያ ጎሳዎች ውስጥ በአንድ ሰው እዝ በባላባቱ ወይም በጎሳ መሪው የሚመራ እንደሆነና የመኢኒት ብሔረሰብም እንደ ብሔረሰብ የጠነከረና አንድ ወጥ ተቋም እንደሌለው ተመልክተናል። ኮሞሮቶች ወይም ባላባቶች ዝናብ አውራጆች እንደሆኑ እንደሚታመንባቸው እና ኮሞሩትነትም በዘር በዘር ውስጥ በፈጠሪ ፈቃድ ለተመረጠው እንደሚተላለፍ አይተናል። እነሱም ጣልቃ የሚገቡባቸውንና የሚፈቷቸውን ጉዳዮች ተመልክተናል። ኮሞሮቶች እሻን በማስከፈል ትልቅ የእርቅ ሥራ እንደሚሰሩ ቀደም ብዬ ገልጫለሁ። በተለይ በቆላው አካባቢ አሁንም እሻን ያስከፍላሉ። ነገር ግን እሻን ከአካባቢው የሚመረጡ ሽማግሌዎችም "ኮሞሩት እሻ" ተብለው ያካሂዱታል።

### 3.1.2. ዞጌሾቢዬቻ /የአገር ሽማግሌዎች/

በመኢኒት ብሔረሰብ ውስጥ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ከሆኑት ውስጥ አንዱና በርካታ ግጭቶችን የሚፈቱት ዞጌሾቢዬቻ ወይም የአገር ሽማግሌዎች ናቸው። እነዚህ የአገር

---

[ⁱ] ወልደየስ ኪኒ ሚያዚያ 2003

ሽማግሌዎች የቤተሰብ፣ የቤት ዘመድ፣ የጎድያ፣ የደፈራና የድንበር ጠብ እስከመዳኘት ድረስ ትልቅ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። የአገር ሽማግሌዎች ያሉበትን ማህበረሰብ ማህበረ-ባህላዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በሚገባ የሚያውቁ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ የሚሰጡት ፍርድ የወጡበትን ማህበረሰብ ሁለንተናዊ ማንነት ስለሚያገናዝብ ተቀባይነቱ ሰፊ ነው። አቶ ብርሃኑ በሽማግሌነት የሚመረጡ ሰዎችን መመዘኛ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> የአገር ሽማግሌዎች የሚመረጡት በአካባቢው ባላቸው ጥሩ ሥነ ምግባር ማለትም በጠብ፣ በሌብነት፣ የሰው ሚስት በመድፈር አይነት ችግሮች የተከሰሱና በችግር ውስጥም የሚገኙ አለመሆናቸው ተረጋግጦ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በንግግር አዋቂነታቸው፣ የብሔረሰቡን ባህል ጠንቅቀው በማወቃቸው እንዲሁም በኑሯቸው ማንነት ጭምር በመታየት ለሽማግሌነት ይመረጣሉ፡፡ አንድ ችግር ሲፈጠር ለዚያ ችግር መፍትሄ ለመስጠት የችግሩ ተካፋይ የሆኑ አካላት ሽማግሌዎቹን በመስማማት ይመርጣሉ፡፡ ችግራቸውን ተከራክሮ ሊያስፈጽምላቸውና እርቅ ያመጣልኛል ያሉትን ሰው ይመርጣሉ፡፡ ግጭት ውስጥ በገቡት በሁለቱም ወገኖች ተቀባይነት ያላገኘ ሽማግሌ ለዳኝነት አይመረጥም፡፡[42]

ብዙ ጊዜ የአገር ሽማግሌዎች ሆነው የሚመረጡት የበቀሉበትን ማህበረሰብ ጠንቅቆ በማወቅ ብቻ ሳይሆን ከእድሜያቸው በመነሳት የሚሰጡት ፍርድ ሚዛናዊ የሆነ፣ በህይወታቸው ለሌላው አርአያ የሆኑና የሚከበሩ፣ የንግግር እውቀታቸው ከፍ ያለና ተናግረው ማሳመን የሚችሉ በመሆን ጭምር ነው። በአገር ሽማግሌነት የተመረጠ ሰው በማዳላትና በሌሎች ወንጀሎች ውስጥ ቢገኝ ከሽማግሌነት ይሻራል ወይም ይወገዳል። አንድ የአገር ሽማግሌ ጠቦችን በመዳኘት ላይ የማይገቡ ጠባዮች ቢታይበት ከሽማግሌነቱ ይነሳና በምትኩ ሌላ ሽማግሌ ይመረጣል፡፡ እሱም የተለያዩ ወንጀሎች ቢሰራ በሰራው ወንጀል እንዲጠየቅ ይደረጋል፡፡ የቢያጌሲች መንደር ኮምሩት አሻ እንዲሁም በርኬታ ጸቦችን በሽማግሌነት የዳኙት ሌላ ከሽማግሌነት ስለሚያስገልሉ ጉዳዮች የሚከተለውን ይገልጻሉ። " በአንድ ወቅት ሽማግሌ የነበረ ሰው እራሱ በጥፋት ውስጥ ቢገኝ ቢሰርቅ፣ ሰው ቢገድል ወይም ሌላውን ንብረት ቢቀማ ከሽማግሌነቱ ይነሳል፡፡"[43] በአጠቃላይ የአገር ሽማግሌዎች አሁንም ድረስ በብሔረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን እየፈቱ ነው።

---

[42] ብርሃኑ ሚያዚያ 2009

[43] ሌሎች ሚያዚያ 2009

### 3.1.3. ኘራይ /ቃልቻ/ የባህላዊ ሃይማኖት

በመእኒት ብሔረሰብ ሌላው የግጭት መፍቻ ተቋም ኘራይ /ቃልቻ/ወይም ባህላዊ ሃይማኖት ነው። ባህላዊ ሃይማኖት ረጅም እድሜ ያስቆጠረ የግጭት መፍቻ ተቋም ነው። በተለይ በጥንት ጊዜ ቃልቻዎች ከፍተኛ ተሰሚነት ያላቸው በመሆኑ በማህበረሰቡ ውስጥ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሄ ሲሰጡ ቆይተዋል። በተለይም ኔሪ የተባለው ቃልቻ ሃይማኖታዊ ኃይልን የተቀዳጀበት ጊዜ እንደነበር ዘሪሁን የሚከተለውን ጽፏል። (The Me'ent call nerey, a witch who used to sway much spiritual power in traditional religion)[44] ኘራይዎች ቃልቻዎች በፈጣሪ ኃይል ነገሮችን የሚያከናዉኑ እና ፈጣሪም የመረጣቸው እንደሆኑ ይታመናል። ቃልቻነት የሚገኘው ከዘር ነው። አንድ ቃልቻ ሲሞት እማኙ ጭምር መንፈሱ በማን ላይ ሲወርድ እንደሚችል ሲጠባበቅ ይቆያል። ከሟቹ ቃልቻ ልጆች ውስጥ የፈጣሪ መንፈስ አንዱን ስለሚመርጠውና መንፈሱ በተመረጠው ልጅ ላይ ስለሚወርድ፣ ሲወርድበትም ከፍተኛ ኃይል ስለሚቀበል ስለሚያጓራና ስለሚያንቀጠቅጠው ህዝቡ መንፈሱ በማን ላይ እንደወረደ ያውቃል። ሁሉም ሰው በእሱ ይመራል። የእሱን ቃል ያከብራል። "ከድሮም ከጥንትም ጀምሮ የአባቴ ነው። በውርስ ነው ያገኘሁት። አባቴም ከአባቱ ነው ያገኘው። ውርስ ነው እየመጣ፣ እየመጣ፣ እየመጣ እስከ እኔ ድረስ የመጣ። አባቴ ጥንትም ቢሆን ከአባቱ ነው፣ አባቱ ደግሞ ከአባቱ ነው እንደገና እኔም ብሆን ያገኘሁት ከአባቴ ነው።"[45]

ቃልቻዎች በህብረተሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ማስረጃ የሌላቸውን ጉዳዮች የሚፈቱ ናቸው። በስውር የተፈጸሙን ወንጀሎች ማለትም በድብቅ ሰው መግደል ወይም መደብደብ፣ ተበድሮ መካድ፣ ከብት መስረቅ፣ ንብረት መዝረፍና የመሳሰሉትን መፍትሄ በመስጠት ይታወቃሉ። በቃልቻነት ያሉት አወቀ እሳቸው ጋ ቀርበው ስላይዋቸው ግጭቶች ምንነት የሚከተለውን ብለውኛል። "እኔ ጋ የሚቀርቡ ጉዳዮች ማስረጃ የሌላቸው ናቸው። ማስረጃ ያላቸው ወደ ህግ ነው የሚሄዱት። ምክንያቱም በዳኝነት፣ በህግ አካላት ነው የሚዳኙት። እኔ ጋ የሚመጡት በባህል ስለሆነ ማስረጃ የሌለ ነው። በባህል ማለት ማስረጃ የሌለ፣ የለም በቃ ... በቃልቻ የሚፈታው ማስረጃ የሌለው ብቻ ነው።"[46] ከፍተኛ የሆነ ክብር ስለሚሰጣቸውም እርግማናቸው ይፈራል። በውሸት እጃቸውን በድፍረት የሚመታና የሚምል የለም። ቃልቻዎች ከስራቸው

---

[44] Zerihun 2008, 98

[45] አወቀ፣ ሚያዚያ 2003

[46] አወቀ፣ ሚያዚያ 2003

በርካታ ረዳቶች አሏቸው፡፡ አንድ ሰው ጉዳይ እንዲታይለት ወደ እነሱ ቀርቦ ካመለከተ ቃልቻዎቹ በረዳቶቻቸው አማካይነት የቃል መልዕክት በመላክ የተከሰሰው ሰው እንዲቀርብ ያደርጋሉ፡፡ የቀረበው ሰው የተጠራበት ጉዳይ ተገልጾለት ስርቆ ከሆነ እንዲመልስ፣ ክዶ ከሆነ እንዲያምን ይጠየቃል፡፡ ይሁን እንጅ በቃልቻው ፊት ማድረግ አለማድረጉን ከተናገረና የእምነት ክህደት ቃሉን ከሰጠ በኋላ ከሳሽና ተከሳሽ ካልተግባቡ ወደ እርግማን ወይም ወደ መሃላ ይሄዳሉ፡፡ ሁለቱም በየተራ በቃልቻው ረዳት የሚሰጣቸውን በትልቅ ሾርቃ /ቅል/ ውስጥ የሞላ ውሃ በእጆቻቸው ይዘው በመንቀንቅ እና በመድፋት የዋሸው ሰው /ከሳሽ ወይም ተከሳሽ/ ከነ ዘሩ እንዲደፋ ይምላሉ፡፡ አንዳንዴ ሁለቱም በየተራ መጥረጊያ ተሰጥቷቸው ግቢውን በመጥረግ የዋሸውን አካል /ከሳሽ ወይም ተከሳሽ/ ከነ ዘሩ እንዲጠረግ ይምላሉ፡፡ በመጨረሻም ወደየመጡበት በመመለስ የእርግማኑን ውጤት ይጠባበቃሉ፡፡ ቃልቻዎች አገሩ ሰላም እንዲሆን፣ ሰብሉ እንዲባረክ የሚያደርጉ እንደሆኑም ይታመናል፡፡ ረጅም ዓመት በቃልቻነት ያሉት አወቀ ፎርሽዋ ባህላዊ ተቋሙ አሁንም በስራ ላይ ያለ መሆኑን ገልጸውልኛል፡፡

በአጠቃላይ በመኢኒት ብሔረሰብ ውስጥ ሦስቱ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ህብረተሰቡን እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡

## 3.2 ዘመናዊ የፍትህ ተቋማት

ዘመናዊ የፍትህ ሥርዓት የሚከናወነው የአገሪቱን የተለያዩ ዘመናዊ ሕጎች መሰረት በማድረግ በቀበሌ የፍርድ ሸንጎዎች፣ በወረዳ፣ በዞን እንዲሁም በክልልና በፌደራል ፍርድ ቤቶች ውስጥ ነው፡፡ ይሄም ተግባሩ ተፈጻሚ እንዲሆን መደበኛ ፍርድ ቤቶች፣ የቀበሌ የፍርድ ሸንጎዎች፣ፖሊስ ጣቢያዎች፣ የመንግሥት የሰላምና የጸጥታ ኮሚቴዎች በማዋቀር ሥራዎችን ይሰራል፡፡ ከዚህ በታች እያንዳንዱን እናያለን፡፡

- መደበኛ ፍርድ ቤት

መደበኛ ፍርድ ቤቶች፣ ከቀበሌ የፍርድ ሸንጎዎች፣ ከፖሊስ ፣ ከመንግሥት የሰላምና የጸጥታ ኮሚቴዎች እሊያም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በጥምረት ይሰራሉ፡፡ በህግ በኩል በማስረጃ የተደገፉ ክርክሮችና ክሶች ውጤት ስለሚያመጡ የግድያ፣ የአካል ጉዳት፣ በሴቶች ላይ የሚደርስ የኃይል ጥቃት፣ ድብደባና ዘረፋ እንዲሁም ሌሎች ማስረጃ ያላቸውና ወዲያውኑ የተፈጸሙ ክሶች ይቀርባሉ፡፡ መደበኛ ፍርድ ቤት አቤቱታዎችን ተቀብሎ ከፖሊስና ከቃቤ ህግ

የሚደርሰውን መረጃ መሰረት አድርጎ በክሳሽ ወይም በአቃቤ ሕጎች ጉዳይ አቅራቢነት አስፈላጊም ሲሆን የምስክሮችን ቃልና ክርክሮችን አዳምጦ ውሳኔ የሚሰጥ የታወቀ አካል ነው።

በመኢኒት ብሔረሰብ ውስጥም ለሚፈጠሩ ግጭቶች የመኢኒት ጎልዲያ እና የመኢኒት ሻሻ የወረዳ ፍርድ ቤቶች በማስረጃ እስከተደገፉ ድረስ የተለያዩ ውሳኔዎችን ይሰጣሉ። በተለይ ከድንበር መጋፋት፣ እንዲሁም በስውር የሚፈጸሙና መረጃ የማይቀርብባቸው ጉዳዮች ሲገጥሙት ጉዳዮቹ በሀገር ሽማግሌዎች ወይም በሃይማኖት መሪዎች እንዲያልቁ ወደዚያው ይልካል።

መደበኛ ፍርድ ቤት የሕግ ተቃርኖና ተጠያቂነት የሌላቸውን ጉዳዮች በሽማግሌዎች እንዲያልቁ ያደርጋል። ሽማግሌዎችም የሚሰጡትን ውሳኔ የሕግ ተቃርኖ እስካልሆነ ድረስ ይቀበላል። የፍ/ብሔር ሕግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 ይሄንን ለማስተናገድ ውስን እድሎች አሉት።

በቀበሌ ቀርበውና ከቀበሌው አቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች ወደ ወረዳው ፍርድ ቤት ይሄዳሉ። ጉዳዮቹም ከወረዳው አቅም በላይ ከሆኑ ደረጃቸውን ጠብቀው ወደ ዞኑ ይተላለፋሉ። ለመኢኒት ብሔረሰብ አባላት በመደበኛው ፍርድ ቤት የተጀመሩ ክሶችን ከወረዳው በላይ ተጉዞ መልስ ለማግኘት ግን በአብዛኛው ከባድ ይሆናል። የመኢኒት ጎልዲያ ወረዳ ፖሊስ አባሻር ዋና ሳጅን አሸናፊ ስለይግባኝ የሚከተለውን ይናገራሉ "ከተጨባጭ ይግባኝ በወረዳ ያለው እስከ ዞን ነው። በዞን ደረጃ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አይቶ ወደ ክልል ነው የሚሄደው። ከዚህ ተነስቶ /ከወረዳው/ ዞን እንኳን ለሚሄድ ሰው አይችልም። እኛ እንኳን አይሱዙ መኪና ለምንን ነው ወደ ማረሚያ ቤት የምንልከው"[47] በአጠቃላይ መደበኛው ፍርድ ቤት በመኢኒት ብሔረሰብ ውስጥ የሚነሱና በህግ የሚያስጠይቁ ግጭቶችን በመፍታት እያገለገለ ነው።

- ፖሊስ

በመኢኒት ብሔረሰብ ውስጥ የብሔረሰቡ ሰላምና ደህንነት ከሚጠበቅባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ የፖሊስ ሰራዊት የሚሰራው ጸጥታን የማስከበርና የህብረተሰቡን ደህንነት የመጠበቅ ሥራ ነው። የፖሊስ ኃይል የመጀመሪያ ስራው የህብረተሰቡ ሰላም ተጠብቆ እንዲኖር ማድረግ ሲሆን ይሄንንም ለማድረግ በተደራጀ መልኩ ይንቀሳቀሳል። ፖሊስ መዋቅራዊ አደረጃጀቱ በአገሪቱ

[47] አሸናፊ ሚሶሬያ 2002።

ውስጥ ባለው መሰረታዊ የፖሊስ አደረጃጀት እንደሆነ የመኢኒት ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ዋና ሳጅን አሸናፊ ይናገራሉ።

"አደረጃቱ ከክልል ጀምሮ ወደ ዞኖች ከዞኖችም ወደ ወረዳ ይደርሳል። እንደገናም ከወረዳው ወደ ታች ወርዶ በየንዑስ ጣቢያው አደረጃጀት አለን" [48] በመኢኒት ጎልዲያ ወረዳ የፖሊስ አደረጃጀት ሦስትና አራት ቀበሌዎች በአንድ ንዑስ ጣቢያ ስር ይሆናሉ። አብዛኛው የቤኤረሰቡ ወረዳዎች ቆላማ ከመሆናቸው የተነሳ አማካሉ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት እንዳስቻላቸው የጨበራ አገልግሎት ንዑስ ኃላፊ ምክትል ሳጅን መኮንን ኮብታ ገልጸውልኛል። ምክትል ሳጅኑ ፖሊስ ጸጥታን በማስከበርና ሰላምን በመጠበቅ ዙሪያ ህብረተሰቡን የሚጠቅም ማገናኛውንም ሥራ እንደሚያከናውን እንዲህ ሲሉ ገልጸዋል። "የኛ ቁልፍ ተግባር ወይም ስራ የአካባቢው ሰላም እንዳይደፈርስ መጠበቅ ነው። ችግር ተፈጥሮ ሲገኝ ደግሞ አጥፊውን ወደ ህግ እንዲቀርብ እንሰራለን"[49] በብሄረሰቡ ውስጥ ሰላም ከሚደፈርስባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የሰው ግድያ ነው። የሰው ግድያ ሲፈጠር በብሔረሰቡ የቆየ ልማድ ደም መመለስና መበቀል እንዲሁም በዚሁ ወቅት ሌሎች የዘረፋና የግድያ ተግባሮች ስለሚኖሩ ፖሊስ እነዚህ ተግባራት እንዳይፈጸሙ የመከላከል እርምጃ ይወስዳል። ቀደም ባለው ጊዜያት ለበቀል የተነሳው የሟች ወገን ወይም ጎሳ ያገኘውን ቢገድል፣ ያገኘውን ከብት ቢዘርፍና አርዶ ቢበላ አያጠየቅም ነበር። አሁን አሁን ከኢህአዴግ ወዲህ ይሄንን ጥፋት የሚያደርሰውም እንዲጠየቅ ለማድረግ አንዳንድ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውንና ፖሊስም ይሄንን ሥራ ለማገዝ ከጉሳና ከሃይማኖት መሪዎች ጋር እየሰራ ነው። የወረዳው ፖሊስ አዛዥ አሸናፊ በዚህ ዙሪያ እየሰሩ ያሉትን እንዲህ ይገልጹታል። "ቀደም ባሉት ጊዜያት በመበቃቀል ብዙ የህይወትና የንብረት ጥፋቶች ይደርሱ ነበር። አሁን ግን ከሀገር ሽማግሌዎችና ከሃይማኖት ሰዎች ጋር ውይይት እያደረግን የገደለ በወንጀል እንዲጠየቅና ተጨማሪ ጥፋት እንዳይጠፋ እያደረግን ነው"[50]

ፖሊስ በተጨባጭ ወንጀል ሲፈጸም ብቻ ሳይሆን እንደሚፈጸምም ጥርጣሬ ሲኖረው ህብረተሰቡን የመጠበቅ ስራ እንደሚሰራ ግልጽ ነው። በአጋጣሚ በሚፈጠሩ ጸቦች በሚደረግ ድብድብና ቀላል የአካል መጉዳት፣ መጠጥ ቤት በሚፈጠሩ ቀላል ግጭቶችና አፍ እላፊዎች፣

---

[48] አሸናፊ ሚያዚያ 2009
[49] መኮንን ሚያዚያ 2009
[50] አሸናፊ ሚያዚያ 2009

ፖሊስ ወዲያው መፍትሄ ሰጥቶ አስማምቶ የሚሸኛቸው ጉዳዮች እንደሆኑ ምክትል ሳጅን መኮንን ኮቤታ ይገልጻሉ። በሌላ ወገን ደግሞ ፈጽሞ ማስረጃ የማይቀርብባቸው ጉዳዮችም እንደሚመጡላቸውና እነዚህንም ጉዳዮች እንደየአግባባቸው ባለጉዳዮቹ አንድም በሽማግሌዎች አልያም በቃልቻዎች እንዲጨርሷው እንደሚሸኟቸው ይናገራሉ። "ቀላል የምንላቸውን ግጭቶች ወዲያው ፈተንና አስማምተን እንልካቸዋለን በህግ የሚያስጠይቁትን ደግሞ ወደ ህግ እንወስዳለን። አንዳንዴ ደግሞ በህግ በኩል ምንም ውጤት የማያመጡ ማስረጃ አልባ ጉዳዮች ሲመጡ በሽማግሌ ወይም በባህል ሃይማት እንዲጨርሱት እንመክራቸዋለን "[51]

ይሁን እንጂ አንዳንዴ እንደ ወንጀሉቹ አይነትና ብዛት የፖሊስም ሥራ መጠኑ ሰፊ ይሆናል። ከከባድ ግጭቶች ማለትም ከቤተሰብ ጠቦች አንስቶ /በተለይ ከሱርማ ጋር/ የጎሳ ግጭቶች፣ በቤተ ዘመድና በቤተሰብ መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ሁሉ ፖሊስ የራሱን ድርሻ ይወጣል። ይሄን መጠኑ ሰፊ የሰላምና የጸጥታ ሥራ ፖሊስ ባለው አደረጃጀት ብቻ የሚወጣው ሳይሆን ሌሎች አደረጃጀቶችን ጨምሮ በመቀጋገዝና በየቀበሌው ከተዋቀሩ የመንግሥት የሰላምና የጸጥታ ኮሚቴዎች ጋር በመተባበር እንደሚሰራና ወንጀለኛም ወደ ኋላ እንዳይቀር እንደሚያደርጉ አሸናፊ የገለጹ ሲሆን ይሄንኑ ሃሳብ በማጠናከርም የትብብር ሥራውን በተመለከተ የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ ፀጥታ አስተዳደር ኃላፊ አቶ ከበደ ኪርቴጆ የሚከተለውን ገልጸዋል። "በቤሔረሰቡ የሚነሱ ግጭቶችን ለማስወገድ ከተነሱም መፍትሔ ለመስጠት የመንግሥት የሰላምና የጸጥታ ኮሚቴዎች እስከ ቀበሌ ድረስ ተደራጅተው እየሰሩ ነው።"[52] በአጠቃላይ ፖሊስ የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት በመጠበቅ ትልቅ ሥራ እየሰራ ያለ ተቋም ነው።

- የቀበሌ የፍርድ ሸንጎ

የቀበሌ ፍርድ ሸንጎ አባላት ሌላው የቤሔረሰቡ ግጭት ፈቺ አካላት ናቸው። በእያንዳንዱ ቀበሌ ውስጥ ቁጥራቸው ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርሱ የቀበሌ የፍርድ ሸንጎ አባላት አሉ። ዋና ስራቸው በህብረተሰቡ ውስጥ ግጭቶች ተፈጥረው ባለጉዳዮች ሲመጡ ለችግሮቹ መፍትሄ መስጠት ነው። የቀበሌ የፍርድ ሸንጎ አባላት ተጠሪነታቸው ለቀበሌ አስተዳደር መሆኑንና አምስቱ የቀበሌ የፍርድ ሸንጎ አባላት የየራሳቸው የሥራ ድርሻም እንዳላቸውም የመረጃ ምንጩ በድሉ ይገልጻሉ።

---

[51] መኮንን ፣ ሚያዚያ 2009

[52] ከበደ ፣ ሚያዚያ 2009

" የቀበሌ የፍርድ ሸንጎ አባላት ተጠሪነታቸው ለቀበሌው አስተዳደር ሲሆን ሊቀመንበር፣ ጸሐፊ፣ ገንዘብ ያዥ እና አባላት ከውስጣቸው ይኖራቸዋል፡፡"[53] የቀበሌ ፍርድ ሸንጎ አባላት በአካባቢው የሚፈጠሩ ችግሮችን ባላቸው አቅም እየፈቱ በህብረተሰቡ መካከል ሰላም እንዲሰፍን ይጥራሉ። ይሁን እንጅ ጉዳዩ ከእነሱ አቅም በላይ ከሆነ ወደ ወረዳው አሳልፈው እንዲታይ ያደርጋሉ። አንድ ባለ ጉዳይ የደረሰበትን በደል፣ ያጋጠመውን ችግር፣ ይዞ ወደ ቀበሌው ያመጣል። እናም የተከሳሹን ማንነትና ጉዳዩን ተከሳሹ ለመፈጸሙ የሚመሰክሩለትን ጠቅሶ ይጽፋል። የቀበሌው ፍርድ ሸንጎም ተከሳሹ በሚኒሻ እንዲመጣ አድርጎ የተከሰሰበትን ጉዳይ ያስረዳል። ሰውዬው ጉዳዩን አልፈጸምኩም ብሎ ከካደ ሸንጎው የከሳሽ ተከሳሽ ምስክሮችን አዳምጦ ውሳኔውን ይሰጣል። የተሰጠው ውሳኔ ትክክል አይደለም ብሎ ይግባኝ የሚጠይቅ ሰው ጉዳዩን ወደ ወረዳው በመውሰድ ግባኝ ማለትና ጉዳዩ እንዲታይለት ያደርጋል። የቀበሌ ፍርድ ሸንጎው የውሳኔ ጣሪያ ውስን መሆንን አቶ በድሉ እንደሚከተለው ይገልጻታል። "የቀበሌ ፍርድ ሸንጎ አካላት እስከ አምስት መቶ ብር ድረስ ቅጣት መቅጣት ይችላሉ"[54]

በአጠቃላይ የቀበሌ ፍርድ ሸንጎ የሚፈጠሩ የድብደባ፣ የዘረፋ፣ እና ሌሎች በማስረጃ ና በምስክር ተደግፈው የሚቀርቡ ግጭቶችን ይፈታል።

- መንግሥት የሰላምና የጸጥታ ኮሚቴዎች

የሰላምና የጸጥታ ኮሚቴዎች በመእኒት ብሔረሰብ ውስጥ የህዝቡን ሰላምና ደህንነት በመጠበቅ ከፍተኛ ሥራና ድርሻ ያላቸው ሲሆኑ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ከተፈጠሩም በፍጥነት ርምጃ ተወስዶ መፍትሄ እንዲያገኙ የበኩላቸውን ድርሻ ይወጣሉ፡፡ የመንግሥት የሰላምና የጸጥታ ኮሚቴ አባላት ቁጥር እንደየቀበሌው ስፋትና ጥበት፣ እንደ ብሔረሰቡ አሰፋፈር፣ እንደተደራጁ ከሃይማኖት መሪዎችና ከባላባቶች ጋር ጭምር እየመከሩ እደሚሰሩ የመእኒት ጎልዲያ ወረዳ የሚኒሽያ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ተፈራ ኮርዲ ይገልጻሉ። "ከሃይማኖት መሪዎች፣ ከጎሳ መሪዎች ጋር በየአስራ አምስት ቀኑ በመገናኘት ስብሰባ ያደርጋሉ። የኮሚቴው አስተዳደር ሪፖርቱን ወደ ቀበሌ ያመጣል "[55]

---

[53] በዙሉ ፡ ሚያዚያ 2005
[54] በዙሉ ፡ ሚያዚያ 2005
[55] ተፈራ ፡ መስከረም 2004

የመኢኒት ቤሌረሰብ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር በመሆኑ በመካከሉ የሚፈጠሩ የግድያ፣ የዘረፋ፣ የሰው ሚስት መድፈር እና ሌሎች ጉዳዮችም ሲከሰቱ ግጭቱ እንዳይባበስና እንዳይዛመት ከፍተኛ ስራ ይሰራሉ። አንድ በቀበሌ ፍርድ ሸንጎ የተፈለገ ሰው ካለ እሱን ወደ ህግ ይዘው በማድረስም ወንጀለኛ ተደብቆ እንዳይቀር በማድረግም ይሰራሉ። የመንግሥት የሰላምና የጸጥታ ኮሚቴዎች በአንድ የሰው ግድያ የተነሳ በሁለት ጎሳዎች በካከል ሊነሳ የነበረውን የመበቃቀል ሂደት እንዴት እንዳስቆሙት ተፈራ እንደሚከተለው ተርከውልኛል።

> በ2003ዓ.ም. ቅርብ ጊዜ ውስት ነው። አንድ የጋምቢ ጎሳ እና አንድ የጃሩ ጎሳ አባላት የሆኑ ይጋጫሉ። ከዚያ የጃሩ ጎሳው የተጣላውን የጋምቢ ጎሳ ሰው በገጀራ ቆራርጦ ይገድለዋል። ይህ ጉዳይ በጋምቢ ጎሳ አባላት እንደተሰማ ከፍተኛ ረብሻ ይነሳል። ጋምቢዎችም ሰው ሞቶባቸዋልና ፈጥነው ወደ ጃሩ ጎሳ በማምራት የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ሲሰነዳዱ የመንግሥት የሰላምና የጸጥታ ኮሚቴዎች ጉዳዩን ፈጥነው በማወቅ እልቂቱ እንዳይፈጸም ከአካባቢው ሚኒሻና የፖሊስ ኃይላት ጋር አድርገዋል። ከዚያም ገዳዩ ተይዞ ወደ ፍርድ እንዲቀርብ እና ጎሳዎቹ ጠባቸውን በሽማግሌዎች እርቅ እንዲጨርሱት ሆኗል። የመንግሥት የሰላምና የጸጥታ ኮሚቴዎች፣ ከአካባቢው የአገር ሽማግሌዎች ጋር ፈጥነው ባይቀናጁ ኖሮ የአንድ ጎሳ ሰው በሌላ ጎሳ ሰው ሲገደል በጎሳዎቹ መካከል የሚፈጠረው የዘርፈያና የግድያ ሁኔታ መጥፎ ይሆን ነበር።[56]

በኢቢቃላይ በዘመናዊ የፍትህ ተቋም ውስጥ መደበኛ ፍርድ ቤት፣ ፖሊስ፣ የቀበሌ የፍርድ ሸንጎ እና የመንግሥት የሰላምና የጸጥታ ኮሚቴዎች ግጭቶች እንዳይፈጠሩ ከመስራት በተጨማሪ የተፈጠሩ ግጭቶች እንዲፈቱ የበኩላቸውን ጥረት ያደርጋሉ።

---

[56] ተፈራ ፣ መስከረም 2004

# 4. የግጭት አፈታት ሥርዓቶች

በብሔረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ግጭቶች እንደሚከሰቱ ሁሉ እነዚሁ ግጭቶች እንደመልክ መልካቸው ወይንም እንደ አይነት አይነታቸው በተለያዩ ተቋማት ይፈታሉ፡፡ በዚያው ልክና መጠንም ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማቱ የየራሳቸው የግጭት አፈታት ሂደትን ይከተላሉ፡፡ ከዚህ በታችም አራት የግጭት አፈታት ሂደቶችን በቅደም ተከተል እናያለን፡፡ እነሱም የሰው ገደያ ግጭት፣ የሰው ሚስት በመድፈር፣ ድንበር በመጋፋት የሚከሰት የግጭት አፈታት ሂደት፣ ግጦሽ የማይቀርብባቸው ጠቦች አፈታት ሂደት እንዲሁም በብሔረሰብ መካከል የሚፈጠሩ ግጭት አፈታት ሂደት ናቸው፡፡

## 4.1 "አሻ" /የግድያ እርቅ/ ሥነ- ሥርዓት ሂደት

በመኤኒት ብሔረሰብ አንድ ሰው ሰው ሲገድል የሚካሄደው የእርቅ ሥርዓት አሻ ይባላል፡፡ አሻ ማለት ቀጥታ ትርጉሙ ካሳ ወይም ጉማ ነው፡፡ የአሻ አከፋፈል ወጥና አንዴ የተደነገገ መሆኑን ኮምሩትብ አሻ ሲሚንቶ በሚከተለው መልክ ይገልጻሉ፡፡ "ሰውን ሰው ሲገድል አሻ ነው እርቁ፡፡ ሰውን ሰው ከገደለ በመሀል የሚደረገው እርቅ አሻ ነው የሚባለው፡፡ በአሻ አከፋፈል ላይ ልዩነት የለም፡፡ የሚከፈለው ስለ ህይወት ነው አሰቦም ሆን ሳያስብ ሰው የገደለ የሚከፍለው አንድ ነው፡፡"[57]

የአሻ አከፋፈል ሂደት አሁን አሁን በሁለት የሚከፈል ሆኗል ፡፡ ክፍፍሉ የመጣው በቆላው አካባቢ የሚኖረው ህብረተሰብ ነባሩን የአሻ አከፋፈል የሚከተል መሆኑና የደጋው ወይም ለከተማው ቅርብ የሆነው ደግሞ ከመንግሥት ጋር የተሳሰረ ሥራ የሚሰራ በመሆኑ ነው፡፡ "ከድሮው ጊዜ አንድ ሰው ሰው ከገደለ አካባቢውን ለቆ ባላባቶች ጋር ይቀመጣል፡፡"[58] በቆላው እና በደጋው /ለከተማ ቅርብ በሆነው/ የመኤኒቶች አካባቢ የተፈጠረውን ልዩነት፣ ሰው የገደለ ሰው በካሳ ብቻ እርቅ አውርዶ መኖር መቻሉ እና ከእርቁ በኋላ ደግሞ ስላጠፋው ጥፋትና ስለ ሰራው ወንጀል ተጠያቂ ይሁን የሚለው አዲስ ሀሳብ የወለደው እንደሆነ በአንድ ወቅት ሰው ገድለው ወደ ቆላው /ባላባቶች/ ጋ የሄዱት አቶ ጥጋቡ የሚከተለውን ይገልጻሉ፡፡ "እዚህ ጋ በሁለት ይከፈላል - በደጋውና በቆላው፡፡ የደጋው ግጭት ሲፈጠር ወደ መንግሥት ቤት ይሮጣል፡፡ የቆላው ግን ወደ ኮምሩት፣ ወደ ባላባት ቤት ይሮጣል፡፡ የቆላው በባህል

[57] ሌሚ ነፀ፡ ሚያዚያ 2003
[58] ሌላ፡ ሚያዚያ 2003

ስለሚተዳደርና ስለሚያምን ነው። በቆላው ገዳይ ባላባት ቤት ከገባ ማንም አይነካውም::" [59] ይሄንን አባባል ሌሎች ይጋሩታል። "ባላባቶች ወደ ቆላው ነው ያሉት:: አንድ ሰው ገድሎ ወደዚያ ቢሄድ 'ደሙን እዚህ ይዞ መጣ' ስለሚባል ከብት ቀጥቅጦ ትልቅ ገበጣ አጥቦ ነው የሚገባው። ባላባቶቹ ጋ ከገባ ደግሞ አሻን ከመክፈል ውጪ ማንም አይጠይቀውም::"[60] ከደርግ መንግሥት ውድቀት በኋላ ጥቂት አካባቢዎች /ከደጋው ክፍል/ ሰው የገደለ ሰው እጁን ለመንግሥት እየሰጠ ቀሪ ዘመዶቹ ደግሞ ባህላዊ የሆነውን እርቅ የአሻን ሥርዓት ይፈጽማሉ::



ከግራ ወደ ቀኝ ኮርሞ አሻ ቀየቾ ጃጃ፣ኮሞሩት አሻ ሴላ ቦሉኮሮይና ኮሞሩት አሻ ሲሚንቶ ሲማቻ

በሙአኒት ቤተሰብ ሰው በግልጽና በሚታይ ሁኔታ ሰው ከገደለ /በስውር ካልሆነ/ የመጀመሪያ ድርጊቱ የሚሆነው ለቤተሰቡ መንገር ነው። የግድያውን ድርጊት የሰሙት ቤተሰቦቹ በፍጥነት ፊላቸውን ከበቀል ለመከላከል መደበቅ ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ምንም ደቂቃ ሳያጠፉ ንብረታቸውን ጭምር የማሸሽ ሥራ ይሰራሉ። "አንድ ሰው ሰው ከገደለ ቤተሰቦቹ በሙሉ በመጀመሪያ የሚገቡት ሽሽት ነው። ምክንያቱም እዚያው ከቆዩ የሟች ወገኖች ሄደው ያለውን ነገር የቤት እቃም ይሁን እህልም ይሁን ስለሚያጠፉባቸው ይሸሻሉ::"[61] በተለይ ግድያው የተፈጠረው በሁለት የተለያዩ ጎሳዎች ከሆነ ጠቡ የግለሰብ ወይም የቤተ ዘመዳሞች መሆኑ

---

59 የጭ ሚያዚያ 2003
60 ያቂ ሚያዚያ 2003
61 ኣሉ ሚያዚያ 2003

ቀርቶ የጎሳዎች ጠብ ይሆናል። ይሄንን ጊዜ በድንገትም ይሁን አስቦ ሰው የገደለ ሰው በአጠቃላይ የሱ የሆኑ የጎሳው አባላት ራሳቸውንና ንብረታቸውን የማሸሸ፣ የማራቅና የመሰወር ሥራ ይሰራሉ። በሚች ወገኖች የሚደርሰው ጥፋትና የበቀል እርምጃ የማይቀር ፈጣን መሆኑን ስለሚያውቁ የማስጠንቀቂያ መልዕክቱ እጅግ በፍጥነትና በጥንቃቄ ይተላለፋል። ጥንቃቄው የሚች ወገኖች ያገኙትን የገዳይ ወገን ሁሉ በጦር ወግተው፣ በገጀራ ቀጥቅጠው ደም ስለሚበቀሉ ነው። በአንጻሩ የሚች ጎሳዎች በፍጥነት እየተጠራሩ ወገናቸው መውደቁንና መገደሉን እንዲሁም የገዳይ ጎሳን ማንነት በመናገር አስቸኳይ የሆነ የበቀል ጦር ሰብቀው ወደ ገዳይ ወገኖች ለመምጣት ይጠራራሉ። በእርሻ ቦታ፣ በገበያ ላይ ወይም በየትኛውም አካባቢ ያለ የጎሳው አባላት ለጥቃት እንዲሰባሰብ መልዕክት ይተላለፋል። "አንድ ሰው አንድን ሰው ሲገድል ኮምሩቶች ከመግቢያቸው በፊት የሰው ንብረት ይጨፈጨፋል። ሃያም ሰላሳም ከብት ዘርፎ አርዶ ቢበላ አይጠየቅም።"[89] ስለዚህ የገዳይ አባት ካለ እሱ፣ አባት ከሌለው ሌላ የቅርብ ሰው ፈጥኖ ወደ አስታራቂ ሽማግሌዎች ይሄዳል። ከዚያም ልጁ ሰው እንደገደለና ከዚህም ጥፋት እንዲወጣቸውና የሚች ወገኖች ከሚፈጽሙት የብቀላ እርምጃ እንዲያድኗቸው፣ ጠቡም ከተለየ ጎሳ ከሆነ እልቂቱ እንዳይበረታ ፈጥነውም መሀል እንዲገቡላቸው ይለምናሉ።



የሚች ወገኖች ለብቀላ ሲነሱ

[89] [illegible] 2009

ሽማግሌዎቹም ጫልኩት የተባለ ዘንጋቸውን ይዘው በፍጥነት በመሄድ የሟች ቤተሰቦች እየገሰገሱ ሲመጡ በመሃል በመሆን ከበቀል እንዲታቀቡ፣ ዝርፊያ እንዳይፈጽሙ፣ የገዳይ ወገኖችም መሳሪያቸውን እንዲመነኑና ይቅርታ እንዲደረግላቸው ለመጠየቅ እነሱን የላኩ መሆኑን በሚከተለው መልኩ እንደሚገልጹ ቀልፍ የመረጃ አቀባዮቼ አቶ ብርሃኑ፣ ኩሞሩት አሻ ሌላ እና ዋየች ነግረውኛል።

ኅንጃይ መንቲት ካንጃይ ኪኖጋቦይ ኩጨይዶይ / ብቀላ ውስጥ እንዳትገቡ። በአሻ እክሳለሁ በለሏልና ተመለሱ።/

የገዳይ ወገኖች ራሳቸውን እስኪደብቁና ሽማግሌ በመሀል እስኪገባ ድረስ ያለውን ክፍተት በመጠቀም የሟች ወገን ሴቶች ወንዶቻቸው ብቀላውን ፈጥነው እንዲፈጽሙ እየዘፈኑና የሟቹን መልካም ነገሮች እያነሱ ያደፋፍራሉ። ወንዶቹ መሣሪያ ካለ መሣሪያ ይይዛሉ፣ ገጀራ ይይዛሉ፣ ጦርና ጩቤ ይይዛሉ። ቤት ያፈርሳሉ ሴቶቹ ደግሞ ወንዶቹን ያሟሙቃሉ።

"እዶ ግጭ ክፎይ ታችካዳይ' /ወንድ ሰው ቢኖር የእከሌን ፈንታ ይገለው ነበር።/ 'እእፎግጭዳይ ባክ ከእሰከኖ' /ወንድ ከሆናችሁ አትልቀቁ ጨርሷቸው/ 'ሃሹ እንዳቦይ' /አሰይ ገደሉት/ እያሉ ያነሳሷቸዋል።

የሟች ወገኖች በእልህና በከፍተኛ ቁጣ እየገሰገሱ ባለበት ሰዓት ሁኔታው ፍጹም ከባድ ይሆናል። አሁን አሁን ለከተማ በቀረቡ ቀበሌዎች የፖሊስ ኃይል እንኳን ሁኔታውን ለማረጋጋት ያዳግተዋል። በተለይ በቆላው ክፍል ያለውን ዝርፊያ በጣም ከባድ ነው። አሻ ሲከፈል በተደጋጋሚ የተገኙት ምክትል ሳጅን መኩንን ኩብታ ሁኔታውን እንዲህ ይገልጹታል። 'እነዚህ እቅርብ አካባቢ ይቻላል። በረሃ አካባቢ ግን አይቻልም። እንደወሰደ ቀጥቅጦ ይበላል፣ አርዶ ይበላል። እንደገና አይያዝም። በቂ የጦር መሣሪያ አላቸው። ጫካ ውስጥ ነው የሚደበቁት። ከእቅም በላይ ነው።' ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ የሚያከብራቸው ሽማግሌዎች መሀል በመግባት ከፍተኛ የሆነ የማረጋጋት ስራ ይሰራሉ።

የሟች ወገኖች ቁጣ የቱንም ያህል ከባድ፣ የቱንም ያህል አስፈሪ ቢሆን የሟች ወገኖች ሀዘኑ ቢያንዘገንገናቸውም ኩሞሩት እኼው /ሽማግሌው/ በመሃል ከገባ እልህና ሲቃቸውን ውጠው

ብርሃኑ፣ ሚያዚያ 2003

መለሰ፣ ሚያዚያ 2003

መኩንን፣ ሚያዚያ 2003

ወደጊዳቸው ይመለሳሉ። አራት የግድያ ጠቦችን ያስታረቁት ዋየች ጃሻ ያጋጠማቸውን ሲተርኩ 'ጫልኩት' የተባለውን ዘንግ ይዘው በመውጣት ለዘረፋ የመጡ የሟች ወገኖችን እንደመለሱ ይናገራሉ። ያጋጠማቸውን እንዲህ አጫውተውኛል። 'ጫልኩት' የተባለውን ዘንግ ይዤ ለሁ። ቀጥታ ለዘረፋ ሊመጡ ሲሉ ወጣሁና ወዲያ ማዶ ቆሜ ለመንኳቸው። 'ዘኤላጋና አኒ ኪቲያንቦይ ኢውንኖና ሾዊንራዱንና ኢስታማንዲሬሳ ሀቱቱዋክ/ ተነግሮኛል፣ እኔ ቆሚያለሁ እንዳትመጡ መንገዳችሁን ይዛችሁ፣ ሬሳውን አንስታችሁ ወደ ቤታችሁ ሂዱ።'/ ስል እነሱም በመንገድ ላይ መጥተው ሬሳቸውን ወስደው ቤት አደረሱ።[66] የሟች ወገኖች ሽማግሌ እስኪገባ ድረስ የዘረፉት ከብትም ካለ ወስደው በፍጥነት አርደው ይበላሉ። እጃቸው የገባ ሰውም ካለ ሊገድሉት ይችላሉ። ሽማግሌ በመሀል ገብቶ ነገሩ ለስለስ ካለ በኋላ እርቁን ለማስቀጠል ከሁለቱም ወገን ያልሆኑ ተጨማሪ ሁለት ሽማግሌዎች ይመረጣሉ። ሽማግሌዎቹም የሟችና የገዳይ ወገኖችን ለማስማማት፣ የተቆጡት የሟች ወገኖች እንዲበርዱ የበደሉት ወገኖች ደግሞ ተረጋግተው ካሳ ከፍለው እርቁ እንዲወርድ የመጀመሪያውና የእሻ ሥርዓቱ መክፈቻ የሚሆነውን አንድ ከብት ቢደበሬን /የመቀበሪያ ከብት/ በስጦታነት ያቀርባሉ።

- ቢደበሬን (የመቅበሪያ ከብት)

የሚያስፈልጉት ሽማግሌዎች ከተመረጡ በኋላ የገዳይ ሽማግሌዎች ፈጥነው የሚልኩት ሲሆን ይኸው የመቀበሪያ ከብት ለሟች ወገኖች የሚሰጠው በማግስቱ ነው። የከብቱ መስጠት አንድም ኮምረዶች ቤበበሮች በመሀል መግባታቸውንና አንድም ሁለቱ ወገኖች / የሟችና የገዳይ/ የሰላም እርቅ ድርድር ውስጥ መግባታቸውን የሚያመለክት ፍቺ ያለው ነው።

---

[66] ቃለ፡ ሚያዚያ 2009



ኮሞሩት አሻ ዋየች ጃሻ የመቀበሪያ ከብት ሲሰጡ

በድሮ ጊዜ /ከደርግ በፊት/ እና አሁንም /በዘመነ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ/ በቆላው አካባቢ የገደለ ወደ ኮሞሩት /ባላባቶች/ ጋር እንደሚገባ ቀደም ብለን አይተናል። ለከተማ ቀረብ ያሉትና ደጋው አከባቢ ያሉት ደግሞ የግድያ ወንጀሉን እንደፈጸሙ እጃቸውን ለፖሊስ ይሰጣሉ። ይሁን እንጂ የመቅበሪያ ከብት ፈጥኖ ከመላክ የሚዘገይ የለም። የገዳይ ሽማግሌዎች ችግሩን ችግራቸው አድርገው ለሟች ሽማግሌዎች ፋታ እንዲሟቸውና እንዲያረጋጉላቸው በሚከተለው መልክ ይጠይቃሉ።

"ኩሱ ጋሜንቴኑቦይ ኩጨንጋይ አባላጋዲያም ኦጎጀ አገናጃናቦይ አምሲዚጎራ"

"እጀ ተሳስቶ ገድያለሁ። መቀበሪያ ከብት ይዤውና ወስደህ፣ ቀጥቅጠህ ቅበርበት። ሰዎች ተቢታትነውብኛል ሦስተኛው ቀን በተመረጠው ቦታ ላይ ተገናኝተን የጦር መመለሻና ልጃገረዱን እሰጥሃለሁ።"[illegible]

የመቀበሪያ ከብቱን የገዳይ ሽማግሌዎች ለሟች ሽማግሌዎች ከሰጡ በኋላ ከብቱ በአገሬው ልማድ መሰረት ሁለት ሰዎች ቀንድና ቀንዱን፣ ላምም ከሆነች ጆሮዎቿን ግጥም አድርገው

[illegible] ቁርጥ፣ ሚያዚያ 2008

ይዘው የሟች የቅርብ ወገን የሆነ ሰው በድንጋይ መሀል ግንባሩን/ሯን መትቶ እንዲሞት/እንድትሞት ያደረጋል። ከብቱ ከሞተ በኋላ በቢላዋ ወይም በስለት ቆዳው ተገፍፎ ሟች እንዲቀበርበት ይደረጋል። የመቅበሪያ ከብት ዋና ዓላማው የከብቱ ቆዳ የአስከሬኑ መገነዣ እንዲሆን ስለሆነ የከብቱ የጾታ ጉዳይ ግምት ውስጥ አይገባም። አቶ መልኬ ስለ ከብቱ ቆዳ እና አቀባበሩ ሚከተለውን ይገልጻሉ። "ሰውየው የሚቀበረው በከብት ቆዳ ነው። ከብቱ በድንጋይ ይቀጠቀጣል፣ ይታረዳል፣ ቆዳው ይገፈፋል። ቆዳው እስከ ጭራው ነው ተተርትሮ የሚወጣው። ከዚያ አረሳው በቆዳው ተጠቅልሉ ሳጥን ውስጥ ይገባና ይቀበራል።[68]

- ቢዶጀኑን (የጦር መመለሻ ከብት)

በቤኤረሰቡ ቋንቋ ቢዶጀኑን የሚባለው ሁለተኛው ከብት የጦር መመለሻ ከብት ይባላል። የሟች ወገኖች ደም ለመመለስ የመዘዙት ጦር ወደ ቦታው እንዲመለስ እና እርቅ እንዲወርድ የሚጠየቅበት ከብት ነው። የሟች ወገኖችም ይሄንን ከብት ሲቀበሉ ለበቀል ከመዝመት መቆጣየውን የሚያመላክት ነው። ሟች በተቀበረ በሦስተኛው ቀን የሚመጣው የጦር መመለሻ የሚባለው ከብት የግድ ወንድ ከብት መሆን ይኖርበታል። ይህንን ከብት "ቴአ" የሚባለው የገዳዩ ታላቅ ወንድም ያዘጋጃል። ገዳይ ታላቅ ወንድም ከሌለው የሱ ተከታይ ያዘጋጃል። እሱም ከሌለ በሌላ የቀረበ ቤተሰቡ የጦር መመለሻ ወይፈን የግድ ይሄዳል።

ኮሞሩት አሼው ሌላ በዚህ ጉዳይ የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተውኛል። "በዘሩ ውስጥ የመጀመሪያው ልጅ 'ቴአ' ከሌለ አባትየው ወይም ሌላ ታላቅ ወንድም ካለ የጦር መመለሻ ብሉ ወንድ ከብት ለነዚያ ይሰጣል። ምክንያቱም ጦር ይዘው ነው የሚዘምቱት ወደዚህ።"[69] የአቶ ሌላን አባባል የሚደግፍ መረጃ የሰጡኝና የገዳይ ወገኖች ለሟች ወገኖች የሚልኩት የጦር መመለሻ ከብት የተማጸኖና የይቅርታ ጥየቃ ምልክት እንደሆነ የሚያስረዱት ደግሞ አቶ ካሳ ናቸው። እንደ ካሳ ገለጻ የገዳይ ወገኖች ለሸማግሌዎቻቸው ከብቱን ሰጥተው "ሀታ እንዲያና እይዱ ኢቫንዳዶር አዮቢዩ እንዲያጋ እንዲጌቺቫኤራ /ይሄንን ወስዳችሁ ስጡ ጦራቸውን ይሰሩ፣ ጦራቸውን ያስቀምጡ፣ ያሳርፉ ይሄ የጦር ማሰሪያ ነው"[70] ይላሉ። ከዚሁ ጋር አብሮ የሚላክ የትንባሆ አይነት አለ። ይህ ትንባሆ በብሄረሰቡ "ዳምጉ" ይባላል። ትምባሆው የሚጨስ

[68] መልኬ፣ ሚያዚያ 2009
[69] ሌላ፣ ሚያዚያ 2009
[70] ካሳ፣ ሚያዚያ 2009

ሳይሆን የሚጎረስ ነው። ትንባሆው የሚሰጠው ከቅጠል ተጨቅጭቆ እንደቂጣ ተጠፍጥፎ ተዘጋጅቶ ነው። እሱም በመቀጠል ይሄዳል። የገዳይ ኮሞሩቶች ለሟች ኮሞሩቶች ይሰጣሉ። ከዚያ ከሦስቱ ውስጥ በእድሜ የሚበልጠው የሟች ኮሞሩት ይጎርስና ለተወሰኑት ሰዎች ይሰጣል ። ትምባሆ ከመጣና ጉርሻው ከተካሄደ በኋላ እንደተረጋጉ ይቆጠራል። ትምባሆ ሰላም የሚያወርዱበት መንገድ አንዱና ማስላሰያቸው ጭምር ነው። በአገር ሽማግሌነት ብዙ አሻዎችን ያስከፈሉት አቶ ሲሚንቶ ሲማቻ የሚከተለውን ነግረውኛል። "ትምባሆ ማለት ሀሳብን አመንጭተን ለእርቁ ሰላም የምናወርድበት ነው። በብሄረሰባችን ትንባሆ ቅጠሉን እየጎረስን ነው የምንሄደው። ከዚያ የሟች ኮሞሩቶች ለገዳይ ኮሞሩቶች ቀጣዩን የጦር መመለሻ ከብት አቅርቡ ሲሉን እናቀርባለን። ከብቱን እናቀርባለን። ያኔ 'ጦር ተመለሰ' ማለት ነው።"[71]

የሟች ኮሞሩቶች፡- ሚታኢዳውዳ ኡሙጃይዶ ጌልያቬው / በቀጠሯችም መጥተናል የጦር መመለሻውን ከብት አቅርቡ።

የገዳይ ኮሞሩቶች፡- ወጂያ ቢዶ ሲያቃቢር ቱአካ / የጦር መመለሻው ከብት ይሄው የሟች

የሟች ኮሞሩቶች፡- ያኢትቢሬ ጉቱ አክ / እናንተም ጦራችሁን መልሱ

በአሻ የእርቅ ሥነ-ሥርዓት የመቀበሪያ እና የጦር መመለሻ ከብቶቹ ከተሰጡ በኋላ የሽማግሌዎቹ ድርድር አሁንም ይቀጥላል። የሟች ወገኖች ከዚህ ቀጥለው የሞተባቸውን ሰው ወደ መቃብር ይሄዳሉ። ይሄ ከመሆኑ በፊት ግን ሙሉ የአሻው ክፍያ የትና እንዴት መከፈል እንዳለበት በሽማግሌዎቻቸው አማካይነት ቀኑ ቀጠሮ ይይዛሉ። ይሄም ቀጠሮ የሚደረገው ከሦስት ቀናት በኋላ ነው። የቀጠሮውን ቀንም ለመወሰን የገዳይና የሟች ኮሞሩቶች ይነጋገራሉ።

የገዳይ ኮሞሩቶች፡- አምቼ አሻ ዋጨና ቲኪሚኒን / አሻ የሚከፈልበት ቀን መቼ እንዲሆን ትሻላችሁ?

የሟች ኮሞሩቶች፡- አሙጌአልኪጂያ አልካዎሬጂያ ዋጭዱ / አሻውን በሚቀጥለው ሦስት ቀን ውስጥ ክፈሉ።

---

[71] ሲሚንቶ ሲማቻ 2003

የጋዳይ ኮሞሩቶች፣ ኪዳኢንምዳቤዩ / ተስማምተናል።

የሁለቱም ወገን ኮሞሩቶች ከተስሟሙ ከሦስት ቀናት በኋላ የአሻውን ሙሉ ክፍያ ቀሪዎቹን አምስት ከብቶችና ልጃገረድ ያዘጋጃሉ።

- ለአሻ የምትከፈል ልጃገረድ ማፈላለግ

በአሻ ሥርዓት የሚከፈለው የታወቀና የተወሰነ ክፍያ ነው። ሰባት ከብትና አንድ ልጃገረድ ማዘጋጀት የገዳይ ወገኖች የማይቀር ካሳቸው ነው። በድሮውና አሁንም በአብዛኛው የቆላ አካባቢ ልጃገረድና ሰባት ከብት ነው በካሳነት የሚሰጠው። ኢህአዴግ አገሪቱን መምራት ከጀመረበት ከ1983ዓ.ም ወዲህ ግን ሴትን ልጅ በአሻ ክፍያ መስጠት እንዲቀር ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው። ይሁን እንጂ ይሄ ጉዳይ በአብዛኛው ተፋጻሚነት እያገኘ አይደለም። አሻው ሰባት ከብት እና በልጃገረዲቱ ፋንታ ተጨማሪ ሌላ ሰባት ከብት በድምሩ በአስራ አራት ከብት ይሁን የሚለውን አስተሳሰብ ለከተሞች ቅርብ የሆነው አካባቢ ተቀብሉት ያለ ቢሆንም በተግባር ግን እንደማያውለው የተለያዩ የመረጃ አቀባዮቼ ነግረውኛል። በመጀመሪያ ደረጃ ሴት ልጅ ስለምትሰጥበት ዋና ምክንያት በቡድን ውይይት ጊዜና የተለያዩ የመረጃ አቀባዮቼ የነገሩኝን ሁኔታ በዝርዝር እንመልከት። "ልጃገረድ የሚሰጥበት ምክንያት ያቺ ሴት ልጅ ከሄደች በኋላ ሟቹ ወንድ ከሆነ ድንገት ሌላ ወንድ ልጅ እንደገና ትወልድና መተኪያ ሆኖ ያን ሟቹን ማረሳሻ ይሆናል በሚል ነው። ሟቿ ሴትም ብትሆን የሚከፈለው በሴትና በከብቶች ነው እንደገና መተኪያ ሌላ ሴት ልጅ ወልዳ ማረሳሻ ታደርጋለች ከሚል ግንዛቤ በመነሳት ነው ።"[72] የአሻ ክፍያ በከብት ብቻ ቢሆን የጠፋውን ነፍስ ሊተካ እንደማይችል ያብራሩት ደግሞ ኮሞሩት አሻ ሆነው አያገለገሉ ያሉት ሌላ በሉኮሮይ ናቸው። "ከብት ቢመጣ ብቻውን የወደቀውን ነፍስ አይተካም። ልጃገረዲቱ ግን የደረሰች ከሆነ ወዲያው፣ ልጅም ከሆነች አድጋ የሞተውን ሰው ወልዳ ትተካለች። ታቀሳቅሳለች። የጠፋውን ትመልሳለች። ለዚያ ነው የምትሰጠው።"[73] ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክሩትና ሴትን ልጅ በአሻ መስጠት ከትንሳኤ ጋር እንደሚያያዝ ሀሳብ የሰነዘሩት ሌላው ታዋቂ የአገር ሽማግሌና ኮሞሩት አሻ ዋየች ጃሻ ናቸው። "ሴት ልጅ የምትሰጥበት ዋንኛ ምክንያት አንደኛ የሞተው ህይወት ስለሆነ ህይወቱን እንስተናል። ሁለተኛ ሴት የተመፈጠችው

---

[72] ኣሌሳቱ ሚያዚያ 2003
[73] ሌሉ ሚያዚያ 2003

የሚቱ ወንድም ያገባና እንደገና ወንድ ልጅ ትወልዳለች ከሚል እባባል ነው።"[74] የሁለቱን ተዋቂ የአገር ሽማግሌዎች አባባል በመደገፍና ከዚያ ውጭ የተለየ ትርጉም እንደሌለውና ሴት ልጅ የምትከፈለው ስትወልድ የሞተውን ስለምትተካው ያሉት ደግሞ ሲሚንቶ ናቸው።[75]



በእሻ የተከፈለችው ወ/ሮ ዶጊያ ኮንኩላይ

ይሁን እንጂ ሴትን ልጅ በእሻ ላለመስጠት ጥረቱ አሁንም እንደቀጠለ ነው። በመሆኑም በጥቂት ቦታዎች ላይ ለውጡ ተግባራዊ እየሆነ ነው። "እንዲቀር ብዙ ጥረት እያደረግን ነው። በተለይ ቶለኛ በሆነው አካባቢ ላይ አትቶናል። ደገኛው ላይ ግን አስቀርተነዋል። በሰባት ከብት ተክተናል።"[76] ከስድስቱ አገልግሎቶች ውስጥ /አገልግሎቶቹ ከሦስት እስከ ስድስት ድረስ ቀበሌዎችን ይይዛሉ/ ሦስቱ ከሆግ ጋር የተያያዘ አካሄድ የሚሄዱ ናቸው። ጋቺት፣ አደይ አበባ

74 [illegible] ሚያዚያ 2003
75 [illegible] ሚያዚያ 2003
76 [illegible] ሚያዚያ 2003

አገልግሎት ልጅን በማስቀረት እየሰሩ ነው፡፡ ቀሪዎቹ ግን ገና ናቸው፡፡ ልጃገረድ እየከፈሉ ነው፡፡ በጨበራ ዙሪያ አርብቶ አደሩ ገና ነው፡፡"[77]

ድፍን አስራ አራት ዓመት በሽፍትነት የኖረውና በኋላም በመንግሥት ምህረት ሰላማዊ ኑሮ እየኖረ ያለው አቶ ጥጋቡ መንገሻ ጫካ የገባው ሰው በመግደል ነው፡፡ በአሻ የሴት ልጅ ክፍያ ጉዳይ ሲገልጽ "ህዝቡ ሦስት አራተኛው መኢኒት የሚያምነውና የሚጠቀመው ባህሉን ነው፡፡ የቆላው በዱሮው ነው የሚሰራው፡፡ ሴት ልጅ ይሰጣል የደጋው በከብት ሴትን ለውጧል፡፡"[78]

የአሻ ሥርዓትን በአስራ አራት ከብት ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ብዙም ፍሬ እንዳላፈራ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት ይቻላል፡፡ የመንግሥት አካላት በተለያየ ጊዜ ስብሰባዎችን በማድረግና ውይይቶችን በማካሄድ ለማስቀረት አሁንም እየጣሩ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ግን በከብትና በሰው መካከል ያለውን ልዩነት በቀላሉ ማጥበብና መቀበል እንዳልቻለ ወይም በአጭሩ በጉዳዩ እንዳላመነበት በሚያስረዳ መልኩ ምክትል ሳጅን መኮንን ኮብታ የሚከተለውን ሀሳብ ሰጥተውኛል፡፡ "ብዙ ጊዜ ህዝቡ ለጊዜው ያፀድቃል፡፡ በአገልግሎት፣ በቀበሌም በወረዳ ደረጃም ብዙ ስብሰባ ይደረጋል፡፡ እስከ ጀንካ ድረስ ተሄዶ ውይይት ተደርጓል፡፡ ያፀድቃሉ ግን እስከ አሁን ያጸደቁት ነገር ተግባራዊ አልሆነም፡፡ ስንገኝ ሁሌ አሻው እየተከፈለ ነው፡፡ ህዝቡ ራሱ ወስኖ አራሱ ያፈርሳል፡፡ ከብት ይተካል፡፡ ቢመጣም ማንም ይወስደዋል፡፡ ልጅቷ ግን ከመጣች ሰውየውን /የሞተውን/ ትተካዋለች ነው ጉዳዩ፡፡ "[79]

አሻው በሴት እንዳይሆን የሚከራከሩ ወገኖች ጉዳዩ ከሰብአዊነት ጭምርም የሚታይ በመሆኑ እንደሆነ በአጽንኦት ይገልጻሉ፡፡ በአሻነት የምትሰጠውም ልጅ በሟች ወገኖች የሚደርስባት አሰቃቂ ግፍና መከራ እንዳለ ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጂ በልጅቷ ላይ የሚደርሰው መከራ በድሮ ጊዜ የነበረ እንጂ በአሁኑ ጊዜ የሌለ እንደሆነ አንዳንዶች ይገልጻሉ፡፡ ወ/ሮ አልጋነሽ ኩትያ በዚህ ጉዳይ የሚከተለውን ይናገራሉ፡፡

> በጥንት ሰዎች የነበረው ሁኔታ የተከፈለችው ልጅ ህፃን ለአቅመ ሄዋን ያልበቃች ከሆነች የሟች ቤተሰቦች ያንገላቷታል፣ ይመቷታል፣ በእለቱ እንደተሰጠችም ይቀጡትሟታል፣ ሁሉ እየመቷት በዚያው የሟቹን ስም እያነሳሱ ይደበድቧታል፣ እቤትም ከሄደች በኋላ ለአቅመ ሄዋን ሳትበቃ ወንዶች እሷን ለመድፈር ይላሉ፡፡

---

77 ፀዳ፣ ሚያዚያ 2009
78 ፕ.ገፁ ሚያዚያ 2009
79 መኮንን አለሙ ሚያዚያ 2009

> እሁን ግን ደህና ነው። ህግ ስላለ አይደፍሩም፣ የተከፈለችውን ልጅ ማጎሳቆልና ግፌታ የለም፡ በድሮ ሰዎች ነው።[80]

የወ/ሮ አልጋነሽን አሳብ ከሚቃወሙት ውስጥ የመኢኒት ጎልዲያ ወረዳ ጸጥታ አስተዳደር ኃላፊ ተከታዩን ሀሳብ ይሰነዝራሉ "ሀሳቡ ወልዳ ትተካለች ነው። ግን በተጨባጭ እያየን ያለው ችግር እንዳንዶቹ ልጆቷን ወስደው የእንቺ አባት ወይም ወንድም ነው ልጃችንን፣ ሰዎችን የገደለው እያሉ ልጆቷን በስነ ሥርዓት አይይዙም፣ ይጨቁናሉ፣ ይበዘብዛሉ እንደፈለጉ ያደርጋሉ።"[81] ከዚህ ውጭ ወንድሟ ሰው በመግደሉ በእሻ የተከፈለችው ወ/ሮ ዱጊያ ኩንኩላይ የደረሰባት ጥቃት ቃላት የማይገልጸው እንደሆንና ህይወቷ ተሰናክሉ እንደቀረች ትገልጻለች።

ለእሻ የምትከፈለው ልጃገረድ የምትመጣው በመጀመሪያ ደረጃ ገዳይ ልጅ ካለው የገዳይ ልጅ ትሆናለች። ገዳይ ልጅ ከሌለው ከዘመዶቹ ትፈለጋለች "የገዳዩ ልጅ ካለች የገዳዩ ልጅ፣ የገዳዩ እህት ካለች የገዳዩ እህት፣ የገዳዩ የወንድም ልጅ ካለች የገዳዩ ወንድም ልጅ ናት። የገዳይ ቤተሰብ ነው ልጅ የሚያወጣው። ሌላው ዘመድ ከብት ነው የሚያወጣው።"[82] የሁለቱ ታናሽ ወንድማቸውን የገደሉት ቀየች ጃጃ ለእሻነት የከፈሉት ልጃቸውን ነው። "ከዚያ ስመጣ ወዲያው አምስት ከብትና የራሴን ልጅ አውጣሁና ዘመዶቼ ከወንዝ ወዲያ ማዶ እኔ ብቻዬን ከወንዝ ወዲህ ሆኜ እሻውን ከፈልኩ።" ወንድሟ ሚስቱን የደፈረበትን ሰው ገድሉ ለእሻ የተከፈለችው ደግሞ ዱጊያ ኩንኩላይ ናት "ከዚያ በኋላ ወንድሜ እጁን ሰጠ እናቴ ደግሞ በዚያ ሰዓት ያለችኝ እንቺን በእሻነት ከከፈልን እኛ ወደ ሜካ እንገባም ብላ ሽማግሌ መሀል ገብቶ ለእሻ ተሰጠሁ።"[83] በመጨረሻም ለእሻ የምታስፈልገው ልጃገረድ ተፈልጋ ከተገኘች በኋላ የቀጠሮው ቀን ይጠበቃል።

- በእሻ የሚከፈሉት ከብቶች ማሰባሰብ

የመጣውን ጥቃት በጋራ መከላከል የጉሳው ግዴታ ስለሆነ ቤተ-ዘመዱ ተሰባስቦ ከብት እንዲያዋጣ አባ ይሰጠዋል። ለእሻ በካሳነት የሚሰጡትን ከብቶች በጋራ ያሰባስባሉ።

---

[80] አሊ ሳዒድ ሚያዚያ 2003
[81] ገበየ ቶኒያ ሚያዚያ 2003
[82] ሴት ሲምንስ ቆርቁኑ ሚያዚያ 2003
[83] ቶኒያ ሚያዚያ 2003

በአጠቃላይ ለእሻ የሚከፈሉት ከብቶች በቁመናቸው ሻል ያሉና ሲያይዋቸው ምነው የማያሰኙ መሆን አለባቸው። ደቃቃ ከብቶች ከሆኑ አሁንም የሟች ወገኖች ተንቀናል የሚል አመለካከት ሊፈጥሩ ይችላሉ። ስለዚህ የገዳይ ዘመድ የሆነ ሁሉ ችግሩን ተጋግዞ ለማለፍ ያለውን ማዋጣቱ የግድ ይሆናል። ማጥቃትም መጠቃትም የሚመጣው በጋራ ነውና።

- ለእሻ የሚከፈል ገንዘብ ማሰባሰብ

ለእሻ የሚያስፈልገው ተጨማሪ ገንዘብ ሰዎቹ ከርቀትም ከቅርብም ለቅሶ ለመድረስ ለሚመጡ ዘመዶቻቸው የሚያወጡት የምግብና የመጠጥን ወጪ የሚሸፍን ነው። ታዬ የገንዘቡ መጠን ከሁለቱ ወገን ባሉ ሽማግሌዎች እንደሚወሰን ያብራራል። የሟች ቤተሰቦች እስከ ሰባት ሺ ብር ሊጠይቅ ይችላሉ። ግን ሽማግሌ በመሀል ይገባና ያደራድራል። እስከ አምስት ሺህ፣ እስከ ሁለት ሺ ሊሆን ይችላል። እንደ ጉዳው አቅም ነው።[64] የሁለቱ ወገን ሽማግሌዎች በሚከተለው መልኩ ይደራደራሉ።

የሟች ኮምሩት፡- ቁምኬ ጉማዋዋ ጋሜሪና አይዲቼ ኩሻሺዮቦ አሳባ / የምናወጣው ወጪ ብዙ ነው ሰባት ሺ ብር ይሰጠን

የገዳይ ኮምሩት፡- ቁሙኬ ሜታ ኢኒድእኑዋ ሜርታ ቤይና ሙካሲኒ / ሰባት ሺ ብዙ ነው አቅልሉልን

የሟች ኮምሩት፡- ቁርሺኬ ባክ ሜንደናንንዋ ጋሜሪና አሱክባክ / አምስት ሺ ይሁንየገዳይ

ኮምሩት፡- አንቲፍሸዋ ሀጨና / ሁለት ሺ ብር ይሁንልን

የሟች ኮምሩት፡- አዳልየም ሺኖራማ ከልኔዲያፉ / ተስማምተናል እንከፍላለን

በአጠቃላይ ለእሼው የሚያስፈልገው የከብትና የገንዘብ መዋጮ በጋራ ይሰበሰባል። ገዳይ የሚጠበቅበት ልዩ ካለው መስጠት ነው። እስከ አራት ቀን ሊቆይ ይችላል። እክሌ ይሄንን

---

[64] [illegible]

ከብት ያውጣ፣ እከሌ ገንዘብ ያውጣ እየተባባሉ የገዳይ ቤተሰቦች ይከፋፈላሉ። ገዳይ የሚያውጣው ልጅ ብቻ ነው።[illegible]

የሟች ወገኖች ለተለያዩ ወጪዎች ያወጡት ወጪ ሽማግሌዎች ተደራድረው በሚስማሙበት መጠን ይሸፈንና ከዚያ ወደ ዋናው አሻ አከፋፈል ይገባል። አሻውንም ለመክፈል የራሱን የቦታ መረጣ ያደርጋሉ።

- አሻ የሚከፈልበት ቦታ መረጣ

በመኢኒት ቤሉረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ የግድያ ግጭት የሚፈታበት የአሻ ሥርዓት የሚካሄደው በሁለት ቦታዎች ነው። አንደኛው በሸጥ /ሸለቆ/ አካባቢ ሲሆን ሁለተኛው በወንዝ ዳር ነው። ከወንዝ ወዲያ ማዶ እና ከወንዝ ወዲህ ማዶ ሆነው አሻው ይከፈላል። በሸጥም ዳር ቢሆን በሼጡ ቢታች በኩል ውሃ ስላለ ችግር የለም ብለው ይከፍሉብታል። በዚህ በተመረጠው አለትና ቦታ የሟችም የገዳይም ወገኖች የሆኑ ሁሉ ይሰበሰባሉ። እንዲህ አይነቱም ሰዓት እጅግ አደገኛና ፈታኝ ነው። የአካባቢው የፖሊስና የጸጥታ ሰዎች ከሽማግሌዎች ጋር በመሆን አሻው በሰላም እንዲጠናቀቅ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ።

የሟችና የገዳይ ቤተሰቦች በተመረጠው ወንዝ ወይም ሸጥ ግራና ቀኝ በርቀት ቆመው በሽማግሌዎቻቸው አማካይነት ቀሪው ድርድር ይካሄዳል። በዚህ ሰዓት ከሟች ወገን እጅግ በጣም የሚፈራው ሞሶኒት ወይም የሟች የእህት ልጅ ነው። "ዋናው ሞሶኒት ነው። የእህት ልጅ ነው እሱ ከብት ሲከፋፈሉ መጀመሪያ ካልደረሰው ቤተሰብንም ሊገድል ይችላል። የገዳይ ቤተሰብም በአሻ ላይ የሚፈራው እሱን ነው እንደ ባህል ነው የሚታዩት እሱ መጣ ከተባለ የሟች ቤተሰብ እንኳን ይሮጣል።"[illegible] ሞሶኒቱ እጅግ በአይነቁራኛ ይጠበቃል። በእልህና በሲቃ ከወዲያ ወዲህ እያስቸገረ በሽማግሌዎች ተው እየተባለ የሚቆየው ሞሶኒት አጋጣሚውን ካገኘ ተፈትልኮ ሊወጣና በገዳይ ወገኖች ላይ ጥቃት ሊሰነዝር ይችላል። በአሻው አከፋፈል ጊዜ የሚፈራው ሞሶኒት ብቻ አይደለም። የሟች ልጆችም የገዳይን ወገኖች አሻግረው ባዩ ጊዜ ተመሳሳይ ጥቃት ለመሰንዘር አጋጣሚዎችን ሁሉ ሊጠቀሙ ይችላሉ።

---

መሰሉ፡ ሚያዚያ 2003

ያቆ፡ ሚያዚያ 2003

የእሼው ቀን በቀጠሮው ሁለቱም ወገኖች ምንም ስለት ይዘው እንዳይመጡ ህግ አስከባሪዎች፣ ፖሊሶች፣ ሚኒሻዎችም ይኖራሉ። ዋና ሳጅን መኮንን ኮብታ የተገኙበትን የእሻ አከፋፋል ሁኔታ እንዲህ ይገልጹታል። "በ2003 ዓ.ም። በባዙም ዜማና በሌላም ቀበሌ ግጭት ተከስቶ እኛ ብዙ ማረጋጋት ሰርተን ሰዎቹ በእሻ እንዲደራደሩና ዘረፋ እንዳይፈጽሙ ጥረናል። እነሱ እልህ ውስጥ ሲገቡ እኛ በማረጋጋት ሰርተናል።"[67] በያርጣ ቀበሌ የአማራጭ መሰረተ ትምህርት መምህር የሆነውና በቀደሙት ጊዜያት በመኢኒት ጎልድያ ሚኒሻ ጽ/ቤት ውስጥ የግጭት መከላከል ሥራ ይሰራ የነበረው አቶ ታዬ መስፍን በእሻ የማስከፈል ሥነ-ሥርዓት ወቅት ከኮምሩት አሻዎቹ ጋር ሰላምን በማረጋጋት ስራው የነበረውን ሁኔታ ፈታኝ እንደሆነ ተርኮልኛል።

- የልጃገረድና የቀሪ ከብቶች ክፍያ

የሽማግሌዎቹ ልፋትና ጥረት ተሳክቶ የሟችና የገዳይ ወገኖች በወንዝ ወይም ሽጥ ማዶና ማዶ ከቆሙ በኋላ ሽማግሌዎቹ ግማሽ ግማሽ መንገድ በመምጣትና በመቀራርብ ድርድሩ በሚከተለው መልክ ይቀጥላል።

የሟች ኮምሩት፡፡ "መንቲያኝ እኙ ኡሳቦይእኞንግ?"

"የእኔን ሰውዬ ገድለሃል። አትከፍለኝም፣ አትሰጠኝም ወይ?"

የገዳይ ኮምሩት፡፡ "ኪጨኒን ጃይ"

"እከፍልሀለሁ።"

የሟች ኮምሩት፡፡ "ኪያቦይ"

"ቶሎ በልና አምጣልኝ"

ከዚህ በኋላ የገዳይ ሽማግሌዎቹ ከኗላቸው እግር እግራቸውን አሳስረው ያመጧቸውን አምስት ከብቶችና ለእሼው የምትከፈለውን ልጃገረድ ይሰጣሉ። በተለይ ልጃገረዷ ስትሰጥ በአካባቢው

---

[67] መዐዛ ጌታቸው 2003

በሚች ቤተ ዘመዶች ከፍተኛ ጩኸትና ለቅሶ ይደመጣል። ልጅቷ እንደተሰጠች "ሜነረዴ አራቢያ ኩኳኩቦይ" ሾሞተው ተነሳ/ ይባላል። የሚች ሽማግሌዎችም ልጅቷን ለሚች እናት ወይም የቅርብ ለሆኑ ሴት ያስረክቧትና ከገዳይ ቤተሰቦች ጋር ወደ ቤታቸው ትሄዳለች። ይሄንኑ ጉዳይ ከስምንት እስከ አስር ዓመት በሚሆን እድሜዋ ለእሻነት የተከፈለችው ወ/ሮ ዶጊያ ኮንኩላይ በሚከተለው መልክ ገልጻዋለች። "ቤተሰቦቹ ለገዳይ ኮምሩቶች ሰጡኝ። ከዚያ በኋላ የኛ ኮምሩቶች ከወንዝ ወዲያ ላሉ የሚች ኮምሩቶች ሰጡኝ። እኔ ስሰጥ የሚቹ ህይወት ተነሳ ብለው ሁሉም ሙሁ ከዚያ አንድ አሮጊት ሴት ተቀበሉኝና ወደ ቤት ተወሰድኩ።"[88]

**የሚች ኮምሩት፡ ሾምቤ መንዴ ኢጉዋ ወሺጋዲያና ጣዲያቦይ / የልጃችሁ ምትክ ይችትና ተቀበሉን።**



**የልጃገረዲቱ እና የቀሪ ከብቶች የእሻ ክፍያ**

[88] ዱኒያ ሚሰኬያ 2009

ልጅቷ ከተከፈለች በኋላ የሚች ወገኖች ከፊት ከፊት የገዳይ ቤተሰቦች ደግሞ ከኋላ ከኋላ ሆነው ወደ ሟች ቤተ ሰቦች ቤት ያመራሉ። በብሄረሰቡ እምነት አንድ ሰው ከሞተ ከዚያው ከደጃፉ ቀብረው በመቃብሩ ላይ ቤት ሰርተው ለሦስት ወር ያህል ሬሳውን ከቃምጹት /ሬሳ አውጥቶ ከሚበላ/ ይጠብቃሉ። እናም የእሼው እርቅ ሥነ ሥርዓቱም ሚጠናቀቀው በዚሁ በሟች ቤተሰቦች ግቢ ነው።

ለዚሁ የእርቅ ማጸኛ የገዳይ ቤተሰቦች በሽማግሌዎች አማካይነት አንድ ከብት ያመጣሉ። ይህ ከብት በቋንቋቸው ቢዲ ሀራዶን ይባላል። የሟች ቤተሰቦች ደግሞ አንድ በግ በሽማግሌዎቻቸው አማካይነት ለገዳይ ሽማግሌዎች ይሰጧቸዋል። ከዚህ ቀጥሎ ለእርቁ ማጽኛ እንዲሆን በሟች ቤተሰቦች ግቢ አቅራቢያ ፊት ብለው የቆሙት የገዳይ ወገኖች ወደ ግቢ እንዲገቡ ለማድረግ አዲስ በር ይቀደዳል ወይም ይከፈታል። የገዳይ ወገኖች በሽማግሌዎቻቸው መሪነት አዲስ ወደ ተከፈተው በር አምርተው በሩ ላይ የተሰጣቸውን በግ በጦር ወግተው ደሙን በሾርቃ /ቅል/ ይቀዳሉ። ከዚያም የቃርዲ ቅጠል ይደባልቁበታል። በጦር የተወጋውም በግ በቢለዋ ይታረዳል። የሚከተለውም መሃላ በሁለቱም ወገኖች ይባላል።

አባገልጊኖ ቡራ ቤርዱ ኳቶን ዙጉምቁና ጂስኪን ቶአከ። ኤቢርሳ ኡሲኔ ቢኩን ኤዲዎኳቶን ዝንጉዲኖ። ናባ ጌኢላ ኩንታኖፉ ኢርሳሚ ኒያባጌዝጉ ከሳባክና ኢረሰቲኒያባና ውዳናጌየላ

በጦር ስንፈላለግ የነበረ በመሆኑ ይሄ ጦር በጉን ወግቶ ተራምደን እንታረቅ፣ እናንተ ላይ እናወርድበት የነበረው ጦር ወደዚህ በግ ይዙር፣ ደም ይፈስስ የነበረው የዚህኛው በግ ይፍሰስና እናንተም ተራምዳችሁ እንታረቅ።

ኮሞሩት እሼው ስላ የመሀላውን ጥቅም እንደሚከተለው ይገልጹል። "በእሻ ሥርዓት፣ በእርቁ ጊዜ በጉ በጦር የሚወጋው በጦር ስንፈላለግ የነበረ በመሆኑ ይሄ ጦር በጉን ወግቶ ተራምደን መታረቅ አለብን ከሚል ነው። እናንተ ላይ እናወርድበት የነበረው ጦር ወደዚህ በግ ይዙር፣ ደም ይፈስስ የነበረው የዚህኛው በግ ይፍሰስና እናንተም ተራምዳችሁ እንታረቅ የሚል ነው። የመቀላቀል ምልክት ነው። "[40]

የሟች ወገኖች በገባሩ በር ወጥተው አዲስ በተከፈተው በር ተመልሰው ይገባሉ። ከሽማግሌዎቹ የእርቁን ሥነ ሥርዓት የሚመራ ኩሳ እሼይ የተባለ ሽማግሌ የቃሩዲ ቅጠልና የበግ ደም

[40] ቁርጦ ሚሳሬ 2009

ከተቀሳቀሰበት ሾርቃ ውስጥ እየረጨ የገዳይንም የሟችንም ወገኖች እንዲገቡ ያደርጋቸዋል። የቃርዲ ቅጠል ከቶም በቀል የሚያገጸ እና ከንዴትም የሚያበርድ እንደሆነ የሚታመን ሲሆን ጠበኞቹ በአዲስ በር በግቢታቸው ነበረው ጠብ ተወግዶ በአዲስ አስተሳሰብና በአዲስ መንፈስ አዲስ ዝምድና መመስረቱን የሚያጠይቅ ነው። አቶ ብርሃኑ ስለዚህ የሚከተለውን ነግሮኛል። "በኋላ በግ ትመጣና በጦር ትወጋለች። ከዚያ በክብ ቅጠል ጠቅለል አድርጎ ደሟን ይቀዳል። ከዚያ ቃርዲ በእንግሊዝኛ እንጻውላ የተባለ ቅጠል ይቀሳቀልና በጉን የወጋው ሽማግሌና የተጣሉት ይቆሙና ይረጫቸዋል።"[90]

**ኣማንዶ ከኢዋሚ / ጠባችሁ ይቀዝቅዝ**

**ዝላኢንጂያኑ / በጠብ አትፈላለጉ**

**ጌያቶላ ሊያዊጊልጊናና ኪእዳ / መበቃቀል ይቅር**

ከዚህ በኋላ የገዳይና የሟች ቤተሰቦች አብረው ይቀመጣሉ። "ጥቂት ቆይቶ የሟች ወገኖች ያመጡት ቢዲ ሀራዶን የተሰኘ ከብት ተይዞ በፊትና በኋላ እግሮቹ መሀል ጦር እንዲያልፍ ይደረጋል። የጦሩ በቢዲ ሀራዶን እግሮች መሀል ማለፍ የአንድነት ምልክትና የሟችና የገዳይ ወገኖችን አንድ የመሆን ምሳሌ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ከዚያም ጦሩን ከሟችና ከገዳይ ወገን የሆኑት ተወካዮች በሽማግሌዎቹ መሪነት ይዘው "ቢያርኪን ቢያታ፣ ቢያርኪን ቢያታ/ጦር ድንጋይ ይውጋ፣ ጦር ድንጋይ ይውጋ" በማለት ሦስት ጊዜ በጦሩ ድንጋይ ይወጋሉ። ጦሩ ድንጋይ እንዲወጋ የሚደረገው ዋናኛ ዓላማ ከዚህ በፊት ለጠላትነት ስንፈላለግ የነበረው በዚህ ጦር ነው። ጦር ድንጋዩ እንዲይዝ፣ የሚወረወርም ከሆነ ድንጋይ ይውጋ። ቁርሾ ሆኖ ሰው አይውጋ ለማለት ነው። "ጦሩን ይዞ ድንጋዩን የሚወጉት ድሮ ስንፈላለግበት የነበረው ጦር ይሄ ነው። ስለዚህ ይሄ ጦር እኔ አንተን ከፈለኩህ ስለዚህ ድንጋይ ይወጋ። የሚወረወርም ከሆነ ይገፋ እደ ላይ የምወረወር ከሆነ ወይም መሳሪያ ከሆነ፣ የሚመታ ከሆነ ሰውን እንዳያደማ ወይም ሰውን እንዳያገኝ ድንጋይ ያግኝ ደረቅ ነገር ይውጋ ብሎ እንደ መሀላ አይነት ነው።"[91] ድንጋይ የወጋው ጦር ሜዳ ላይ በቂጡ ይተከልና ሜፉ ወደ ሰማይ እንዲያይ ይደረጋል። ይሄም ሰው እንዳያይ ለማድረግ ነው። በመቀጠል የመጣው ከብት መሀል አናቱን በድንጋይ ጠቀጥቅጦ ይገደላል።

[90] ዶቶ፡ ሚዚያ 2003

[91] ሴቶ፡ ሲሚንቶ፡ [illegible] ሚያዚያ 2003



በድንጋይ ተቀጥቅጦ የተገደለው ከብት

መሀል እናቱን በድንጋይ ተመትቶ የተገደለው ቢዲ ሀራዶን ቃርዶ ሥጋው ይበለታል። እንጀቱን ጨምሮ የተለያዩ ክፍሎቹ ለሴቶች በመስጠት የወተት እንጀቱ ፈጥኖ ውስጡ ያለው ታልቦ እንዲጠበስ ይደረጋል። እስከ አሁን ያየናቸው የሥነ ሥርዓቱ አካሎች እየተከናወኑ የማሽላ ገንፎ ይገነፋል፤ ትንሽ ዱቄት ከገዳይ ቤተሰብ፤ ትንሽ ዱቄት ከሟች ቤተሰብ ተዋጥቶ ሁለት ጣሰር ተጥዶ ይገነፋል። ሴት ከሆንች አሮጊት የወር አበባ ማየት ያቆመች ወንድ ከሆነ እንደዚያው በጣም ሽማግሌ የሆነ ገንፎውን ያገነፋሉ። በመኢኒት ብሔረሰብ የበቆሎ ገንፎ ባህላዊ ምግብ ሲሆን ለእሻ እርቅ ቀን የሚዘጋጀው ግን የማሽላ ገንፎ ነው። ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት በቆሎ አንዴ ብቻ ፍሬዎቹን አብቅሎ ስለሚቆምና ዳግመኛ ፍሬውን በግንዱ ላይ ስለማይሰጥ አንዴ ኖሮ የማለፍን ምስጢር ስለሚገልጽ ነው። በተቃራኒው ማሽላ ግን ስለሚያዘረዝርና ከአንዴ በላይ ፍሬውን የሚሰጥ ስለሆነ የዳግም ውልደት ምሳሌ ወይም ዳግም ዘር የመቀጠል ምስጢርን ስለሚገልጽ ነው። ማሽላን ከሟች ጋ በማመሳሰል፤ የሟችን ሞቶ አለመቅረትና በእሷው በምትሰጥ ልጅ የሚገኘውን ዘር የመቀጠል ሁኔታ ለማጠየቅ ነው። ከዚህ በኋላ የሚደረገው የእንጀት ማገበብ ሥርዓት ነው። የቢደ ሀራዶን እንጀት በዘሀቅጮሎዎች /እንጀት አንባቢዎች/ መገበብ ይጀምራል።

እንጀት አንባቢዎቹ እንጀቱን በጥሞና እየተመለከቱና እያነበቡ የእርቁን መስመርና አለመስመር ያባሉ። እርቁ ችግር እንዳለበትና እንደሌለበት፣ የአካባቢውና የህዝቡ እጣፈንታ ምን እንደሆነ ያዩበታል። በዚህ ጊዜ ችግር ነው ያሉትን ነገር ይናገራሉ። ጥሩ የሆነ ነገርም ካነበቡ እርቁ የሰላም መሆኑን ያሳውቃሉ።

ሙሉች ሚታ ጉምያ ጋሻይ ሸቲኒዬ ዲቶላ ጌስኪንኩንታ ዬላይዴን ጉጋ ሻዬይ አሻ ጊያጋሻዬ

እርቁ ሰላም ነው፣ እርቁ የሰመረ ነው፣ ህዝቡም ችግር አይገጥመውም፣ ሀገሩ ሰላም ይሆናል።

ጥቂት ቆይቶ የእርቁ ማጠቃለያ የሆኑ ሥርዓቶች ይቀጥላሉ። ከሚችና ከገዳይ ቤተሰቦች ውስጥ ቱእዎች ወይም የመጀመሪያ ልጆች እንዲቀርቡ ይደረጋል። ቱእዎቹ ሁለት እጆቻቸውን ወደ ጭኖቻቸው ለጥፈው ጎን ለጎን እንዲቀመጡ ይደረጋል። ከዚያ በኋላ በሽማግሌዎቹ እጅ በአንድ ሸርቃ /ቅል/ ቃርሚ የተቀላቀለበትን ደም እንዲጠጡ ይደረጋል። ይሄም የአንድነትና የዕርቅ ምሳሌ ነው። ሽማግሌውም "አሬንዬ አሬነዋ ኩቹኩራው ቃኘኝባይቦይ ገላኮን ኮደክ" /ተዋደዱ። አንድ ሁኑ። በፍቅር ኑሩ። ጠላትነት ይቅር፣ ይጥፋ።"ብሉ ይመርቃቸዋል።[92]

ምርቃቱ እንዳለቀ ሽማግሌዎቹ የተጠበሰውን የወተት እንጀት በቱእዎቹ አፍ ውስጥ አድርገው አይኖቻቸው ሳያረግቡ እንዲተያዩ ያደርጋሉ። ከዚያም ሁለቱም የወተት እንጀቱን እጃቸውን ሳያንቀሳቅሱ፣ አይኖቻቸውን ሳያረግቡ እየተያዩ እየበሉ ይቀራረባሉ። በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎች ይመርቃሉ። "ካያምኬራቶናቦይ አዲወ ስካሀራዲያና ጋቦይ ሊያዱይ አሞሙና ከባራኦረኖም ከኬዶፕ" /ዐይን ለዐይን ስትተያዩ የነበረው መጠላላት ቀርቶ ከአሁን በኋላ እንድነት ፍጠሩ - ተያዩ።/"[93]

---

92 [illegible] 2009
93 [illegible] 2009



የሚችና የገዳይ ቤተሰቦች በአንድ ሾርቃ /ቅል/ ሲጠጡ

ውጥም ሲቀራረቡ ደግሞ ከሽማግሌዎች አንዱ የተወጠረውን የወተት አንጀት በጦር እንዲበጠስ ያደርጋል። ከዚያ በኋላ ቂአዎቹ እንዲሳሳሙ ይደረጋል። የአንጀቱ መወጠር በሁለቱ ወገኖች መካከል ተከስቶ የነበረውን ውጥረት ማሳያ ሲሆን፣በጦር መበጠሱ ደግሞ የውጥረቱን መርገብና መቤጠስ የሚያሳይ ነው። በመቀጠል ሽማግሌዎች የተጠበሰውን ሥጋና የማሽላ ገንፎውን በአንድ ይደባልቃሉ። ባሊጋሉ የነበሩትንም

"ኩቹኩሬመዋዋቦይ አልትኬ ጋኒያ ሃ እቀላቅላችኋለሁ። አንድ ሆናችሁ አብራችሁ ኑሩ" ይሏቸዋል። እናም በመጨረሻ ከተቀላቀለው ገንፎና ስጋ ቀምሰው በእርቁ ሥነ ሥርዓት ላይ ለተሳተፉት ሁሉ ያከፋፍላሉ። በእለቱም የተዘጋጁ ሌሎች እንደ ቦርዴ እና ጠጅ አይነት መጠጦች ይጠጣሉ። የእርቁም ሥነ ሥርዓት በዚሁ ይጠናቀቃል። ከዚህ በኋላ የሚችና የገዳይ ወገኖች በገበያም ይሁን በመንገድ ቢገናኙ ሰላም ተባብለው ከማለፍ በስተቀር በውስጣቸው የሚቀር ቂም የለም። ይሁን እንጂ የአሻ ሰባት ከብቶች ተጠቃለው በማይከፈሉበት እና በጊዜና በቀጠሮ በሚቀየበት ኢጋማሚ ከብቶቹን ጨርሰህ ከፈለኝ በሚል ጠቦች ሊነሱ ይችላሉ። ከዚያ ውጭ ምንም አይነት ግጭት አይፈጠርም ቀደም ባሉት ጊዚያት በደርግና ከዚያ በፊት የገደለ አሻ ከከፈለ በመንግሥት የማይታሰር የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የገደለ ሰው ወደ እስር ሲሄድ አሻው በዘመዶቹ እየተከፈለ እስሩን ጨርሶ ሲመጣ በሰላምና በነጻነት ይኖራል።

## 4.2 "ማጠብ" /የደፈራ እርቅ/ ሥነ ሥርዓት ሂደት

በመኢኒት ቤሔረሰብ ከባድ ቅጣት ከሚያመጡትና ከባድ ጸብ ከሚፈጥሩት ውስጥ አንዱ የሰው ሚስት መድፈር ነው። ይህ አይነቱ ግጭት ከባድ የሆነው በብሔረሰቡ ባህል ሚስት ህጋዊ ከሆነ ባልዋ ውጭ የማትሄድ በመሆኑና ከሄደችም አምላክን የሚያስቆጣ ሥራ በመስራቷ የሚመጣው ቅጣትም ከእሷ አልፎ ወደ ባልዋ ከባልዋም አልፎ ለልጆቿ የሚተርፍ እንደሆነ ስለሚታመን ነው። በመኢኒት ቤሔረሰብ ባህል የሰው ሚስት በጣም ተከባሪ ናት ። "ቀደም ባሉት ጊዜያት አብዛኛው የመኢኒት ቤሔረሰብ ሴቶች የሚያምኑት በቃልቻ ስለሆነ እግራቸውን እንኳን ወደ ታች ቢዘረጉ ሰው አይራመዳቸውም። ምክንያቱም ቢዘረጉ ተደፍረሻል የሚል አባል ስለሚናር የሚቀመጡት ስብስብ ብለው ነው። ሁለተኛ የተቀመጡበትን ቅጠል ሌላ ሰው መጥቶ አይቀመጥበትም።"[94] በመሆኑም የመኢኒት ወንድ እንደዚህ አይነቱን ስህተት ላለመስራት ይጠነቀቃል። አሁን አሁን ግን እንዲህ አይነቱ ግጭት እየበዛ መጧል። የሆና ሆና ሴቷ አውቃም ይሁን ሳታውቅ ከባልዋ ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብታደርግ ወደ ቤት ገብታ ለባልዋ ምግብ አትሰጥም፣ መጠጥ አታቀርብም። ወ/ሮ አልጋነሽ ሚስቶች የሰሩትን ስራ በግልጽነት እንደሚናገሩ ይገልጻሉ። "አብዛኛዎቹ ባሎቻቸውን አምነው የሚኖሩ እሉ አብዛኞቹ ደግሞ ይባሉጋሉ። ከባሏ ውጪ የምትሄድ ሴት ባህሉ ስለማይፈቅድ መንገድ ስትሄድ ወይም ከቤት ወጥታ ግንኙነት ተፈጽሞባት ከሆነ ስትመለስ ግልፅ ሆና ነው ለባሏ የምትናገረው።"[95] ቀኖዬ ጃጃም የወ/ሮ አልጋነሽን ገለጻ በማጠናከር የሚከተለውን ይናገራሉ። "የተደፈረች ሴት እቤት ገብታ ህፃን ልጅ ቢኖራት እንኳን ጡት አታጠባም፣ ልጅዋን አትይዝም።"[96] የብሔረሰቡ የተደፈረች ሴት ለባልዋ እውነቱን የምትነግርበት በርካታ ምክንያቶች አሏት። በጋብቻቸው ወቅት እንዳቸው ከአንዳቸው ውጭ ላለመሄድ የገቡት ውል መኖሩ አንዱ ነው። እንደዚያ የሚያደርጉት ከሷ ውጪ ሌላ ሰው ጋር ከተገናኘች ምግብ ሰርታ ስታቀርብ ያ ሰውዬ ይሞታል ከሚል እምነት ነው። ወልደየስ ይሄንን ያጠናክራሉ። "ምክንያቱም ቀደም ሲል ሲጋቡ ከሷ ሌላ፣ እሷም ከሱ ሌላ እንዳታውቅ ውል አለ። ስለዚህ ወይ እሷ ትሞታለች ወይ እሱ ይሞታል የሚል እምነት አለ።"[97] ከዚያም ውጭ አብዛኞቹ የሚያምኑት በቃልቻ በመሆኑ እንዳይሞቱ ስለሚፈሩ እንደሆነ ተዋቂው የእነር ሽማግሌ ሌላ ይገልጻሉ። "እግዜር ያየኛል ብላ፣ ቃልቻ ይገለኛል ብላ ነው። ቁማ /እግዜር/ አይቶኛል ብደብቅ እሞታለሁ ስለዚህ ባፍር ለአንድ ቀን

---

[94] ቁርጥኑ ሚያዚያ 2009
[95] አል ጋነሽ አለሙ ሚያዚያ 2009
[96] ቀኖዬ ሚያዚያ 2009
[97] ካሱ ሚያዚያ 2009

ነው ከምሞት ብላ ትናገራለች።"[98] እንደሌሎቹ እምነት እውነቱን አውጥታ ባትናገርና ባሏ ቢሞት በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ በሚቀጠቀጠው ከብት አንጀት ላይ በሚስቱ መባለግ ምክንያት እንደሞተ በአንጀት አንባቢዎች ስለሚታወቅ ሌላ የግድያ ጣጣ ይዞም ስለሚመጣ ነው። "ሴትየዋ በስውር ከውጭ ሰው ጋር ተገናኝታ ለባልዋ ምግብ የምትሰጥ ከሆነ ባልዋ ታሞ ይሞታል። ከዚያ ለሱ መቅበሪያ ከብት ሲቀጠቀጥ በምን እንደሞተ በዚያ ላይ ይታወቃል። ከዚያ የሟቹ ወገን የሆነው ጉሳ ጠብ ያነሳል። ግጭቶች ተፈጥረው ይጋደላሉ።"[99] ከዚህ ተጨማሪ ሴትየዋ ብትደብቅ በልጆቿ ፊንጢጣ ላይ ቶርሳ የተባለ በሽታ ምልክት ሆኖ ስለሚወጣ ትጋለጣለች። "የምትናገርበት "ቶርሳ" የሚባል ነገር አለ። ከደበቀች የልጆች ፊንጢጣ ወደ ውጪ ይወጣል። ያ ሲታይ የሚባለው ይቺን ሴት ሌላ ደፍሯት ደብቃለች ይባላል። ስለዚህ የተደፈረች ሴት ለባሏ እከሌ ደፈረኝ ብላ ትናገራለች።"[100]



አስተጉሚ ብርሃኑ ወርቁ በስተግራ፣ አንጀት አንባቢው ቃንግሪ ዶሪከረ በመሀል

[98] ሌዩ፡ ሚያዚያ 2003
[99] ኬኔ፡ ሚያዚያ 2003
[100] ፀቻ፡ ሚያዚያ 2003

ከላይ ባሉት ምክንያቶች የተነሳ ከሷልዋ ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመች ሴት ወደ ሽማግሌ ሚስቶች ሄዳ የሆነውን ትናገራለች። ከማን ጋር ግንኙነት እንዳደረገችና እንዴት እንደተፈጠረ ታብራራለች። ከዚያም የአገር ሽማግሌዎች እንደሰሙት የደፋሪውን አባት አስጠርተው ጉዳዩን ያሳውቃሉ። በማወቅም ባለማወቅም ትደፈራለች። እና እከሌ ደፍሮኛል በምትል ሰዓት የምትናገረው ለወንዶቹ ሽማግሌዎች አይደለም። ለሽማግሌዎቹ ሚስቶች ነው። ከዚያ ሴቶቹ ለሽማግሌዎቹ ይነግራሉ። ከዚያ ሽማግሌው ለልጁ አባት "ልጅህ የእከሌን ሚስት ደፍሯልና ይዘህ ና" ይባላል።"[101] አንዳንዱ ባልየው ምግብና ጨሞ/ቡና/ አለመስጠቷን ሲያይ ጉዳዩን ይረዳል። እናም ከማን ጋር ችግሩ እንደተፈጠረ ጠይቆ ችግሩን ወደ ሽማግሌዎች ያቀርባል። የሰው ሚስት ያባለገ ሰው በባሏ ሊደርስበት የሚችለውን በቀል በመፍራት እራሱን ያሸሻል። ሽማግሌዎች በመሀል ገብተው ካሳ ከፍሎ ሴትየዋን በበግ ወይም በፍየል ደም እስከሚያጥብ ድረስ ይደበቃል።

ተጠርጣሪው ፍየል ወይም በግ ይዞ እንዲመጣ ይደረጋል። ፍየሉ ወይም የበጉ በተጠረጠረው ሰው በእንጨት ቀጥቅጦ ይገደልና አንጀቱ በአንጀት አንባቢዎች እንዲታይ ይደረጋል። የአንጀት ማንበብ አስፈላጊነት ሰውየው በትክክል ከሴትዋ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸሙን ለማረጋገጥ አንደኛው ነው። "አንጀት ማስነበብ እንደ እምነት ነው የሚታየው። አንጀት አንባቢው በትክክል ያውቃል ብለን ነው የምናምነው። አንጀቱን አንብቦ ደፍረሃል ነበር ተብሎ ይናገራል። ሰውየውም እኔ ስህተተኛ ነኝ። በቃ ወንድሚን ልካስ ብሎ አንድ ጊደርም ሆነ ወይፈን አምጥቶ ከሚስትየው ባል ጋር ሽማግሌዎች አስታርቀው ያስናብቱታል።"[102] ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ሴትየዋ ከዚህ ውጭ ከሌላም ሰው ጋር ግንኙነት አድርጋ እንደሆነና ተጨማሪም እንዳለባት ለማረጋገጥ ነው። "እንዲህ ዓይነት ነገር ገጥሞኛል። እከሌ ነው ካለች ፍየል ይገድልና አንጀት በሚያዩ ሰዎች አንጀት ይታያል። አንጀት የሚያዩ ሰዎች ያረጋግጣሉ። አንድ ሰው ጋር ብቻ ነው የሄድሽው ወይስ ሌላ አለ የሚለውን ሌላ ካለ መካድ አትችልም። በአንጀት ላይ አይተው እስከ አራት ድረስ የሰረቀችን አመለኛን ሴት ያወጡበት አለ።"[103] በዚሁ አንጀት በማንበብ በቢያገሊች መንደር ተዋቂ ከሆኑት ሰዎች ውስጥ አንጀት አንባቢው ቃንግሪ ዶረክሪ አንጀት ውስጥ ማንኛውም እውነት ፍንትው ብሎ እንደሚታያቸውና በትክክል እንደሚያውቁት ነግረውኛል። "እኔ የተናገርኩት መሬት ጠብ ስለማይል ያምናሉ። ነገር ግን

---

[101] ሉሉ· ሚያዚያ 2003

[102] ቁርጉኑ · ሚያዚያ 2003

[103] ወልደሃኔ-ሚያዚያ 2003

አሁን የተሰየ እምልኮ የጀመሩ /የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች/ ወደኔ አይመጡም፡፡ ለላም አደጋና ሞት፣ ጦርነትም ሲመጣ አንብቤ እውቀዋለሁ፡፡"[104]

የእንጀት ማገበብ ለአንባቢዎቹ የተሰጠ ጸጋ በመሆኑ በጣም የተደበቁ ታሪኮችም ይወጣሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እልፎ እልፎ የእንጀት ንባቡን የሚጠራጠሩ አሉ፡፡ እንደዚህ አይነት ሰዎች በመቀሺታቸው ብዙ ክፉ ነገር እንደሚደርስባቸውና እንደሚጎዱም ይታመናል፡፡

አንድ ሰው ተጠርጥሮ ፍየል ይዞ ከመጣ በኋላ ፍየሉ ተቀጥቅጦ የሚገደለው በእንጨት ነው፡፡ በሞት ጊዜ ከብት የሚቀጠቀጠው በድንጋይ ሲሆን በማጠብ ጊዜ በእንጨት የሚቀጠቀጠው ሁለቱም ስህተቱን የሰሩት ሰዎች በህይወት ያሉ በመሆናቸው ነው፡፡ አቶ ብርሃኑ የድንጋዩንና የእንጨቱን ምሳሌ እንደሚከተለው ይተርኩታል፡፡ "ድንጋይ የሞት ተምሳሌት ሲሆን እንጨት የህይወት ምሳሌ ነው፡፡ ዱላ የሚመረጠው ሁለቱም /ደፋሪና ተደፋሪ/ በህይወት ስላሉ ነው፡፡ የሞቱ ቢሆን ለምሳሌ በሞትና በውርስ መካከል ቢሆን የሚቀጠቀጠው በድንጋይ ነው፡፡ ስለዚህ ፍየሉ በዱላ ይመታና ፍየሉ ከሞተ በኋላ አንጀቱ ይወጣና ይነበባል፡፡ [105]

ይሁን እንጂ በቆላማው የመኢኒቶች አካባቢ ሥርዓቱ ሁሉ ጠንከር ስለሚል የእጥበት ስርዓቱ የሚካሄደው በፍየልና በበግ ደም ሳይሆን በበሬ ደም ነው፡፡ ከባሏ ውጭ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመች ሴት የምትታጠበበት በበሬ ነው፡፡ "ከባሏ ውጪ ወሲብ የፈጸመች ሴት በደም የምትታጠበበት ትርጉም ከስራችው ኃጢአት ነፃ ሆናለች፣ በፍየል፣ በበግ ወይም በከብት ደም ወደ ጎዥ ወደ ሻሻ አካባቢ በከብት ነው፡፡ ወደ ባቹማ ነው በፍየል በበግ፣ ጌሻና ሻሻ ባህሉን ጠንከር ያደርጋሉ፡፡" [106]

በደጋው አካባቢ ለእጥበት የሚውሉት ፍየል ወይም በግ ለስረያ ያልደረሱ ቁብ ወይም ወጠጤ ናቸው፡፡ ይህም በንጹህ እንስሳት ደም የመታጠብ ምልክት መሆኑን አቶ በድሉ ይናገራሉ፡፡ "ወጠጤ፣ወይም ቁብ የሚመረጠው ሁለቱም ለወሲብ ያልበቁ በመሆኑ ወጠጤው ማንባባት ያልጀመረ በመሆኑ ንፁህ የሆኑ በመሆናቸው በንፁህ እንስሳ ደም ታጥበን እንንፃ በሚል ነው፡፡ ከሁለት አንዱ የሚታረዱት ለዚህ ነው፡፡"[107]

---

104 [illegible]፣ ሚያዚያ 2003
105 ብርሃኑ፣ ሚያዚያ 2003
106 [illegible]፣ ሚያዚያ 2003
107 በድሉ፣ ሚያዚያ 2003

የማጠቢያው እንስሳ ከተዘጋጀ በኋላ ሽጥ አካባቢ ተፈልጎ የማጠብ ሥነ- ሥርዓቱ ይካሄዳል። ሥነ · ሥርዓቱን ለማከሄድ ሽማግሌዎች ከሁለቱም ወገን ያልሆነ አንድ ሰው ይመርጣሉ። ያ የተመረጠው ሰው ደፋሪው ግንባሩን ብሎ በገደለውና በታረደው በግ ደም ሴትየዋን ያጥባታል። ገደም የምትታጠብበት ዋናው ምክንያት በባህላችን አዲስ ሆኗል፣ በደም ታጥቦ አዲስ ሆኗል። ብልግና ስለሰራች ሁለተኛ አትሰራም አዲስ ናት ማለት ነው።"[108]

ከዚህ በመቀጠል ሁለቱም የሞተውን ፍየል ወይም በግ እንዲራመዱ ወይም እንዲሻገሩት ይደረጋል። "ሁለቱም በጉን ወይም ፍየሉን የሚራመዱበት ዋና ምክንያት ከስህተት ወደ ትክክለኛነት፣ ከሀጢዓት ወደ ጽድቅ የመመለሳቸው ምሳሌ ነው። "የሚራመዱት ያ ኃጢዓቱ፣ ያ ስህተቱ እዚያ እንዲቀር ነው።"[109] ከዚህ በኋላ የሰው ሚስት የደፈረው ሰው ለካሳ ያዘጋጀውን እንደ ከብት ይሰጣል።

ሽማግሌዎችም እንዲህ አይነቱ ስህተት እንዳይደገም መክረው ለእርቁ ማጠናቀቂያ የምትሆን ሳንቲም አፕሬ ላይ በመወሰን አብረው ቦርዴ እንዲጠጡ በማድረግ እርቁን ያጠናቅቃሉ። ከዚህ በኋላ ባልም ሚስቱን ይዞ ወደቤቱ ይሄዳል ሚስቱን ከደፈረበት ጋርም ቢገናኙ አብረው የሚበሉ አብረው የሚጠጡ ይሆናሉ። "ሽማግሌዎችም እንግዲህ የቀን ጉዶሉ አለ ምናልባት በማወቅም ባለማወቅም ይሆናልና አንተም ተው ስለዚህ የአንተ ካሳ ይኸውልህ ታረቁ ይሏቸዋል- ይታረቃሉ። ከዚያ ደፋሪው የተወሰነ ሳንቲም ሽማግሌ የሚወስነውን የተወሰነ ቅጣት ያወጣና መጠጥም ቢሆን ይጠጣሉ ከዚያ በኋላ ጠጥተው ይለያያሉ ቂም አይያያዙም።"[110]

## 4.3 "ሽባ" /የድንበር ጠብ/ ግጭት የአፈታት ሂደት

በመአኒት ቤሔረሰብ ውስጥ በሽማግሌዎች ከሚፈቱት በርካታ የግጭት አይነቶች ውስጥ አንዱ የድንበር ጸብ ነው። አንድ ሰው በድንበር በሚፈጠር ግጭት ችግር ውስጥ ቢገባ ጉዳዩን ይዞ ወደ ሽማግሌዎች ያቀርባል።

---

[108] መልሴ፡ ሚያዝያ 2009
[109] ካሴ፡ ሚያዝያ 2009
[110] ዌርካ፡ ሚያዝያ 2009

"ድንበር ስንል ሁለት ድንበርተኞች ነው። የቦታ ፀብ ከተፈጠረ የአንድ ጎሳና የአንድ ጎሳ ከሆኑ የአካባቢ ሽማግሌዎች አሉ፣ ከነሱ ድሮ ድንበራችሁ የቱ ነበር? ክሱ አትለፉ ብለው የቀድሞ ድንበራቸውን በመለየት የድንበር እንጨት ተክለው ያስማሟቸዋል።"[111]

የሚመረጡት ሽማግሌዎች በከሳሽና በተከሳሽ ፍላጎት ነው። ይሁን እንጂ ሽማግሌዎቹ ተቀናቃኞቹ ጠብ ውስጥ የገቡበትን ድንበር ጠንቅቀው የሚያውቁ ናቸው። ግጭት የገቡበትን መሬትና እውነተኛ ድንበሮቻቸውን ወይም ወሰኖቻቸውን ካላወቁ በፍጹም እራሳቸውን ለአሸማጋይነት አያቀርቡም።

ከሳሽና ተከሳሹ በሽማግሌዎች ፊት የየራሳቸውን መከራከሪያ በሚከተለው መልኩ ያቀረቡባሉ።

ከሳሽ፡ ኢች አካናፊቺያን ቦይ / አንተ የእኔ ድንበር ገፍተሃል።/

ተከሳሽ፡ አኒ ካኮም( ኮባቦም) / እኔ የአንተን ድንበር ገፍቼ አላፈረስኩም።/

በሁለቱ ወገኖች መካከል ክርክሩ ከቀጠለና ሽማግሌዎቹም ካዳመጡ በኋላ ተወያይተው ውሳኔ ያሳልፋሉ።

ሽማግሌ፡ ኢች አይ ቡዲቲ አኞ አካናፊች ቦይና አይስባክ ሚታ ጨዋ ኢደልክ ሽማግሌዎ ሴኔ

አፊች ኮሪያ / እኛ ወስነናል። አንተ ገፍተህ አይተናል። ውሸታም ነህ። ከጥንት ጀምሮ እያረሳችሁ ያላችሁት ድንበራችሁ ይሄ ነው። ስለዚህ በድሮ ድንበራችሁ ሂዱ።/

በመሆኑም በአብዛኛው የሽማግሌዎቹን ፍርድ አክብረው የሚቀበሉ ሲሆን ፍርዱ ተዛብቶብኛል ያለ ሰው ግን ወደ መንግሥት ሕግ አቤት ይላል።

## 4.4. የእርግማን እርቅ ሥነ - ሥርዓት ሂደት

አንድ ተበድያለሁ ያለ ወይም ጠላቱን እስረግማለሁ ያለ ሰው ወደ አካባቢው የሃይማኖት አባቶች ቃልቻዎች ጋ ይሄዳል። በቃልቻው ግቢ ጥቂት በመቆየት ለቃልቻዎቹ ረዳቶች በትድሚያ ጉዳዩን ያሳውቃል። በመቀጠልም ተራው ሲደርስ የተበደለ ሄዶ ለባለቃልቻው ተንበርክኮ ጉዳዩን ይናገራል። እከሌ ደብድቦኛል፣ የእገር ሽማግሌጋም ብሄድ ከዶኛል፣ ህግም ጋ

[111] ወልደየስ፣ ሚያዝያ 2000

ብሄድ ማስረጃ የለኝም። ስለዚህ በምናምነው እምነት አስጠሩና ይካሰኝ ብሎ ለቃልቻው ይናገራል። አንዳንዱ የጠረጠረውን አስጠርተው እንዲጠይቁለት፣ አንዳንዱም ማስረጃ የለውም ብሎ ስለካደው በፊታቸው እንዲምል እና እዚህም በእሳቸው ፊት ከካደው እንዲረግሙለት ይጠይቃል። ቃልቻው ጉዳዩን ካዳመጡ በኋላ የተጠረጠረውን ሰው እንዲመጣ በቃል ወይም በጽሑፍ መልዕክት በረዳቶቻቸው ይልካሉ። መጥሪያ የደረሰውም ሰው ፈጥኖ ወደ ተጠራበት ቦታ ቀጠሮውን አክብሮ ይመጣል።

ያስጠራው ሰው ከመጣለት በኋላ ጉዳዩን ይገልጣል። ከዚያ ላስማማችሁ ይላል። የተጠራው ካመነ "ጋምጫላቸ" ዝንጅብል እኝኩ እንትፍትፍ ብሎ ያስታርቃቸዋል። ካላመነ ተበዳዩን ጠርቶ ሁለቱን ፊት ለፊት ያነጋግራል። ተበዳይም "ከካደ የእርስዎን እጅ ይምታና ይማልልኝ እኔም የእርስዎ ደጆ ጠርጌ እሄዳለሁ" ይላል። ከዚያ ግራዋና "ካስካች" ወይም "ናጫ" የተባሉ ቅጠሎች ተቆርጠው ታስረው ይመጣሉ። ሁለቱ ቅጠሎች የተመረጡበት ዋና ምክንያት ቅጠሎቹ ለእቃ ማጠቢያነት የሚውሉ በመሆናቸው ነው። ግራዋ ንፁህ ነውና ያነፃል ብለው ይመርጡታል። ከዚያ ቃልቻው ተከሳሹን "ወንድሜ አንተ የሰው ንብረትን በልተሃል። በህይወት ብትኖር ከዚያ የተሻለ ንብረት ታመርታለህ። ነገር ግን ይሄን እንቢ ካልክና ከካድክ ልፍቀድለትና ይርገም" ይሉታል። ተከሳሹም "እሺ ይፍቀዱለትና ይርገም" ካለ ሰውየው በቀጥታ ይፈቀድለትና በ ሸርቃ /ቀርቅሃ/ ውሃ ይቀርብለታል። ቀጥሎም ግራዋና ናጫ ይቀርባል ። አሁንም በድጋሚ ቃልቻው ተከሳሽን ይጠየቃል። "ትፈቅድለታለህ" ይባላል። "እሺ" ሲል ሰውየው ካላመነ ከሸርቃው /ቀርከሃ / ውስጥ ያለውን ውሃ ከሳሽ ወይም ረጋሚው "እኔ እውነት ተናግሬ ይሄ ሰውዬ ስለካደ እዚህ ከርከሃ /ሸርቃ/ ውስጥ እንዳለው ውሃ ህይወቱ ይደፋ" ብሎ ውሃውን ይደፋዋል። ከዚያ በኋላ ግራዋውንና ናጫውን ይዞ በሚሰጠው ቦታ ላይ "እኔ እውነት ተናግሬ ከሆነ የሱ ዘር ይጠረግ፡እኔ ውሸት ተናግሬ እንደሆን የኔ ዘር እንዲህ ይጠረግ" ብሎ የተሰጠውን ቦታ ይጠርጋል። ከዚያ ለዚህ ስውዬ ጥንት የቀርከሃ ቁርጥራጮች አሁን አሁን ደግሞ ጨሌዎች በዘር ተያይዘው ይቀበል። ርግማኑ ከተጠናቀቀና ከተሰነባበቱ በኋላ ሁለቱም ውጤቱን በቤታቸው ሆነው ይጠባበቃሉ። በውሸት የማለ እርግማኑ መቼም ቢሆን ይደርስበታል ተብሎ ይታመናል። በውሸት የተረገመም ካለ እርግማኑ እንደማይነካው ይታመናል። እንዲያም ሆኖ ረጋሚው የረገመው ሰውዬ ቤት የሚባላ ነገር አይበላም፣ የሚጠጣም ነገር አይጠጣም። ከጠጣና ከበላ ግን የረገመው ርግማን ወደሱ ይተላለፋል ተብሎ ይታመናል።

በሌት መድፈርም ጉዳይ ከስ ቢቀርብ ቃልቻው የተጠረጠረውን አስመጥቶ ይጠይቃል። ተከሳሹ አላደረኩም ካለ እንዲረግምለት ያደርጋል።ቃልቻ ጋ ሄደው ሚስቴን ደፍሯል ሲል ያኛው አልደፈርኩም ይላል። "እኔ ደፍሬ እና አሁን በውሸት ክጄ ከሆነ እርግማኑ ደርሶብኝ በሞትኩ ጊዜ ዘመዶቼ ሬሳዬን ከቤት ትተውና ሳልቀበር እዚህ መጥተው መጀመሪያ የደፈርኩበትን ወንደል ካግ ፍየሉን ከዚያም የእርቁንም ከፍለው ይቅበሩኝ። አንተም ውሸታም ከሆንክና በሀሰት እኔ ላይ ስለማልክ አንተም እንደእኔሙት" ይባባላሉ በቃልቻው ፊት። ከእርግማኑ በኋላ ያ ሰውዬ ከሞተ ዘመዶቼ መጀመሪያው ቃልቻው ጋር መጥተው አስሬ የሞተው እዚህ በመረገሙ ነው ብለው ለቃልቻው ካሳ ይከፍላሉ። በቃልቻ ላይ የሚደረገው እርቅ ላይ ዝንጅብልና ቡና ይሰጣቸዋል። ሽማግሌዎችም ባሉበት ቁጭ ብለው እዚህ ቃልቻ ፊት ታርቀናል። ቃልቻው እውነተኛ ነው። የኛ ሰው ከዚህ በፊት እንቢተኛ ሆኖ ነበር ይሄ ቃልቻ ረግሞት ስለሞተ በሱ ይቅር። ሞቱ እንዳይዛመት እኛ እርቁን እንፈጽም ይላሉ። ከዚያ የቃልቻው ሙሪ ዝንጅብል ነከሶ ያመጣና ለአንደኛው ይሰጣል ከዚያ ሌላኛው ይነክሳል፣ ቀጥሎ ቡና ያመጣል እጃቸውን ወደ ኋላ ሸርበው በአንድ እቃ ውስጥ እንዲጠጡ ይደረጋል። ዝንጅብሉን ነክስ ፣ነክስ እያደረጉ እስከ ልጅ ልጅ ቤተሰቡ ሁሉ ይነክሳል። ቡናውም ጀርባ ላይም ያለች ልጅ ብትሆን እንኳን እንድትቀምስ ጠብ ይደረግላታል። ከዚያ "ሂዱና ቅበሩት" የሚል መልዕክት ከቃልቻው ሲሰጥ ሄደው ይቀብራሉ።

- ከእርግማን በኋላ ያለ እርቅ

አንድ ከሳሽ ተከሳሽን በቃልቻው ፊት አስረግሞ ከተለያዩ በኋላ ከሳሹ ጉዳዩን አንዴ ለሚያምነው አላልፈልና ተረጋግቶ ኑሮውን ይቀጥላል። ነገር ግን ተከሳሽ ልረገም ያለው በድፍረት ከሆነ እርግማኑ ቀን ቆጥሮ መድረሱ በቤተሰቡ ዘንድ ይታመናል። እናም የተረጋሚው ከብቶች፣ ንብረቱ፣ ልጆቹ፣ ሚስት ወይም ዘመዶቹ መታመም፣ አለዚያም መሞት ይጀምራሉ። በዚህ ጊዜ ተረጋሚው በቀጥታ ወደ ቃልቻው ጋ በመመለስ በፊት በድፍረትና በውሸት መማሉን አሳውቆ በድፍረቱ በመማሉም ምክንያት የደረሰበትን መከራ ገልጦ ቃልቻው ይቅር እንዲለውና ከከሳሹም ጋር አስታርቆት እርግማኑ እንዲሻርለት ይጠይቃል። ቃልቻውም ጉዳዩን መርምሮ ተበዳይን ካሳ እንዲከፈል ያደርጋል። እንደገናም የበዳይ ወገኖች ይጠራሉ። በዳይም ሳጠፋው ጥፋት እንደ ጥፋቱ አይነት ተመጣጣኝ ካሳ ለተበዳይ ይከፍላል።

በመጨረሻም ቃልቻው ዝንጅብል ነክስ ነክስ አድርጎ ለረዳቱ ይሰጠዋል፡፡ ረዳቱም በተራው ዝንጅብሏን ነክስ ነክስ አድርጎ ለተረጋሚው ይሰጠዋል። ተረጋሚው ሰውዬም እንደ እነሱ ነክሶ ለቀሪ ዘመዶቹ በሙሉ ይሰጣል። ዘመዶቹ ከህጻን እስከ አዋቂ ድረስ ዝንጅብል የመንከስ ሥርዓትን ይፈጽማሉ። በአካባቢው ለሌሉትም ዝንጅብሏ ትወሰድላቸዋለች፡፡ ከዚያ በኋላ የቡና ቅጠል በቀዝቃዛ ውሃ ሆኖ ይሰጣቸዋል። ቡናው መጀመሪያ ቃልቻው ፋት ካሉለት በኋላ በቅል ተደርጎ እንደየ እድሜ ተከተላቸው ለአባትና ለእናት ከዚያም ለመጀመሪያ ልጅ ተሰጥቶ ፋት ፋት እያሉ በመቀባበል ይቃመሳሉ። ቡናና ዝንጅብሉ የተመረጠበትን ምክንያት ቃልቻው አወቀ ፎርሽዋ የሚከተለውን ብለዋል። "ቡና እና ዝንጅብሉ የተመረጠው ከጥንት አያቶቻችን ወይም ቃልቻዎች የተቀበልናቸው ነገሮች ናቸው። ዝንጅብል የሚሰጠው ሌላ ነገር ቢሰጥ ስለማያረካቸው ነው። የቡና ቅጠሉም ቀዝቃዛ ውሃ ላይ ተጨምሮ የሚሰጠው ነገሩን ያብርድላችሁ፣ ያቀዝቅዝላችሁ ለማለት ነው።" [112]



ቃልቻ አወቀ ፎርሽዋ በመሀል አስተርጓሚ ብርሃኑ ወርቁ በስተቀኝ

በአጠቃላይ ከእርግማን በኋላ ያለ እርቅ የሚከናወነው የተረገመው ሰው ጥፋቱን አምኖ የተረገመበት ቃልቻ ጋ ሄዶ እርቁን እስኪፈጸመ ድረስ እርግማኑ ከልጅ ወደ ልጅ እየተሸጋገረ የዚያ ሰው ቤተሰቦች የሆኑ በሙሉ እንደሚያልቁ ስለሚታመን ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የተረገመው

[112] አወቀ ፣ ሚያዚያ 2003

ስውና የቅርብ ዘመዶቹ ይሞቱና እርግማኑን ሄዶ እንዲቀር ወይም እንዲወገድላቸው የሚሆደርግ ይጠፋል። በዚህም የተነሳ እርግማኑ ረጅም ዓመት ያስቆጥራል።

## 4.5. የብሔረሰብ ግጭት የአፈታት ሂደት

የመኢኒት ብሔረሰብ ከሌላ ተጎራባች ብሔረሰቦች ጋር ያለው ግንኙነት በአብዛኛው ጥሩና ሰላማዊ የሚባል ነው። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ከሱርማ ብሄረሰብ ጋር ግጭት ውስጥ ይገባል። ቁልፍ የመረጃ አቀባዮቹ በመኢኒትና በሱርማ ብሔረሰብ መካከል ስላለው ግጭት የሚከተለውን ይላሉ፡፡ "ይሄ ጸብ የቆየ እና አንድ ጊዜ በእርቅ ሲስማሙና መልሰው ሲፋረሱ የኖረ ነው::"[113] ሁለቱ ብሔረሰቦች ብዙ ግዜ ግጭት ውስጥ የሚገቡት ከከብት ዘረፋ ጋር ተያይዞ በሚመጣ ግጭት ነው። በተለይ ሱርማዎች አርብቶ አደሮች በመሆናቸው ከከብት ዘረፋን እንደሚያዘወትሩና ይሄም ጉዳይ ብዙ ጊዜ ለግጭት ዳርጓቸዋል። የመኢኒት ጎልዲያ ወረዳ ሚኒሻ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ተፈራ ኮረዲ ውሃና የግጦሽ መሬት ፍለጋ የጸብ መቀስቀሻ መንገዶች መሆናቸውን ይናገራሉ "ሱርማዎች አይቀመጡም። ብዙ ጊዜ ሳርና ውሃ ፈልገው ይሄዳሉ። ወሃ ሲጠፋ ደግሞ ይገባሉ። እንዲህ እያሉ ወደ መኤኒት መጥተው ከብት ይዘርፋሉ::"[114] የአቶ ተፈራን ንግግር የሚያጠናክር መረጃ የሰጡኝ ደግሞ የመኢኒት ሻሻው ካሳ ናቸው "ከሌብነት ጀምሮ ከዚያ ወደ ሰው ህይወት ማጥፋት ደርሶ ያ አሁን በሽማግሌም ተብሎ ከሽማግሌ አቅም በላይ ሆኖ ወደ መንግሥት ሄዷል።"[115] ከዚህ በተጨማሪ ይሄንን ጥናት ሳካሂድ በመኢኒት ወረዳዎች በተለይ በመኢኒት ሻሻ በነበርኩ ጊዜ በሁለቱ ብሔረሰቦች መካከል ግጭት ተፈጥሮ የመንግሥት አካላት ግጭቱን ለማብረድ ከየብሔረሰቦቹ የአገር ሽማግሌዎች ጋር እየመከሩ ነበር።

በሁለቱ ብሔረሰቦች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ስር ሰድደው የከፋ ጥፋት እንዳያመጡ በሁለቱም ወገኖች ያሉ ኮሞሩቶች/ባላባቶች/ ወይም ታዋቂ የአገር ሽማግሌዎች ተመርጠው ለሁለቱም ገለልተኛ ቦታ የሆነና ከሁለቱም ብሔረሰቦች መኖሪያ ክልል ውጭ የሆነ ቦታ ላይ እንዲመጡ ይደረጋል። ብዙ ጊዜ የዲዚ ብሔረሰብ ከተማ የሆነችው ቱም እና ቤሩ ፣ የቤንች ከተማዋ ማጂ ተመራጭ ናቸው። በዕርቅ ሥርዓቱ ላይ በመኢኒት በኩል ከተገኙት ውስጥ የአገር ሽማግሌው የተገኙት አቶ ዋኖች ጃሻ የሚከተለውን ይላሉ። "በቅርቡ ጊዜ በ2003

[113] ከአቶ [illegible] ሚያዚያ 2003
[114] [illegible] መስከረም 2004
[115] ከአቶ [illegible] ሚያዚያ 2003

ተመርጨኤ ቱም ከተማ ሄጀ በስርማና በመኢኒት መካከል በተፈጠረው ጠብ አስታራቂ ሆኛለሁ። ቱም የዲዚ ብሄረሰብ ዋና ርዕስ ከተማ ነች። ለሁለቱ ብሄረሰብ የሚያማክለው ቱም ከተማ ነው እዚያ ነው የሄድነው።"[116] እንዲህ አይነቱን ጠብ ብዙ ጊዜ የሚፈታው መንግሥት ሲሆን በተጓዳኝ የሚሰሩም አካላት አሉ ከእነዚህ ውስጥ በአራቱ አጎራባች ብሔረሰቦች በዲዚ፣ መኢኒት፣ ስርናማና በቤንች መካከል የሚፈጠሩትን ግጭቶች በማብረድ ሥራ ላይ የሚሰራው ማርሲኮር የተሰኘ ድርጅትም ይጠቀሳል። "ማርሲኮር /ግጭት አስወጋጅ ኮሚቴዎች ናቸው/ በስርማና በዲዚ፣ በመኢኒት መካከል በሚፈጠር ግጭት ይሰራሉ"።[117]

ሁለቱ ብሔረሰቦች በጋብቻ ጥምር ይተሳሰራሉ። ይሁን እንጅ ሁሌም በሚነሱ የዘረፋ ወንጀሎች ነፍስ ይጠፋፋሉ። በ2003ዓ.ም. የተፈጠሩት ግጭቶች ጠንከር ያሉ ነበሩ። ከሁለቱም ወገን የሚወለዱትና በስርማ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግሥት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ አብርሃም ባርቡሌ በከብት ዘረፋ ተነስቶ በርካታ ነፍስ የጠፋበትን የብሔረሰቦች የግጭት አፈታት ሂደት እንደሚከተለው ተርከውልኛል።

> ግጭቱ ሲነሳ ከሁለቱም ወገን መበቃቀል ይኖራል። ስለዚህ የመንግሥት ኃይላት ግጭቱን ለማብረድ ለሁለቱም ብሔረሰቦች የጎሳ መሪዎችና የሃይማኖት አባቶች መልዕክት ይልካሉ። ከዚያም በመጡት ባላባቶች አማካይነት ውይይቱ የሚደረግበትን ቦታ ይመርጣሉ። የውይይት ቦታው ከተወሰነ በኋላ ውይይቱ እንዲካሄድ የተወሰነበት አካባቢ ባላባት የሚያስፈልገውን እንደ ምግብ፣ መጠጥና ማረፊያ ያሟላል። በስብሰባውም የመንግሥት አካላት ባሉበት ጸቡን ማን እንዳስነሳው የማጣራት ሂደት ይደረጋል። ጉዳዩን የሚያጣሩት ደግሞ ባላባቶቹ ናቸው። ከዚያም በባላባቶቹ የተበረፈ ንብረት እንዲመለስ ይወስናሉ። ውሳኔያቸውንም በሚመሩት ህዝብ ዘንድ ተግባራዊ ለማድረግና ዳግመኛም በጦር ላለማፈላለግ ከየብሔረሰቡ ባላባቶች በሚመረጡ ሦስት ሦስት ኮሞሮቶች የመሃላ ሥነ ሥርዓት ይካሄዳል። ማሃላው እንዲጸና ኮሞሮቶቹ የታረደውን ከብት ደም በመረማመድ ይሸጋገሩታል። በመቀጠል ድንጋይ በጦር በመውጋት ተማምለው ይለያያሉ። ኮሞሮቶቹ ወደየ ግቢታቸው ሲሄዱ መሃላቸው እንዲጠበቅና እንዲጸና ለህዝባቸው ይናገራሉ።[118]

በሌላ በኩል በሁለቱ ብሔረሰቦች መካከል የሚፈጠረውን ጸብ ለማብረድ ከባላባቶቹ ጋር ከፍተኛ ጥረት እያደረገ የሚሰራው ፖሊስ ነው። ፖሊስ ግጭቱን ለማብረድ ከኮሞሩቶቹ /ባላባቶቹ/ ጋር ጥረት ያደርጋል። ባላባቶቹን በማደራጀትና ውይይት እንዲያደርጉ፣ ህዝቦቻቸውን እንዲያረጋጉ

---

116 ቀሃገ፡ ሚያዚያ 2003
117 ነሲ፡ ሚያዚያ 2003
118 አብርሃም መብራቶም 2004

ያገባል። የመኢኒት ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ዋና ሳጅን አሸናፊ ቺሪዋሌ የኮሞሩቶቹን ሚና በተመለከተ የሚከተለውን ብለውኛል።

የአገር ሽማግሌዎቹ ከተመረጡ በኋላ ተሰብስበው የግጭቱን ምክንያትና የደረሰውን መጠን ይወያያሉ። ውይይቱ በአዳራሽ ውስጥ ወይም በአንድ ሰፊ የመወያያ ቦታ ላይ ሊሆን ይችላል። ከውይይቱ በኋላ በአገር ሽማግሌዎቹ አማካኝነት የተዘረፉ ከብቶች በህይወት ካሉ እንዲመለሱ ይደረጋል። በመቀጠልም ጥፋቱን ዳግመኛ ለላመፍጠር መሳሪያና ጦር በመያዝ የድንጋይ መውጋት ሥነ ሥርዓት ይደረጋል። የድንጋይ መውጋት ሥነ ሥርዓቱ የሚካሄደው ለጠብ የተማዘዙበት መሳሪያ ወይም ጦር ሰው እንዳይወጋ እና ህይወት የሌለውን በድን እንዲወጋ ለማመላከት ነው። በመጨረሻም እርድ ተካሂዶ ሊለያዩ ወደ መጡበት ቤሔረሰብ ተመልሰው ዳግመኛ ግጭት እንዳይነሳ ይመክራሉ። [119]

ይሁን እንጂ እንደ አስተዋዮቹ የመረጃ ሰጪዎቹ አባባል የመኢኒት ብሔረሰብ አባላት የኮሞቱቶቻቸውን ቃልና መሀላ አክብረው ራሳቸውን ከበቀልና ከዘረፋ ሲቆጥቡ የሱርማ ብሔረሰብ ግን ግድያና ከብት ዘረፋውን አላቆሙም።[120]

- በኮሞሩቶች ፊት የሚደረግ መሀላ

ሌላው ከግድያ ጋር ተያይዞ በጣም ከባድ ጉዳዮች በብሔረሰቡ ደረጃ ሲያጋጥሙም ኮሞሩቶች ተጠርተው መሃላ ያስምላሉ። በስውር የሚካሄዱ የግድያ ወንጀሎች ምንም አይነት ማስረጃ ስለማይቀርብባቸው ለመፍታትና ፍርድ ለመስጠት እጅግ አዳጋች ናቸው። እንደዚህ አይነቶቹ ስውር ወንጀሎች በቃልቻም እንደሚፈቱ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ጉዳዩ ከግለሰብ ጉዳይነት አልፎ የጎሳ፣ ከጎሳም አልፎ ብሔረሰባዊ መልክ ሲኖረው ኮሞሩቶች በጉዳዩ ይገባሉ።

በዚ ጊዜ በአንድ አካባቢ የሚፈጸምን ስውር ወንጀል ለማውጣትና እውነታውን ለማረጋገጥ የሚቻለው የኮሞሩቶችን እጅ እንዲመቱ ወይም /መሀላ እንዲፈጽሙ/ በማድረግ ነው። እንዲህ አይነት ወንጀሎች ሲሰሩና የአገሬው ሰው በጥርጣሬ ውስጥ ሲወድቅ ኮሞሩቶች ወደ አካባቢው እንዲጠሩ ተደርጎ በአካባቢው ያለው ሰው እና የተጠረጠሩ በሙሉ በኮሞሩቱ/ገዥናብ አውራጁ/ ፊት ቀርቦ የመሀላ መፈጸም ስነ ስርዓት ያደርጋል።

ሀገሩ መሰመር ሰርቶ እየመጣ ኮሞሩቱ በተቀመጠበት የክብር ቦታ ላይ ጉዳዩን ወይም ድርጊቱን አልፈጸምኩም ሲል የኮሞሩትን ሥም ጠርቶ እውነት ብሎ ይምላል። ምናልባት ጉዳዩን ለጊዜው ደብቆ ወይም ስውር ያለ ሰው ካለ የቱንም ያህል በልቡ ቢይዘው በኮሞሮቶች ፊት ሲቀርብ ጥፋቱን

[119] አቶ... ሚያዚያ 2003
[120] ቀሣ... ሚያዚያ 2003

እንደፈጸመ ይናገራል። ምክንያቱም ኮሞርቶች ንጹሃንና ለህብረተሰቡ ጠባቂዎች ጭምር ስለሆኑ እነሱ ፊት መዋሸትና መካድ ለቤሔረሰቡ አባላት ፈጽሞ አይሆንላቸውም። የመሀላው ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞ ጉዳዩን ፈጽሚያለሁ ወይም ድርጊቱን አድርጊያለሁ የሚል ሰው ከጠፋ/ ካልተገኘ/ ያ ጉዳይ ወይም ጥፋት ኮሞሩቱ በሚያስተዳድረው ግዛት ውስጥ እንዳልተፈጸመ ኮሞሩቱ በእርግጠኛነት ይናገራል። በዚህም አንዳች ጥርጣሬ አይገባውም። ኮሞሩቶችም በሚያስተዳድሩት ግዛት ህዝብ ፍጹም ታማኞቸው እንደሆነ ያምናሉ። በአጠቃላይ የመኢኒት ቤሔረሰብ ከላይ በተመለከትናቸው አይነት የግጭት አፈታት ሂደቶች ጉዋቶችን በመፍታት የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት ያስጠብቃል።

## 5. በአሁኑ ጊዜ በብሔረሰቡ ውስጥ በሥራ ላይ ያለው ግጭት ፈቺ ተቋም

በመኢኒት ቤሔረሰብ በአሁኑ ጊዜ በስራ ላይ ያለው የግጭት አፈታት ተቋም በውሉ የተለየ አይመስልም። ለከተማው ቅርብ በሆነበት እና የመሰረተ ልማት ዝርጋታ በጥቂቱም ቢሆን በደረሰባቸው አካባቢዎች ዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት በትክክል እያገለገለ ነው። ይሁን እንጂ ከከተማ በራቁትና ቆላማ በሆኑት አካባቢዎች ደግሞ የባህላዊው አስተዳደር ጠንክር ያለበት ሁኔታ ይስተዋላል። "ህዝቡ ሦስት አራተኛው መኢኒት የሚያምነውና የሚጠቀመው ባህሉን ነው።"[121] አቶ በድሉም ይሄንን የሚያጠናክር ነገር ይናገራሉ። "ከተማ ጥግ ላይ ያለው ዘመናዊ ሥርዓቱን ይጠቀማል። ሩቅ አካባቢ ያሉት ባህላዊ ሥርዓቱን በዋናነት ይጠቀማሉ።"[122]

ይሁን እንጂ አንዳንዶች ይሄንን ሀሳብ አይቀበሉም። እንዲያውም ዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት ዋና ነው የሚል አስተያየት አላቸው። "በድሮ ጊዜ ዝም ብለው ወደቃልቻ ነበር የሚሄዱት፤ በአሁኑ ጊዜ ግን ወደ ቀበሌ ይሄዱና እንደኛው ከካደ ማህበራዊ ፍርድ ሸንጎ ወደምታምኑት ቃልቻ ሂዱ ይሉና ይሄዳሉ።"[123] እንደ ቁልፍ የመረጃ አቀባዩ አባባል ሰዎች መጀመሪያ የሚሄዱት ወደ ዘመናዊ የፍትህ ተቋማት ነው። ከዚያ ደርሰው መፍትሄ ሳያገኙ በሚቀሩባቸው ጉዳዮች ላይ መፍትሄ ለማግኘት ግን እንደሚመጡ ይናገራሉ።

ለከተማው በቀረበው ክፍል በተለይ በመኢኒት ጎልዲያ ወረዳ ባሉ በርካታ ቀበሌዎች የባህል ፃይማኖት ተከታዮቻችን የሚመሩት ቃልቻው አወቀ ፎሮሽዋም የሚያረጋግጡት የባህል ጉዳዩ

121 [illegible] ሚያዚያ 2003
122 [illegible] ሚያዚያ 2003
123 [illegible] ሚያዚያ 2003

እየተዘዋወሩና እንዲያውም እነሱ ጋ ሰዎች ከመምጣታቸው በፊት ወደ መደበኛው የፍትህ ቦታ ጎራ እንደሚሉ ነው። በተለይ ቀደም ባለው ዘመን (ከኢህአዴግ በፊት) ለሚነሱ አብዛኞቹ ግጭቶች ህዝቡ የሚዳኘው በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት እንደነበር የገለጹት አቶ አወቀ፣ በተለይ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት በአካባቢው እየተስፋፋ በመምጣቱም ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ባህላዊ ሃይማኖታቸውን እየተው ወደ ዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት መሄድ እያዳበሩ መምጣታቸውን ይገልጻሉ።

ይሁን እንጂ አሁንም የባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ህብረተሰቡን እያገለገለ እንደሆነና ሰፊ ስራ እየሰራ እንደሚገኝ ሲገልጹ የሚከተለውን ብለዋል። "መጀመሪያ የሚሄዱት ቀበሌ አመራሮች ጋ ነው። ከቀበሌ አመራር አቅም በላይ ከሆነ ለወረዳ፣ ወረዳ ፍርድ ቤቱም ደግሞ ይሄ ነገር ማስረጃ የለውም ስለዚህ ሄዳችሁ በባህል ጨርሱት ብሎ የመለሳቸውን ነገር ነው። ምክንያቱም ከሀደት ነገር ስለሆነ ፆ ሰውዬ እስከመጨረሻው ድረስ እየካደ ስለሚሄድ ያንን ነገር ብቻ ነው የማስተናግደው።" አንዳንዶች ደግሞ ከዚህ የተለየ አስተያየት ይሰጣሉ።

ባህላዊ የፍትህ ተቋማቱና ዘመናዊው ተደጋግፈው እየሰሩ እንደሆነ ይገልጻሉ። ምክንያቱ ደግሞ የአንዳንድ ግጭቶች ባህሪም እንደሆነ ያብራራሉ። የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ በድሉ ካሳ የሁለቱን የፍትህ ሥርዓቶች ጠቀሜታና በስራ ላይ መሆን የገለጹት በሚከተለው መንገድ ነው። "አንዳንድ ጊዜ በባህሉ የፍትህ ሥርዓት የሚሄድ ነገር አለ። ለአንዳንዱ ደግሞ የሚሻለው በዘመናዊ የፍትህ ሥርዓቱ መሄድ ነው።"

ከተለያዩ አውራና ተባባሪ የመረጃ ምንጮቼ ለመረዳት እንደሞከርኩት፣ በተለይ የሰው ግድያን በተመለከተ የሚደረገው የእሻ ሥርዓት በጣም ሥር የሰደደና የጠነከረ ነው። 'ሰውን የገደለ ሰው ለእሻ ከፍ፣ እንዲት ልጃገረድና ሰባት ከብቶችን ይስጥ' የሚለው የቆየ ልማድ ጸንቶ እየኖረ ነው። በዘመን ኢህአዴግ ሴትን ልጅ ከከብት ጋር ደባልቆ ከመስጠት 'በምትኳ ሌላ ሰባት ከብት ይተካ' የሚለው አቅጣጫ ፈጽሞ የረባ ውጤት ያለማምጣቱም የሚያመላክተው የባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ጠንክሮ መዝለቁን ነው።

---

[illegible] 2009
[illegible] 2009

በአሁኑ ጊዜ ዋንኛ የፍትህ ሥርዓት የምንለው ሁለቱም ነው፡፡ አቶ ካሳ ዋንኛ የፍትህ ሥርዓቱና አይሉ የሚገኘው የባህሉ እንደሆነ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡ "ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ትንሽ መንግሥት ከሚሰራው ሥራ አይሉ ነው እየተገኘ ያለው፡፡ አንዳንዴ ስንሰራው እያመሰበ ያስቸግረናል፡፡ ምክንያቱም አካባቢው ያልተማረ ከመሆኑ የተነሳ በዚያ በባህሉ ነው አይሉ የሚገኘው፡፡"[illegible]

በተለይ በአሁኑ ጊዜ በተጨባጭ ያለው ነገር ሲታይ ከዘመናዊ ህግ ጋር ያለው አካሄድ ገና እንደሆነ የሚናገሩት ደግሞ የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ ፀጥታ አስተዳደር ኃላፊ የሆኑት አቶ ከበደ ኪርቴዶ ናቸው፡፡ "አሁን በተጨባጭ የተሻለው ከጠለፋ፣ ከግድያ፣ ከከባድ የአካል ጉዳት ጋር ተያይዞ ፍትህ እያገኘ ያለው ከዘመናዊ የፍትህ ሥርዓት ነው፡፡ ትናንሽ ነገሮችን ፀቦችን ግን በዚያው ይመጣሉ፡፡ "[illegible]

በአጠቃላይ ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው በመኢኒት ብሔረሰብ ዘንድ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት ከዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት ጋር በመተጋገዝ ሆኖ ህብረተሰቡን በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ በተለይ ደግሞ በአርብቶ አደሩ አካባቢ አሁንም ዋንኛ የፍትህ ሥርዓት በመሆን እንደቀጠለ ነው፡፡ በተንጻጻሪ ደግሞ ዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት በደጋውና ለከተሞች ቅርብ በሆነበት አካባቢ ዋንኛው ሥርዓት ነው፡፡

## 5.1 ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ሲታይ

የመኢኒት ብሄረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ረጅም ዘመን ያሳለፈ ቢሆንም ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር የራሱ ብርቱና ደካማ ጎኖች ይስተዋሉበታል፡፡ ቀጥሎ እነዚህን ብርታቶቹንና ድክመቶችን በዝርዝር እናያለን፡፡

- **ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ካሉት ጠንካራ ጎን**

ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ካሉት ጠንካራ ጎኖች ውስጥ የመጀመሪያው ጥቅም በስውር የተሰሩ፣ ምንም አይነት ማስረጃ የማይቀርብባቸው ወንጀሎችን በማጋለጥ ለተበዳይ ፍትህን መስጠቱ እና ጥቅምንም ማረጋገጥ መቻሉ ነው፡፡ ለምሳሌ

[illegible] ካሳ፡ ሚያዚያ 2003
[illegible] ከበደ፡ ሚያዚያ 2003

በ1990ዓ.ም. በመኤኒት ጎልዲያ ወረዳ ባቼማ ቀበሌ 02 ነዋሪ የሆነው ጋዴ ዲጋሳ በስውር ሰው ገድሎ በጥርጣሬ ታስሮ ነበር። ግን ወንጀሉን ስመፈጸሙ ምንም ማስረጃ ስላልነበረ ተጠርጣሪው ሲፈታ በአካባቢው ባለው ሺናፕ በተባለ ቃልቻ ተረገመ:: ተረጋሚው የኋላ ኋላ ሆዱ በማቤቱና ሊሞት በመድረሱ ግድያውን በስውር መፈጸሙንና ሌሎችም የስርቆሽ ተግባራትን ሲያከናውን እንደነበር ተናዘዘ። ይህም የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ የግጭት መፍቻ ተቋማት ከሆኑት ውስጥ የባህል ሀይማኖት /ቃልቻዎች/ ለማህበረሰቡ አባላት ፍትህንና ጥቅምን እያረጋገጡ እንደሆነ የሚያሳይ አንድ ማስረጃ ሲሆን ተመሳሳይና ተቀራራቢ የሆኑ ክስተቶች በተለያዩ የመረጃ አቀባዮቼ ነግረውኛል።

ከቀልና፡ የመረጃ አቀባዮቼ አንዱ የሆኑት አቶ ካሳም ይሄንኑ የሚያጠናክር ሀሳብ ይሰነዝራሉ:: "ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ከዘመናዊው የሚሻልበት መንግሥት የማይፈታቸው ነገሮች በባህል ሊፈቱ መቻላቸው ነው።"[illegible] ይህንን የአቶ ካሳን አባባል በተጨማሪ ማስረጃ ለማጠናከር ለአንድ ወንጀል ማስረጃ ካልተገኘ ወይም ደግሞ ምስክሮች ካልቀረቡ ወይም ደግሞ በሀሰት ለሚመሰከሩ ጉዳዮች ዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት ምንም ክፍተቱን የሚዘጋበት መንገድ እንደሌለው መረዳቱ በቂ ነው። በአንጻሩ ባህላዊው ግን ለህብረተሰቡ የተሻለና ጠቃሚ ሆኖ ይገኛል::

ማስረጃ የሌላቸውን ጉዳዮች ወደ ቃልቻ ዘንድ በመሄድ፣ ሰውየው በትክክል አልወሰድኩም ወይም አልገደልኩም ያለውን ነገር ዳኝቶና ረግሞ በሚቀጥለው ያ ሰውዬ ጉዳት ከደረሰበት በኋላ ወይም ጉዳት የሚያመጡ ነገሮች ሲገጥሙት በሰራው ስህተት ምክንያት የመጣበት ችግር እንደሆነ ያምናል። ችግሮቹ ደግሞ ሰፍተውና ጎልተው ከሱ አልፈው ለወዳጅ ዘመዶቹ እንደሚተርፉ ስለሚያምን፣ የሰራው ስራ የቱንም ያህል ከባድ፣ የቱንም ያህል አሳፋሪ ቢሆን ምህረትን ከመጠየቅና የዋሸበት ቦታ ሄዶ በውሸቱ መጸጸቱን፣ በሰራው ሥራ መጎዳቱን ከመግለጽና ይቅርታን ከመጠየቅ አይቦዝንም። ይቅርታውን ሲያገኝ ደግሞ የበደለውን ይከሳል:: ይሄንን ሁኔታ በሚገባ ከፈጸመ በኋላ ራሱን አረጋግቶና ከሞራልና ከስነ ልቡና ስቃዩ ተገላግሎ ከባለጋራው ጋር መተማመንን ፈጥሮ ኑሮውን ይቀጥላል:: በሌላ ወገንም ያለው ተበዳይ፣ ጥቃቱንና ጉዳቱን ለእምነት መሪው ከገለጸና እስምሎ ካስረገመ በኋላ፣ ጉዳዩን ከጭንቅላቱ አውጥቶ ባመነበት እምነት በማስረከብ አንድ ቀን ለሚያገኛት እውነቱ ታምኖ ከእህህታው ተላቆ ኑሮውን ይቀጥላል። በአስተርጓሚነት መረጃ ሲሰጡኝ የቆዩት አቶ ብርሃኑ የሚከተለውን

[illegible] ካሳ ሚሪሳ 2009

ይናገራሉ። "ቢቃልቻ መዳኘታቸው ጥሩ ነው። በእነሱ ዘንድ ማስረጃ የሌላው ነገር ይወጣል።"[129] ቀጣዩ ትረካ የዘመናዊ የፍትህ ሥርዓቱ የማይፈታቸውን ችግሮች የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ፍትሃዊ ሆኖ እንዴት መልስ እንደሚሰጣቸው የሚያረጋግጥ ነው።

በመኢኒት ጎልዲያ ወረዳ ጥቅምትሸት ቀበሌ ቶሞ የሚባለው ቃልቻ ዘንድ የተፈጸመ ታሪክ ነው። አንድ ሰው ሰው ገድሎ ዞን ላይ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲጠየቅ ወንጀሉን አልፈጸምኩም ብሎ ይከዳል። ማስረጃ ስላልነበረ ይለቀቅና ኑሮውን መኖር ይጀምራል። የሟች ቤተሰቦች ደግሞ በህጋዊ መንገድ ፍርድ ቤት ቀርበው ስለተረቱ በባህላዊ መንገድ እንሄዳለን ብለው ቶሞ ጋ ይሄዳሉ። ከዚያ ሰውየው /ገዳዩ/ ቶሞ ጋ ቀረበ። ቶሞ ጥያቄውን ሲያቀርብለት ወንጀለኛው አመነ። ተሞም ሦስት ምስክሮች አቁሞ ቃሉን ተቀበለና ፍርድ ቤት ከዶ ቶሞ ጋ በማመኑ በመጀመሪያ የገደለው እሻ ተከፈለ። ከዚያ በኋላ ቶሞ በሚኒሻ አሳጅቦ ከምስክሮች እና ከእምነት ቃሉ ጋር አድርጎ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይልከዋል። ከዚያ በኋላ በነፍስ ገዳይነት እስር ቤት ወረደ።[130]

ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ካሉት ጠንካራ ጎኖች ውስጥ ሁለተኛው የተበደለ እንዲካስ በማድረግ ቂምና በቀል እንዳይዛመት በማድረግ ፍትህንና ጥቅምን መስጠቱ ነው። በተለይ እንደ ግድያ አይነት ከባድ ወንጀሎች ሲፈጠሩ ተያይዞ የሚመጣው አለቀት፣ ውድመትና ጥፋት ከፍተኛ ነው። ይህንን ለማስቀረት ወንጀለኛው በሰራው ሥራ እንዲጠየቅ አድርጎ ቀሪው ማህበረሰብ ግን ወደ መበቃቀል እንዳያመራ በዳይና ተበዳይ በባህላቸው መሰረት ተማምለውና ተሸማግለው ሰላማዊ ኑሮ እንዲኖሩ ማድረጉና በካሳ ክፍያ ፍትህንና ጥቅምን ማረጋገጡ ነው።

ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ካሉት ጠንካራ ጎኖች ውስጥ ሦስተኛው የፍትህ አካላቱ ታማኝነት ነው። በራሱ ምርጫ የሚያምናቸውንና የሚያከብራቸውን ሰዎች በሽማግሌነት መርጦ 'እነሱ ይዳኙኛል፣ ፍትህ ያስጡኛል' ብሎ የቀረበ ባለጉዳይ በሽማግሌዎቹ የሚሰጠውን ውሳኔ ሲቀበልም ስለ ትክክለኛና ተገቢ ውሳኔያቸው ያለው ቦታ ትልቅ ነው። የሚያከብራቸውና የሚመሩት፣ ከፈጣሪ እንደተመረጡ የሚያምናቸው ሰዎች ጉዳዩን ሲያዩለት፣ ሲከራከሩለትና ሲወስኑለት ወይም ሲወስኑበት ውጤቱን ለመቀበል ብዙ

---

129 ቁርጥ፣ ሚያዚያ
130 በቀለ፣ ሚያዚያ 2009

አያሳግተውም። በድንበር መጋፋት የሚነሱትን ክርክሮችና ግጭቶች የሚዳኙለት ክርቀት የሚመጡና ባህሌን፣ አኗኗሬንና የቀደመ ድንበሬን የማያውቁ ናቸው ብሎ ስጋት አይገባውም። የአገር ሽማግሌዎቹም በስኑ ምግባራቸው የተመሰከረላቸውና ፍርድም የማያዛቡ እንደሆኑ ስለሚታመኑ የሚሰጡት ፍርድ ትክክለኛ ፍትህ እና ጥቅምን የሚያረጋግጡ ናቸው።

ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ካሉት ጠንካራ ጎኖች ውስጥ በአራተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው ለሁሉም የተደነገገው ሥርዓት የህብረተሰቡን አባላት በአንድነት የሚገዛና በሁሉም ደረጃ ተፈጻሚ መሆን መቻሉ ነው። በብሔረሰቡ አውቆም ይሁን በመጠጥ ላይ በሚነሳ ድንገተኛ ጸብ ሰው የገደለ ሰው ነፍስ አጥፍቷልና የሚክሰው በነፍስ ነው። ሰባት ከብቶችና አንዲት ልጃገረድ መስጠት አሻው ለዘመናት የተዳደረበት ህጉ ነው። በሌላም ግጭት በውድም ይሁን በግድ የሰው ሚስት ጋር ግንኙነት የፈጸመ ሰው ወንጀሉ አንጀት ውስጥ ተነበቦ ከተረጋገጠበት ሴቲቱን በደም ማጠቡና ባልየውን በሬ ሰጥቶ መካሱ የግድ ነው። ሁለቱም ወንጀሎች ሲፈጸሙ ፍትህ የሚገኘው በተቀመጡት ህግና ደንቦች በመሆኑና የሰው ማንነት ታይቶ ከፍም ዝቅም የማይሉ በመሆናቸው ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ፍትህና ጥቅምን በማረጋገጥ በኩል ከፍተኛ ጥንካሬ እንዳለው ያሳያሉ።

ከቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ አንዱ የሆኑት እና አራት የግድያ ጠቦችን በኮሞሩት አሻነት የመሩት አቶ ዋየቶ ጃሻ ወንድማቸውን ገድለው እስራታቸውን ከጨረሱና መላ ቤተሰባቸውን አሻ ከፍለው ከታረቁ ወይም ከካሱ በኋላ፣ ከቀሪ ወንድሞቻቸው ጋር በሰላም እንዲኖሩ ያደረጋቸው ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ነው። መደበኛው ፍርድ ቤት ተገቢውን እስር ፈርዶባቸው እስራቸውን ጨርሰው ወጥተዋል። ይሁን እንጂ ከማህበረሰቡ ጋር ለሚያደርጉት መቀላቀልና ለቀጣይ ሰላማዊ ህይወታቸው ምንም የሰጣቸው ዋስትና አልነበረም። ተመልሰው ወደ ቤተሰቦቻቸው፣ ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው ሲደባለቁ የጠበቃቸው መገለል ነው። ይሁን እንጅ ለዚህ ሁሉ ችግር ሰላማዊውንና ፍትሃዊውን መፍትሄ የሰጣቸው የባህላዊው ሽምግልና ነው። ዋየቶ አሻ ሲከፍሉ ከእላቸው ውጪ መላ ቤተሰቡ ከሚች ወገን አብሮ ነው የጠበቃቸው። ይሄ የመገለላቸው ውጤት እና በዘመናዊ የፍትህ ሥርዓት ያገኙት ቅጣት ለማህበረሰባዊ ህይወታቸው ዋስትና ያለመሆኑ መገለጫ ነው። አሻውን ከከፈሉ በኋላ ግን እንደቀድሞ ኑሯቸው ሰላማቸውንና ደህንነታቸው ተጠብቆ የጋራ ኑሯቸውን ከዘመዶቻቸው ጋር እንዲኖሩ አስችሏቸዋል። ይኼ ምሳሌ የሚያረጋግጠው የባህላዊውን ሽምግልና ፍትህዊነትና ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን ሞራላዊ፣ ማህበረሰባዊና ሥነ ልቡናዊ ጥቅም ነው። እንዲህ አይነቱን ፋይዳ

አስመልክቶ Uten የሚከተለውን ይላል። "የአፍሪካ ህዝብ ባህሉን እጅግ ያከብራል። ባህላዊ ተሳትፎው ከጥልቅ ስሜት፣ ከከፍተኛ ፍቅርና ከልባዊ ቀረቤታ የሚመነጭ ነው ይህም ባህላዊ ተነሳሽነትና ውስጣዊ ስሜት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሄ ለማፈላለግ ከፍተኛ ሚና አለው።"[131]

- ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ያለው ደካማ ጎን

ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ከላይ የተዘረዘሩት ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም የራሱ የሆኑ ደካማ ጎኖችም አሉት። እነሱንም በዝርዝር ስናይ የመጀመሪያው ፍትህንና ጥቅምን ለማረጋገጥ ተነስቶ ፍትህንና ጥቅምን መልሶ የሚረግጥ መሆኑ ነው። አንድ ሰው ሰው ከገደለ በካሳነት የምትሰጠው ልጃገረድ ናት። ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ነፍስ ጠፍቷል፣ ወንጀል ተሰርቷል አጥፊው መቀጣት አለበት ብሎ የሚሰጠው ፍርድ ሴት ልጅ ሴት ብቻ ሆና በመፈጠሯ ያለምንም ጥፋቷ ደም ማድረቂያ እንድትሆን በመስዋዕት በግነት ማትረብ ነው። ገዳይ በተራ ምክንያት ወይም መጠጥ ላይ በሚነሳ ግጭት ሰው ሲገድል ይችላል። ጥፋቱ የሚያመጣውን ችግርም በመረዳት ለሟች ወገኖች በዘመዶቹ ጥረትና ርብርብ ካሳና ልጃገረዷን ከሰጠ በኋላ እሱ የራሱን የተደላደለ ኑሮ ሲኖር እሷ በደመኞቿ ቤት እንድትኖርና ለከፋ ስቃይ እና እንግልት እንድትጋለጥ ያደርጋታል። አቶ ወልደየስ ሴትን ልጅ በካሳነት መስጠት የባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ድክመት እንደሆነ ተገቢም አለመሆኑን በመግለጽ የሚከተለውን ሀሳብ ያቀርባሉ። " ልጃገረድ የመከፈሉ፣ የሰው ነፍስን ያህል ነገር እንደ እቃ ቆጥሮ በዚያ ይከፈል የማለቱ በጣም ይከብዳል። ከህግ ጋርም ሲነፃፀር ወንጀል ነው" [132]።

የመረጃ አቀባዩ ወ/ሮ ዶኒያ ኮንኩላይ ወንድሟ በገደለው ሰው በአሻነት ተከፍላ ለበርካታ ዓመታት እሷ በችግር ስትማቅቅ እሱ የራሱን የተደላደለ ህይወት እየኖረ እንደሆነ ገልጻልኛለች። ይሄም ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ፍትህንና ጥቅምን በማረጋገጥ በኩል ያለበትን ሰፊ ድክመት የሚያሳይ ነው። ጥፋቱን የሠራውና የገደለው ሳይሆን መከራውን እየተቀበሉ ያሉት ያለበደላቸው የፍትህ ሥርዓቱ ቀንበሩን የጣለባቸው ልጃገረዶች ናቸው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ /በኢህአዴግ ዘመን/ በአንዳንድ የመኢኒት ጎልድያ ቀበሌዎች ዘንድ፣ የገደለ ሰው ሴትን ልጅ ለአሻ ሥርዓት በካሳነት ከሚሰጥ ይልቅ በሴቷ ምትክ ተጨማሪ ሰባት ከብቶች ጨምሮ

---

131 ዝኒ ከማሁ

132 ወልደየስ፡ ሚያዚያ 2003

የካሳ ክፍያው በአስራ አራት ከብት እንዲያልቅ እየተደረገ ነው። ይህኛውም አካሄድ ፍትህና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር የራሱ ሰፊ ክፍተት እንዳለው መረዳት ይቻላል። አስራ አራት ከብቶችን ለካሳንት ለመስጠት የሚጠይቀው የኢኮኖሚ አቅም የብሔረሰቡን አባላት የሚፈትን መሆኑ አይቀርም። አቶ ካሳም ይሄንን የሚደግፍ ሀሳብ ይሰነዝራሉ። ". . . አስራ አራት ከብትም በገንዘብ ሲሰላ ወደ ሃያ ሺ እና ሰላሣ ሺ ሄደ ማለት ነው። ይሄም መቅረት አለበት የሚል ሃሳብ አለኝ"[133]።

ከዚህ ሌላ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ፍትህንና ጥቅምን በማረጋገጥ በኩል ያለበት ሁለተኛው ትልህ ድክመት በካሳ ስም ወንጀሎች ተድፈንፍነው እንዲቀሩ ማድረጉ ነው። አንድ የራሱ ያልሆነችን ሴት የመድፈር ወንጀል የፈጸመ ሰው ጥፋቱን ካመነና ሴቲቱን በደም ካጠበ፣ እንዲሁም ለባሏ ካሳ ከከፈለ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ የጣለውን ቅጣት ፈጽሟልና አይጠየቅም።

የመረጃ አቀባዩ አቶ መልኬ፣ በመኤኒት ጎልዲያ ወረዳ ጥቅምትሸት በተባለ ቀበሌ፣ ግባው የተባለ ሰው አንዲት ሴት ደፍሮ የነበረውን የእርቅ ሥርዓት እንደሚከተለው ገልጾታል። ". . . ከዚያ አንድ ጊደር ለባልየዋ ካሳ ሳከ። አንድ በግ አምጥቶ በዱላ ቀጠቀጠና ደም ሲወጣ፣ የቆጮ ቅጠል መሀል ላይ ተሰንጥቆ የሴትየዋ አንገት ላይ ተደርጎ በላዩ ላይ ደሙ ፈሰሰ። ከዚያ በኋላ ሴትየዋ ወደ ቤቷ ተመለሰች"[134]። እንዲህ አይነቱ የፍትህ ሥርዓት ውሳኔ አስገድዶ መድፈር በወንጀል የሚያስቀጣ መሆኑን ወደ ጎን የሚጥልና የሴቷን ጥቅሞችና ፍትህ በማረጋገጥ በኩል ትልህ ድክመት ያለበት እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነው። አንዲት ሴት በኃይል ስትደፈር የሚደርስባት የኃይል ጥቃት መኖሩ አይቀርም። ያለ ፍላጎቷ እየተደፈረች ነውና የሚደርስባት የስነ ልቡናና የሞራል ድቀት የረጅም ጊዜ ስቃይዋ እንደሚሆን አያጠራጥርም። ማንነቷ፣ ስብዕናዋ እንዲሁም የሰብዓዊነት ክብሯ ጭምር ይረጋገጣሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከኃይል ጥቃቱ፣ ከሥነ ልቡና ድቀቱ፣ ከሞራል መላሸቁ በተጨማሪ ለተለያዩ በሽታዎች መጋለጥም ሊያጋጥማት ይችላል። በተለይ የልጅቷ እድሜ እና አካላዊ ማንነት የጥቃት መጠኑን የበለጠ ከፍና ዝቅ ሊያደርገው ይችላል። አንዲት ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች ሴት አካሏ የሚደረግባትን የወሲብ ጥቃት መቋቋም ካልቻለ እንደ ፊስቱላ ላሉት ከባድና አስቃቂ በሽታዎች ልትጋለጥ ትችላለች። በተለይ በብሔረሰቡ መገኛ ሁለት ወረዳዎች በመኤኒት ጎልዲያና በመኤኒት ሻሻ ወረዳዎች ውስጥ የጤናና የትምህርት ሽፋን ካለመኖሩ የተነሳ የሴቷ በህክምና መረዳት

133 ካሳ፣ ሚያዝያ 2009
134 መልኬ፣ ሚያዝያ 2009

አለመቻል ጥቃቷና ጉዳቷ የእድሜ ልክ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ይሄንን ሁሉ ችግሮች መርምረን የመድፈር ወንጀል ማለት ከፍተኛ ጥቃት መሆኑን ስንረዳ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ የሚያሳልፈው ቅጣትም ይሁን ቅጣቱን ተፈጻሚ አድርጎ በካሳ ስም መስማማት ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱን በዚህ በኩል ያለበትን ድክመት ያሳያል፡፡ የመኢኒት ሻሻ ወረዳ ነዋሪ የሆኑት አቶ ካሳ ይሄንን አካሄድ እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡ "ሚስት ለባሏ መደፈሯን ስትናገር ባል ለሽማግሌዎች ሄዶ ይናገራል፡፡ ከዚያ ኮሞሩቶች ይልካል፤ ከደፋሪው ጋር ሲስማሙ አንድ ፍየልና አንድ በሬ ያመጣል፡፡ በፍየሉ ደም ያጥባታል፡፡ ከደፋሪውም ጋር ይታረቃሉ፡፡ ደፋሪው ከዚያ ወደ ህግ አይቀርብም"[136] ፡፡ ወንጀለኛ ካሳ ከፍሎና እርቅ አውርዶ፤ ሳጠፋው ጥፋት ተመጣጣኝ ቅጣት ካላገኘ በፍትህ ሥርዓቱ ላይ ፍትህንና ጥቅምን በማረጋገጥ በኩል የሚታይ አንድ ደካማ ጎን ነው፡፡

ባህላዊው የፍትህ ሥርዓቱ ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ካሉት ደካማ ጎኖች ውስጥ ሦስተኛው የካሳ ክፍያውን መስጠት የቻለና ኢኮኖሚያዊ አቅሙ የጠነከረ ሰው ላይ የሚያመጣው የጠነከረ ፍትህና ጥቅም አለመኖር ነው፡፡ የሰው ሚስት የደፈረ ሰው ሽማግሌዎች ልኮ በአንድ በሬና በአንድ በግ መስዋዕትነት ጉዳዩ የሚጠናቀቅ ከሆነና በወንጀል የማያስጠይቅ ከሆነ በርካታ ከብቶች ያለው ሰው ወንጀሉችን ለመስራት የሚያግደው ያለ አይመስልም፡፡ ከዚህ አንጻር ደፋሪው በህግና በወንጀል የማይጠየቅ ከሆነ ጥፋቱን ለመቆጣጠርና ለማረም ያለው እድል አናሳ ሆኖ የሚታይ ይመስላል፡፡

በአጠቃላይ የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ከላይ የተዘረዘሩት ጥንካሬዎችና ድክመቶች ይታዩበታል፡፡

## 5.2 መደበኛው ፍርድ ቤት ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ሲታይ

መደበኛው ፍርድ ቤት ከባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ይልቅ የተሻለ አገልግሎት በመስጠት ፍትህንና ጥቅምን የሚያረጋግጥበት በርካታ ጉዳዮች አሉት፡፡ መደበኛው የፍትህ ሥርዓት ፍትህንና ጥቅምን ከማረጋገጥ አንጻር ካሉት ጠንካራ ጎኖች ውስጥ የመጀመሪያው በተጨባጭ ማስረጃ ላይ በመመስረት ጥፋተኛን ለፍርድ ማቅረቡ ነው፡፡ አንድ ሰው ሰውን ቢገድል ወይም

[136] ካሳ ሚሬሳ 2008

አንዲት ሴት 'ተደፍሬያለሁ' ብትል ተጠርጣሪው ጉዳዩን ለመፈጸሙ በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርቶና አስፈላጊም ሲሆን የምስክሮችን ቃል በማዳመጥ ውሳኔ መስጠቱ ነው፡፡ ይሄም አንድ ተጠርጣሪ ጉዳዩን ፈጽሞታል ከሚል ተቀራራቢ ግምትና በማመን ላይ ከተመሰረተ ውሳኔ በመጠበቅ ለበዳዩም ይሁን ለተበዳዩ ወገን ትክክለኛ ፍትህና ጥቅምን ለመስጠት ያስችላል፡፡

የመደበኛ ፍርድ ቤት ፍትህንና ጥቅምንም የማረጋገጥ ሁለተኛው ጥንካሬው ማንም ይሁን ማን ወንጀል እስከሰራ ድረስ የህግ ተጠያቂ ማድረጉ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በካሳ ክፍያ ስም ተድፈንፍነው በዚያው የሚያልቁ ወንጀሎች እንዳይኖሩ ያደርጋል፡፡ አንድ ሰው በሰራው ወንጀል በህግ የማይጠየቅ ከሆነ ተጨማሪ ወንጀሎችን የማይሰራበት መንገድ የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በጥፋቱ ያልተቀጣ ከስህተቱ የሚማርበት እድል አይኖረውም፡፡ በመኢኒት ብሔረሰብ ሰው የገደለ ሰባት ከብቶችና ልጃገረድ በካሳነት ለሟች ወገኖች ከከፈለ እንዲሁም የሰው ሚስት አስገድዶ የደፈረ፣ እሷን በደም አጥቦና ለባሏ ካሳ ከከፈለ፣ ጉዳዩ የውሽን ስም ያነሳ ውሸ ይሁን እንደሚባለው ተረት ስለ በደልና ጥቃቱ ሳያነሱ አጥፊውም ሳይቀጣ በዚያው ይቀራል፡፡ መደበኛው ፍርድ ቤት ግን የገደለም ይሁን የደፈረ በወንጀሉ እንዲጠየቅ ስለሚያደርግ ፍትህንና ጥቅምን በማረጋገጥ በኩል የጎላ ድርሻ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በመኢኒት ብሔረሰብ አንድ ግድያ ሲፈጠር አጥፊው ራሱን በሚደብቅበትና በሚሸሽግበት ጊዜ የገዳይ ወገኖች እሱን ባያገኙም የገዳይ ወገን የሆኑ ሰዎች ላይ ጥቃት ማድረስና ንብረት ማውደምም ይፈጽማሉ፡፡ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ሽማግሌዎች በመሀል ገብተው የበቀል ጥቃቱን እስከሚያስቆሙ ድረስ የሚወድመውን ንብረትና ጥፋት የሚያስመልስትና በወንጀልነት የሚጠይቅበት መንገድ የለም፡፡ ነገር ግን በመደበኛው ፍርድ ቤት እንዲህ አይነቱ የበቀል እርምጃ ተገቢ ያልሆነና መልሶ አድራጊውን በወንጀል የሚያስጠይቀው በመሆኑ የገዳይ ወገኖች ከእንዲህ አይነቱ የበቀል እርምጃ እንዲቆጠቡና የህይወትም የንብረትም ውድመት እንዳይደርስ በመከላከል ገዳይ በወንጀሉ እንዲጠየቅ አድርጎ የገዳይ ወገኖችን የህይወትና የንብረት ደህንነትን በመጠበቅ ፍትህና ጥቅምን በማረጋገጥ ጠንካራ ሚና ይጫወታል፡፡

ፍትህንና ጥቅምን በማረጋገጥ በኩል የመደበኛው ፍርድ ቤት ሦስተኛውና ዋናው የጥንካሬ ማህያ የሴትን ልጅ ሰብአዊ መብት ማረጋገጥ መቻሉ ነው፡፡ በመኢኒት ብሔረሰብ የግድያ ጸብ በእርቅ የሚደመደመው ሰባት ከብቶችን ከልጃገረድ ጋር ቀላቅሉ በመስጠት ነው፡፡ ይሁን እንጅ ልጃገረዲቱ በተሰራው ጥፋት ውስጥ ምንም የሰራችው ስህተት የለም፡፡ የመኢኒት ጎልዲያ ወረዳ ነዋሪ የሆኑት ዋየች ጃጓ ታናሽ ወንድማቸውን በመጠጥ ተገፋፍተው ስለገደሉ ለመታረቂያነት

ውሳኔንት የሰጡት የገዛ ልጃቸውን እንደሆነ ነግረውኛል። ዶጊያ ኮንኩላይ በአስር ዓመቷ ለአሻንት የተሰጠችውና ህይወቷ ከአስር ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ በስቃይ፣ በመከራና በሀዘን ውስጥ እንዲሆን የዳረጋት ወንድሟ በጦር ሰው ስለገደለ ነው። የዱማ ዳሽ ቀበሌ በዋሪ የሆኑት አቶ ጥጋቡ መጠጥ ቤት በጦር የወጋቸውን ሰው በጦር ወግተው ስለገደሉ አሻ የሰጡትና እርቅ ያወረዱት ሴት ልጃቸውን በመስጠት ነው። የእሳቸው አባትም ተገድለው አራስ ልጅ በአሻንት ተሰጥቷቸው ልጅቷ ለረጅም ዘመን የእሳቸው ካሳ እየተባለች እንዳለች ነግረውኛል። የቢያጌሊች መንደር ነዋሪ የሆኑት አቶ ይፋይ ጸንጎ ልጃቸውን የገደለባቸው ሰው እድሜዋ ከአምስት ዓመት ያልበለጠ ልጅ በአሻንት ሰጥቷቸውና ካሳ ተቀብለው እያሳደጉ እንደሆነ በመስክ ቆይታዬ በግቢያቸው ተገኝቼ አይቻለሁ። በአጠቃላይ በመኢኒት ብሔረሰብ ያለው ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት ሴትን ልጅ እንደ አንድ መገልገያ ቁጥሮ በካሳነት መከፈል ሲሆን መደበኛው ፍርድ ቤት ግን ይኼንን በማስቀረት ወንጀል የሰራው ሰው በህግ እንዲጠየቅ ስለሚያደርግ ፍትህንና ጥቅምን በማረጋገጡ በኩል የተሻለ ደርሻ እንዳለው ማየት ይቻላል።

በአጠቃላይ ስናየው ዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት የሰው ልጆችን ሰብዓዊ መብት እንዲከበር፣ በተለይ የሴቶች መብት እንዳይጣስ የሚያደርግና ዘረፋን፣ ግድያን ጨምሮ ዙሪያ መለስ ግጭቶችን ማስወገድ ስለሚችል ለማህበረተሰቡ ፍትህን በመስጠትና ጥቅምን በማረጋገጥ በኩል የተሻለ ይመስላል።

## 5.3 መደበኛ ፍርድ ቤት እና ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ያላቸው ትብብር

ሁሉም የሚፈጠሩ ግጭቶች በአንድ አይነት የፍትህ ሥርዓት ተስተናግደው መፍትሄ ያገኛሉ ማለት እንደማይቻል ከሚፈጠሩ የግጭት አይነቶችና ምክንያታቸው መረዳት ይቻላል። በመሆኑም የፍትህ ሥርዓቱን የተሟላ አድርጎ የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት በተሻለ ሁኔታ አሟልቶ ለመገዝ የሚፈጠሩ ግጭቶችን እንደ ባህሪያቸው መፍታት ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር ማስረጃ የሌላቸው፣ በድብቅ የተፈጸሙ ግድያዎችና የገንዘብና የንብረት መካካዶች በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት የሚፈቱ ከሆነ ውጤቱም ጥሩ ይሆናል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ የግጭት አፈታት ወቅት፣ ወንጀል መሆናቸው የሚረጋገጡ ጉዳዮች ሲገኙ ጉዳዩን ለመደበኛው ፍርድ ቤት አሳልፎ መስጠት ይኖርበታል።

በሌላ ጎኑ ማስረጃ ያላቸውና ወደ ህግ መቅረብ የሚችሉ ጉዳዮች በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ቢዳኙ የተሻለ ይሆናል።

በመኤኒት ቤሔረሰብ ግጭቶችን በመፍታት ባህላዊው የፍትህ ሥርዓትና ዘመናዊው /መደበኛው/ የፍትህ ሥርዓት የማይተካኩ ሚና ስላላቸው ሁለቱም የየራሳቸውን አገልግሎት እያበረከቱ ነው። ከዚህም የተነሳ አንዱ የአንዱን ክፍተት በመሙላትና በመደጋገፍ ስራዎችን እየሰሩ ነው። የጋራ ዓላማቸው የህብረተሰቡን ደህንነት ማስጠበቅ መሆኑ የመጀመሪያ የመደጋገፊያ መንገዳቸው ነው። ስለዚህም በዋናነት በብሔረሰብ ጠብ / አሁን በተጨባጭ ከሱርማ ብሔረሰብ ጋር/፣ በሰው ግድያ /ነፍስ በማጥፋት/ እንዲሁም ማስረጃ በማይቀርብባቸው ወንጀሎችን ላይ በጋራ እየሰሩ ነው።

ትብብሩ ማዕከል የሚያደርገው የግጭቶችን አይነት እንደሆነ ደግሞ አቶ ካሳ ይናገራሉ "አንዳንድ ጊዜ በባህሉ የፍትህ ሥርዓት የሚሄድ ነገር አለ፡፡ ለአንዳንዱ ደግሞ የሚሻለው በዘመናዊ የፍትህ ሥርዓቱ መሄድ ነው።"[136] የሚፈጠሩት የግጭት አይነቶች የሚፈቱበት የየራሳቸው ስርዓትና አግባብ እንዳላቸው በርካታ ተመራማሪዎች የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡ የግጭቶቹን የአፈጣጠር ሰበብ፣ የተጋጭዎቹን ሁለንተናዊ ማንነት ማየትና ለመፍትሄውም ተገቢውን አቅጣጫ ማስቀመጥ ይሞክራሉ። በቃልቻነት የሚታወቁት አቶ አወቀ ፎሮሸዋ ከመንግሥት ጋር ተስማምተው የሚሰሩበትን አግባብ ሲያስቀምጡ የሚከተለውን ብለዋል፡፡ "እኛ ተግባብተን እንሰራለን መጀመሪያ የሚሄዱት ቀበሌ አመራሮች ጋ ነው፡፡ ከቀበሌ አመራር አቅም በላይ ከሆነ ለወረዳ፣ ወረዳ ፍርድ ቤቱም ደግሞ 'ይሄ ነገር ማስረጃ የለውም ስለዚህ ሄዳችሁ በባህል ጨርሱት' ብሎ የመለሳቸውን ነገር ነው።"[137] የአወቀን አባባል የሚያጠናክሩት ሌላው ሰው ታዋቂው የአገር ሽማግሌ ኮምሩት አሼው ሲሚንቶ ሲማቻ ናቸው፡፡ "ፍርድ ቤቱ ከባህል ጋር የተሳሰረውን ወደኛ ይልካል። እኛም ወደዚያ የምንልከው አለ፡፡"[138] የመኤኒት ጎልድያ ወረዳ ፀጥታ አስተዳደር ኃላፊ አቶ ከበደ ደግሞ ትብብር መኖሩን ሲገልጹ "ባህላዊና ዘመናዊ የፍትህ ሥርዓቶች በትብብር ነው የሚሰሩት። አንድ ላይ ተቀናጅተን እየሰራን ነው፡፡"[139] ብለዋል፡፡ የቅንጅቱን አይነት ደግሞ የወረዳው ፖሊስ አዛዥ ዋና ሳጅን አሸናፊን እንዲህ ይገልጹታል፡፡ "ከየሥስት ወር ግንኙነት እናደርጋለን። የፀጥታ ፎረም አለን የሃይማኖት መሪዎች ምን

---

[136] ካሳ፣ ሚያዝያ 2009
[137] አወቀ፣ ሚያዝያ 2009
[138] ሲሚንቶ፣ ሚያዝያ 2009
[139] ከበደ፣ ሚያዝያ 2009

መስራት እንዳለባቸው ለህግ ጉዳዮችን እንዴት እንደሚያቀርቡ እንወያያለን። የጎሳ መሪዎች ጋር እየተወያየን እየሰራን ነው። "[140] አሸናፊ መደበኛው የፍትህ ተቋም እና ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት ተቋም ቢጋር እየሰሩ ያሉበትን አካሄድ ለማሳየት እንዲያስችል አስራ አምስት ዓመታትን ሙሉ ተድፈንፍኖ የኖረ ወንጀልን በማጋለጥ የባህላዊው የፍትህ ሥርዓት የዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት አጋር መሆኑን እንዴት እንዳሳየ የሚከተለውን ታሪክ በዋቢነት ያስቀምጣሉ።

> አንዱ ግርሻቤና ቀበሌ ውስጥ ሰው በድብቅ ገድሎ ይቆያል። የሟች ወገኖችም ሰዋቸውን ማን እንደገደለው ባለማወቃቸው አስረግመው ዝም ይላሉ። በዚያ ግዛት በየትኛውም ቦታ በድብቅ ወንጀል ቢሰራ ሺ ቤንች የሚባለው ቦታ ወዳለው ታዋቂ ቃልቻ ጋ ሄደው ነው የሚያስረግሙት። እናም ገዳዩን ማንም ይሁን ማን በሉው አስረገሙት። ሰውዬውን ገድሎ 15 ዓመት የቆየው ሰው በቅርቡ በ በ2002 ዓ.ም ወደ ቃልቻው ጋር መጣ። እናም ያ ሰውዬ ከሽማግሌዎች ጋር መጥቶ ወንጀሉን እንደሰራና ሰውዬውን እንደገደለው ለቃልቻው ነገረው። ቃልቻውም ወንጀልህን ካመንክ ያንተ ዘሮች ካሳውን ይክፈሉ አንተ እጅህን ለመንግሥት ስጥ ብሉ ከሽማግሌዎች ጋር እያያዘ ወደኛ ላከው። ገዳዩም ወጥቶ እጁን ሰጠ። የእሱ ዘመዶችም እሻውን ከፈሉ።[141]

ከላይ እንደምንረዳው የሁለቱም የፍትህ ሥርዓቶች መደጋገፍ የሚያመጣውን የተሻለ ውጤት ነው። አንድ የግድያ ወንጀል ቢፈጠር ግጭቱን ፈጥኖ ለማብረድና ዘላቂ የሆነና በመተማመን ላይ የተመሰረተ እርቅ ለማውረድ ሁለቱም የፍትህ ሥርዓቶች የማይተካካ ሚና ይኖራቸዋል። በግድያው ሳቢያ የሚቀሰቀሰውን የመበቃቀል መንፈስ ለማስወገድና ወንጀለኛውን በሰራው ወንጀል ለመዳኘት መደበኛ ፍርድ ቤት መቅረቡ ተመራጭ ነው። በዚያው መጠን ደግሞ የገዳዩ መታሰር ወይም ለህግ መቅረብ ብቻውን በቀሪ ወገኖች ላይ የሚፈጠረውን የበቀል ስሜትና ደም የመመለስ ቁጣ ለማብረድ በባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ መዳኘት ያስፈልጋል። ኮሞሩት አሻው ሲሚንቶ ሲማቻ የሁለቱ የፍትህ ሥርዓቶች የትብብር መንፈስና አስፈላጊነትን እንደሚከተለው ይገልጹታል። "ኬኦ/ሥጫሌ እስከ ደርግ ባለው ሥርዓት ሰው የገደለ ወንጀለኛ አይታሰርም። ኢህአዴግ ከገባ ግን የገደለ ሄዶ ይታሰር እናንተ ግን ብቀላ እንዳይዛመት በባህላችሁ ፈጽሙ እያለ ከጎናችን ስለሚሰለፍ እኛ በዚያው አይነት እየቀጠልን ነው ያለነው። እሻ ካልተከፈለ ብቀላ አለ ስለዚህ እሻ ከፍለን ብቀላው ይቀራል።"[142] ሲሚንቶ እንደሚያስረዱት ወንጀለኛው በጥፋቱ

---

[140] አሸናፊ፣ ሚያዚያ 2009
[141] አሸናፊ፣ ሚያዚያ 2009
[142] ሲሚንቶ፣ ሚያዚያ 2009

ሲጠየቅ የበቀል ጦር ከሟች ወገኖች እንዳይሰነዘር የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ መኖር አስፈላጊ መሆኑን ነው።

ዘላቂ ሰላም ለማውረድ ለዘመናት በቆየው ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት አሻው መከፈል ይኖርበታል። አሻ ከተከፈለና የሟችና የገዳይ ቤተሰቦች በመካከላቸው የተነሳውን ውጥረት መርገቡን የሚያበስረውን አንጀት በጥርስ ይዞ በጦር የመበጠስ ድርጊት ከተከናወነ፣ እንዲሁም የአንድነት ምልክት የሆነውን የማሽላ ገንፎ እና ጠሩ የወረደበትን በግ ሥጋ ቀላቅለው በአንድነት ከተመገቡ፣ በስተመጨረሻም የምንፈላለግበት ጦር ሰው ሳይሆን ድንጋይ ይውጋ ብለው ከማሉ በኋላ በቀሪ ዘመዶቻቸው መሀል የተነሳው መበቃቀል ይወገዳል።

ኮምሩት አሼው ዋየች ጃጃ ፊላቸውን እንደ አንድ ምሳሌ ያቀርባሉ። እሳቸው ወንድማቸውን ገድለው መደበኛው ፍርድ ቤት እስር ወስኖባቸው ዓመታትን ቆይተዋል። በሰሩት ወንጀል የተወሰነባቸውን ፍርድ ጨርሰው ሲመጡ ገዳይ ናቸውና የበቀል እርምጃ እንዳይወሰድባቸው በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት አሻ ከፍለው በመተማመን ላይ የተመሰረተ እርቅ አውርደው በሰላም መኖራቸው የሁለቱ ሥርዓቶች የትብብር ውጤት እንደሆነ ይገልጻሉ።7 ዋየች በአንዱ የፍትህ ሥርዓት ብቻ ተዳኝተው ቢሆን ኖሮ ውጤቱ የተለየ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። በባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ብቻ ጉዳያቸው ቢታይ ባጠፉት ጥፋትና በሰሩት ወንጀል የማይቀጡ ሲሆን በዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት ብቻ ታይተው ቢሆን ኖሮ እስራታቸውን ጨርሰው ወደ ማህበረሰቡ ሲቀላቀሉ የበቀላ ጦር የማይቀርላቸው ይሆናል። በሁለቱም የፍትህ ሥርዓቶች የገቡበትን ግጭት መፍታት በመቻሉ በወንጀላቸው ተቀጥተው ባጠፉት ነፍስ ካሳ ሰጥተው ሰላም አውርደዋል።

በመሆኑም ቢፈረስበ አንድ ግድያ ተፈጸሞ አሻ እንዲከፈል እርቁ ከተጀመረ በኋላ የሚጠናቀቀው ልጃገረዷ ለሟች ወገኖች ስትሰጥና ቀሪው የእርቅ ስኑ ሥርዓት ከተከናወነ በኋላ ነው። በተለይ ልጃገረዲቱ እና ቀሪ ከብቶችን በሚረካከቡበት ሰዓት የሟችና የገዳይ ወገኖች ከወገዝ ወይም ከሸጥ ማዶና ማዶ የሚቆሙ በመሆኑ የሟች ወገኖች እልህና ንዴት እንዲሁም የበቀል ስሜታቸውም ኃይለኛ ይሆናል። አንዳንዶቹ የሟች የቅርብ ዘመዶች በተለይ ታላቅ ወንድም ወይም ሟች ልጆች ካሉት እየተንደረደሩ ለመምጣት ይጋበዛሉ። በእንደዚህ አይነቱ የአሻ እርቅ ሥኑ ሥርዓት ላይ ፖሊስና የአካባቢ የጸጥታ ኃይላት በመገኘት ከፍተኛ የማረጋጋት ሥራ ይሰራሉ። በዚህም የአገር ሽማግሌዎች ደም እንዳይዛመትና መበቃቀል

እንዳይኖር ሲሰሩ የመንግሥት ኃይላት ደግሞ የእርቁን ሥነ ሥርዓት በሰላም እንዲካሄድ የበኩላቸውን ጥረት ያደርጋሉ።

በሚያዝያ ወር 2003 ዓ.ም፤ በባዙም ዜማ ቀበሌ ግጭት ተከስቶ የግድያ ወንጀልን በማረጋጋት ላይ የተሳተፈው የፖሊስ ባልደረባው መኮንን፤ ከሽማግሌዎቹ ጋር እንዴት እንደተባበሩ፣ ተጋጩዎቹ እልህ ውስጥ ሲገቡ የማረጋጋትና እሻው በሰላም እንዲጠናቀቅ እንዲሁም የሟች ወገኖች ዘረፋ እንዳይፈጽሙ በማድረግ መስራቱን እንደሚከተለው ገልጾልኛል።

> ባዙም ዜማ ቀበሌ ላይ የእሻ ሥርዓቱ ሲካሄድ ሲል እኛ /ፖሊሶች/ ጸጥታውን ለማስከበት ተልከን ሄድን። የእሻ ሥነ ሥርዓቱ በሚካሄድበት ቦታ ደርሰን ከሽማግሌዎቹ ጋር ከተነጋገርን በኋላ እሻው የሚከፍልበት ቦታ ሰዓት ሲደርስ የመጡት የሟች ዘመዶች መሳሪያ አለማያዛቸውን አረጋገጥን። ጦር ይዞ የሚመጣ ቢገኝ ጥቃት ለመሰንዘር ስለሚመቸው የኛ ስራ ጦርና ስለት ይዘው እንዳይቀርቡ ማድረግ እና የሥነ ሥርዓቱን ሰላም መጠበቅ ነበር። እናም ሥነ-ሥርዓቱ በሰላም ሲጠናቀቅ እኛም ተመለስን። [143]

ከመኮንን ገለጻ የምንረዳው ፖሊስ የግድያ ወንጀሎች ሲፈጠሩ ተያይዞ የሚቀሰቀሰው የበቀል ርምጃ እንዳይስፋፋ የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ የሚያደርገውን የእርቅ ሂደት እገዛ ነው። መኮንን በሌላ ግድያ ጠብ የእሻ ሥርዓት ላይ ተገኝቶ ያጋጠመውንና የሟች ወገኖች የወሰዱትን የበቀል እርምጃ ወደ ህግ በማድረስ ያከናወኑትን እንደሚከተለው ገልጾልኛል።

> የእሼው ድርድር ሲካሄድ የሟች ቤተሰቦች ተራምደው ጉዳት እንዳያደርሱ ሽማግሌ የማደራጀትና የሟች ቤተሰብን የማረጋጋት ስራ እንሰራለን። ህግና ጸጥታውን ለማስከበር ትጥቅ ይዘን ነው የምንሄደው። የሟች ወገኖች ስሜት ውስጥ ገብተው አደጋ ለማድረስ ሊሉ እንጠብቃለን። አንዴ ዱግ ቀበሌ ላይ "ካይዲኮር" የተሰኙ ትልቅ ታዋቂ ሰው በጦር ተወግተው ሞተው የሳቸው ልጆች ቀጥታ ሮጠው የገዳይ ቤተሰቦችን ዘርፈው ሁለቱም ልጆች ከስምንት በላይ ወረዳ ድረስ ሄደው ለአንድ ሳምንት ታስረው ተመልሰው እሼው ተከፍሏል።[144]

ከሰው መግደልና በስወር ከተፈጸሙ ወንጀሎች በተጨማሪ አልፎ አልፎም ቢሆን በሌሎች የግጭት ማስወገድ ጉዳዮች ላይም ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ እና ዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት ትብብር ያደርጋሉ። በዚህ ዘርፍ ከሚጠቀሱት ውስጥ የድንበር መጋፋትን በተመለከተ የሚነሱ ጠቦችን ሽማግሌዎች እንዲዳኟቸውና ውሳኔ እንዲሰጡባቸው መደረጋቸው ነው። ታዋቂው የአገር ሽማግሌ ሌላ በሉኮሮይ ፍርድ ቤት አንዳንዴ የድንበር መጋፋት ጉዳይን ጭምር

---

[143] መኮንን ሚያዚያ 2003
[144] መኮንን ሚያዚያ 2003

ሄዳችሁ በአገር ሽማግሌ ጨርሱ ብሉ እንደሚመልስና እንደሚልክላቸው እነሱም ዳኝተው ውጤቱን ወደ ፍርድ ቤት እንደሚልኩ እንደሚከተለው ገልጸውልኛል፡፡

> ጉዳዩ የተፈጸመው በግምት የባሬ ሁለት ዓመት አካባቢ ነው፡፡ እዚሁ ቢያጌሊች ቀበሌ ሦስት ሰዎች በድንበር ተጋጭተው ነበር፡፡ ሰዎቹ ስማቸው አንደኛው ባይሉዳኝ ሽምበሌ፣ ሁለተኛው ሜሉ ካርበዳ ሲሆን ሦስተኛው ደግሞ ገሴ ሴላ ነው፡፡ ፍርድ ቤት ሄደው ሲካሰሱ ድንበሩ በአገር ሽማግሌዎች ይታይና መልሱን ይላኩልን ብለው ጉዳዩን ወደኛ ላኩት፡፡ ከዚያ ሽማግሌ ሆኜ ተመርጬ እቦታው ድረስ ሄደን አየን፡፡ 'ድሮ የኔ ቦታ ይሄ ነው፣ የኔ ቦታ ይሄ ነው' ብለው ተባባሉ፡፡ ከዚያ እኛ ድንበሩን አይተን 'በዚህ ቀጥታ ቢሆን አይሻላችሁም ወይ? እንደዚህ ቢሆን ትስማማላችሁ ወይ?' ብለን ወሰንን፡፡ እነሱም እናንተ ካላችሁ እሺ ብለው አስማምተናል፡፡ እኛም እስከ ወረዳ ድረስ አስማምተናል ብለን መልስ ጽፈናል፡፡[145]

በአጠቃላይ መረዳት እንደሚቻለው በመኢኒት ብሔረሰብ ውስጥ ባህላዊና ዘመናዊው የፍትህ ስርዓት እየተደጋገፉና እየተመካከሩ አገልግሎት ላይ መሆናቸውን ነው፡፡ ግጭቶች ሲከሰቱ ከህገ መንግሥት ጋር በማይጋጭ አትጣጫ ትብብር እያደረጉ እንደሆነና መዋቅራዊ ግንኙነት እንዳላቸው በአጽንኦት የገለጹልኝ አሸናፊ ቺሪቋሌ ናቸው፡፡ "ግጭቶች ሲፈጠሩ ከህገ መንግሥት ጋር በማይጋጭ አትጣጫ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት መሪዎችና ታዋቂ የሆኑ ግለሰቦችን ይዘን ሽማግሌዎችን ታች ድረስ አዋቅረን ችግሮችን እየፈታን ነው፡፡"[146] ይሁን እንጅ በሁለቱ አካላት መካከል ያለው የግጭት አፈታት ጥምረት ገና በእንጭጩ ያለ ነው፡፡ ጅምሩ ጥሩ የሚባል አይነት መሆኑን ግን መናገር ይቻላል፡፡ ወንጀል የፈጸመ ወደ ህግ እየቀረበ በቀሉ እንዳይቀጥል የቀሩት ወገኖች ስምምነት እያደረጉ መቀጠላቸው የሚደገፍ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ትብብሩና የጋራ ስራው የብሔረሰቡን አካላት ያዳረሰ አይደለም፡፡ የተደረጉ በርካታ ውይይቶችና ስምምነቶች የጠነከረ ለውጥ ገና አላመጡም፡፡ አሁንም ድረስ አብዛኛው አርብቶ አደር የሚተዳደረው በባህሉ ነው፡፡ ሴት ልጅ በአሻ መከፈሏ ቀርቶ በከብቶች ይለወጥ የሚለው ሀሳብ ከሦስት ቀበሌዎች ውጭ ተፈጻሚ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ትብብሩ ሩቅ መንገድ የሚቀረውና ህብረተሰቡ ጋር ለመድረስ ትግል የሚጠይቅ ነው፡፡

---

145 ሴት፣ ሚያዚያ 2003

146 አሸናፊ፣ ሚያዚያ 2003

## 5.4 ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ለመደበኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ያለው አስተያየት

ለረጅም ዓመታት በኖረና ጸንቶ በቆየ ልማድ ላይ አንድ አዲስ አስተሳሰብ ብቅ ሲል ሁለቱን አዋህዶ ለመጓዝ ወይም ሁለቱንም ጎን ለጎን ለማስቀጠል የሚገጥመው ፈተና ቀላል አይሆንም። በፍትህ ሥርዓትም ላይ በባህላዊውና በአባት አደሩ ሥርዓት መካከል የሚኖረው አንድነትና ልዩነትም የሚገለጸው በህብረተሰቡ ውስጥ በሚኖራቸው ሁሉን አቀፍ መስተጋብር ነው። ለዘመናት በጸናውና ቤጠበቀው በባህላዊ የፍትህ ሥርዓት ለኖረው የመኤኒት ብሔረሰብም በቅርቡ ብቅ ያለው /ከባህሉ አድሜ አንጻር/ የመደበኛ ፍርድ ቤት አሰራሩ ቶሎ የሚዋሀድ ሆኖ አልተገኘም። ይሁን እንጅ ከጊዜ ጊዜ፣ ከአደር አደር ሁኔታዎች መቀያየራቸውና አዲሱም እየሰፋና እየጎለበተ አንዳንድ ጊዜ እየተጋጨ ሌላ ጊዜ እየተዋሀዱ መቀጠላቸው አይቀርም።

እንደ ቀልፍ የመረጃ አቀባዮቹ ከሆነ ባህላዊው የፍትህ ስርዓት የዘመናዊውን ፍርድ አልቀበልም ወይም አይሆንም ያለበት አጋጣሚ እንደማያስታውሱ ገልጸውልኛል። ይሁን እንጅ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት የዘመናዊ ፍርድ ቤት የወሰነውን የመሻር እና አልቀበልም የማለት መብት እንደሌለው ከበደ ይናገራሉ። ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት የመደበኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ የመሻር መብት የለውም።[147] ባህላዊው የፍትህ ሥርዓቱ ህልውናውን ጠብቆ ሊቆይ የሚችለው የአገሪቱ ገዥ ህግ የሆነውንና የህጎች የበላይ የሆነውን ህገ መንግሥት እስካከበረና የሚቃረን ሀሳብ እስካላመጣ ድረስ መሆኑን ቆና ሳጅን አሸናፊም ይጠቅሳሉ። ከዚህ አንጻር መረዳት የምንችለው ባህላዊው የፍትህ ሥርዓቱ የዘመናዊውን የፍትህ ሥርዓት ወይም የመደበኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን የመሻር አቅም እንደሌለው ነው።

ታዋቂው የአገር ሽማግሌውና በርካታ ሽምግልናዎችን በማሸማገል የረጅም ዓመት ልምድ ያላቸው የመረጃ ምንጬ ኮምሩት አሻ ሴላ በሉኮሮይ መንግሥት የወሰኑትን ውሳኔ ሽሮባቸው እንደማያውቅና እነሱም የሻሩት የመንግሥት ውሳኔ እንደሌለ ገልጸው፣ እንዲያውም በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት የሴጡትን የእሳቸውን ውሳኔ ትክክል አይደለም በማለት ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ይዞ የሄደ ባለጉዳይ ውሳኔያቸውን ማሻር እንዳልቻለና መደበኛው ፍርድ ቤት ውሳኔያቸው ትክክል መሆኑን እንዳጸናላቸው እንደሚከተሰው ገልጸውልኛል።

---

[147] ከበደ ሚሬሳ 2003

> ጉዳዩ የተፈጸመው ከሁለት ዓመት በፊት ነው /2001ዓ.ም/ ። አንዱ ሰው አንዲቷን አግብቶ በሥጉ ሥርዓት እየኖረ ነበር። ከዚያ አንድ ልጅ ከወለደች በኋላ እንደ አጋጣሚ በእግዚአብሔር ሞት ትሞታለች። ከዚያ ጥሎሽ የከፈልኩት ይመለስ ብሎ አሸማገሉኝ ብሎ እኛ ጋር ይመጣል። እኛም ይሄንን አናውቅም በባህላችንም የለም። እኛ የምናውቀው ሚስት ያልወለደች ከሆነ ሲያገባት የጣለላት ጥሎሽ ይመለሳል። የወለደች ከሆነ ጥሎሽ አይመለስም አልንና ውሳኔ ሰጠን። ሰውዬው ግን ትክክል አይደለም የጣልኩት ይመለስልኝ ብሎ ድርቅ አለ። እኛም ይሄንን እንግዲህ ፍርድ ቤት ይፍታው ብለን ከሳሹንና የሚስትየዋን አባት ሁለቱን አያይዘን ፍርድ ቤት ላክን። ፍርድ ቤት ስንልክ ፍርድ ቤቱ ትክክል ናችሁ ብሎ አጸናልን። የወሰናችሁት ትክክል ነው ብሎ መልሷል። ከዚያ ውጪ እስከአሁን እኛም የሻርነው የለም እሱም የሻረው የለም። [148]

ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት የመደበኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ የመሻር መብት የለውም የሚለውን የአቶ ከበደን አባባል አንዳንድ የመረጃ ምንጮቼ ጥያቄ ውስጥ ይከቱታል። እንዲያውም መረጃዎቼ እንደሚያረጋግጡት ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት የዘመናዊውን የፍትህ ሥርዓት ውሳኔ አሳማኝ በሆነ መልኩ ያስቀየረበት አጋጣሚ መኖሩን ነው። ለማስረጃ ከሚቀርቡት ትርክቶች ውስጥ አንዱ ታዋቂው የሃይማኖት መሪ አወቀ ፎርሽዋ ያጋጠማቸው ነው። አንድ ሰው ባልሰራው ስራ በሀሰት ተመስክሮበት ወንጀለኛ ተብሎ አምስት ዓመት ከተፈረደበት በኋላ ቃልቻው በሀሰት የመሰከረውን ሰው ረግመውት እሱም ከሦስት ዓመት በኋላ ችግር ሲደርስበት ተመልሶ መጥቶ በሀሰት መስክሮ ሰው እንዳሳሰረና የግድያ ወንጀሉን የፈጸመው እራሱ መሆኑን ገልጾላቸዋል። የኋላ ኋላ ጉዳዩን የሰማው የቡኑ ፍርድ ቤት አወቀ ቃላቸውን እንዲሰጡ አድርጎቸው ሰውየው መግደሉን እንዳመነ ተናግረው በሀሰት የተፈረደበት ሰው ከእስር ተፈትቶ ነፍሰ ገዳዩና በሀሰት መስክረው ወደ ወህኒ መውረዱን የቃሰረው ደግሞ መፈታቱንንና ነጻነቱን ማግኘቱን እንደሚከተለው ነግረውኛል።

> በ1994 ዓ.ም ነው። አንደኛው ወንድምዬው የተገደለው ሻሪያ ቀበሌ ነው። ገዳዩ ያለው ጉማ ቀበሌ ውስጥ ነው። በመጀመሪያ ሁለቱ ሰዎች አብረው እዚህ ጨበራ ከተማ ላይ ጠጥተው ይሄዳሉ። ሁለት ወንድና አንድ ሴት ያቺ ልጅዋን አዝላለች። አንደኛው ገፍትሮ ሲጥል ከኋላ ተከትሉ የነበረው ሰውዬ ጃኬቱን ያወልቅና ይሄኛውን ይገፈትራል-ይወድቃል። ከዚያ ወደ ቤቱ ሄዶ ይቆይና ማታ ላይ ጦሩን ተቀብሎ ደፈጣ ያደርግና ጃኬቱ ነጭ በመሆኑ ብቻ ሌላውን ሰው ልክክ አድርጎ ገደለው። ያሰበው ሳይሆን የሞተው ሌላ ሰው ይሆናል። የሟች ወገኖች ልጃቸውን መገደል በሰሙ ጊዜ ለበቀል ይነሳሉ። ይሄም ሰው ራሱ ገድሎ ልጄን የገደለው መጀመሪያ የተጣላው ሰው ነው ብሎ ይመሰክራል። ከዚያ ያልገደለው ሰውዬ ገለሃል ተብሎ ባላወቀው ምክንያት ተያዘ። በዚህ ጊዜ

---

[148] ሌላ፣ ሚያዚያ 2003

ገድለሃል የተባለው ሰው ከሰውየው ጋር ተጣልተው እንደነበር አምኖ በፍጹም እንዳልገደለ ቢናገርም የሚያምነው አልተገኘም። በዚያ ላይ ይጠላው የነበረው ሰው፣ ሰውዬውን በጦር ወግቶ የገደለው ሰው ገድሏል ብሎ ምስክርነቱን ስለሰጠበት መደበኛው ፍርድ ቤት የምስክሩን ቃል ማስረጃ በማድረግ በሀሰት በተያዘው ሰው ላይ የአምስት ዓመት እስራት ፈረደበት። ፍርዱ ከተሰጠ በኋላ ሰውዬው እስር ቤት ገባ። ቤንች ማጂ ዞን ሚዛን ከተማ ማረሚያ ቤት ነው የታሰረው።

ልጃቸው ሰው ገድሏል በመባሉ ምክንያት አባቱም እናቱም ተቸገሩ። ሌላ እልቂት እንዳይፈጠርም አሻ ከፈሉ። ይሁን እንጅ ቤተሰቦቹን ጠርቶ 'አባካችሁ ሄዳችሁ ቃሌቸው አውቀ ፎርሽዋ ጋ እርገሙ እኔ አላደረኩም። ባላደረኩት ነገር እናንተም ተሰቃይታችኋል እኔም እዚህ ጋር ተሰቃይቻለሁ። አባካችሁ እዚያ ጋ ሄዳችሁ ተኙና ተገዘቡለሉ። ባደረኩት ነገር እናንተም ብትሰቃዩ ችግር የለም። እኔም ብሰቃይ ችግር የለም። ግን እኔ ያላደረኩት ነገር ስለሆነ ያ ቃልቻ እውነትን ያውጣልን' ብለው መጡ። እኔ ጋር መጥተው እንዲረገም አደረጉ። እርግማኑ ተካሂዶ ጥቂት ዓመታት አለፉ። ሰውዬውም በሀሰት እንደታሰረ ጊዜው አመለጠ።

ከዚያ በተራገምን በሦስት ዓመታት ውስጥ የገዳዩ ቤተሰብ ሦስት ልጅ በአንዴ ከዚያም አራተኛና አምስት ልጅ በተከታታይ ሞቱበት። በዚህ ጊዜ ያ በሀሰት መስካሪው የሰራው በደል እንደመጣበትና እርግማኑ እንደደረሰ አወቀ። ከዚያም ወደ እኔ መጥቶ 'ከዚህ በፊት በስህተት እከሌ ነው የገደለው ያልኩት ውሸት ነው። እኔ ነኝ የገደልኩት። በሀሰት የመሰከርኩበት ያ ሰውዬ ለሟች ወገኖች በአሻ የከፈላቸው ሰባት ከብቶች በአጠቃላይ ይመለሱ፣ በአሻ የሰጧትም ልጅ ትመለስለት እኔ ልከፈል። ልጆቼ ሞተውብኝ ከሚያልቁ ከፍዬ ብድን ይሻላል' ብሎ ነገረኝ።

እኔም ጉዳዩን ከሰማሁ በኋላ እንዳለው እንደገና የነዚያ ምትክ ከብቶች ቀጥታ ለታሰረው ሰው ቤተሰቦች ተከፈሉ። በአሻነት የጠሰጠችው ልጅ በህይወት ስላለች እሷም ተመለሰች ። የዚህ ሰውዬ ጉዳይ ቀስ በቀስ ወሬው አገር አዳረሰ። ቤተሰቦቹም ጉዳዩን እንደገና እንዲታይላቸው ጠየቁ ። ጉዳዩ ወረዳውን አልፎ እስከ ዞን ድረስ ተሰማ።

ከዚያም ድንገት ከዞን አንድ ደብዳቤ ደረሰኝ። ደብዳቤው ከሚዛን ከተማ ከከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የመጣ ነው። የተጠየኩት ሰውዬው እኔ ጋ ተረግሞ እንደነበረና አሁን በሀሰት መመስከሩን ማመኑን በግልጽ እንዳብራራ ነው። እኔም ስለተጠራሁ ሚዛን ከተማ ሄድኩና ቃሌን ሰጠሁ። ሰውዬው በሀሰት ሰው ወንጀሉ እንዳላስረና ገዳዩ እራሱ እንደሆነ መናገሩንና ማመኑን አስረዳሁ። ሰውዬውም አሁን ያመነው ርግማኑ ስለደረሰበት እንደሆነ አብራራሁ ። ከዚያ በኋላ እውነተኛ ገዳዩና በሀሰት መስካሪው ተይዞ ሄዶ እስርም ገባ። ያኛው ሰውዬም ነጻ ወጣ። [illegible]

[illegible] አበበ፡ ሚያዚያ 2003

የቃልቻው አወቀ ፎርሸዋ ትረካ የሚያስረዳው መደበኛው ፍርድ ቤት የምስክር ቃል ስለሰማ ብቻ አለበደሉና ያስሰራው ሰው እንዳሰረ ነው። በሀሰት ገድለሃል ተብሎ የተወነጀለው ሰው ከህግ በላይ መሆን ስላልቻለ መደበኛው ፍርድ ቤት የቆረጠለትን የእስር ትዕዛዝ ለመቀበል ተገዷል። በዚህም የተነሳ ለሥጋ ልቡና እና ለሞራል ጉዳትም ተዳርጓል። መደበኛው ፍርድ ቤት ስለፈረደበት ሊጎናጸፋቸው የሚገቡ መብቶቹ ሁሉ ተነፍገው ወንጀለኛ ተብሎ ተሰቃይቷል። ቤታሰረባቸው ዓመታት ሁሉ ሊያከናውናቸው የሚገቡ የህይወት ግቦቹ በጠቅላላ ተኮላሽተዋል። በአንጻሩ በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ተስፋ ያጣው ታሳሪ ትክክለኛ ፍትህ ለማግኘት ቤተሰቦቹን ወደ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት እንዲሄዱለት ተማጽኗል። በመደበኛው ፍርድ ቤት ያጣውን ፍትህና ነጻነት በአባት አደሩ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት ለመጎናጸፍ ጥሯል። አንድ ቀን እውነት እንደምትወጣና ነጻነቱን እንደሚጎናጸፍ ያመኑት ታሳሪውና ቤተሰቦቹ ፍትህን ለማግኘት ያደረጉት ጥረት የኋላ የኋላ ፍሬ አፍቶላቸዋል። ከሦስት ዓመታት በኋላ እንኳን መደበኛው ፍርድ ቤት የወሰነውን ፍርድ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ውሳኔውን አስቀይሮላቸዋል።

ባህላው የፍትህ ሥርዓቱ የመደበኛውን የፍትህ ሥርዓት ውሳኔ በማስቀየሩ በኩል ከላይ የተጠቀሰውን አይነት ተጨማሪ ማስረጃዎች ከተባባሪ መረጃ አቀባዮቼም ጭምር አግኝቻለሁ። ዋና የመረጃ ምንጮቼ ከሆኑት ውስጥ የመደበኛው የፍትህ ሥርዓት አካል የሆኑት የወረዳው ፖሊስ አዛዥ አሸናፊ ይሄንን እውነት ለማጠናከር የሚከተለውን ገጠመኝ ነግረውኛል።

"በሀሰት የሚመሰክሩ ሰዎች አሉ። ተበዳዮች ደግሞ ውሳኔው ትክክል አይደለም ሲሉ ቃልቻዎች ጋር ሄደው ያስረግጣሉ። በኋላ እርግማኑ ሲደርስ በሀሰት የመሰከሩት ሰዎቹ ወደ ቃልቻ ሄደው ባለፈው ቀርቤ የመሰከርኩት በሀሰት ነው። እከሌ አልሰረቀም ወይም ያንን ነገር አላደረገም ብለው ይናገራሉ። በዚህ ጊዜ የንብረት መመላለስ ሁሉ ይደረጋል።"[150]

አሸናፊ፣ ቃልቻው አወቀ ፎርሸዋ ጋ እንደ አጋጠመው አይነት ተመሳሳይ ሁኔታዎች እንደሚፈጠሩ ካብራሩ በኋላ በተለይ መደበኛው የፍትህ ሥርዓት በውሳኔ የሰጣቸው ንብረቶች ጭምር በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት በኩል አልፎ አልፎ ቢሆንም እንኳን እንደሚለወጡ ተኪታዩን ታሪክ በመንገር ያስረግጣሉ።

---

[150] አሸናፊ፣ ሚያዝያ 2003

> በ1999 ዓ.ም የመኢኒት ጎልዲያ ወረዳ ዋና ከተማ የሆነችው ባቱማ ውስጥ አንድ ከብት ወደ ጓልቀባ ቀበሌ ተሰርቆ ይሸጣል። ከዚያ ከተማ ውስጥ ያለ ትልቅ ሰው ነው ፍርድ ቤት ሄዶ ሰውየው እንደሆነ መስክሮ ከዚያ በኋላ ሰውየው ውሣኔውን ከተቀበለ በኋላ ንብረቱ ወደ ሌላው ሰው እንዲሄድ ይደረጋል። በኋላ ተጎጂና ባለንብረት የነበረው ሰው ጥቅምትሽት ቀበሌ /ሺ. ቤንች መረዳ ውስጥ/ ወዳለው ቃልቻ ሄደው ያመለክታሉ ። እሳቸውም መስካሪውን ጠርተው ከብቱ የማን እንደሆነ ሲጠይቁት 'እኔ የመሰከርኩት ሀሰት ነው ብሎ' ይናገራል። በዚህም የተነሳ የቀድሞው ውሳኔ ተሽሮ ከብቱ ለቀድሞ ባለቤት የተሰጠበት ሁኔታ አለ።" [151]

በተግባር ከተፈጸሙት ጉዳዮች የምንረዳው መደበኛው ፍርድ ቤት የምስክሮችን ቃል አዳምጦ ውሳኔዎችን ቢሰጥም ውሳኔዎቹ ሁሌ ትክክልና ፍትሃዊ ናቸው ማለት እንደማይቻልና ፍርድ ተበይኖባቸው ወህኒ የወረዱ ሰዎችም በትክክል አጥፊና ወንጀለኞች ላይሆኑ እንደሚችሉ ነው። እናም ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት የመደበኛውን የፍትህ ሥርዓት ውሳኔዎች እያስለወጠ ትርጉም ያላቸው ስራዎችን እየሰራ መሆኑን ነው።

## 5.5 መደበኛው ፍርድ ቤት ለባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ውሳኔ ያለው አስተያየት

መደበኛው ፍርድ ቤት የባህሉን ውሳኔ የሚሽርበት አጋጣሚዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚያመላክቱ ገለጻዎች ከመረጃ አቀባዮቹ ተሰንዝረዋል። ". . . ከህገ መንግሥት ጋር በማይጋጭ አቅጣጫ. . ."[152] የሚለው የመኢኒት ጎልዲያ ፖሊስ አዛዥ ዋና ሳጅን አሸናፊ ገለጻም የሚሰጠው ቀጥተኛ ትርጉም ይሄን ይመስላል። ይሁን እንጂ የመረጃ አቀባዮቹ በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ውሳኔ ስጥተው የተሸረበትን የሚያስታውሱት ጉዳይ አላገኘሁም። ከዚያ ይልቅ የወሰኑትን ውሳኔ እንዲያጸድቁላቸው ታዋቂ የአገር ሽማግሌ የሆኑት ሲላ ገለጸውልኛል።

> ቢጋቢቻ መካከል ላይ አንድ ሰውዬ አግብቶ ነበር ከዚያ አንድ ልጅ ከወለደች በኋላ እንደ አጋጣሚ በእግዚአብሔር ሞት ትሞታለች። ከዚያ ጥሎሽ የከፈለኩት ይመለስ ይላል። እኛም ይሄንን አናውቅም እኛ የምናውቀው

---

[151] [illegible]፣ ሚያዚያ 2003
[152] [illegible]፣ ሚያዚያ 2003

ያልወለደች ከሆነ ጥሎሽ ይመለሳል። የወለደች ከሆነ ጥሎሽ አይመለስም አልን። ይሄንን እንግዲህ ፍርድ ቤት ይፍታው ብለን ሁለቱን አያይዘን ፍርድ ቤት ስንልክ ፍርድ ቤቱ ትክክል ናችሁ ብሎ አጸናልን። የወሰናችሁት ትክክል ነው ብሎ መልሷል። ከዚያ ውጪ እስከአሁን እኛም የሻርነው የለም እሱም የሻረው የለም።[153]

ነገር ግን ምንም እንኳን ጥሩ ሊባል የሚችልና ፍትሃዊ የሆነ የፍትህ ውሳኔ በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ቢተላለፍ ከህገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ውጭ ወይም ተቃራኒ ሆኖ ቢገኝ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችልበት መንገድ ያለ አይመስልም። John ይሄንን ጉዳይ በሚከተለው መልክ ይገልጸዋል። " ህገ መንግሥታዊ መፍትሄዎች አልፎ አልፎ የሚተገበሩ ይሁኑ እንጂ ግጭትን ለሌላ ጊዜ ከማስተላለፍ የዘለለ ሚና የላቸውም[154]።

ለማጠቃለል ያህል በሁለቱም የፍትህ ሥርዓቶች ውስጥ የሚሰጡ ውሳኔዎች በአሳማኝ ምክንያቶች የመለወጥ ካለባቸው የሚለወጡበትን እድል ዝግ ላለማድረግ የሚያስችል አካሄዶች መኖር ይኖርባቸዋል።

## 6. በመኤኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት ሥርዓት ላይ የተደረገ አጠቃላይ ትንተና

በዚህ ርዕስ ስር የመኤኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት የተመሰረተባቸው ማህበራዊ እሴቶች ምንነት፣ የሥርዓቱ ብርታቶችና ድክመቶች ምንነት፣ ሰዎች ወደ ስርዓቱ ጉዳያቸውን ይዘው የሚሄዱበት መሰረታዊ ምክንያት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቱ ማህበራዊ ሰላምን ከማስጠበቅ አንጻር ያለው ፋይዳ፣ የባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ከጊዜ፣ ከቦታና ቢሮክራሲን ከማስቀረት አንጻር ያለው ተመራጭነት፣ እንዲሁም ሥርዓቱ ለአረጋውያን፣ ለሴቶችና ለህጻናት የሰጠውን ቦታ ተዘርዝረዋል።

[153] [illegible] 2009
[154] Burton, 1988,38

## 6.1 የባህላዊ የፍትህ ሥርዓት ማህበራዊ እሴቶች

መኢኒት ብሔረሰብ ለዘመናት ጠብቆ ያቆያቸው የራሱ የሆኑ ማህበራዊ እሴቶች አሉት፡፡ እነዚህ እሴቶች ከዘመን ዘመናት እየተሸጋገሩ ዛሬ ላይ የደረሱ ናቸው፡፡ እነሱም ሃይማኖታዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራ ባህላዊ እሴቶች ናቸው፡፡

- ሃይማኖታዊ እሴቶች

ምንም እንኳን በመኢኒት ማህበረሰብ ውስጥ የክርስትና (ኦርቶዶክስና ፕሮቴስታንት) እና የእስልምና ሃይማኖቶች ያሉ ቢሆንም አብዛኛው ሰው የሚተዳደረው በባህላዊ ሃይማኖቱ ነው፡፡ በመሆኑም ለባህላዊ የሃይማኖቱ መሪዎች፣ ለሃይማቱ መተዳደሪያ ደንቦች እና ህጎች ተገዥ ነው፡፡ ባህላዊ ሃይማኖቱ በረጅም ዘመን ቆይታው ማህበረሰቡን በመምራት፣ ተግባብቶ እንዲኖር በማድረግ፣ የሚነሱ የተለያዩ ግጭቶችን በመፍታት ከፍተኛ ሚና ሲጫወት ኖሯል፡፡ ማህበረሰቡም በማህበረሰቡ ደንቦች እየተገዛና እየታዘዘ ኖሯል፡፡ ሃይማኖቱ የተጣላን በማስታረቅ፣ የተበደለን እንዲካስ በማድረግ እያገለገለ ይገኛል፡፡

- ኢኮኖሚያዊ እሴቶች

የመኢኒት ብሔረሰብ በአብዛኛው የሚተዳደረው በእርሻና በከብት ርቢ በመሆኑ የኑሮ መሰረቱም እነዚህ ሁለት ነገሮች ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ የራሱን ማንነት ጠብቆ እንዲቆይ፣ እንዲቀጥል ከሚያደርጉ ነገሮች ውስጥ ኢኮኖሚ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ የመኤኒት ብሔረሰብ በበርካታ ጉዳዮች ተከፋፍሎ እንደመኖሩ ሁሉ የአንዱ ጎሳ ከአንዱ ጎሳ ጠንክሮ ከሚታይባቸው አንዱ ኢኮኖሚያዊ አቋሙ ነው፡፡ የብሄረሰቡን አባላት ወደ ግጭት ከሚከቱት ምክንያቶች ውስጥ ኢኮኖሚ አንደኛው ነው፡፡ በድንበር መጋፋት፣ በስርቆሽና በመሳሰሉት የሚነሱት ጠቦች መሰረታቸው ኢኮኖሚ ነው፡፡ ሰው የገደለ እና እሳ የሚከፍል ሰው ቢያንስ ሰባት ከብቶችና ልጃገረድ በካሳነት መስጠት አለበት፡፡ በጥሎሽ ጊዜም አግቢው ወንድ ለሴቷ ቤተሰብ ቢያንስ ከሰባት ከብቶች ያላነሱ ይሰጣል፡፡ በማህበረሰቡ በከብት ብዛቱ የታወቀና ለአንዲት ልጃገረድ ጥሎሽ መስጠት የቻለ ሰው የቻለውን ያህል (ጥሎሽ እስከሰጠ ድረስ) ሚስት ማግባት ይችላል፡፡ ለምሳሌ አቶ ጥጋቡ ስድስት ሚስቶች እንደነበሯቸው ነግረውኛል፡፡ በአንጻሩ የወደዳትን ልጅ የራሱ ለማድረግ አቅም ያጣ ወጣት በዘርፌያ ከብቶችን ለሚሟላት የሚያስብበት ጊዜም አለ፡፡ በብሔረሰቡ ውስጥ የጠብ መነሻ ከሆኑት ውስጥ አንዱ የጥሎሽ ከበት ማጣት መሆኑን የነገሩኝ

አቶ ብርሃኑ ይሄንን ይናገራሉ። " ጎረምሳ ልጅ ካለና ጥሉሽ የሚሰጠው ካጣ ወደ ዘረፋ ሊገባና ግጭት ሊፈጥር ይችላል።"[155]

- ማህበረ- ባህላዊ እሴቶች።

የመአኒት ብሔረሰብ ከፍተኛ እሴቶች ከሆኑት አንዱ ቱባ ባህሉ እና ማህበራዊ ህይወቱ ነው:: ከእነዚህም ውስጥ የጌ ናቸው ብሉ በመጠበቅና በመንከባከብ ከልጅ ልጅ ሲያስተላላፋቸው የቆዩ በርካታ ባህላዊ እሴቶች አሉት። ከእነሱም ውስጥ እውነትን መናገር አንዱና ትልቁ የብሔረሰቡ መገለጫ እሴቱ ነው። ከባልዋ ውጪ ከሌላ ሰው ጋር አውቃም ይሁን ሳታውቅ የግብረ- ሥጋ ግንኙነት የፈጸመች ሴት የሆነውንና ያደረገችውን ነገር ሁሉ ለባልዋ ደፍራ እውነቱን ትነግረዋለች። ውሸት እና ደብቆ መኖር የኋላ ኋላ በባሏና በልጆቿ ላይ መከራ ማምጣት እንደሆነም ታምናለች። ስለዚህም የግብረ ስጋ ግንኙነት ከሌላ ወንድ ጋር መፈጸሟን ትናገራለች። ባልዋም ሚስቱን የደፈረበትን ሰው ለመበቀል ወይም እንዲከሰው ለመጠየቅ ይኑላል። የደፈረውም ሰው እራሱ በሰራው ስህተት ቀድሞ ለአስታራቂ ሽማግሌዎች ያደረገውን ሁሉ ተናግሮ የበደለውን ሰው ካሶ ይታረቃል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የሰው መግደል ጉዳይ ነው:: ሰው የገደለ ሰው ነፍስ በሱ እጅ እንደጠፋ ካወቀ በኋላ መግደሉን አምኖ ነው ፈጥኖ ወደ ሽማግሌዎች የሚሄደው ወይም ሰው የሚልከው። ይህንን አይነት እውነትን የመናገር ባህል ብሔረሰቡ ጠብቆ ያቆየውና ማህበራዊ ሰላሙን ለማረጋገጥ ከሚጠቀምበት ስኑ ልቡናዊ እና ሞራላዊ እሴቶቹ አንዱ ነው::

በዚህም እውነት እውነቱን የመናገር ባህል የወንጀልን ክትትል፣ የክስንና የይግባኝን ውጣ ውረዶች እየቀነሰ የኖረበት አንዱ መንገዱና እሴቱ ነው። የወረዳው ፖሊስ አዛዥ አሸናፊ የሚናገሩትም ይሄንን የሚያጠናክር ነው። "በወረዳችን ግን ከሰረቀ ሰርቂያለሁ፣ ከገደለ ገድያለሁ ስለሚል ችግሩን አቅልሎታል"[156]

ሌላው ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ባህላዊ እሴቱ ከባልዋ ውጪ የግብረ- ሥጋ ግንኙነት የፈጠረች ሴት በትክክል መደፈሯ እና አለመደፈሯ የሚረጋገጥበት፣ ግንኙነት ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረ ሰው ጉዳዩን መፈጸሙና አለመፈጸሙ የሚታወቅበት የአንጀት ማንበብ ስርዓት

[155] ብርሃኑ ፡ ሚያዚያ 2009
[156] አሸናፊ ፡ ሚያዚያ 2009

ወይም ልምድ ነው። ይህንን ተግባርም የሚያከናውኑ በዘርፉ የሰለጠኑና የተካኑ ሰዎች አሉ። አንጀት ማገበብን ከልጅነታቸው ጀምሮ የተማሩት ቃንግሬ ዶረከረ አንጀት በማንበብ ስህተት እንደማይሰሩና ወንጀሉ ተሰርቶ እንደሆነና እንዳልሆነ እንዲሁም ሌላ ተመሳሳይ ጥፋት መኖሩን አለመኖሩን እንደሚያውቁ ነግረውኛል። ማህበረሰቡም የእነኝህን አዋቂዎች ቃል አምኖ የሚኖር ነው። ይህ የአንጀት ማገበብ ልምድ አንዳንዴ እጅግ ተደራራቢና የተደበቁ ተመሳሳይ ሚስጥሮችን እንደሚያወጣ ህብረተሰቡ ያምናል። በዚሁ ከባሏ ውጭ የግብረ- ሥጋ ግንኙነት ያደረገች ሴት ከፀባችበት ስህተት ወይም ርኩሰት የምትወጣበት፣ የምትነጻበት ወይም የምትቀደስበት ባህሉ ሌላው ባህላዊ እሴቱ ነው። ይሄም ባህላዊ እሴቱ የማጠብ ሥርዓት ሊሆን የማጠብ ሥነ ስርዓት ዘማዊ የነበረችውን ሴት ንጹህ የሚያደግና እንደ ቀድሞዋ ለባልዋ ተወዳጅ የሚያደርጋት ሥርዓት ነው።

> ከባሏ ውጪ ወሲብ የፈጸመች ሴት በደም የምትታጠብበት ትርጉም ከሰራችው ኃጢአት ነጻ እንድትሆን ነው። በደጋው አካባቢ ለእጥበት የሚውሉት ፍየል ወይም በግ ለስሪያ ያልደረሱ ቂብ ወይም ወጠጤ ናቸው። ይህም በንጹህ እንስሳት ደም የመታጠብ ምልክት ነው። ወጠጤ፣ ወይም ቂብ የሚመረጠው ሁለቱም ለወሲብ ያልበቁ በመሆኑ ወጠጤው ማንባባት ያልጀመረ በመሆኑ ንፁህ የሆኑ በመሆናቸው በንፁህ እንስሳ ደም ታጥበን እንንፃ በሚል ነው። ከሁለት አንዱ የሚታረዱት ለዚህ ነው። [157]

ይህ የማጠብ ባህል የበደለ የሚክስበት ጭምር በመሆኑ የሰው ሚስት ጋር የግብረ- ሥጋ ግንኙነት ያደረገና በሴቷ ባል የበቀል ርምጃ እንደሚወሰድበት አውቆ የተሸሸገ ሰው፣ አጥፊነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ለበደለው ሰው ካሳ በመስጠት የእርቅ ሥርዓት ፈጽሞና ሰላም አውርዶ የቀድሞ ኑሮውን በተረጋጋ ሁኔታ እንዲቀጥል ያስችለዋል። በሌላም በኩል ባሏ የሞተባትና ሌላ የምታገባም ሴት በዚሁ የማጠብ ባህል የመንጻት ሥርዓት ይደረግላታል። ይህ በመኤኒት ቤተሰብ አባላት ዘንድ የሚደረገው የመንጻት ሥርዓት ዓለም አቀፋዊ ግንዛቤ ያለው መሆኑን በተለያዩ ማስረጃዎች መገንዘብ የሚቻል ይመስለኛል። ይህ የማንጻትና የመቀደስ አስተምህሮት ዓለማቀፋዊ ገጽታ እንዳለው በማሳያነት ከሚጠቀሰው ውስጥ በዓለም ላይ ገናን ከሆኑ ሃይማኖቶች አንዱ የሆነው የክርስትና ሃይማኖት የመንጻት ወይም የመቀደስ ሥርዓት አንዱ ነው። በገነት ውስጥ ይኖር የነበረው አዳም ከሚስቱ ሔዋን ጋር ፈጣሪ የሰጣቸውን ትዕዛዝ ጥሰው ከተረገሙ በኋላ አምላክ በገባላቸው ቃል መሰረት ክርስቶስ በስጋ ተገልጦ በመስቀል ላይ በደሙ እንደዋጃቸውና እንደቀደሳቸው ይተርካል። በመጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ታሪክ

---

[157] ዘድቁ ሚያዚያ 2003

በአራት ዘሌዋውያን ውስጥም በደም የመንጻትና የመቀደስ ታሪክ እንደሚከተለው ተጽፎ እናገኛለን።

> ለቅድስናም የሚሆነውን ሁለተኛውን አውራ በግ አቀረበ። አሮንና ልጆቹም በአውራው በግ ራስ ላይ እጆቻቸውን ጫኑ። አረደውም። ሙሴም ከደሙ ወስዶ የአሮንን የቀኝ ጆሮውን ጫፍ፣ የቀኝ እጁንም አውራ ጣት፣ የቀኝ እግሩንም አውራ ጣት አስነካው። የአሮንንም ልጆች አቀረበ። ሙሴም የቀኝ ጆሮቻቸውን ጫፍ የቀኝ እጃቸውንም አውራ ጣት፣ የቀኝ እግራቸውንም አውራ ጣት ከደሙ አስነካ። ሙሴም ደሙን በመሰዊያው ዙሪያ ረጨ። "[158]

ከላይ በተጠቀሱት ጥቂት ግን ሰፊ ተቀባይነት ባላቸው አስተሳሰቦች በመነሳት በደም የመንጻት ባህል ረጅም እድሜና ታሪክ እንዳለው እንዲሁም የመኤኒት ብሔረሰብም ባህላዊ እሴቱ የሆነው የማጠብ ሥርዓት አለማቀፋዊ ግንዛቤ እንዳለው መረዳት ይቻላል። ከዚሁ ከመኤኒት ብሔረሰብ በርካታ ባህላዊ እሴቶች ከሆኑት ውስጥ ሌላው ተጠቃሽ የአሻ ሥርዓት ነው። የአሻ ሥርዓት ሰው አውቆና አስቦበትም ይሁን ሳያውቅና በድንገት ሰው ከገደለ ከሟች ወገኖች ጋር የዕርቅ የመግባቢትና በሰላም አብሮ የመኖሪያ መንገድ ነው። ይህ ለዘመናት የቆየው ባህላዊ እሴት አሁንም ድረስ የብሔረሰቡን አባላት የሚፈጠሩ ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ፣ ተቻችለው እና ይቅር ተባብለው በመካከላቸው መተማመንን ፈጥረው እንዲኖሩ አድርጓቸዋል።

በተለይ በአሻ ሥርዓቱ የገዳይ ወገኖች ለሟች ወገኖች በካሳነት የሚከፍሉት ሰባት ከብት እና አንዲት ልጃገረድ የሥርዓቱ ዋና መገለጫዎች ናቸው። ሰባቱ ከብቶች እንዳሉ ሆነው የአንዲቱ ልጃገረድ መሰጠት ዋና ምክንያት ልጃገረዷቱ ከሟች ወገኖች ጋር ተጋብታ በደምና በሥጋ የተሳሰረ ዝምድናን ለማበጀትና ጠላትነትን በመዋለድ በአዲስ የሥጋ፣ የደምና የአጥንት አንድነት ለማስተሳሰር ነው። ይሄም ባህል በራሱ ብሔረሰቡ ከዓለማቀፋዊ ግንዛቤና አስተሳሰብ የሚጋራው የራሱ እምነትና አስተሳሰብ እንዳለው የሚያስገነዝብ ነው።

የጎለም ህዝብ ሲሶ በሆነው የህብረተሰብ ክፍል የሚታመነው መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚተርከው ፈጣሪ እንኳን ከሰው ልጆች ጋር የነበረውን የዘመናት ጠብ አስወግዶ ባደረገው ዘላለማዊ እርቅ ዋና መንገዱና የዕርቅ ማጸኛ ውሉ ከሰው ልጆች ጋር በሥጋና በደም መተሳሰር ነው። ይህ መንገድ የተፈጸመው ደግሞ የመተሳሰሪያ ገመዱ በሆነችው በልጃገረድ (ቅድስት ድንግል

---

[158] ዘሌዋውያን 8፡22-24

ማሪያም) ነው። ከኋ በተገኘው ፍሬ ማሪና የሰው ልጆች የጸብ ግድግዳቸውን አፍርሰው አባትና ልጅ የመሆንን ስልጣን እንዳገኙ መጽሐፉ ይተርካል። "የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው።"[159] ይሄም አለማቀፋዊ ትርክት የመኢኒት ብሔረሰብ በልጃገረድ ሳቢያ ከሚያደርገው ደምን የማድረቅ፣ ጠላትንትን የማስወገድ እና መተማመንን የማጽኛ ሥርዓት ጋር ይመሳሰላል። ስለዚህ የመኢኒት ብሔረሰብ ቁልፍ ባህላዊ ሥርዓት የሆነው አሻ ለዘመናት የህብረተሰቡን ደህንነትና ሰላም የሚያስጠብቅ ትልቅ እሴቱ ነው። በአጠቃላይ የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት እነዚህ መርሆች ላይ የተመሰረተ ነው። ምንም እንኳን ጠንካራ የሆነ ማዕከላዊ አስተዳደር ሳይኖረው ቢዘልቅም እያንዳንዱ ጎሳ የራሱ የሆነ አደረጃጀትና መሪ ያለው በመሆኑ ለጎሳው በቆሙት ማህበራዊ ደንቦች ላይ የጸና አቋም አላቸው።

የብሔረሰቡ አባላት ጥቃትንም ደስታንም በጋራ የመከላከል የቆየና የጸና ልማድ አላቸው። አንድ ግጭት ሲፈጠር በተለይ የግድያ ጥቃቱ ከግለሰብ ጥቃት በላይ ይሆናል። ጠቡ በአንድ ጎሳ አባላት መካከል ከሆነ ጠቡ የቤተዘመድ ጠብ ይሆናል። ጠቡ በቤተሰብ መካከል ከሆነም አጥፊው ከቀሪ ዘመዶቹ ጋር ይነጠላል። ጠቡ ደግሞ ከሁለት ጎሳ አባላት በተገኙ ሰዎች መካከል ከሆነ ጠቡ በሁለቱ ጎሳዎች መካከል ይሆናል። ይህ የሚያሳየው የብሔረሰቡ አባላት ጥቃትንም ይን ደስታን በጋራ የመውጣት የቆየ ልማድ እንዳላቸው ነው።

አንድ ግድያ ሲፈጠር የሟች ቤተሰቦች ተጠራርተው ለበቀል የመተመማቸው ጉዳይ በአንጻሩ የገዳይ ወገኖች ትንሽ ትልቅ ሳይሉ ፊላቸውን ለማዳን የሚያደርጉት የጋርዮሽ የመከላከል ሥራ የማህበራዊ አንድነታቸው ጥንካሬ ነው። አንድ ሰው የግድያ ወንጀል ሲፈጽም በአሻ ለመታረቅ ለእሻ የሚሆነው ክፍያ እንዲሁ በፍጥነት የሚውጣጣ ነው። ስለዚህ የገዳይ ወገን የሆነ ተጠራርቶ "አንተ ይሄንን ከብት አዋጣ፣ እናንተ ይህኛውን ከብት አዋጡ፣ ቀሪዎቻችሁ ይህኛውን ከብትና ገንዘብ አዋጡ" ተባብለው የሚመጣውን የብቀላ ጦር ለመመለስ የሚያደርጉት ስራ የማህበራዊ አንድነታቸው መገለጫ ነው። ባህላዊ የፍትህ ስርዓቱን ወይም አሻን ለመክፈል አይመለከተኝም የሚል አካል የለም። በተለይ የቅርብ ዘመዶች የሆኑ ከብት የማዋጣት ግዴታ አለባቸው። ቀሪ የገዳይ ወገኖች / የጎሳው አባላት/ በእርቁ ቀን የመገኘትና ሥነ- ሥርዓቱን የመሳተፍ ግዴታ አለባቸው። ይህ አይነቱ ማህበራዊ አንድነት የሚንጸባረቀው በገዳይ ወገን ብቻ

---

[159] ዮሐ.፩፡፲፪

እንዲጠናቀቅ በማድረግ ሊደርስ የሚችለውን ሞት፣ ጥፋትና ውድመት ፈጥኖ የመቆጣጠር ትልቅ ጥንካሬ አለው፡፡

2. የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ቋሚ ህጎች ያሉት መሆኑ ሌላው ጥንካሬው ነው፡፡ ሰው አውቆም ይሁን ሳያውቅ የገደለ ሰው ለዘመናት ሲሰራበት የቆየው ደንብና ሥርዓት አለውና በዚህ ሥርዓት ይዳኛል፡፡ የበደለ በካሳነት ምን እንደሚከፍል እና የተበደም በምን እንደሚካስ የተደነገገ ቋሚ ውሳኔ ስላለው "እነሰኝ ወይም በካሳው ተበድያለሁ" የሚሉ ክርክሮች አይነሱም፡፡ በመሆኑን በፍትህ ሥርዓቱ ወቅት የሚነሱ ጥያቄዎች ባለመኖራቸው ላለመታረቅና እርቅን አሽፈረኝ ለማለት የሚከፈቱትን ክፍተቶች አስቀድሞ የዘጋ ነው፡፡ በአሻ እርቅ ወቅት እንዲት ልጃገረድና ሰባት ተጨማሪ ከብቶች መስጠት ለዘመናት ሲሰራበት ያለና በቤተሰቡ አባላት ዘንድ የታወቀ ህግ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሰው ሚስት የደፈረ ሰው የሚከሰው፣ ከሱ ጋር ተያይዞም የሚፈጸመው የዕርቅ ሥርዓት የተደነገገ በመሆኑ በዳይንም ተበዳይንም የሚያግባባና ለዘመናት ተከብሮ የቆየ ደንብ ነው፡፡ በባህላቱ የዕርቅ ሥርዓቱ ማስረጃ የሌላቸው ጉዳዮችም በባህላዊ ሃይማኖትና መሪዎችና በኮሞሩቶች የሚወሰኑ በመሆኑ ችግሮች ሲፈጠሩ የሚዳኙበት ቋሚ ህግ መኖሩ የህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ አንዱ የጥንካሬ ጎኑ ነው፡፡

3. በለቀታዊ ሰላምን ማምጣት ሌላው የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ጥንካሬ ነው፡፡ የአሻ ሥርዓትም ይሁን ግጠብና ሌሎች ግጭት አፈታቶች ደንባቸው እንዴ የተቀመጠ ብቻ መሆናቸው ሳይሆን ህብረተሰቡ አምኖ የሚያከብራቸውና ችግሩን በዘላቂነት የሚፈታባቸው ጭምር ናቸው፡፡ ግጭት መቆሙ ወይም ለጊዜው መብረዱ የአንድን ማህበረሰብ ሰላም አያስጠብቅም፡፡ ዘላቂ የሆነ ሰላም ማምጣትና በሰዎች ልብ ውስጥ መተማመንን ማምጣት አለበት፡፡ በመሆኑም ገዳይ የአሻ ሥርዓቱን በሚገባ ፈጽሞ ከታረቀ በኋላ ወይም አንድ ሰው የሰው ሚስት በመድፈሩ ይቅርታ ጠይቆ ሴቲቱን አጥቦ ባልየውን ከካሰው በኋላ፤ ወይም ሽማግሌዎች ውሳኔ ከሰጡና አልያም የሃይማኖት መሪዎችና ኮሞሩቶች ፍርድ ካጹኑ በኋላ፤ በበዳይና ተበዳይ መካከል የሚከሰት ችግር አይኖርም፡፡ በገበያ ቦታ፣ በለቅሶና በሌሎች ማህበራዊ አጋጣሚዎች ቢገናኙ በመካከላቸው የሚታይ የመጠላላትና ያለፈውን ቂም እያነሱ መወቃቀስ አልያም ወደ ዳግም ቁርሾ ውስጥ መግባት የለም፡፡ ዋየች ጃሻ ወንድማቸውን ገድለው ከመላው ቤተሰባቸው ጠብ ውስጥ ገብተውና ተሸሽገው እንደቆዩ ገልጸው አሻ ከከፈሉና በባህላዊው የእርቅ ሥርዓት ሰላም ካወረዱ በኋላ ከቀሪ ወንድሞቻቸውና ዘመዶቻቸው ጋር በሰላም

እየኖሩ እንደሆነ ይገልጻሉ። " አሻውን ከከፈልኩ በኋላ በሰላም መኖር ችያለሁ"[160]። ይህ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ለህብረተሰቡ የሰጠው ትልቅ ጸጋ ነው። የመንግሥታት ህጎች ይሄንን የመተማመንና ዘለቄታዊ ሰላም ማምጣት እንዳልቻሉ በርካታ አጥኚዎች የሚናገሩት ነው፤ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ግን የነበረውን ጸብ ከማስወገድ ባለፈ ዘላቂ ሰላምን በማጽናት ዋንኛ ነው። የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት የማይተካ ሚና እንዳለው ይታወቃል።

4. የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ሌላ ጠንካራ ጎን በተለይ የሰው መግደል እና ከሰው ሚስት ጋር የሚደረግን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ጎን የሚዳኝበት ህግ ጠንካራና የተቀመጡት የካሳ ክፍያዎች የኢኮኖሚ ጥንካሬን የሚፈታተኑ መሆናቸው ነው። በተለይ የአሻ ክፍያ የሚያስከፍለው መስዋዕትነት ከባድ በመሆኑ ሰዎች ወደ ግድያ ወንጀል እንዳይገቡ ያደርጋቸዋል። በካሳነት የሚሰጠው የከብት ብዛት ሰባት መሆን፣ ካለች ከቤት ከሌለች ከትርብ በመድ ተፈልጋ የምትሰጠው ልጃገረድ እንዲሁም ተጨማሪ የሚደረግ ሀዘንተኛን የመመለሻ የገንዘብ ክፍያ የብሔረሰቡ አባላት ካላቸው ኢኮኖሚያዊ አቅም አንጻር ከባድ በመሆኑ ወደ ወንጀል ውስጥ እንዳይገቡ ያደርጋቸዋል። ጠበቅ ያለ ህግ መኖሩና ተፈጻሚነቱ የግድ መሆኑ የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ አንድ ጥንካሬ እንደሆነ የመረጃ አቀባዩ ከበደም በመስማማት የሚከተለውን ይናገራከሉ። "ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ያለው ጣጣ ብዙ ነው። የሚከፍለው ከብት ብዛት፣ የልጃገረዷ ጉዳይ፣ የተጨማሪው ገንዘብ ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ሰው ግድያ እንዳይፈጸም ያግዛል።"161

5. ምንም ማስረጃ የሌላቸው በድብቅ የተሰሩ ወንጀሎችን ማውጣት መቻሉና ብሔረሰቡ የኔ ነው ብሎ ተፈጻሚ የሚያደርገው እና ተፈጻሚ እንዳይሆን የሚያደርግ ቢኖር ከሌሎች ጋር ተግባብቶ ለመኖር የማይችልበት ሁኔታ ስላለ ተቀባይነቱ ሰፊ መሆኑ ሌላው የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ጠንካራ ጎን ነው።

---

[160] [illegible]፡ ሚያዚያ 2009
[161] [illegible]፡ ሚያዚያ 2009

- የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ድክመቶች

ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ጥንካሬዎች እንዳሉት ሁሉ ጉልህ የሆኑ ድክመቶች እንደሚንጸባረቁበት የቤሌረሰቡ አባላት፣ የሃይማኖት መሪዎችና የጎሳ መሪዎች ጭምር እያመኑ መጥተዋል።

1. በድንገት ለሚፈጠር ጠብ ማብረጃ በአሻ ሥርዓት ሴት ልጅ በካሳነት መከፈሏ ትልቁ የፍትህ ሥርዓቱ ድክመት ነው። አካባቢው ለመሀል አገር ሩቅ ከመሆኑና የማህበረሰቡ አባላትም የትምህርት እድል ለዘመናት ያላገኙ በመሆናቸው ስለ ሰው ልጅ ሰብአዊ መብት፣ ስለ ሴቶች ጥቃትና የጾታ ተጽዕኖ የግንዛቤ እጥረት አለባቸው። በአብዛኛዎቹ የጸብ መንስኤዎች ደግሞ ድንገተኛና በመጠጥ የሚፈጠሩ ከመሆናቸውም በላይ፣ በአካባቢው ለጥናት በቆየሁበት ወር ውስጥ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል አባላት ጠጅና ቦርዴ ሲጠጡ አይቻለሁ። መጠጥ ቤቶች ከማለዳ እስከ ምሽት ይሰራሉ። ሴቶችና ወንዶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጎልማሳና አዛውንቶች በቡድንም በተናጠልም ሲጠጡ አይቻለሁ። ከምንም በላይ ደግሞ እናቶች በእዝል እንኳን ለያዟቸው ህጻናት ጠጅ ሲያጠጡ ተመልክቻለሁ። ስለዚህ የመጠጥ አቅርቦቱ በተለይ የጠጅ ሰፋ ያለ በመሆኑ ግጭቶች በተራ አለመግባባት ይፈጠራሉ። ባላባቱ ኬኒ ቀኛዝማች ጋሊ የአረቄ ንግድ ከመስፋፋቱ ጋር ተያይዞ ግጭቶች መብዛታቸውን ነግረውኛል። መረጃ የሰጡኝ ቀጥራቸው ከሃያ በላይ ሰዎች በሙሉ የግጭቶች ዋና መቀስቀሻ መጠጥ እንደሆነም ነግረውኛል። ስለዚህ በረባው ባልረባው ለሚፈጠሩት ግድያዎች በመስዋዕትነት የምትቀርበው ሴት ናት። ሴቷ ጡት ከምትጠባ ህጻን እስከ ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ድረስ ልትሆን ትችላለች። ከዚህ አንጻር ሴት ልጅ ላይ የሚደርሰው የሰብአዊ መብት ጥሰት የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ጉልህ ድክመት ነው። በመኢኒት ጎልዲያ ወረዳ ጉማ ቀበሌ ነዋሪ የሆነችው ዶጊያ ኮንኩላይ ወንድሟ በፈጸመው ግድያ በአሻ ሥርዓት ካሳ ተሰጥታ ለአካላዊ፣ ለስነ- ልቡናዊና ለሞራል ጥቃት ተጋልጣለች።ያገቢት ባሻቸው ጊዜ እየፈቷት አሁንም የሚች ወገኖች ንብረት ሆና መቀመጧንና ሌላ ማግባትም ሆነ ወደ ሌላ አካባቢ መኮብለል በወንድሟና በዘመዶቿ ላይ ጥቃትን መጋበዝ እንደሆነ በማመን በችግር ተቆራምዶ መኖር ግዴ እንደሆነ ነግራኛለች። በመሆኑም የመንግሥት አካላትና የጎሳ መሪዎች፣ የሃይማኖት

አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች በአንድነት በመምከር ሴት ልጅ በአሻ መከፈሏ እንዲቀር እየመከሩ በአንዳንድ ቀበሌዎችም ተግባራዊ ለማድረግ እየጣሩ ነው፡፡ ሴት ልጅ መሰጠቷ ቀርቶ በሴቷ ፋንታ ሌሎች ተጨማሪ ሰባት ከብቶች ለአሻ እንዲሰጡና አሼው በአጠቃላይ በአስራ አራት ከብት እንዲያልቅ እያደረጉ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ስር የሰደደውንና ለዘመናት የቆየውን አስተሳሰብ መለወጥ የሚቀል ስራ አልሆነም፡፡ ውሳኔዎች ቢተላለፉም ተፈጻሚነት አላገኙም፡፡

2. ሴትን በደም ማጠብ ሌላው የባህላዊው የፍትህ ሥርዓቱ ድክመት ነው፡፡ ሁልጊዜ አጥፍታለች ተብላ በደም የምትታጠበው ሴቷ ናት፡፡ ይሁን እንጅ ከሰው ሚስት ጋር የግብረ - ሥጋ ግንኙነቶች የሚፈጸሙት ሁሌም በኃይል ብቻ አይሆንም በጋራ ስምምነትም ሊፈጠር ይችላል ይሁን እንጅ ለተፈጠረው ነገር ሁሉ በደም ታጣቢዋ ሴቷ ነች፡፡ ከዚህም ሌላ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ለሴቷ የሰጣት መብት አናሳነትን የሚያረጋግጠው ሴቷ በውርስ ስትገባም (ስትወረስም) በደም የምትታጠበው እሷ መሆኗ ነው፡፡

3. በተለይ ከባሏ ውጭ የግብረ- ሥጋ ግንኙነት ፈጽማለች የተባለች ሴት ጉዳዩን መፈጸም አለመፈጸሟ የሚረጋገጠው እንዲሁም ተጠርጣሪው ጉዳዩን መፈጸም አለመፈፀሙ የሚረጋገጠው እንጀት በማንበብ በመሆኑ ይሄንን በቂ መረጃ ነው ብሎ መቀበሉ ተገቢነት ያለው የማይመስልና የባህላዊው የፍትህ ሥርዓት አንዱ ደካማ ጎን ነው፡፡

4. በተለይ በቆላማው የመኢኒቶች ክፍል አሁንም የባህላዊ ሥርዓቱ ጠንክሮ የሚሰራበት ነው፡፡ የሰው ነፍስ ያጠፋ ሰው አሻ እስከ ከፈለ ድረስ በመንግሥት ህግ እንዳይጠየቅ መፈለግ አለ፡፡ ይሄ ጉዳይ ደግሞ ማንም አሻ እስከ ከፈለ ድረስ መግደል ቀላል የሚሆንበትና ወንጀለኛን በወንጀሉ ተጠያቂ እንዳይሆን የሚያደርግ ነው፡፡ ስለዚህ ይሄ አስተሳሰብ ከፍትህ ሥርዓቱ አንጻ ጉልህ ድክመት የሚታይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓቱ የራሱ ጥንካሬዎችና ጉድለቶች እንዳሉት ተመልክተናል፡፡ በሥርዓቱ የሚታዩት ድክመቶቹ እየተቀረፉ፣ ጥንካሬዎቹ ደግሞ የበለጠ ጠንክረው እንዲቀጥሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 6.3 ጠበኞች ወደ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት እንዲሄዱ የሚያደርጋቸው መሰረታዊ ምክንያት

በመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊና ዘመናዊ ፍትህ ሥርዓቱ ሥራ ላይ ያሉ ቢሆንም የብሔረሰቡ አባላት በአብዛኛው በመካከላቸው የሚፈጠረውን ግጭትና አለመግባባት ለማስወገድ ከመደበኛው ወይም ዘመናዊ ፍርድ ቤት ይልቅ የባህላዊ ፍትህ ሥዓቱን መርጠው ይሄዳሉ። ጠበኞች ጉዳያቸውን ወደ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓቱ የሚወስዱበት የተለያዩ ምክንያቶች አሏቸው። እነሱንም ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታለን።

1. ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት በቅርበት ያለ እና ያለ ብዙ ውጣ ውረዶች በአቅራቢያቸው መገኘቱ ነው። በተጋጭዎች መካከል የሚፈጠርን የድንበር ግጭት ለመፍታት ሁለቱ ተከራካሪዎች የሚሄዱት ወደ ጎረቤቶቻቸው ነው። ከዚያም ከሰፈራቸው የቆየውን ድንበር በትክክል ያውቃሉ የሚሏቸውን ሽማግሌዎች ይመርጣሉ። ሽማግሌዎቹም የሚዳኙትን ጉዳይ ወይም የመሬቱ ወሰን የት ድረስ እንደነበረ ቀድመው የሚያውቁ ስለሆነ ፍርዳቸውን ሳይወሉ ሳያድሩ ይሰጣሉ። ይህ ፈጣን የመፍትሄ አሰጣጥ ተበዳይና የተከሰሰ ሰው በቶሎ የጀመሩት ክርክር ውሳኔ እንዲያገኝና ምንም አይነት ተጨማሪ የጊዜና የቢሮክራሲ ውጣ ውረዶች እንዳይኖሩባቸው ያደርጋቸዋል። በዚህም ምክንያት ቀበሌ ድረስ ሄዶ የፍርድ ሸንጎ አባላት ተሰብስበው ውሳኔ እስኪያስተላልፉ ድረስ የሚኖረው ርቀት በአጭር የሚቋጭ በመሆኑ የብሔረሰቡ አባላት የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱን ይመርጣሉ። ብሔረሰቡ በሚኖርባቸው ሁለት ወረዳዎች ውስጥ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ በተለይ መንገድ አለመኖር የዘመናዊ የፍትህ ውሳኔው ላይ ቅሬታ ቢኖር በይግባኝ ለመከራከርና ጉዳዩን ሩቅ ቦታ ሄዶ ለመከራከር የማያስችልና ሰፊ ውጣ ውረድ ያለው በመሆኑ ጭምር ነው።
2. ማስረጃ የሌላቸውና ምስክር ማቅረብ የማይቻልባቸው ወንጀሎችም መፈጠራቸው ሌላው በምክንያትነት የሚጠቀስ ነው። መደበኛው ፍርድ ቤት ሊመልሳቸው የማይችላው እነዚህን ክሶች በመደበኛው ፍርድ ቤት መልስ ሊሰጥባቸው ስለማይችል የብሔረሰቡ አባላት ለእንደዚህ አይነት ችግሮችም መልስ የሚያገኙት በባህላዊው የፍትህ ሥርዓቱ

ነው። "በባህል ሃይማኖት በተለይ በቃልቻ ያምናሉ። ከደበቅሁኝ ዘሮቼን ከማስጨርስ እኔ ታስሬ ልውጣ፣ ዘሮቼም ካሳ ይክፈሉ፣ ብለው ይናገራሉ።"[162]
በአብዛኛውም ወደ ባህሉ የሚሄዱት ጉዳዮች በማስረጃ መደገፍና መረጋገጥ የማይችሉት በመሆናቸው ወደ ሃይማኖት መሪዎቻቸው ጋ በመሄድ የጠረጠሩትን ሰው በማስጠራት መሀላ እንዲያደርግና የተጠየቀበትን ወንጀልም አልፈጸምኩም ካለ በቃልቻው እንዲረገምላቸው በማድረግ ውሳኔ ስለሚያገኙ የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱን ይመርጡታል።

3. ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛው የቤሔረሰቡ አባላት የትምህርት እድል ያላገኙ በመሆናቸው በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ላይ እምነት አለመጣልና ዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት የሚሰጣቸውንም መብቶች ያለማወቅ የሚጠቀሱ ናቸው። ዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት በሌቶች፣ በህጻናትና በአረጋዊያን ላይ ያለው የህግ ድንጋጌ እንዲሁም የአንድ ሰው ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ምን እንደሆኑ ባለማወቃቸው የሚያውቁትን የባህላዊ የፍትህ ሥርዓት ይመርጣሉ።

4. የመኢኒት ብሔረሰብ የራሱ ማንነት መገለጫ የሆኑ ባህሉቹን አክብሮ የሚኖርና ኅብረው ባህል እምኒታ ያለው በመሆኑ በግጭቶች ወቅት የተሻለ መፍትሄ አገኛለሁ ብሎ የሚያምነው ሲወርድ ሲዋረድ በኖረውና ባህሉ ላይ ነው። ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት ተቋሞቹም የተገኙት በዚሁ የባህልና የማንነት ሽግግር በመሆኑ ለባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ከፍተኛ እምኒታ አለው። ኮሞሩቶቹ /ባላባቶቹ/ ጎሳውን የሚመሩ፣ ቃልቻዎቹ ሃይማኖቱን የሚያስተዳድሩ፣ ሽማግሌዎቹ ባህሉን ጠንቅቀው የሚያውቁና በተለያየ መልኩም ሥራዎቻቸው የሚታወቁ በመሆናቸው በእነሱ የሚሰጠው ፍትህ ላይ የተሻለ እምኒታ ስላለው ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱን ይመርጣል።

## 6.4 ባህላዊ ሥርዓቱ ማህበራዊ ሰላምን የማምጣትና የማስጠበቅ ፋይዳው

ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ በየጊዜው የሚመጡለትን የጠበኞች ግጭት ከመፍታት አልፎ ማህበራዊ ሰላምን የማስጠበቅና የማረጋጋት ፋይዳው ከፍ ያለ ነው።

---

[162] ዘይቱ፣ ሚያዚያ 2003

የሰው ልጅ በውስጡ ስር ከሰደዱ ልማዶች ውስጥ አንዱ ጥቃትን በጥቃት መመለስ ወይም ብቀላ ማካሄድ ነው። ስለዚህ የሟች ወገኑን ደም ለመመለስ መነሳቱና ደም መበቀሉ የረጅም ጊዜ የሰው ልጅ ታሪኩ እንደሆነ እንረዳለን። አንድ ግድያ ተፈጽሞ የአጥፊው ወደ ህግ መቅረብና የቅጣት ውሳኔ ማግኘት ብቻ ማህበራዊ ሰላምን ያመጣል ብሎ ማሰብ ለመኤኒት ብሔረሰብ ማህበረሰብ የማይዋጥ ነው። ጥቃቱ የደረሰባቸው ወገኖች የጥቃት አጸፌታ ማድረጋቸው አይቀርም። እናም የተነሳውን ግጭት አርግቦ መበቃቀልን፣ ተያይዞ የሚመጣውን ጥፋት፣ የንብረትና የህይወት ውድመት በማስቆም ብሎም የደፈረሰውን ሰላም ንጹህ ሰላምን መልሶ በማምጣት ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት የማይተካ ሚና አለው። ቁልፍ መረጃ አቀባዩ ከሆኑት አንዱ ዋየች ጃሻ ወንድማቸውን በመጠጥ ኃይል ተገፋፍተው ከገደሉ በኋላ ጥላቻ ውስጥ የገቡትና ለበቀል ይፈልጉት የነበሩት በገዛ ወንድሞቻቸውና ዘመዶቻቸው ነበር። በጥፋታቸው ተጸጽተው በእሻ ሥርዓት ሲታረቁም እሳቸው ብቻ ከሽማግሌዎቻቸውጋር ከወንዝ ወዲህ ቀሪ ዘመዶቻቸው ከወንዝ ወዲያ በመሆን እሻ ከፍለዋል። እርቁ ከተካሄደ በኋላ ግን ከዘመዶቻቸውና ከቀሪ ወንድሞቻቸው ጋር በሰላምና በፍቅር ኖረዋል። ለቅሶ ላይ በጦር ሰው ገድሎ እሷን በእሻንት የከፈላት የዶጊያ ኮንኩላይ ወንድሟ በዚያው አካባቢ ከጠበኞቹ ምንም ሳይደርስበት ሁለት ሚስቶች አግብቶና ወልዶ በሰላም እየኖረ እንደሆነ ነግራኛለች።

የሰው ሚስት የደፈረ ሰው ጥፋቱን አምኖ የካሳ ክፍያ ፈጽሞ ሲገኝ በባላጋራው በድጋሚ አይፈለግም። በእንድ ማህበራዊ አጋጣሚ ድንገት ደፋሪና ሚስቱ የተደፈረችበት ቢገናኙ የሚፈጠር ችግር አይኖርም። ይቅርታ ጠይቆ፣ ሽማግሌ አቁሞ ተደፋሪ ሚስቱን በደም አጥቦላታልና አይፈራም፣ አይበረግግም። ሚስትየዋም አውቃም ይሁን ሳታውቅ ተደፍራ ስትገኝ እውነቱን ለባሏ ተናግራና በደም ታጥባ ከፍርሃቷ፣ ቤቷን ከመምራትና ከመስራት ተገልላ የቆየችውን ትታ እለምርዋን ከሚሞግታት የህሊና ስቃይ ተገላግላ እንደቀድሞዋ ለባልዋ ተወዳጅና ፊኪዋ ሚስቱ ትሆናለች። ባልም ይሄንን በመቀበል በእንድ ስህተት ደጋግሞ በመነዝነዝ አያስቃያትም። ሁሉም ነገር ያለፈና እርጌ በመሆኑ የሚያደፈርሰው ሰላም አይኖርም። ትዳርም ወደ ቀድሞ ትዳርነቱ በማጠብ ይመለሳል፣ የገደለም ሴት ልጅ በእሻ ሥርዓት ሰጥቶ የሞተው ዘር እንዲቀጥል አድርጓልና የቀደመው ሰላማዊ ኑሮ ይመለሳል። በአጠቃላይ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት አንድ ጠብ ተፈጥሮ ተያይዞ የመጣውን የጥላቻና የመበቃቀል መንፈስ ከማጥፋቱም በላይ የቀደመውን ፍጹም ሰላማዊ ኑሮ ለመመለስ ችግር ውስጥ በገቡት ወገኖች መካከል የመተማመን ስሜት ያመጣል። በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ

በአንድ ጉዳይ ግጭት ውስጥ የገቡ ሰዎች በባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ተዳኝተው ጉዳያቸውን ከቋጩ በኋላ በስራ ቦታና በማህበራዊ ገጠመኞቻቸው ላይ ቢገናኙ በጥርጣሬ እየተያዩ በስጋት አይበረግጉም። የሟች ወንድምና ገዳይ በአንድ ጠባብ መንገድ ብቻቸውን ቢሄዱ እንኳን በፍርሃትና ሥጋት አይተያዩም። እንዲህ አይነቱ የመተማመን መንፈስ የሚዳብረው በባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ውጤት እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ከዚህ በተጨማሪ የዘወትር የሆኑና መቋጫ የሌላቸው የሚመስሉ ጥያቄዎችን በመመለስ ማህበራዊ አንድነት ተጠብቆ እንዲኖር ያደርጋል። ይሄም በሃይማኖት ተቋሞች የሚገኝ እምነት ላይ የተመሰረተ ነው። አባላቱ ወደ ባህል ሃይማኖቶች ሄደው መልስ ከተሰጣቸው ወይም ካሰረገሙና እርግማኑ ከተካሄደ በኋላ ሰዎች የሚጠብቁት ውጤቱን እንጅ ጥያቄውን እያንከባለሉ ጊዜያቸውን አያጠፉም። የባህላዊ የፍትህ ሥርዓት መሪዎችን ቃል በማክበር ይኖራሉ።

## 6.5 የባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ከጊዜ፣ ከቦታና ቢሮክራሲን ከማስቀረት አንጻር

ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ለባለ ጉዳዮች ቅርብ ከመሆኑና የሚያስወጣው ወጪም ወደ መደበኛው ፍርድ ቤት ሲኬድ ከሚወጣው እጅግ በማነሱ እንዲሁም ቢሮክራሲያዊ ውጣ- ውረዱ በጣም አነስተኛ በመሆኑ ተገልጋዮች እንደሚመርጡት ማረጋገጥ ይቻላል። የመኤኒት ቤሔረሰብ በአገራችን ካሉና የመሰረተ- ልማት ዝርጋታ የላቸውም ከሚባሉት ብሔረሰቦች አንዱ ነው። የስልክ፣ የመብራት፣ የመንገድ፣ የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች አስፈላጊ መሰረተ- ልማቶች የሉትም ማለት ይቻላል። ምናልባትም የሁለቱ ወረዳዎች የመኤኒት ጎልዲያ እና የመኤኒት ሻሻ ወረዳ ዋና ከተማዎች ባቹማ እና ጀሙ ካልሆኑ በቀር ቀሪው ክፍል እርስ በርእርሱ የሚገናኝበት የመሰረተ- ልማት የለውም። አንዳንዱ የወረዳው ቀበሌ እስከ ሃያ ሦስት ሰዓት የእግር መንገድ ጉዞ እንደሚያስፈልገው የመረጃ አቀባዮቹ ቢኒያምና በድሉ ነግረውኛል። አርዐቶ አደር የሆነው ክፍልም የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ባለመሆኑ ወደ ዘመናዊ / መደበኛ ፍርድ ቤት ለመሄድ እንኳን አቅሙ ፍላጎቱም የለውም። እንደ መረጃ አቀባዮቹ አገላለጽ ከሁለትና ሦስት ዓመታት በፊት ከዞኑ ዋና ከተማ ሚዛን ተፈሪ ከተማ ወደ ባቹማ እና ጀሙ የሰማኒያ አምስት እና የመቶ አስራ አምስት ኪሎ ሚትር ርቀትን ለመሄድ ሁለትና ሦስት ቀን ያስፈልግ እንደነበረ ነግረውኛል። ጥናቱን ባጠናሁበት ጊዜ ተጨባጭ ሁኔታ  እንኳን ግጭት

ውስጥ የገባ አንድ ሰው ቀርቶ የመንግሥት መስሪያቤቶች እንኳን ከወረዳው ወደ ተለያዩ የገጠር ቀበሌዎች ለመሄድ ይቸገራሉ። እስረኞችን እንኳን ለመላክ ምን ያህል እንደሚቸገሩ የወረዳው ፖሊስ አባል አስናፊ ገልተውልኛል። "በተጨባጭ ሁኔታ ይግባኝ በወረዳ ያለው እስከ ዞን ነው። በዞን ደረጃ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አይቶ ወደ ክልል ነው የሚሄደው። ከዚህ ተነስቶ /ከወረዳው/ ዞን እንኳን ለሚሄድ ሰው አይችልም። እኛ እንኳን አይሱዙ መኪና ለምንን ነው ወደ ማረሚያ ቤት የምንልከው። በወረዳችን ግን ከሰረቀም ሰርቂያለሁ፣ ከገደለም ገድያለሁ ስለሚል ችግሩን አቅልሎታል።"[163] ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶች መሰረት አድርገው የሚቆሙት የሰራቸውን ማህበረሰብ ሁለንተናዊ ማንነት መሰረት አድርገው ነው። እንደ መኤኒት ባለው ብሔረሰብ ደግሞ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶቹ ከዘመናዊዉ የፍትህ ሥርዓት የተሻለ አገልግሎት ይሰጣሉ። ቢጋራ ላለው ማህበራዊ ሰላምም ዋና ዋስትና ነው። "ብዙ ነገሮች ሳይለፉ እዚያ ጋ ተቋጥተው፣ ሰው እዚሁ ጋ ተስማምቶ ማህበራዊ ህይወቱን በጋራ እንዲኖር የሚያደርገው አካሄድ ለዚህ ህዝብ ይጠቅማል።"[164] አንድ ግጭት ሲፈጠር የማህበረሰቡ አባላት ግጭቱን ማን እንደፈጠረው ማወቃቸውና አጥፊውም ማመኑ ማህበረሰቡ ችግሩን በአቅራቢያው እንዲፈታው ያደርገዋል። የታመኑ ጉዳዮች ደግሞ በፍጥነት ዘላቂ ሰላም የሚያገኙት በባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ነው። በመካከል መካድ ቢፈጠሩም አንድም በባላባቶቻቸው ሁለትም በሃይማኖት መሪዎቻቸው ውሳኔ የሚቋጩ ናቸው። ስለዚህ ከውጣ ውረድና ከተንዛዛ ቢሮክራሲ በጣም የተሻሉ ናቸው። አቶ ካሳም ይሄንን ሁኔታ የሚያጠናክር ሃሳብ ይሰነዝራሉ። "አካባቢው ላይ ያሉ ሰዎች እዚያ ውስጥ ማን እንዳጠፋ ይውቃሉ። ስለዚህ ያ ያጠፋውን እዚያው እንዲክስ፣ እንዲከፍል አድርጎ በማስማማት በጣም የተሻሉ ናቸው።"[165] በአጠቃላይ የመኤኒት ብሔረሰብ በመደበኛው ፍርድ ቤት ችግሩን እየፈታና የይግባኝ መብቶችን እየተጠቀመ ይኝዝ ቢባል እውነታው ከዚህ የተለየ ነው የሚሆነው። ችግሮቹን ከመፍታትና ዘላቂ ሰላምን ከማምጣት ይልቅ ውጤቱ የተንዛዛ ቢሮክራሲ ይሆናል። አንድ ጉዳይ በቀበሌ ፍርድ ሸንጎ ባያልቅለት ወደ ወረዳው ዋና ከተማ መጓዙ የግድ ይሆንበታል። በዚህም ጊዜ ለባለጉዳዩ የመንገድ፣ የስንቅና የማደሪያ አገልግሎቶች ማግኘት አስቸጋሪ ይሆንበታል። እንደ ያርጣ አይነት በቆላው የሚኖሩ ቀበሌዎችን ብንወስድ ለዚህ ችግር ከፍተኛ ተጠቂዎች ይሆናሉ። ወደ ወረዳው ዋና ከተማ

[163] አቶ[illegible]፣ ሚያዝያ 2009
[164] [illegible]፣ ሚያዝያ 2009
[165] [illegible]፣ ሚያዝያ 2009

ለመድረስ የሀያ ሦስት ሰዓት የእግር መንገድ የሚጠይቅ ከሆነ ከወረዳው በላይ የሆኑ ጉዳዮች ከተከሰቱና ጉዳዩ በወረዳው አቅም ባያልቅለት ወደ ዞኑ ዋና ከተማ ሚዛን ተፈሪ ከተማ ሄዶ ጉዳዩን ማቅረብና ውሳኔ እንዲያገኝ መከራከር ይኖርበታል፡፡ ይሄ ጉዳይ አንድ አይነት ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የሚፈጀው የራሱ ቀን አለ፡፡ ጉዳዮች በተገቢው ፍጥነትና ሰዓት የመከናወናቸው እውነታ ደግሞ ሌላው አስቸጋሪ ገጽታ ነው፡፡ እንዲያም ሆኖ ጉዳዩ ከዞኑ አቅም በላይ የሆነ ጉዳይ ቢያጋጥመው የክልሉ ዋና ከተማ ሀዋሳ ለመድረስ እጅግ በጣም ረጅም ጉዞ ተጉዞ ለተለያዩ ጉዳዮች የሚያስፈልጉትን ወጪዎች አሟልቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይሄን አይነቱ ሁኔታ ደግሞ ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ ህዝብ የሚቻል አይመስልም፡፡ ስለዚህ በባህላዊ ፍትህ ሥርዓቶች ችግሩን መፍታቱ ከጊዜ፣ ከቦታ እና ከቢሮክራሲ አንጻር ሲታይ በየትኛውም መልኩ የተሻለ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

## 6.6 ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ከአረጋውያን፣ ከህጻናትና ከሴቶች አንጻር

የመኢኒት ቤሔረሰብ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት አረጋዊያንን እንዲሁም ሴቶችና ህጻናትን የሚያዩበት የራሱ መንገዶች አሉት፡፡ ሥርዓቱ ለአረጋውያን፣ለሴቶች እና ለህጻናት የሰጠውን ቦታ ከዚህ በታች በዝርዝር እናያለን፡፡

- ከሴቶች አንጻር

በመኢኒት ቤሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ የሴቶች ሚና ዝቅተኛ ነው፡፡ አሁን አሁን እየቀነሰ ቢመጣም  በግድያ ጠብ ላይ የሚች ወገኖች ወንዶቻቸው የሚቹን ደም እንዲመልሱ የሚገፋፉትና የመቀስቀስ ስራ ይሰራሉ፡፡ ከዚያ ውጭ በእሻ አከፋፈልና በመጨረሻው የእርቅ ቀን እንዲገኙ ይደረጋል፡፡ በዕለቱ የሚደረገውን የገንፎ ማገንፋት ሥራም ይሰራሉ፡፡ ጨዋ ወይም ቡንቻ (ቡና) የሚያፈሉትም እነሱ ናቸው፡፡ ከዚያ ውጭ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ለሴቷ የሰጣት በጎ ጎን ብዙም የለም ማለት ይቻላል፡፡

ከቤቷ ውጭ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብትፈጥር፣ ባሏ ቢሞትና የባሏ ወንድም በውርስ ቢያገባት፣ብደም የምትታጠበው ሴቷ ናት፡፡ አንድ ሰው እንደደፈራት ቢታወቅና ሰውዬው ለሽምግልና ተጠርቶ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ የፍየል አንጀት ከተነበበ በኋላ የአንጀት አንባቢውን ውሳኔ የመቀበል ግዴታ አለባት፡፡ አንጀት አንባቢው ትክክለኛውን ጉዳይ ያውቃል

ተብሎ ስለሚታመን ያላትን የመቀበል እጣ ወድቆባት ይታያል፡፡ ከዚያ ውጭ በምንም አጋጣሚ ሰው የገደለ የቅርብ ዘመዷ እሻ እድርጎ የሚከፍላትና እሱ ባጠፋ እሷን ክሶ የራሱን ህይወት አደላድሎ የሚኖርባት ሴቷ ናት፡፡

ሴት በራሷ ህይወት ላይ የማዘዝና የመኖር ስልጣኗ በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ስር የወደቀ እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ ወንድሟ ለገደለው ሰው በእሻነት የተሰጠችው ዶጊያ ኮንኩላይ ወደ ሟቹ ዘመዶች ቤት ስትገባ እድሜዋ ከአስር ዓመት በታች እንደሆነና በእሻ አከሰጠችበት ሰዓት ደምር ተነገር የማያልቅ ጥቃት እንደደረሰባት አውግታኛለች፡፡ እንደ ዶጊያ አባባል በለቅሶው ሰሞን የሟቹ ወገኖች ለለቅሶ ሲመጡ አብዛኞቹ በኩርኩም ይመቷት እንደነበረ፣ ህጻን ልጅ እንኳን አላዘለው በድንጋይ ወፍጮ እህል ትፈጭ እንደነበረ፣ ከእርሻ ውላ ከሟች እስከ ማታ ያስፈት እንደነበረ፣ ምግብ በመከልከል ያስርቧት እንዲሁም የቤቱን ሥራ ሰርታ ስትጨርስ ዘመዶቻቸው ቤት ተልካ ስራ ትሰራ እንደነበረ ነግራኛለች፡፡ ዶጊያ እንደምትለው ከሟች ቤት በቆየች በሁለት ዓመት ውስጥ የሟች ወንድም ደፍሯታል፡፡ በመሆኑም ሚስት አድርጎና ቤት ሰርቶ አስቀምጧታል፡፡ ይሁን እንጂ ሁለት ልጆች ከወለደችለት በኋላ አባርሯታል፡፡

ዶጊያ በእሻ ተሰጥታ የደረሰባትን ስትነግረኝ ከቤት መባረሯ ብቻ ሳይሆን የልጆቿ አባት ታናሽ ወንድም ደግሞ ወርሷታል፡፡ እሷ ለዚያ ቤተሰብ ከእቃ ተለይታ የማትታይና በእሻ የተከፈለች በመሆኗ ወርሶ ያገባትም ሰው አንዲት ሴት ልጅ አስወልዶ ከቤቱ አባሯታል፡፡

ዶጊያ ገደሉ በእሻነት እንድትከፈል ካደረጋት ወንድሟ ጋር ተጠልላ እየኖረች ቢሆንም ወንድሟ ግን ሁለት ሚስቶቹ ጋር ጥሩ ኑሮ እየኖረ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግድያ ግጭት ሲነሳ ሴቶች ሮጠው ለማምለጥ ስለማይችሉ ወይም አቅማቸው ስለሚደክም ለጥቃት ተጋላጮች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የምንረዳው ባህላዊው የፍትህ ሥርዓቱ ለሴቶች ሰብዓዊ መብትና ለእኩልነታቸው የሰጠው ቦታ አለመኖሩን ነው፡፡

- ከአረጋውያንና ከህጻናት አንጻር

የሙኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት ለአረጋውያን የተሻለ ቦታ የሰጠ ነው፡፡ አረጋውያን ካላቸው ልምድና እውቀት የተነሳ ግጭቶች ሲፈጠሩ እነሱን ለመዳኘት ይመረጣሉ፡፡ ግጭት በተፈጠረ ሰዓት ከየወገናቸቸው ፊት በመቆም ግጭቱ በሰላማዊ መንገድ እንዲቋጭ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የቤተሰብ ጠብ፣ የቤት ዘመድ ግጭት፣ የድንበርና የመሳሰሉት ላይ

የሚሰጡትም ውሳኔ በአብዛኛው ተግባራዊ ይሆናል። በአሻ እርቅ ወቅት የማሽላ ገንፎ የሚያገኙት በእድሜ የገፉት ሰዎች ብቻ ናቸው። ይሄም የእርቅ ሥርዓቱ የሰጣቸው ክብር ነው። ይሁን እንጂ አንድ የግድያ ወይም የብሔረሰብ ጸብ ሲፈጠር በሚካሄደው እልቂት የሟች ወገኖች ከፍተኛ እልህ ውስጥ ስለሚገቡ እነሱም ተጠቂ ይሆናሉ።

ህጻናትን በተመለከተ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት የሰጠው ቦታ በጣም ዝቅተኛ ነው። በእርግጥ ህጻናት ጥፋት ቢያጠፉ በአብዛኛው የሚጠየቁት ወላጆቻቸው ናቸው። በአሻ የእርቅ ስነ-ሥርዓት የመጨረሻ እለት እንዲገኙ ይደረጋሉ። የቀሩት ሂደቶች የእርቁ ሁኔታ ያልተጠናቀቀ በመሆኑ ድንገት ለሚፈጠሩ ችግሮች ተጋላጭ እንዳይሆኑ በማሰብ እንዲገኙ አይደረጉም። ከዚያ ውጭ ህጻናት በግድያ ጊዜ ከሚጠቁትና ከፍተኛ ሥነ ልቡናዊ ጥቃት ከሚደርስባቸው ክፍሎች ዋናዎቹ ናቸው። በተለይ ሴት ህጻን ለአሻ ክፍያነት ጡት የምትጠባና በእዝል እንኳን ያለች ብትሆን ትሰጣለች። አንዳንዶቹ እንዲያውም ገና እነሱን ማሳደግ ተጨማሪ ስራ እንደሚሆን ስለሚያምኑ ጎልቶ የሚወጣ ጥላቻ በህጻናቱ ላይ ያድርባቸዋል። ለረጅም ጊዜም በሟች ቤት ስለሚቆዩ የሟች ወገኖችም የሞተባቸውን የመርሳት እድላቸው ጠባብ ይሆናል። ህጻናቱ እንደ ህጻንነታቸው የሚያጠፉት ጥፋት ቢኖር ለመታገስ የሚያስችል እድል በሟች ወገኖች ውስጥ ቦታው ዝቅተኛ ይሆናል።

በኢብቶላይ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ለአረጋውያን የተሻለ ቦታ ሲኖረው ለህጻናት በተለይም ለሴት ህጻናት ያለው ቦታ ዝቅተኛና የህጻናትን ሰብአዊ መብቶችና ድንጋጌዎች የሚቃረን ይመስላል።

# ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በተለያዩ ስድስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው። እያንዳንዱ ምዕራፍ የራሱ የሆነ ምልዓትን ጠብቆ የቀረበ ነው። ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ማህበረ- ባህላዊና አካባቢያዊ ገለጻ፣ የጥናቱ ምንነት፣ በርዕሱ ዙሪያ የተሰጡ ንድፈ-ሀሳቦችና ተዛማጅ ሥራዎች፣ የተጠናው ማህበረሰብ ግጭት የሚፈታባቸው መዋቅሮች፣ ማህበረሰቡ ግጭቶችን ሲፈታ የሚከተላቸው ሂደቶች፣ ወደ ተጠናው ማህበረሰብ ብዙ ጊዜ የሚቀርቡ የግጭት አይነቶችና የተሰጡ አይነተኛ ውሳኔዎች፣ ጥናቱ በተጠናበት አካባቢ በመደበኛ ፍርድ ቤትና በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት አሰራር መሀከል ያለው ግንኙነት፣ ትንተና እና የማጠቃለያ ሀሳቦች ተካትተውበታል። በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ ጥናቱን ለማካሄድ መነሻ የሆነው ጉዳይ ወደ አገራችን ደቡባዊ ክልል በመጓዝ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ከፍትህ አካላት ስለ መኢኒት ብሄረሰብ የሰማሁት፣ በቤንች ማጂ ዞን ፍትህና ጸጥታ መምሪያ የትምህርት ምርምርና ስልጠና ክፍል በየሦስት ወሩ እያዘጋጀ የሚያወጣው ‹‹ያካር›› ጋዜጣ በሚያዚያ እና በሐምሌ ወር 1999 ዓ.ም በባህል አምዱ ሥር ስለ ብሄረሰቡ ያወጣውን የባህላዊ የፍትህ ሥርዓት በማንበቤ፣ፖፑሌሽን ሚዲያ ሴንተር ባወጣው ‹‹ሙሉ ሰው›› በተሰኘው የአጫጭር ልቦለዶች መድበል ውስጥ በውድድር ያለፈ ‹‹እሹ›› የተሰኘ አጭር ልቦለድ እንዲሁም በ2002ዓ.ም መጨረሻ ላይ በግሌ ባሳተምኩት ‹‹ሦስቱ ትዝታዎች›› የተሰኘ የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ ውስጥ ስለብሄረሰቡ መጻፌና በ2002 ዓ.ም ታህሳስ ወር ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ከብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን ጋር ተሳስሮ በተከበረው 5ኛው ዓለም አቀፍ የፌደራሊዝም ኮንፈረንስ ላይ ለመሳተፍ ወደ አዲስ አበባ የመጡ የአካባቢው ተወላጆች እና የባህል ልዑካንን አነጋግሬ ባህላዊ የፍትህ ሥዓቱ አሁንም የሚካሄድ መሆኑን ስለገለጹልኝ እንደሆነ ተቀምጧል። ለጥናቱ የተመረጠው ስልትም ገላጭ /Descriptive/ እንደሆነ ተጠቅሷል ጥናቱ የቤተ- መጻሕፍት ንባቦች፣ ቃለ- መጠይቆች፣ የቡድን ውይይት፣ የመዛግብት ዳሰሳና የመስክ ቆይታ በማድረግ ተሰርቷል። የመስክ ቆይታው የተሳካና የሚፈለገውን መረጃ ያሟላ እንዲሆን አጥኚው ከመጀመሪያ ጀምሮ ልዩ ልዩ ደብዳቤዎችን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እና ከአዲስ አበባ ባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ በማጻፍ። ወደ ሚጠናው ህብረተሰብ ዘልቆ ለመግባትም ከደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባህልና ቱሪዝም ደብዳቤዎችን በማጻፍ እንዲሁም መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በተዋረድ የቤንች ማጂ ዞንና የየወረዳዎቹ አስተዳደሮች ለጥናቱ የሚያግዝ ደብዳቤ በመስጠት እንዲሁም ብሔረሰቡ በዋናነት የሚገኝባቸው ሁለት ወረዳዎች የወረዳዎቹ ባህል ቱሪዝምና

የመንግሥት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤቶች አጋዥ ሆነው ጥናቱ ተጠንቷል፡፡ አጥኚው በመስክ ቆይታው መረጃዎችን ለማግኘት በተለያዩ ቀበሌዎች በመዟዟር በግጭት ዙሪያ የሰሩ፣ የአካባቢውን ባህል ጠንቅቀው የሚያውቁ የአገር ሽማግሌዎችን፣ የሃይማኖት መሪዎችን እንዲሁም በርዕሱ ዙሪያ ተሳትፎ የነበራቸውን ሰዎች ቃለ መጠይቅ ከማድረግ በተጨማሪ የሰው መግደል የእርቅ ስነ-ሥርዓት አሻ በቅንብር ተፈጥሯዊ መንገድ ሲከወን ተከታትሏል፡፡

በቤኔረሰቡ ውስጥ ግጭት የሚፈቱባቸው ባህላዊ ተቋማት ሦስት እንደሆኑና ኮሞሩት/ባላባቶች/ ወይም የጎሳ መሪዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች /ቃልቻዎች/ እንዲሁም ታዋቂ የአገር ሽማግሌዎች እንደሆኑ ተገልጸዋል፡፡ ጥናቱ በሦስተኛው ምዕራፉ የብሄረሰቡ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ከሚፈቷቸው በርካታ ግጭቶች ውስጥ የሰው መግደል፣ የሰው ሚስት የመድፈር፣ የድንበር ጸብ፣ ከቤኔረሰብ ጋር የሚነሳ ጠብ እንዲሁም በባህል ሃይማኖት የሚፈቱ ግጭቶችን ሂደት አሳይቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወደ ብሄረሰቡ የግጭት መፍቻ ተቋማት ብዙ ጊዜ የሚቀርቡና አይነተኛ ውሳኔ የተሰጣቸው የግጭት አይነቶችና ውሳኔዎች ከሃብትና ከንብረት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች፣ የቤተሰብ ጠቦች፣ ወንጀሎች፣ የቡድን ጠቦች እንደሆኑ ዘርዝሯል፡፡ በጥናቱ አምስተኛ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ በመደበኛ ፍርድ ቤትና በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት መሀከል ስላለው ግንኙነት ተዘርዝሯል፡፡ ባህላዊውና ዘመናዊው/መደበኛው ፍርድ ቤት/ ሁለቱም ይህ ጥናት በተጠናበት ጊዜ በአገልግሎት ላይ መሆናቸውና የሚፈጠሩትም ግጭቶች እንደ ባህሪያቸው በሁለቱ ተቋማት እንደሚፈቱ ያሳያል፡፡ ሁለቱ ተቋማት አንዳንድ ግጭቶችን በመፍታት የተሻሉባቸውን ጎኖች አብነት በመስጠት ያብራራ ሲሆን የትብብር ሥራቸው ያለውን መልክና በውሳኔ አሰጣጣቸውም አንዱ የአንዱን ውሳኔ የሻረበት ሁኔታ እንደሌለና እንዲሁም የባህሉ የፍትህ ሥርዓት መደበኛው ፍርድ ቤት ወስኖት የቆየውን ውሳኔ በአሳማኝ ምክንያት እንደሻረ ይሄንንም ለማድረግ መደበኛው ፍርድ ቤት ለባህላዊው የፍትህ ተቋም ደብዳቤ ጽፎ እንዲረጋገጥ እንዳደረገ ገልጽዋል፡፡ በኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች ውስጥ ያሉት ህጎች ለባህላዊው የፍትህ ሥርዓት የሰጡት ቦታ ውስን መሆንና እነሱም ግጭቶች ሲፈጠሩ የሚፈቱበት መንገድ ቂምና በቀልን አጥፍቶ ዘላቂ ሰላምና መተማመንን ለማምጣት አለመቻሉ፣ በአንጻሩም ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ይሄንን ማድረግ መቻሉ ተተንትኗል፡፡ ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ለህብረተሰቡ ማህበረሰባዊ፣ ሞራላዊና ሥነ-ልቡናዊ ጥቅሞችን በመስጠት ከፍ ያለ ቦታ እንዳለው ለማሳየት ሞክሯል፡፡

የባህላዊና የዘመናዊ የፍትህ ሥርዓቶች ያላቸው ጥንካሬና ጉድለት ተተንትኗል፡፡ የባህላዊ የፍትህ ሥርዓት ለህብረተሰቡ የመኖሪያ አካባቢ ቅርብ፣ ወጪ ቆጣቢና ቢሮክራሲ የሌለው መሆኑና የዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት ደግሞ ወጪ የሚያስከትል ይግባኝ ብሎ ብዙ ርቀት ሰዎች ሊሄዱበት የማይችል እንደሆነ ጥናቱ ይተነትናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቱ ሴት ልጅን በአሸንት ስላነት/ መክፈሉ የሴቶችን ሰብዓዊ መብት የሚጥስ ጉዳይ ከመሆን አልፎ በካሳንት የተሰጡ ህጻናት የሚደርስባቸውን ጥቃትና ግፍ ለማሳየት የሞከረና ይህም ዋና ድክመቱ እንደሆነ ያመላክታል፡፡ ሴትን ልጅ በአሻ እንዳትከፈል እና በምትኳ ሰባት ከብት እንዲጨመር ለማድረግ የሚደረገው የዘመናዊና የባህላዊ የፍትህ አካላት ትብብር ሴትን ልጅ ከመታደግ አንጻር መልካም ቢሆንም አሻ በአስራ አራት ከብት ክፍያ ይፈጸም ማለት ግን ዞር ዞር ሌላ አኮኖሚያዊ ጫና ማህበረሰቡ ላይ ማድረግ እንደ ሆነ ተተንትኗል፡፡ እነዚህን ከብቶች ማግኘት ያልቻለ ሰው በአሻው መታረቅ ስለማይችል የግድ ከብቶቹን ለማግኘት ሲል ለላ ወንጀል ወይም ዘረፋ ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ተጠቁሟል፡፡

በአጠቃላይ በመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊው የግጭት አፈታት ሥርዓት ከዘመናዊው ጋር እተጋገዘ ለህብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጠ እንደሆነ ይህ ጥናት ያመለክታል፡፡

# ይሁንታ

አብዛኛው የመኢኒት ብሔረሰብ በቀን ከቀን የህይወት መስተጋብሩ ውስጥ የሚያጋጥሙትን ግጭቶች እየፈታ ሰላማዊ ህይወቱን የሚያገኘው በባህላዊው የፍትህ ስርዓት መሆኑ ተገልጾዋል። እናም የባህላዊ ሥርዓቱ ደንቦች እንዲዳብሩ ማህበረ- ባህላዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው እንዲጠነክር አንዳንዶች ደግሞ እንዲሻሻሉና እንዲቀሩም ጭምር የይሁንታ ሃሳቦቼን ከዚህ በታች አስፍራለሁ።

1. ሴትን ልጅ በአሻንት መክፈል ፈጽሞ የሚቀርበት መንገድ ቢፈጠር እናም የአሻ ክፍያው በሰባት ከብቶች ብቻ ቢጸና።
2. ከባሏ ውጭ የግብረ- ሥጋ ግንኙነት ፈጽማለች የተባለች ሴት በፍየል አንጀት ማንበብ ብቻ የመደፈር አለመደፈሯን ትክክለኛነቱን ከማረጋገጥ በተጨማሪ የማረጋገጫ መንገዶች እንዲኖሩት ቢደረግ፣ ለምሳሌ በሃይማኖታቸው እውነቱን ለማረጋገጥ የመሀላና የእርግማን ሥነ- ሥርዓቶች ቢኖሩ ።
3. የመንግሥት አካላትና የአገር ሽማግሌዎች ስምምነት ላይ የደረሱበት በአሻ ክፍያ ሴት ልጅ እንዳትሰጥ የሚያደርገውና በሷ ምትክ ተጨማሪ ሰባት ከብቶች ጨምሮ የካሳ ክፍያውን የከብት ቁጥር ወደ አስራ አራት ከፍ የሚያደርገው ስምምነት አሁንም ለተጨማሪ ወንጀሉች (አስራ አራት ከብት ማግኘት ስለሚከብድ እነሱን ለሟሟላት ህብረተሰቡን ለዘረፋና መሰል ተግባራት ሊያጋልጠው ስለሚችል) የከብቶችን ቁጥር ቀንሶ ከልጃገረዷ ውጪ በሰባት ከብት ብቻ እንዲያልቅ ቢደረግ።
4. ወንጀል የፈጸመ ሰው ወደ መደበኛው ህግ ሄዶ ቀሪ ቤተሰቦቹ ግን ከመበቃቀል እንዲነጹና መተማመናቸው እንዲጎለብት የሚደረገው የአሻ ሥርዓት አከፋፈሉ ከልጃገረድ ውጭ በሰባት ከብቶች ጸንቶ ተጠናክሮ ቢቀጥል።
5. በጆምር ላይ ያለው የሁለቱ የፍትህ ተቋማት ትብብር የሚታዩባቸውን ክፍተቶች በመወያየትና በመተማመን አንዱ የአንዱን ጉድለት በመሙላት በጋራ መስራቱን ቢያጠናክሩ።
6. አንድ ሰው የግድያ ወንጀል ሲፈጽም በሱ ዙሪያ ያሉ ሰዎችንና ንብረትን በጅምላ የማጥፋትና የመግደል ሁኔታው እንዲታረም የጎሳ መሪዎች ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶች እንዲካሄዱ ቢደረግ ለዚህም ሁሉን አቀፍ ትብብር ስለሚያስፈልግ

የፍትህ አካላት፣ የዘርፉ ምሁራን፣ የክልልና የዞን የብሔር ብሔረሰቦች ምክር ቤቶች፣ በሰላምና ደህንነት ላይ የሚሰሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጭምር የበኩላቸውን ድርሻ ማበርከት ቢችሉ።

# ጥቅስማ


Adebayo, Adedji, Comprehending Africa Conflicts in Adebayo Adedeji (ed).Comprehending Africa Conflict: the search for sustainable peace and good governance, London, ed, cooks, 1999.

Aweke Hmzaye, Mosaic Culture and peoples of South Nation,Naiionalites and peoples,Regional State.Hawassa:Africa Prienting PLC 2007.

Bender,M.L. and et al (eds.), Languages in Ethiopia. London: oxford University Press,1976.

Burton,Johan In Conflict and Communication: The use of Controlled Communication in International RELATION. New York: the free press,1969.

Cervenka, Ldenke. The unfinished Quest for unityo African and OAU London: Julian Fridaman publisher Ltd,1977.

Coser, Lewis A. The Function of social conflict. New York and Basic books inc, Publishers, 1956, pp: 24.

_______ Continuities in the Study of Social Conflict, the free press, New York, 1970.

Deutsch, M. The Resolution of Conflict. New Haven: Yale university, press,1973.

Fisher, Stanrey, Z. "Traditional Criminal Procedure in Ethiopia". The American Journal of Competative Law. New York: Anronicus Publishing Company, inc: vol, 19, no 4, 1971,pp : 709-746.

Gove, Philip B. and the Merriam-Webster Edittorial Staff. Webster's third New International Dictonary. Massachusetts: G and C. Merriam Company Publishers,1976.

Jeong, Ho-wan, Peace and conflict studies an Introduction. England Ashgate publishing Ltd , 2000.

Kreidier,W. Creative conflict resoulation: more than 200 Activites forkeeping peace in the class room.Glenview, IL: Scott, Foresman and Company,1984.

Kuper, Adam and Jussica Kuper (eds), the social sience Encyclopidia, (2nd ed.) London:Rutledge, 1996.

Leslau, Wolf. English- amharic Context Dictionay. Wiesbaden: Otto harrassowitz, 1973.

Levinson,David and Melvin Ember (eds) Encyclopedia of Cultural Antropology. New York: Henry Holt and company inc. vol.1,1996.

Medhane Tadesse, The Quest for conflict settlement in Ethiopia's Territory, Addis Ababa , 2004.


Mesfin Yilma and Mesfin Bantayehu. Dealing with the large scale violence: is comprehensive academic Training needed? (Paper prepared on conflict resolution for a workshop organized by APCMC on behalf of initiative Africa, Dec, 6-7) Addis Ababa, Ethiopia, 2007.

Oliver, Ramsbotham, et al. Contemporary conflict Resolution. London: Polity Press, Cambridge,1984.
Organiztion of Africa Union Charter, Addis Ababa, OAU, 1963.
The Charter of the United Nations, 1945.
The Europe World Year Book, Part One: International Organizations, 46th edition, London, England 2005, vol, 1.
Wolfgang, Hienrich, Building the peace: Experience of collaborative peace building in Somalia (1993-1996). UK: Ipswich Book Company Ltd. 1997.
Zartman, William I. and Francis M. Deng (ed), Conflict Resolution in Africa. Washington, D.C: the Brooking Institution, 1991.
Zerihun Doda, the Ethno-history Me'enit Ethnic Group, South Nation, Nationalities and People's Regional Government. Institute of language , Culture and History study, Department of History and Heritages, 2008.

ማንተመሥላሴ ወልደ መስቀል፣ የኢትዮጵያ ባህል ጥናት። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣1960።
ሰለሞን ታፍ እና ሌሎች፣ ሙሉ ሰው እና ሌሎች ልቦለድ ታኮች። ፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር ከኖርዌይ ህጻናት አድን ድርጅት ጋር በመተባበር፣ አዲስ አበባ፣ 2002ዓ.ም።
ተመስገን ምንዋጋው፣ "ህገሰባዊ የግጭት መፍትሄ ሥርዓት በዶኮ ጋሞ"፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማማያነት የቀረበ፣ 1998ዓ.ም።
ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፣ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ፣1951።
አምሳሉ አክሊሉ፣ አጭር የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣1976።
አብርሃም ታደሰ፣ "ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሔረሰብ"፣በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማማያነት የቀረበ፣1999ዓ.ም።.
አንዱዓለም አባተ፣ ሦስቱ ትዛታዎች። ፋርኢስት ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣2002ዓ.ም።
ደስታ ተክለ ወልድ፣ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ፣ 1962።
ዳንኤል አሰባቸው ፣ "ጋብቻ ትውፊት በመኢኒት ብሔረሰብ" ለቢ.ኤ ዲግሪ ሚሚያነት የቀረበ፣ 1984ዓ.ም።

የወንድወሰን አውላቸው፣ "የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደርና የግጭት አፈታት"፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማማያነት የቀረበ፣ 1998ዓ.ም።
የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ። ብርሃንናሰላም ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣1980።
የደቡብ ቤሔር፣ ቤሔረሰቦችና ህዝቦች ፕሮፋይል፣2001ዓ.ም።
ያሬድ ጋዜጣ። ሚያዚያ እና ሐምሌ ወር እትም 1999 ዓ.ም።
ይልማ ተፈራ፣ "የሽምግልናና እርቅ ሥርዓት በወላይታ"፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማማያነት የቀረበ፣ 1998ዓ.ም።

# የቤንች ማጂ ዞን ካርታ




ምንጭ፡- የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግሥት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት

# መረጃ የሰጡ አካላት ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም | እድሜ | የመኖሪያ አካባቢ | የስራ ድርሻ | ሃይማኖት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሰላ በሱኮርይ | 54 | ቢያንሊች | ታዋቂ የአገር ሽማግሌ ( ኮሞሩት አሻ) | ቃልቻ |
| 2 | ሊሚኒቶ ሺማቻ | 55 | ጎማ | ገበሬ፣ የአገር ሽማግሌ (ኮሞሩት አሻ) | ቃልቻ |
| 3 | ዋኖቶ ጃሻ | 47 | ዱማ | የአገርሽማግሌ /ኮሞሩት አሻ/ | ቃልቻ |
| 4 | ዶኒያ ኩንኩላይ | | ጉማ | አርሷደር | ቃልቻ |
| 5 | ብርሃኑ ወርቁ | 46 | ዱማ | በመኢኒት ጎልድያ ወረዳ ጤና ጽ/ቤት የሥርዓተ ፆታ ኦፊሰር | ኦርቶዶክስ |
| 6 | አወቀፎርሽዋ | 48 | ዱማ | ቃልቻ | ቃልቻ |
| 7 | ቃንገሬ ዶሪከሬ | 60 | ቢያንልች | ገበሬና እንጆት አንባቢ | ቃልቻ |
| 8 | ካሳ ከበደ | 48 | ሻሸ | የመኢኒት ሻሻ ወረዳ ም/ቤት ም/አፈ ጉባዔ | ፕሮቴስታንት |
| 9 | ወልደየስ ዶሌ | 44 | ሽርሽር | የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የበሽታ መከላከል ዋና የሥራ ሂደት መሪ | ኦርቶዶክስ |
| 10 | ኬኒ ቀኖዠማኙጋሊ | 56 | ካንቲ | አርሷደር (ኮሞሩት) | ቃልቻ |
| 11 | አሊጋንሽ ኩትያ | 36 | አሪ | የቤቶች ተወካይ አርሶ አደር | ቃልቻ |
| 12 | ሰዒድ ይመር | 36 | ጀመ | መዘጋጃ ውስጥ | ሙስሊም |
| 13 | ዋና ሳጅን አሸናፊ ቺሪዋሌ | 40 | ሻሪያ | የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ | ኦርቶዶክስ |
| 14 | ምክትል ሳጅን መቱንን ከፐታ | 40 | ጨበሬ | የጨበሬ አገልግሎት ጥበቃ ኃላፊ | ኦርቶዶክስ |
| 15 | ታፍ መሰፍን | 30 | ጨበሬ | ነጋዴ | ኦርቶዶክስ |
| 16 | በደሉ ካሳ | 33 | ባቹማ | የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግሥት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ | ኦርቶዶክስ |
| 17 | መልኬ ኬላኔ | 35 | ጉማ | የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ ማስታወቂያ ጽ/ቤት ም/ኃላፊ | ፕሮቴስታንት |
| 18 | መንገሻ ወርቁ | 33 | ዲልቀባ ማያ | የጥበቃ ሠራተኛ | ፕሮቴስታንት |
| 19 | ከበደ ኬርቴጆ | 31 | ግርሻዲና | የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ ፀጥታ አስተዳደር ኃላፊ | ኦርቶዶክስ |
| 20 | ጥጋቡ መንገሻ | 37 | ዱማ | ገበሬ ( ከ10 ዓመት በላይ በሸፍትነት የኖረ | ቃልቻ |
| 21 | ይፋይ ጾንን | 37 | ቢያንሊች | ገበሬ | ቃልቻ |
| 22 | ቀፊራ ኮርዲ | 40 | ባቹማ | የመኢኒት ጎልድያ ወረዳ የሚኒሻ ጽ/ቤት ኃላፊ | ኦርዶክስ |